አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የብሄር ብሄረሰብ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋሉ የልዩ ልዩ ተላውጦዎች ተጽእኖ (የአመለካከት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት)

በእሸቱ ወንድሙ

ሚያዚያ 2007ዓ.ም.
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የብሄር ብሄረሰብ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋሉ የልዩ ልዩ ተላውጦዎች ተጽእኖ (የአመለካከት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር መርሀ ግብር
ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የተከናወነ ጥናት

በእሸቱ ወንድሙ

ሚያዚያ 2007 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**የብሄር ብሄረሰብ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋሉ የልዩ ልዩ ተሳውጦዎች ተጽእኖ (የአመለካከት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነትና ልዩነት)**

በእሸቱ ወንድሙ

2007 ዓ/ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ------------------------------------ | ------------------------------ |
| ------------------------------------ | ------------------------------ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ------------------------------------ | ------------------------------ 25/10/2007 |
| ------------------------------------ | ------------------------------ |

# ምስጋና

ለዚህ ጥናት መሳካት ከርዕስ መረጣ ጀምሮ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝና የሥራዬን ሂደት በየጊዜው በመከታተል በማቃናትና በማዳበር ከዚህ ደረጃ እንዲደርስ ከቀና ስኑ-ምግባር ጭምር ለረዱኝ አማካርዬ ዶ/ር ኑሩ መሀመድ ያለኝን አክብሮትና ከፍተኛ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ትምህርቱን እንድማር ወደዚህ ዩኒቨርሲቲ ለላከኝ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍልና ለተቋሙ ባልደረቦች ጭምር ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የተዘጋጀውን የአመለካከት፤የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ እና የችሎታ ምዘና ፈተናን ከሥነ-ልቦና አንጻር ሙያዊ በሆነ መንገድ ጊዜያቸውን መስዋእት አድርገው በማየትና በማስተካከል ለረዱኝ የሥነ-ልቦና ትምህርት ክፍል ባልደረባ ለሆኑት ዶ/ር ተካ ዘውዴ እና ለዶ/ር በላይ ተፈራ፣ የተዘጋጀውን የችሎታ ምዘና ፈተና መደበኛነቱን እንዲጠብቅ ሙያዊ እገዛ ላደረገልኝ ለሃገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ፣ የዚሁ መስሪያ ቤት የዘርፉ ባለሙያ ለሆኑት ለአቶ ጌትነት ማሞ፣ በመረጃ ትንተና ወቅት የመረጃ አተናተን ሂደቱ የትኛውን መንገድ መከተል እንዳለበት ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ከአማካሪዬ በተጨማሪ ሂደቱን ላመላከቱኝ የሥነ-ትምህርት ጥናት ክፍል ባልደረባ ለሆኑት ለዶ/ር ደሳለኝ ጫልሳ የከበረ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በአማርኛ የተዘጋጀውን የአመለካከት፤ የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ አቻዊ ትርጉሙን ጠብቆ የትርጉም ሥራውን በማከናወን ለረዳኝ ለአቶ ይልማ ደምሴ፣ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ትብብር እንዲያደርጉልኝ የትዕዛዝ ደብዳቤ ለጻፉልኝ ለትግራይ ትምህርት ቢሮና ለትምህርት ቢሮ የትምህርት ጥራት  የስራ ሂደት ፈጻሚ ለሆኑት ለአቶ ንጉሴ ትኩ፣ ለአፋር ትምህርት ቢሮና ለቢሮው ም/ቢሮ ኃላፊ አቶ ደራሳ መሀመድ ኢብራሂምና የስርአተ-ትምህርት ሰራተኞች፣ ለገዋኔ ወረዳ የትምህርት ጥራትና ሱፐር ቪዥን ዋና ስራ ሂደት ለሆኑት አቶ ቡሽራ ጀማል፣ ለጅማ ዞን ትምህርት ጽ/ቤትና የጽ/ቤቱ ኃላፊ ለሆኑት አቶ ዑመር አባገሮ፤ ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበባቸው ትምህርት ቤቶች በመረጃ ሰበሰባ ወቅት በናሙና መረጣና ለፈተና ሂደቱ ቅድመ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለረዱኝና ያለምንም ክፍያ መጠይቁንና ፈተናውን አብረው ቆመው ተማሪዎቹን በጥንቃቄ ላስሞሉልኝ የትምህርት ቤቶች ር/መምህራን፣ የክፍል ሀላፊዎች፣ የየትምህርት ቤቱ ዩኒት አስተባባሪዎች፣ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ተጠሪዎች፣ መምህራንና ተማሪዎች በሙሉ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለእናቴ ይደብቡ ሞገስ፣ ለአመሀ ወንድሙ፣ ለኢሳያስ ወንደሙ፣ ለየሸዋጸሐይ ወንድሙና የምዘና ፈተናዎችንና መጠይቆቹን በማባዛት ለረዳችኝ ወ/ት ምጽላል ኃ/ጊዩርጊስና የተሰበሰበ መረጃን በSPSS የመረጃ ማስፈሪያ ፕሮግራም ላይ በጥንቃቄ በመመዝገብና የአርትኦት ሥራውን ለረዳችኝ ለባለቤቴ ወ/ሮ ብርቱካን ወርቁ፣ ለልጆቼ ለሊዲያ እሸቱና ሚኪያስ እሸቱ እንዲሁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለጥናቴ መረጃ ለሰጡኝ በሙሉ ላደረጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ ከልብ የመነጨ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

## ምዕራፍ አንድ

ገፅ

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................ 1

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር ........................................................................... 4

1.3 የጥናቱ ዓላማ ..................................................................................... 17

1.3.1 ዝርዝር አላማ ............................................................................ 18

1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ....................................................................... 19

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................................................... 20

1.6 የጥናቱ ወሰን ..................................................................................... 21

## ምዕራፍ ሁለት

2 ክለሳ ድርሳን

2.1 ህብረ ብሄር ምንነት ........................................................................... 23

2.2 ህብረ ብሄርነት ከልሣነ ብዛህ አንጻር ሲታይ ........................................... 25

2.3 ህብረ ብሄርነት በኢትዮጵያ ................................................................. 27

2.4 የልሣነ-ብዛህነት እንደ ሀብት ወይስ እንደ ኪሳራ ...................................... 29

2.5 የቋንቋ ምርጫ በልሳነ ብዙ ሀገር ........................................................ 32

2.6 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚመለከት የቀረበ አጭር ቅኝት ....................... 34

2.6.1 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ .......................................... 34

2.6.2 የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት ሲሰጥ ያለው አገልግሎት- ......... 35

2.6.3 አማርኛ እንደ ማስተማርያ ቋንቋነት ያለው ሚና .................................... 36

2.7 የአማርኛ ቋንቋ ሚና በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ........................... 37

2.8 አመለካከትና ፍላጎት የሚጠኑበት መስክ........................................................... 39

2.9 የፍላጎትና የአመለካከት ምንነት ........................................................................41

2.9.1 ፍላጎት ምንድነው?..........................................................................................41

2.9.1.1 ፍላጎትና የሁለተኛ የቋንቋ ትምህርት ......................................43

2.9.1.2 የፍላጎት ጠቀሜታ..........................................................................45

2.9.1.3 ፍላጎት በትምህርት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ...........................46

2.9.1.4 ፍላጎትን የማጥናት አስፈላጊነት ..................................................48

2.9.1.5 የተማሪዎችን ፍላጎት የማወቅያ ዘዴዎችና መንገዶች.................50

2.9.1.6 የፍላጎት መመዘኛ ..........................................................................53

2.9.1.7 የትምህርት ፍላጎት መመዘኛ ቅኝት........................................54

2.9.1.8 በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች..................55

2.9.1.8.1 ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ግምት.56

2.9.1.8.2 የመምህሩ የማስተማር ዘዴ.....................................57

2.9.1.8.3 የመምህሩ ስብእና ................................................. 60

2.9.1.8.4 ተማሪዎች ስለ አንድ ርዕስ ጉዳይ ያላቸው ተነሳሽነት..62

2.9.1.8.5 ተማሪው የሚገኝበት አውድና ማህበራዊ ጉዳይ............62

2.9.2 አመለካከት ምንድነው?.....................................................................65

2.9.2.1 አመለካከትን የማጥናት አስፈላጊነት ..................................65

2.9.2.2 የአመለካከት መፈጠርና መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች ....67

2.9.2.3 አመለካከት በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ .69

2.9.2.4 ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ አመለካከትእንዲያዳብሩ የሚደጋገፉ ሁኔታዎች.......71

2.9.2.5 የአመለካከት መመዘኛ/መለኪያ/ ፈተና ..................................73

2.9.3 የፍላጎትና የአመለካከት ጥናት በሥርአተ-ትምህርት ዝግጅት ወቅት ያለው ጠቀሜታ....73
2.10 ከጾታ አንጻር በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚስተዋል የፍላጎት ልዩነት....75
2.11 የትምህርት ውጤት ....78
2.11.1 በትምህርት ውጤት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች....79
2.11.1.1.ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት ....79
2.11.1.2. የማስተማር ዘዴ....81
2.12 በአመለካከት በፍላጎትና በትምህርት ውጤት መካከል ያለ ዝምድና....81
2.13 የአመለካከት፣ የፍላጎት፣ የንሺ. እና የስኬት ግንኙነት....83
2.14 እድሜና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት....84
2.15 ማህበራዊ-ትምህርት ሞዴል....92
2.15.1 ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ንሺነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ....96
2.15.2 በማህበረሰብ-ትምህርታዊ ሞዴል ላይ የሚቀርቡ አስተያየቶች....97
2.16 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶች ....97

## ምዕራፍ ሶስት

3. የጥናቱ ዘዴ....101
3.1 በየደረጃው የሚገኙ የጥናቱ አካላዮች አመራረጥ ዘዴ....101
3.2 የዞኖችን አመራረጥ ዘዴ....102
3.3 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ዘዴ....103
3.4 ለሙከራና ለዋናው ጥናት የክፍሎች አመራረጥ ዘዴ....105
3.4.1 ለሙከራ ጥናት የክፍሎች አመራረጥ ዘዴ ....105
3.4.2 ለዋና ጥናቱ የተመረጡ ክፍሎች ብዛት ....106
3.5 የተጠኙ ተማሪዎች የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ....108

3.5.1 በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ መረጃ ሰጪዎች ብዛት ............................109
3.5.1.1 ለሙከራ ጥናቱ የተመረጡ መረጃ ሰጪዎች..............................111
3.5.1.2 ለዋና ጥናቱ ናሙና መረጃ ሰጪዎች..........................................113
3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ..................................................115
3.6.1. የጽሁፍ መጠይቅ ..................................................................115
3.6.2 ቡድን ተኮር ውይይት.............................................................120
3.6.3. የችሎታ መመዘኛ ፈተና ........................................................122
3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ ...............................................................126
3.8 ከመረጃ ሰጪዎች የተሰበሰበ የመረጃን ምላሽ ማጣራት...........................129

## ምዕራፍ አራት

4. የመረጃዎች ትንታኔና ውጤት-..........................................................131
4.1 የመረጃ ትንታኔ አጠቃላይ መግለጫ..................................................131
4.2 የሙከራ ጥናቱ የመረጃ ትንታኔ .....................................................131
4.2.1 ለሙከራ ጥናቱ የተሰበሰበ መረጃና የመረጃ ምንጮች.........................131
4.2.2 በሙከራ ጥናቱ ላይ የየክልሉ የተማሪዎች የእድሜ ሁኔታ .............132
4.2.3 በሙከራ ጥናቱ ላይ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣
የትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና እድሜ መካከል ያለ
የግንኙነት ደረጃ ............................................................133
4.2.4 በሙከራ ጥናቱ በክልሎች፣ መካከል ያለ የፍላጎት፣
የአመለካከትና የውጤት ልዩነት..............................................135
4.2.4.1. በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል
ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ............................135

4.2.4.2 በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት ያለ የአመለካከት ልዩነት ....................................136

4.2.4.3 በሙከራ ጥናቱ በክልል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለ ልዩነት....................................................138

*4.2.5 ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ግብአትና በዋና ጥናቱ ወቅት የተደረገ ማስተካከያ*..........................................................................140

4.3 የዋና ጥናት የመረጃ ትንታኔ..................................................................143

4.3.1 ለዋና ጥናቱ የተሰበሰበ መረጃ ....................................................143

4.3.2 ለዋና ጥናቱ መረጃ የሰጡ የየክልሉ ተማሪዎች የእድሜ ሁኔታ......144

4.3.3 በተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣ ፍላጎት፣ አመለካከትና በእድሜ መካከል ያለ የግንኙነት/የዝምድና/ ደረጃ........................146

4.3.3.1 ከአፋር ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት................................................149

4.3.3.2 ከኦሮሚያ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት...............................................151

4.3.3.3 ከትግራይ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት................................................153

4.3.4 በክልሎች፣ በፆታና በመኖሪያ አካባቢ መካከል ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት................................163

4.3.4.1. በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋውን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ..................................................................164

4.3.4.2. በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት የሚስተዋል የአመለካከት ልዩነት ..................................................170

4.3.4..3. በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የትምህርት
የችሎታ ምዘና ውጤት ንጽጽር ........................................184
4.3.4.4 ከጾታ አንጻር ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት .190
4.3.4.4.1 በአፋር ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን
የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ..................................193
4.3.4.4.2 በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በጾታ መካከል
የሚስተዋል የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ...................196
4.3.4.4.3 በትግራይ ክልል ተማሪዎች በጾታ መካከል
የሚስተዋል የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ....................199
4.3.4.4.4 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጾታ መካከል
የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት..........202
4.3.4.5 ከገጠርና ከከተማ ተማሪዎች አንጻር የፍላጎት፣ የአመለካከትና
የውጤት ልዩነት........................................................205
4.3.4.5.1 በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል
የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት በተመለከተ
ክልሎቹ በተናጠል ሲታዩ ................................................210
4.3.4.5.1.1 በአፋር ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል
የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት.....210
4.3.4.5.1.2 በኦሮሚያ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል
የሚስተዋል የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት ....214
4.3.4.5.1.3 በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል
የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት.....217
4.4 ዋና ዋና የግኝቶች ገለፃና ትንታኔ፣ ........................................................221

4.4.1 በክልሎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነትን አስመልክቶ የቀረቡ ግኝቶች ....221
4.4.2 እድሜ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና ተጽእኖ ....226
4.4.3 ከጾታ አንጻር የፍላጎት፣የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት ....231
4.4.4 ከገጠርና ከከተማ አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት በመማር ሂደት የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካክትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት ....236
4.4.5 አጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በሚከተለው ዲያግራም መሰረት እንደሚወሰን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል...239

## ምዕራፍ አምስት

5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ ....242
5.1. ማጠቃለያና መደምደሚያ ....242
5.1. የመፍትሄ ሀሳብና አስተያየት ....248
ዋቢ መጻሕፍት ....**251**
አባሪ 1 :- ሙዳየ ቃላት .... **264**
አባሪ 2 :- በአማርኛ የተዘጋጀ የአመለካትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ ....267
አባሪ 3 :- በአፋን ኦሮሞ የተዘጋጀ የአመለካትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ ... 271
አባሪ 4 :- የቡድን ተኮር ውይይት መነሻ ጥያቄዎች .... 274
አባሪ 5 :- የመመዘኛ ፈተና ጥያቄዎች .... 276

አባሪ 6 ፡- መረጃን ለመተንተን ያገለገሉ አማራጭ ቀመሮች ............................ 282

አባሪ 7 ፡- የመረጃ ትንታኔ ውጤት ጥሬ መረጃዎች .......................................... ..286

አባሪ 8 ፡- የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አስተማማኝነትን

የሚያሳይ ጥሬ መረጃ................................................................... 298

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ገፅ

ሰንጠረዥ አንድ ሀ :- ከክልል አንጻር የት/ቤቶችና የተመረጡ ክፍሎች ብዛት ........106

ሰንጠረዥ አንድ ለ :- ከክልል አንጻር ለዋናው ጥናት የት/ቤቶችና የተመረጡ ክፍሎች ብዛት ........107

ሰንጠረዥ ሁለት፡- ከክልሎች አንጻር ለሙከራ ጥናቱ የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛት ......112

ሰንጠረዥ ሶስት :- ለሙከራ ጥናቱ አካባቢ ስብጥርን መሰረት በማድረግ በናሙናነት የተመረጡ መረጃ ሰጪ ተማሪዎች ........112

ሰንጠረዥ አራት፡- ለዋና ጥናቱ በናሙናነት የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛትና ክልላዊ ስብጥር ........114

ሰንጠረዥ አምስት፡- ለዋና ጥናቱ ተጠኚዎች የተወሰዱበት የቦታ ወይም የአካባቢ ስብጥር ........115

ሰንጠረዥ ስድስት፡-- የአመለካከትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቆች የአስተማማኝነት ደረጃ በክሮምባክ አልፋ........119

ሰንጠረዥ ሰባት፡- የፈተና ዓይነት ዝርዝር ........123

ሰንጠረዥ ስምንት፡- ለሙከራ ጥናቱ ከየክልሉ የተመረጡ ተማሪዎች እድሜ ........133

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- በሙከራ ጥናቱ ወቅት የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ግንኙነትን የሚያሳይ ........134

ሠንጠረዥ አስር፡- በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር የሚስተዋል የፍላጎት ልዩነት........135

ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት ያለ የአመለካከት ልዩነት ........137

ሰንጠረዥ አስራ ሁለት :- በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርት ውጤት የተስተዋለ ልዩነት ........138

ሰንጠረዥ አስራ ሶስት፡- የየክልሉን ተማሪዎች የእድሜ ደረጃን የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ........................................................................145
ሰንጠረዥ አስራ አራት፡- በተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣ ፍላጎት፣ አመለካከትና በእድሜ መካከል ያለ ግንኙነት ..................................................146
ሰንጠረዥ አስራ አምስት፡- ከአፋር ተማሪዎች የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነት ........................................................149
ሰንጠረዥ አስራ ስድስት፡- ከኦሮሚያ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነት ...................................................151
ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፡- ከትግራይ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት ...................................................153
ባርግራፍ አንድ፡- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መጀመር ያለበትን ደረጃ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽን የሚያሳይ ባር ግራፍ ........................................160
ሰንጠረዥ አስራ ስምንት ፡-በክልሎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት የአማካይ ልዩነትን የሚያሳይ መደበኛ የሂሳባዊ ስሌት ትንተና ውጤት ..............................164
ሰንጠረዥ አስራ ዘጠኝ፡- በክልል ተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋል የፍላጎት ልይት ትንተና አጭር መግለጫ........................................................................165
ሠንጠረዥ ሀያ፡- በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት የልይይት ትንተና ዝርዝር መግለጫ..................................................................166
ሰንጠረዥ ሀያ አንድ፡- በቋንቋ ትምህርት ፍላጎት በተመሳሳይ የስብስብ ረድፍ ላይ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ ........................................................169
ሰንጠረዥ ሀያ ሁለት ፡- የክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የአመለካከት የአማካይ ልዩነትን የሚያሳይ የሂሳባዊ ስሌት መደበኛ የትንተና ውጤት ..................171
ሰንጠረዥ ሀያ ሶስት ፡- በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተውል የአመለካከት የልይት ትንተና አጭር መግለጫ........................................................................172
ሠንጠረዥ ሀያ አራት፡- በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የአመለካከት የልይይት ትንተና ዝርዝር መግለጫ ..................................................173

ሰንጠረዥ ሀያ አምስት፡- በአመለካከት በተመሳሳይ የስብስብ ረድፍ ላይ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ ....................................................................175

ሰንጠረዥ ሀያ ስድስት፡- መደበኛና አሀዛዊ የሆነ የቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና የውጤት ትንተና ....................................................................184

ሰንጠረዥ ሀያ ሰባት፡- በክልሎቸ መካከል የቋንቋው ትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤት የንጽጽረ ትንተና አጭር መግለጫ....................................................................185

ሰንጠረዥ ሀያ ስምንት ፡- በክልል ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርት የምዘና ፈተና ውጤት አማካይ ልዩነት የንጽጽር ትንተና ዝርዝር መግለጫ....................186

ሰንጠረዥ ሀያ ዘጠኝ፡- -፡- የችሎታ ምዘና ውጤት በተመሳሳይ ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ ....................................................................189

ሠንጠረዥ ሰላሳ ፡- አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ክልሎች በወንድና በሴት መካከል የሚስተዋል የአማካይ ልዩነትን ለማየት ሲባል የተከናወነ የቡድን ስሌት ....................................................................190

ሠንጠረዥ ሰላሳ አንድ፡- ከጾታ አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ክልሎች ላይ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ንጽጽር ........................191

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሁለት፡- በአፋር በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካኝ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ....................................................................194

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሶስት፡- በኦሮሚያ ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት....................................................197

ሰንጠረዥ ሰላሳ አራት ፡- በትግራይ ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ....................................................200

ሰንጠረዥ ሰላሳ አምስት ፡- በአዲስ አበባ በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት ....................................................................203

ሰንጠረዥ ሰላሳ ስድስት ፡- ከገጠርና ከከተማ አንጻር የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት....................................................................206

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሰባት:- በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር ..................207

ሰንጠረዥ ሰላሳ ስምንት፡- በአፋር ክልል ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት ............................210

ሰንጠረዥ ሰላሳ ዘጠኝ:- በአፋር በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር ........211

ሰንጠረዥ አርባ ፡- በኦሮሚያ ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት ...............................................214

ሰንጠረዥ አርባ አንድ ፡- በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር ..........................................................................................215

ሰንጠረዥ አርባ ሁለት፡- በትግራይ ክልል ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት ............................218

ሰንጠረዥ አርባ ሶስት፡- በትግራይ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ መመዘኛ የፈተና አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር ..................................................................219

ሰንጠረዥ አርባ አራት፡- የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ትስስር .......................................................239

# አህፅሮተ ጥናት(Abstract)

የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነው የአማርኛ ትምህርት ለኢ-አፊፊት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት በሚሰጥበት ጊዜ ትምህርቱ ለየክልሉ ተማሪዎች መስጠት የሚጀምርበት የትምህርት ደረጃ ሲታይ በአፋር ክልል፣ በደቡብ ክልልና በጉራጌ ህብረተሰብ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ነው። በትግራይና በሱማሊያ ክልል ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ነው። ስለሆነም በአማራው፣ በኦሮሚያና በሱማሊያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአፋርና በሌሎች ክልሎችም የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ የተለያየ በመሆኑ ምክንያት፤ ተማሪዎቹ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት እድሜና የክፍል ደረጃ የተለያየ እንዲሆን አድርጎታል። ይህ ልዩነት መኖሩ ደግሞ በቋንቋው ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል ይገመታል። ስለዚህ የጥናቱ ዋና ዓላማ ልሳነ ብዙ የሆነ ህብረተሰብ በሚኖርባት ሀገራችን ኢትዮጵያ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እየተማሩ ባሉበት ጊዜ ትምህርቱን ከአንደኛ፣ ከሶስተኛና ከአምስተኛ ክፍል እና ከተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ መማር የጀመሩ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት ምን እንደሚመስል በማየት እና በተላውጦዎቹ(variables) መካከል የሚኖር የእርስ በርስ ግንኙነት ምክንያት በቋንቋው ትምህርቱ ላይ የሚኖርን ተፅእኖ መመርመር ነው። ጥናቱ የተከናወነው በአፋር ፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ሲሆን ከአራቱም ክልሎች ከሙከራ ጥናቱ ጋር ሶስት ሶስት ዞኖችን በድምሩ አስራ ሁለት ዞኖችን በእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል። ከተመረጡ ዞኖችም ሁለት ሁለት ትምህርት ቤቶችን በቀላል የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ መሰረት በድምሩ 20 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። ከትምህርት ቤቶቹም 1012 ተማሪዎች አካባቢያዊና ጾታዊ ስብጥራቸውን እንዲጠብቅ በማድረግ በስብጥራዊ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተመርጠዋል። ከዛም ማእከላዊነቱን የጠበቀ የችሎታ መመዘኛ ፈተና፣ የፍላጎትና የአመለካከት መለኪያ መጠይቅ ተዘጋጅቶ የእስተማማኝነትና የትክክለኛነት ደረጃ ከተረጋገጠ በኋላ መረጃ ተሰብስቧል። ከየትምህርት ቤቱ ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራንም በምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት መረጃ ተሠብስቧል። ከዛም በውስን የአመለካትና የፍላጎት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቅና በፈተና የተሰበሰበ መረጃ በSPSS ሶፍት ዌር ላይ ከተደራጀ በኋላ መጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ትንታኔ ተሰጥቶበታል። በቡድን ተኮር ውይይትና በልቅ የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ በአይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም በገለፃ አማካኝነት ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል። ከላይ በተገለጹት የመረጃ አተናተን ዘዴ መሰረት ተተንትኖ የተገኘው ውጤት ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ባላቸው አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ግንኙነት መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል። ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውና ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ በተቃራኒው ዝቅተኛ ፍላጎትና አሉታዊ አመለካከት ያላቸው በትምህርቱ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል። ከዚህ አንጻር የአፋር ክልል ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ትግራይ ክልል ከኦሮሚያ ክልል አንጻር ሲታይ ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እና ትምህርቱን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት፣ በትምህርቱ ላይ ያለ አመለካከትና በትምህርቱ የሚመዘገብ የችሎታ ምዘና ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። ከእድሜ አንጻር የተገኘው ውጤት ሲታይ ደግሞ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ ሲጨምር ለትምህርቱ ያላቸው በጎ አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከከተማና ከገጠር ተማሪዎች አንጻር የተገኘው ውጤት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት በልጦ ተገኝቷል። ከግኝቶቹም በመነሳት የመፍትሄ ሀሳብና አስተያየት ቀርቧል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ (Back ground of the study)

ትምህርት የተደራጀና ሳይንሳዊ የሆነ እውቀትንና ክህሎትን የማስተላለፊያ መሳሪያ ስለሆነ ለአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት መሰረት ነው፡፡ የአለም ስልጣኔ አሁን የደረሰበት ደረጃ መድረስ የቻለው ከትምህርት በተገኘ ዕውቀትና የተግባር ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ብዙ ሃገራትና በየሀገራቱ የሚገኙ ማህበረሰቦች ልጆቻቸው መደበኛ የሆነ እውቀትና ክህሎትን እንዲገበዩላቸው ወደ ትምህርት ቤት እየላኩ የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን እንዲማሩ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ እያስተማሩ ካሉት የትምህርት አይነቶች ውስጥም አንዱ የቋንቋ ትምህርት ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርት በትምህርትነት ከመሰጠቱም በተጨማሪ የትምህርት ማስተላለፊያ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖም እያገለገለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርትን ማስተማር ከሌላው በተለየ መልኩ ፊርጀ ብዙ ጠቀሜታ እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም ቋንቋ ለትምህርት ማስተላለፊያ መሳሪያነት ከማገልገሉም በተጨማሪ ለማህበረሰባዊ፣ ክልላዊ፣ አገር አቀፋዊና አለም አቀፋዊ ተግባቦት ከማገልገሉም ባሻገር ለባህል ሽግግር፣ ለኢኮኖሚ እድገት እና ለፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ እያገለገለ ስለሚገኝ ጠቀሜታው ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋ በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኘውን የባህል፣ የአኗኗር፣ የእሴት አጠቃቀም ሥርዓት ወ.ዘ.ተ...መግለጫም መመስረቻም ስለሆነ ቋንቋ አንድን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብን መፍጠሪያ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በርካታ ሀገሮች በትምህርት ፖሊሲያቸው ውስጥ አስገብተው ሁለትና ከዚያን በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን መርጠውና ስርአተ-ትምህርት ቀርጸው እያስተማሩ ይገኛሉ(Fasold, 1984 እና Webb and Sure, 2000)፡፡

ከዚህ አንጻር ቋንቋን በሚመለከት የሚከናወን ጥናት ወይም የሚሠነዘር ሐሳብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሀገራዊና ማህበራዊ ጉዳይን፣ ትምህርትን፣ የአንድን ህብረተሰብ ማንነትን፣ ባህላዊ ዳራን፣ ፖለቲካዊ ስርአትን፣ ሀገራዊ ግንኙነትን፣ ክልላዊ ልማትንና ታሪካዊ እሴትን ስለሚዳስስ በዙሪያው የሚከናወንን ጥናት ፊርጀ ብዙ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ቋንቋ ከሚሰጠው ጠቀሜታ በመነሳት ሀገራት በቋንቋ እቀዳ ወቅት ሥነ-ማህበራዊ፣ ስነ-ልሣናዊ፣

ማህበራዊ-ሥነልቦና (Social Psychology)፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በማጥናት፣ ከጥናቱ የሚገኝን ውጤት በግብአትነት በመጠቀምና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የቋንቋ እቀዳቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ (Appel,1992)::

የቋንቋ ትምህርት ለአፊ-ፊትና ለኢአፊ-ፊት ተማሪዎች በሚሰጥበት ጊዜ በሰፊ ጥናት ላይ የተደገፈ መረጃን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት የሚባለው በነዚህ ምክንያቶች ነው:: በቋንቋ እቀዳ ወቅትም ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎችን በማጥናትና ከሚገኘው የጥናት ውጤት በመነሳት የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ሆነ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን አቅዶ ለህብረተሰብ ማስተማር አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል።

በተለይም የቋንቋ ትምህርትን ለዜጎች ለማስተማር ተብሎ ሥርአተ-ትምህርት በሚቀረጽበት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ስሜት የንሺ ሁኔታ፣ ባህላዊ ዳራ፣ አካባቢያዊ ሁኔታና ተፅእኖ፣ የእውቀት ደረጃንና እድሜን ከግምት ውስጥ በማስገባት መቅረጽን የግድ ይላል። ይሄንን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ የቋንቋ ትምህርትን ማከናወን በመማር ማስተማሩ ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን አስቀድሞ ለመፍታት ስለሚያገለግል የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን በሚያደርግ ሂደት ላይ ጠቀሜታው የጎላ ነው(Harmer,1991; Rubinsen, 2001; Gardner & Masgort, 2003; Gardner, 2007 and Browen,2007)::

ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ተመራማሪዎች አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ማህበራዊ አውድና እድሜ በትምህርቱ ላይ እያሳደሩ ያለው ተጽእኖ ምን እንደሚመስል ለማወቅና በዙሪያው የሚስተዋሉ ችግሮችን አሰቀድሞ ለመፍታት ሲሉ ከተለያዩ ማእዘናት የተለያዩ ጥናቶችን እያከናወኑ ይገኛሉ። በዚሁ ሂደት በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የሚከሰቱ አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖችን በመለየት የሚታዩ አዎንታዊ ጎኖች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በአሉታዊ ጎኖቹ በኩል የተስተዋሉ ችግሮች ደግሞ መፍትሄ እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ናቸው (Krashen, 1982 & 2009; Gardner & Masgort, 2003; Gardner, 2007; and Browen, 2007):: የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም ባከናወኑት ጥናት ሃገራት እያስተማሩ ያለውን የአንደኛና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ውጤታማ ማድረግ እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። ተቋማቱም በአፍ መፍቻ ቋንቋና በሁለተኛ ቋንቋ የንባብ ችሎታ ዙሪያ ጥናት በማከናወን የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየት የመማር ማስተማር ተግባሩ መስተካከል እንዳለበት የመፍትሄ ሀሳብ አቅርበዋል(USAID,2004 እና 2010)::

ከመፍትሄዎቹም ውስጥ አንዱ በስርአተ-ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ የህብረተሰቡን ፍላጎትና የትምህርቱ አስፈላጊነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመለየትና በማረጋገጥ ስርአተ-ትምህርቱ እነዚህን ርእሰ ጉዳዮች ታሳቢ አድረጎ መዘጋጀትና መቀረጽ እንዳለበት በመፍትሄ ሀሳብነት አቅርበዋል። የጥናቱ ውጤትንም በተመለከተ የሚመለከታቸው ሀገራት በመፍትሄነት እየተገለገሉበት እንደሚገኙ ይገመታል። በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በትምህርትነት በሚሰጥበት ጊዜ የተማሪዎችን አመለካከት፣ ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎትና የእድሜ ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ትምህርቱ መሰጠት እንዳለበት ያስገነዝባሉ (Krashen, 2009; Gardner, 2007; and Browen, 2007)።

በሀገራችን ኢትዮጵያም አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ የትምህርት አሰጣጡ የሚከተለውን ህገ-መንግስታዊ ማእቀፍን መሰረት አድርጎ ነው። ይሄውም አማርኛ የፌደራሉ የስራ ቋንቋ መሆን አለበት በማለት በህገ-መንግቱ አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 2 ላይ በግልጽ ተቀምጧል። የማስታወቂያ ሚኒስቴር 1994 ዓ/ም ባዘጋጀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የማስፈጸም አቅም ግንባታ እስትራቴጅና ፕሮግራሞች በሚለው መጽሀፍ ላይም እንደቀረበው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን የአማርኛ ቋንቋን መማር እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው።

ስለዚህም ለቋንቋ ትምህርቱ ስርአተ-ትምህርት ተዘጋጅቶለት በአንደኛና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እንዲሰጥ ተወስኖ ትምህርቱ የአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆነው የሀገሪቱ ክልሎችና ብሄር ብሄረሰቦች በሙሉ ቋንቋውን መማር እንዳለባቸው በተወሰነው መሰረት ውሳኔው ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ይሁን እንጂ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የአመለካከት፣ የፍላጎት የውጤትና የእድሜ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክትና በልዩነቱ የተከሰቱና የሚከሰቱ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል በጥናት ላይ የተደገፈ መረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን የሚያረጋግጥ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል በቂ መረጃ የለም። የትምህርት አሰጣጡ በበቂ ጥናትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ምክንያት ወጥ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ስርአትን የተከተለ አይደለም። በመሆኑም በትምህርት አሰጣጡ ዙሪያ በርካታ ክፍተቶችና ችግሮች ይስተዋሉበታል።

በሚስተዋሉ ክፍተቶች ዙሪያ በቂ መረጃን ሊሰጥ የሚችል ሰፋ ያለ ጥናት ያለመከናወኑ ደግሞ በስርአተ-ትምህርት ዝግጅት ላይም ሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር መፍጠሩ እንደማይቀር ይገመታል፡፡ ስለዚህ ከላይ ከቀረበው መሰረተ ሀሳብ ላይ በመነሳት ያለውን የመረጃ ክፍተት በተወሰነ ደረጃ ለመሙላትና በዙሪያው የተስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳ ዘንድ ይሄንን ጥናት ማከናወን አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ ለዚህ ጥናት ዳራዊ የመነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.2 ለጥናቱ መነሻ ችግር

ከላይ በጥናቱ ዳራ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ለህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና ውጤት ምን እንደሚመስል ባለመጠናቱ በትምህርቱ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች ወይም አሉታዊ ጎኖች ከነመነሻ ምክንያታቸው ጭምር ከግምት ባለፈ በውል አይታወቅም፡፡ ስለሆነም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች በዝርዝር ባለመጠናታቸው ምክንያት ለችግሮቹ ማስተካከያ እየተሰጠ ነው፣ ለማለት ያዳግታል፡፡ ስለዚህ ከላይ በተነሱ ምክንያቶች መነሻነት ይሄንን ጥናት ማከናወን አስፈላጊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም በስፋት የሚታየው ርእሰ ጉዳይ የህብረ-ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና የእድሜ ደረጃ፣ አካባቢያዊ ሁኔታ(ገጠርና ከተማን በሚመለከት) ከትምህርቱ ውጤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት(ትስስር)ና ተጽእኖ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽን የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ የፍላጎትና የአመለካከት ምንነትን በተመለከተና በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ምን እንደሚመስል በመስኩ ምሁራን ዘንድ የሚቀርቡ ንድፈ-ሀሳቦችንና አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው አጠር አድርጎ መመልከት ይቻላል፡፡

ይሄውም ፍላጎትንና አመለካከትን በጋራ ከሚያስተሳስራቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ሁለቱም ተላውጦዎች በብዛት በስነ-ልቦና የጥናት መስክ ውስጥ የሚጠኑ መሆናቸው ነው፡፡ Skinner (1989) ፍላጎትና አመለካከት እንደ ንሺ ሁሉ በሥነ-ልቦና የጥናት ዘርፍ ውስጥ በስፋት ከሚጠኑ ተለውጦዎች ውስጥ እንደሚገኙ ያስረዳሉ:: ይሁን እንጂ ተላውጦዎቹ በተናጠል ሲታዩ ካላቸው ባህሪ አንጻር ደግሞ ሁለቱም የየራሳቸው የሆነ መለያ ባሕሪ ያላቸው ናቸው፡፡

አመለካከት ማለት እንድ ግለሰብ ስለ አንድ ርእሰ ጉዳይ/ስለ አንድ ነገር/ ያለው ስሜት፣ ግንዛቤና እይታን የሚመለከት ነው፡፡ ፍላጎት ግን አንድን ተግባር ለማከናወን መሻትን /መፈለግን/ መሠረት ያደረገ ስለሆነ ተግባርና ግብ ተኮር የሆነ ውስጣዊ ስሜት ነው:: ስለዚህ ፍላጎት አንድን ተግባር በመምረጥ እንዲተገበር የሚያደረግ፤ ግብን መሰረት ያደረገ ንቃተ ህሊናዊ ስሜት ነው፤ይሉታል(Craing, 1979 እና Turne, 1997):: ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ፍላጎት አላማን መሰረት ያደረገ ከተግባር ጋር የሚያያዝ ተላውጦ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ፍላጎት ወደ ተግባር የሚያስገባ ስሜትን የሚመለከት ሲሆን አመለካከት ማለት ግን ስለ አንድ ነገር ያለ ግንዛቤን፣ አስተሳሰብን ወይንም እይታን የሚመለከት ነው(Gerry,1970)፡፡ አመለካከት ከግንዛቤና ከእይታ ጋር የተያያዘ ነው፤ ሲባል ግንዛቤው ወይም እይታው አሉታዊ አለበለዚያም አዎንታዊ የሆነ አስተሳሰብን /ስሜትን/ የያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ተማሪ ለሂሳብ ትምህርት ወይም ለህክምና ሳይንስ ትምህርት አዎንታዊ ወይንም አሉታዊ ግንዛቤ ይዞ ተገኘ ማለት ተማሪው ለትምህርቶቹ ያለው አመለካከት ምን አይነት እንደሆነና በምን ያህል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት ነው፡፡

ተማሪው ለትምህርቶቹ አዎንታዊ ወይንም አሉታዊ ግንዛቤ አለው ማለት ትምህርቶቹን ለመማር መርጧቸው ወደ ተግባር ይገባል ማለት ግን አይደለም፡፡ ስለዚህ አመለካከት ስሜት ወይንም ግንዛቤ ተኮር ሲሆን፤ ፍላጎት ደግሞ በስሜትና በግንዛቤ ላይ ብቻ የሚያቆም ሳይሆን በተግባር ለመሳተፍ መምረጥንና መነሳሳትን የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ፍላጎት አዎንታዊ የሆነና ተግባር ተኮር ስለሆነ ከአመለካከት የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይሄም ማለት አመለካከት ከአፌክቲቭ ዶሚየን (Affective domiain) ጋር የተያያዘ ሲሆን ፍላጎት ግን አንድን አላማ ወደ ተግባር ለመቀየር መፈለግን የሚመለከት ሆኖ በተወሰነ ደረጃ ከሳይኮሞተር ዶሚየን (Psychomotor domian) ጋር ግንኙነት ያለው ነው፡፡

ሁለቱ ተላውጠዎች በተናጠል ሲታዩ ደግሞ Hurlock (1996 እና 1972) ፍላጎት ማለት ወደ ግብ፣ አላማና ተግባር ሊመራ የሚችል ውስጣዊ ስሜት እንደሆነና ይሄም አንድን ነገር ከመውደድና ከመፈለግ የሚመጣ ውስጣዊ ሃይል ነው፤ በማለት ይገልፃሉ:: Bätz et al.(2010) አገላለጽ ፍላጎት ውስጣዊ ንሺ (Intrinsic motivation) ከሚለው ቃል ጋር አንድ እንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡ Skinner (1985) William (1890)ን ጠቅሰው ፍላጎት የታቀደ ዓላማን ከግብ ለማድረስ ሲባል ለሚከናወን ተግባር ዝግጁ ሆኖ መገኘትን የሚመለከት ነው፡፡ በተለይም ፍላጎት ከውስጣዊ ንሺ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡

ስለዚህ አንድን ተግባር ለማከናወን መሳብን /መማረክን/ መሰረት የሚያደርግ ውስጣዊ ስሜት ነው:: ይሄም ተላውጦ በአብዛኛው በስነ-ልቦና የጥናት ዘርፍ ውስጥ በስፋት የሚጠና ሲሆን አንድን ነገር ከመውደድ ጋር ተያይዞ ነገሩን በተግባር ለመፈተሽ መነሳሳትን ወይም ለመምረጥ ዝግጁ መሆንን የሚመለከት ውስጣዊ ስበት ነው፡፡ ስለዚህ ፍላጎት ህያው የሆነ /ቀጣይነት ያለው ሆኖ/ ስለ አንድ ነገር ጥቅሙን አሠራሩን በተግባር ለማወቅና ለመፈተሽ የሚገፋፋ ውስጣዊ ሃይል ነው፤ በማለት የመስኩ ምሁራን ሰፊ ማብራሪያ ያቀርባሉ::

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የምሁራን ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ፍላጎት ማለት ከአንድ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ወደ ተግባርና እንቅስቃሴ ለመግባት የሚያነሳሳ ውስጣዊ ስሜትና ኃይል ነው:: ይሄውም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናወን መምረጥንና መፈለግን የሚመለከት ሆኖ በስነ-ልቦና የጥናት መስክ ውስጥ በስፋት የሚጠና የተላውጦ አይነት መሆኑን ከምሁራኑ ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል::

የአመለካከትን ምንነት በተመለከተ ደግሞ እንደ ፍላጎት ብያኔ ሁሉ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይገልጹታል፡፡ ይሁን እንጂ የምሁራኑ ብያኔ ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን ከሚያቀርቡት ሀሳብ መረዳት ይቻላል፡፡ የስነ-አእምሮ ሰዎች ቃሉን ከዝንባሌ፣ ከዝግጁነትና ከእይታ/ከአስተያየት/ አንፃር ይገለገሉበት እንደነበረ ነው፤ የሚገልጹት፡፡ Gerry (1970) አመለካከት ከግለሰባዊና ማህበራዊ ተግባር የሚመጣ ነው፡፡ ማህበራዊ ሲባል እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ለሚከተለው የጋራ አቋም በጽናትና በእይታ አንድ መሆንን የሚመለከት ነው፡፡ ግላዊ ተግባር ሲባል ደግሞ አንድ ሰው ከአካባቢው የሚያዳብረውና በተፈጥሮው የሚኖረው ግላዊ ግንዛቤንና እይታን መሰረት ያደረገ ነው፤ይሉታል፡፡ በተጨማሪም Gerry (1970) የአመለካከት ምንነትን ሲገልጹ አንድን ሁኔታ ወይም ተግባርን የመውደድና የመጥላት ወይንም የመፈለግና

የመራቅን (approach-avoidance) አቅጣጫን የሚያመለክት ስሜት ነው። አመለካከት መላምታዊ ሆኖ ስለ ክፍሎች ወይም ቡድኖች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ የሆነ ግምገማዊና ግምታዊ እሳቤን፣ ስሜትንና እምነትን ይዞ መገኘትን የሚመለክት ነው።

አመለካከት የተደራጀና ተከታታይነት ያለው ሆኖ ሰዎች ወይንም ቡድኖች ከሚገኙበት ማህበራዊ አውድና አካባቢያዊ ሁኔታዎች አንጻር የሚፈጠር አእምሮአዊ፣ ስሜታዊ እና ባሕሪያዊ ክስተት/ለውጥ/ እንደሆነ ይገልፃሉ (Gagne,1977 እና Malim and Birtch,1998)። ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው አመለካከት ከውልደት በኋላ በእድገት ሂደት የምናዳብረው የስብእና ክፍል ነው(Kuppasway,1984 እና Aggarwa,1998)። ይሄንንም ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን ወዘተ የመውደድ የመጥላት፣ የመደገፍ ወይም የመንቀፍ፣ የመቅረብ ወይም የመራቅ.....ዝንባሌንና ስሜትን የሚያመለክት የስብእና ዘርፍ ነው። እነዚህ ባህሪያት ደግሞ በውስጣችን ሊጠነሰሱ የሚችሉት በተለይ እራሳችንንና አካባቢያችንን ለይተን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ይነሳና በሂደት የምናዳብረው ሂደታዊ የሆነ የባህሪ ለውጥ እደሆነ ነው፣ ምሁራኑ የሚገልጹት(Gardner, 2007; Aggarwa, 1998; Kuppasway,1984; Skinner, 1985; Bugleski,1971 እና Gerry, 1970)።

Hurlock (1996) አመለካከት ከትምህርት ጋር ተያይዞ ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ለትምህርት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ነው። ይሄውም ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ጠቀሜታ አለው ብለው የሚገምቱ ከሆነና ስለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ይኖራቸዋል ይላሉ:: Hurlock (1996) እና Lightbown (2011) ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ተነሳሽነት ያላቸው ከሆኑ ደግሞ በሚማሩት ትምህርት ውጤታማ እንደሚሆኑ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ። በተቃራኒው ተማሪዎች አንድን ትምህርት መማር፤ ምንም ጥቅም አይሰጥም ወይም ትምህርቱ ከባድ ነው ወይም ምቾት አይሰጠኝም ብለው የሚገምቱ ከሆነ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት አይኖራቸውም። በመሆኑም በሚማሩት ትምህርት ውጤታማ መሆን እንደማይችሉ ይገልጻሉ።

Gardner (2007) እና Skinner (1985) በተመሳሳይ መልኩ አመለካከት በአንድ የትምህት አይነት ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖ ምን እንደሆነ በሚከተለው መንገድ ያስቀምጣሉ፡፡ ይሄውም ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳም በትምህርቱ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ለአንደኛና ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የነዚህ ተላውጦዎች መኖር ወይም ያለመኖር በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖን ያሳድራሉ ይላሉ፡፡

Gardner (2007) በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ዘንድ አመለካከትና ፍላጎት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ በቂ መረጃ ማግኘት ከተቻለ፤ በዙሪያው የሚከሰቱ ችግሮችን አስቀድሞ ለመፍታት ወይንም ማስተካከያ ለመስጠት ስለሚረዳ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በተለይም የመስኩ ምሁራን እንደሚሉት ፍላጎት እና ተነሳሽነት ከአዎንታዊ አመለካከት የሚገኙ ናቸው፡፡ አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና ተነሳሽነት ለውጤታማ ተግባር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላላቸው እንደ ሌሎቹ የተላውጦ አይነቶች በስፋት መጠናት አለባቸው የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ(Gardner & Masgort, 2003; Bugleski,1971 እና Krashen, 2009)፡፡

Krashen (1982 እና 2009) የቋንቋ ለመዳን መሰረት በማድረግ ካነሷቸው አምስት የመላምት ፅንሰ-ሀሳቦች ውስጥ አንዱ ከስነ-ልቦና ዘርፍ ጋር በማያያዝ የቀረበው መላምት ነው፡፡ ይሄውም የስብእና ክፍሎችን (አመለካከትን፣ ዝንባሌን፣ ፍራቻን፣ ንሺንና ፍላጎትን) መሰረት ያደረገ (The Affective Filter hypothesis) ነው፡፡ እንደ Krashen (1982 እና 2009) አባባል አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌና ተነሳሽነት ለቋንቋ ለመዳና ትምህርት ጠቀሜታቸው ሰፊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩልም Brown (2005 እና 2007) ባዘጋጁት መጽሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ምክንያቶች ውስጥ ማህበራዊ፣ ስነ-ልሳናዊ፣ እድሜ፣ ስነ-ልቦናዊ ተጽእኖ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ከስነ-ልቦና ተጽእኖ ውስጥም በዋናነት የሚጠቀሱት አመለካከት፣ ንሺ፣ ዝንባሌና ፍላጎት ናቸው፡፡ እነዚህ ተላውጦዎች ደግሞ በሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽእኖ አድራጊ እንደሆኑ የተለያዩ ጥናቶችን በማጣቀስ በጽሁፋቸው ውስጥ አስፍረዋል፡፡

በተጨማሪም ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ Garry (1970); Mackey (1968) እና Gardner (2007) ውጤታማ ትምህርት ለማከናወን ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነአመለካከት፣ ተነሳሺነት፣የመማር ፍላጎትሊኖረው እንደሚገባ በጥናት ላይ ተደገፈ ገለጻ አቅርበዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት ያለ እንቅፋት እንዲከናወን እና አጥጋቢ ውጤት እንዲመዘገብ ከተፈለገ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት የመማር ፍላጎትና አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል ይላሉ (Garry, 1970; Mackey,1968; Gardner,2007; Brown, 2007 እና Lightbown, 2011)::

Harmer(1991) እና Evans(1965) ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ አመለካከትና ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል:: ይህ ሆኖ ከተገኘ በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤትን እንደሚያስመዘግቡና በአንፃሩ አዎንታዊ አመለካከትና ፍላጎት ከሌላቸው ደግሞ በተለየ ሁኔታ ውጤታቸው ዝቅ ከማለቱም በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይም ችግር እንደሚፈጥር ያስገነዝባሉ፡፡ በተለይም በSkinner (1989); Aggarawal (1998); Gardner & Masgort (2003); USAID (2010 እና 2004) ላይ የቀረበን ሀሳብ በስፋት መመልከት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ *ፍላጎት፣ አመለካከት፣ መነሳሳት(Orientation) እና ንሺ (Motivation) በተማሪዎች ባህሪ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ በተለያዩ አጥኚዎች በተጠኑ የጥናቶች ግኝት በስፋት ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ McCombs(1997); Tudor (1996); Hancock (2001); Bugelski(1971);* Lightbown (2011) *እና Gardner (2007) መመልከት ይቻላል::*

በሌላ በኩል ፍላጎት ከንሺ ጋር ያለውን ግንኙነትን ስንመለከት ደግሞ *ፍላጎት የንሺ ዋናኛው አካል እንደሆነ ሊረሣ አይገባም በማለት የንሺ ሌላኛው አካል እንደሆነ ይገልፃሉ(Harmers, 1991;* Lightbown, 2011 *እና Gardner, 2007):: በዚህም ረገድ ብዙ የሥነ-ልቦና ሊቃውንት ፍላጎት ከውህዳዊ ንሺ (Integrative motivation) ጋር ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑም በላይ በተማሪዎች ውጤት ላይም አዎንታዊ አስተዎጽኦ እንዳለው ይገልጻሉ:: ንሺ ከአዎንታዊ አመለካከት የሚመጣ መሆኑን ጭምር ምሁራኑ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡*

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሠረት ፍለጎት፣ አመለካከትና እና ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚሆኑ በስፋት ያስገነዝባል (Lightbown, 2011):: በሌላ በኩል ስንመለከት ደግሞ የተማሪዎች ውጤት ከቦታ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከጾታ አንፃር ሲታይ ደግሞ የተለያየ ሆኖ ይስተዋላል:: ለዚህም ምሁራን እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት

የፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ ተነሳሽነት ካለመኖር ጋር ተያይዞ የሚመጣ ከመሆኑም በተጨማሪ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ሁኔታዎች እና የተማሪው የእድሜ ደረጃ በምክንያትነት ሲጠቀሱ ይስተዋላል። በአንጻሩ ደግሞ ማህበራዊ ሁኔታዎች እና የተማሪው የእድሜ ደረጃም በተማሪዎች ተነሳሽነት፣ ፍላጎት እና አመለካከት ላይ ተጽእኖ ስለሚኖራቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ግንኙነት ስለሚኖራቸው ተማሪዎቹ እንደየ ትምህርት አይነቱ ከትምህርት ቤት፣ ከክልልና ከመኖሪያ አካባቢ አንጻር የሚያስመዘግቡት ውጤት ሲታይ በአንዱ ከፍተኛ በሌላው ደግሞ አነስተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ይስተዋላል(Hurlock,1980; Grray,1970; Webb, 2000 and Krashen, 2009)::

ይሄንንም ለማረጋገጥ በተደረገ ጥናት የተማሪዎች ፍላጎት አመለካከት፣ ዝናባሌ እና ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማየት አጥኝው በ1997 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ እንድ ዞን ውስጥ በሚገኙ በሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች /በትምህርት ቤቶች መካከል/ በሚማሩ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ጥናት አከናውኖ ነበር። በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ ዝናባሌ እና ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገባቸውንና በተቃራኒው ከፍተኛ ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ ዝናባሌ እና ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውን ጥናቱ አመልክቷል። በተላውጦዎቹ መካከል ያለው የተጽዕኖ መጠን በሚታይበት ጊዜ የተለያየ መሆኑንም ጥናቱ የጠቆመ ሲሆን ተጽእኖውን በተመለከተ ደግሞ በአንዳንዱ ተላውጦ ላይ በቀጥታ፤ በሌላው ላይ ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑንም ጥናቱ አመልክቶ ነበር።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Gardner & Masgoret (2003) ፍላጎት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ሲገልጹ፣ አመለካከትን በተመለከተ ደግሞ በሁለተኛ የቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሆነ አመልክተዋል (Garry,1970 እና Freeman,1991)። በሌላ በኩል ውጤት፣ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ውስጣዊ ንሺና ውስጣዊ ዝንባሌ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማየት በተከናወነ የጥናት ውጤት መሰረት ፍላጎት ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ ከውጤት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው አሳይተዋል። ስለዚህ ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረተ የሁለተኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት ሲዘጋጅ ከተማሪዎች ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ዝንባሌ እና ተነሳሽነት ጋር ተጣጥሞ መዘጋጀት እንዳለበት ያስገነዝባል።

ስለዚህ በሃገራችን ኢትዮጵያ ተማሪዎች አንደኛና ሁለተኛ ቋንቋን በትምህርትነት እንዲማሩ ሲደረግ ስለ ቋንቋው ያላቸው ፍላጎት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በስርአተ ትምህርት ቀረጻ ወቅት በየክልሎቹ ያለውን ነባራዊ ሁኔታና ተላውጠዎቹ የሚገኙበትን ደረጃ በጥናት አረጋግጦ ቀረጻውን ከዛ አንጻር ማከናወንን ይጠይቃል፡፡ ይህንን መሰረት ያደረገ ዝግጅት ውጤታማ የሆነ ትምህርት ለማከናወን ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ይሄውም በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ዝንባሌና የንሺ ሁኔታን በማጥናት ስርአተ ትምህርትን ማዘጋጀት /መቅረጽ/ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ከዚህ ጋርም ተያይዞ የመስኩ ምሁራን እንደሚገልጹት አንድ ስርአተ-ትምህርት በሚዘጋጅበት ወቅት ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ዝንባሌና የንሺ ሁኔታን በማጥናት መቀረጽ አለበት ይላሉ፡፡

የስርአተ-ትምህርት ዝግጅቱ በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ የሚያልፍ ከሆነ የትምህርት ፕሮግራምን ለማሳደግ፣ የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ለትምህርቱ አመቺ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመምረጥና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን አስቀድሞ ለመከላከል ይረዳል (Bickley, 1990; Bugleski, 1971 እና Craig, 1979)፡፡ በተጨማሪም ትምህርታዊ ምርምሮችን ለማከናወን፣ የፈተና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት (ለማውጣት) እና የሚዘጋጀውን ስርአተ-ትምህርት ከተማሪዎቹ ዝንባሌ፣ አመለካከትና ፍላጎት ጋር አጣጥሞ ለማዘጋጀት ይጠቅማል በማለት ይገልጻሉ(Bickley, 1990; Bugleski, 1971 እና Craig, 1979)፡፡

ይሁን እንጂ ከላይ ከቀረበው ርዕሰ ጉዳይ አንፃር እየተሠራበት ያለው የሃገሪቱን የአንደኛና የሁለተኛ ቋንቋ ሥርአተ-ትምህርትን ስንመለከት ሥርአተ-ትምህርቱ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ስለመሆኑ የተጠና ጥናት መኖሩን ለማየት ተፈልጎ ጥናቶችንም ሆነ በዙሪያው የተጻፉ ጽሁፎችን በተፈለገው መጠንና ይዘት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ሆኖም ግን የሃገሪቱ የሁለተኛ ቋንቋ ሥርአተ-ትምህርት መነሻ የሚያደርገው የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የትምህርት ፖሊሲም ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ወይንም በመረጡት ቋንቋ መማር የሚችሉ መሆኑን መብት የሚሰጥ ነው። ይሄም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይና አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል። የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በተመለከተ በ1986 ዓ/ም ላይ በቁጥር 3.5.3 የወጣው ድንጋጌ የአማርኛ ቋንቋ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት ያገለግል ዘንድ በትምህርትነት ይሰጣል ይላል:: ይሄውም መሠረት የሚያደርገው የሃገሪቱን ህገ መንግስት አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ ሁለትን ነው።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ "አማርኛ የፌደራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል።" በማለት ቀርቧል። ይሄውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ህዳር 29 ቀን 1987ዓ/ም የጸደቀ መሆኑን ያረጋግጣል። እንዲሁም በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና የኦዶቪዥዋል መመሪያ (1994፣62-65) ባዘጋጀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጅና ፕሮግራሞች መጽሔት ላይም ቋንቋን በተመለከተ የቀረበው ሀሳብ እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል::

> *አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት እንዳላቸው ያረጋግጣል። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች የፌዴራል መንግስት የሥራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ እንዲማሩም ያደርጋል። ፖሊሲው ህፃኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋው እንዲማር መብት ቢሰጠውም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን እንዲማር የሚያደርግ ነው። አማርኛ የጋራ መግባቢያ ቋንቋችን እንዲሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተወካዮች አማካኝነት የወሰነና በህገ-መንግስታችን ውስጥ እንዲሠፍር ያደረገ በመሆኑ ተማሪው አማርኛን የመማር ግዴታ እንዲኖርበት ማድረግ ትክክለኛ ነው(በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና የኦዶቪዥዋል መመሪያ 1994'62-65)::*

*ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ* ወይም *የመጀመሪያ ቋንቋ ሆኖ በትምህርትነት መሰጠት እንዳለበት የሚያስገነዝብና ትምህርቱም ተግባራዊ መሆን እንዳለበት የሚያረጋግጥ ሆኖ መገኘቱን ነው።* እንዲሁም በ1986 ዓ.ም በትምህርት

ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ እና በአሁኑ ወቅት እየተሠራበት ያለው የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ሲታይ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጎን ለጎን ለሁሉም ክልሎች በትምህርት አይነትነት ሊሰጥ እንደሚገባ ትኩረት የተሰጠው ስለሆነ በአንዳንድ ክልሎች በምርጫቸው መሰረት የማስተማሪያ ቋንቋ በመሆን እያገለገለ ይገኛል:: ስለዚህ

- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአፊ-ፊት ተማሪዎች ከ1-12ኛ ክፍል፣ ለኢ-አፊፊት ደግሞ ከ3-10ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት እንዲሠጥ የተወሰነ በመሆኑ በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃም ትምህርቱን ከአንደኛ ክፍልና ከሶስተኛ ክፍል መማር ለሚጀምሩ ብሄረሰቦች ወይንም ክልሎች ብቻ ስርአተ ትምህርት ተዘጋጅቶ ትምህርቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለኢ-አፊፊት ደግሞ ከ11ኛ-12ኛ ክፍል ከክልሉ ቋንቋ ወይም አማርኛ በአማራጭነት እንዲማሩት ተወስኗል::

- በአማራ ክልል፣ በአፋር ክልል፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ መስተዳደር ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ስድስተኛ ክፍል በማስተማሪያ ቋንቋነት እና ከ1ኛ-12ኛ ክፍል ባለው ደረጃ ደግሞ በትምህርት አይነትነት ሲሰጥ በሌላ በኩል ደግሞ በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ መስተዳደር የሚገኙ ተማሪዎች እንግሊዘኛን ብቻ በሁለተኛ ቋንቋነት ከ1ኛ-12ኛ ክፍል ስለሚሰጥ በድምሩ ሁለት ቋንቋዎችን እየተማሩ እንደሚገኙ ካለው መረጃ ማረጋገጥ ይቻላል::

- በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ ሶማሊያና ሌሎች ክልሎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አማርኛንና እንግሊዘኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በድምሩ ሶስት ቋንቋዎችን ይማራሉ:: በየክልሉ ያሉ የሌሎች ብሄር- ብሄረሰብ (ህብረ-ብሄረሰብ) ተማሪዎችም የክልሉን ቋንቋ ጨምሮ ሶስት የሁለተኛ ቋንቋዎችን በትምህርትነት የሚማሩ ተማሪዎች እንዳሉ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት መመልከት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል በትገራይ ክልል ውስጥ ያሉ ብሄረሰቦች ኢሮፕና ኩናማ የክልሉን ቋንቋ ጨምሮ ሶስት የሁለተኛ ቋንቋዎችን እንደሚማሩ የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ ይሄውም ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ እንግሊዘኛን፣ አማርኛንና ትግርኛን መማር እንዳለባቸው ነው የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው፡፡

- ተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ ሲታይ ደግሞ ከክልል ክልል የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን።

- በተለይም 12 ክፍል የጨረሱ የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ሲቸገሩ ይስተዋላሉ። ሀሳብን ለመግለጽ መቸገሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ በስራ ቦታም ሆነ በየዩኒቨርስቲው በብዛት እየተስተዋለ ይገኛል።

- በመሰናዶ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ከሚሠጡት ፈተናዎች ውስጥም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አልተካተተም። ይሄውም ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት እና አመለካከት ሊቀንስ እንደሚችል ይገመታል።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ ለኢ-አፊፊት ተማሪዎች በአፋር ክልል፣ በደቡብ ክልልና በጉራጌ ህብረተሰብ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል። በትግራይና በሱማሊያ ክልል ከሶስተኛ ክፍል፣ በኦሮሚያ ክልል ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል። ይህ ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር የአማርኛ ቋንቋ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርትነት እንዲሰጥ ከቀረበው መመሪያ አንጻር ሲታይ የተለያየና ወጥነትን ያልተከተለ የትምህርት አሰጣጥ ስርአት እንዲኖር አድርጎታል። ስለዚህ ተማሪዎች ቋንቋውን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃ ከክልል ክልል የተለያየ ሆኖ ይገኛል። በዚሁ መሰረት በአማራው፣ በኦሮሚያና በሱማሊያ፣ በትግራይ፣ በደቡብ፣ በአፋርና በሌሎች ክልሎችም የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚማሩበት የክፍል ደረጃ የተለያየ በመሆኑ ምክንያት፣ ተማሪዎቹ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት እድሜና የክፍል ደረጃ የተለያየ እንዲሆን አድርጎታል። የእድሜ ልዩነት መኖሩ ደግሞ በቋንቋው ትምህርት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም።

የተማሪዎችን እድሜ በማስመልከት የመስኩ ምሁራን ሲገልጹ እድሜ እየጨመረ ሲሄድ የሰው ልጅ አዕምሮ፣ አካል፣ የአስተሳሰብ ሁኔታ፣ ተግባርን የማከናወን ሁኔታ፣ የአመለካከት እና የተነሳሽነት ሁኔታ እየተለወጠ ይሄዳል(littlewood,1984; Webb, 2000 እና Krashen, 2009)። የአፍሪካ ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን መማር የሚጀምሩበት እድሜ ከ7 አመት በኋላ ስለሚሆን በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይገልጻሉ። እንደ Cook (2001) እና Feer-Man (1991) አገላለጽ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ታዳጊዎች በሂደት

ከአዋቂዎች በተሻለ ሁኔታ በቋንቋ ችሎታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሚደርሱና እንደ አፈፊት በቋንቋው መናገር የሚችሉ መሆኑን ያቀርባሉ(Lightbown, 2011)። ስለዚህ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር መጀመር ያለበት የዕድሜ ደረጃ /ክልል/ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን መማር በሚጀምርበት የዕድሜ ክልል ላይ መሆን አለበት በማለት ይገልጻሉ (Lightbown, 2011; Cook,2001 እና Feer-Man,1991)።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ርእሰ ጉዳዮች አነሳሽነት አጥኚው የብሄር-ብሄረሰብ ተማሪዎች የጋራ መግባቢያ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና ውጤት ምን እንደሚመስል በማየት በክልል ተማሪዎች ዘንድ ያለውን ልዩነትና ተመሳስሎ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማረጋገጥ ሲባል ይሄንን ጥናት ማከናወን አስፈላጊ እንዲሆን ያደርገዋል። ስለዚህ አጥኚው በዙሪያው ያሉ የችግሮችን ስፋትና ጥልቀት ለይቶ ለማየት ሲል በሀገሪቱ ክልሎች ስር የሚገኙ ተማሪዎችን የመረጃ ምንጭ እንዲሆኑ በማሰብ ክልሎችን በናሙናነት መርጦ ይሄንን ጥናት ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። በተጨማሪም ለብሄር-ብሄረሰብ (ህብረ-ብሄረሰብ) ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ሲሰጥ፡-

- በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት፣ተማሪዎች ለሁለተኛ እና ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ፍላጎት ምን እንደሚመስልና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚዳስስ ጥናት አለመካሄዱ፣
- የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት የሚያስተምሩ ክልሎች ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምርበት የክፍል ደረጃና የተማሪዎች የእድሜ ደረጃ በመለያየቱ ምክንያት፣ ለምሳሌ ያህል በአፋር ክልል ከአንደኛ ክፍል፣ በትግራይ ክልል ከሶስተኛ ክፍል፣ በኦሮሚያ ክልል ከአምስተኛ ክፍል አንስቶ ትምህርቱ መሰጠት ይጀምራል። በአንጻሩ ደግሞ በአማራው ክልል፣ በአዲስ አበባና በድሬደዋ መስተዳድር ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምረው ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖም በማገልገሉ የተነሳ በክልሎች ዘንድ የትምህርት አሰጣጥ ልዩነት መኖሩን መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት፣
- በሌላ ክልል ተምሮ ለምሳሌ በኦሮሚያ፣ በሱማሊያና በትግራይ የሚገኙ ተማሪዎች እስከ አምስተኛና ስድስተኛ ክፍል የደረሱ ተማሪዎች ወደ አዲስ አበባ በተለያየ ምክንያት

ሲመጡና ትምህርቱ አዲሳባ ሆነው ለመማር ቢፈልጉ ካሉበት የክፍል ደረጃ ጀምሮ መቀጠል ሲቸገሩ መስተዋሉና እንደገና ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ለመማር መገደዳቸው፣

- የሥራ ቋንቋን በተመለከተም በኦሮሚያ ክልል ኦሮሚኛ፣ በትግራይ ክልል ትግርኛ፣ በሱማሊያ ክልል ሱማሊኛ ሲሆን በአፋር ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራው ክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አማርኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እያገለገለ በመሆኑ ምክንያት፣
- አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እንዲሰጥ በፌደራል ደረጃ እየተዘጋጀ ያለው ስርአተ ትምህርት በየክልሉ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሚያሳድረው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ ምን እንደሚመስል በበርካታ ሰዎች በግምት በርካታ አስተያየቶች እየተሰጡ ይገኛሉ። ነገር ግን በዚህ በሰለጠነው አለም እየተሰጠ ያለው አስተያየት ከግምት በዘለለ በጥናት ላይ የተደገፈና በተጨባጭ መረጃ ላይ ተደገፎ የሚቀርብ አይደለም። ስለዚህ ግምታዊ እሳቤን መሰረት አድርጎ፤ ይሄነው ብሎ ሀሳብ ከመስጠት ይልቅ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተጨባጭ መረጃን መሰረት ያደረገ ምላሽና አስተያየት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት፣
- ትምህርቱን ከአንደኛ ክፍልና ከሶስተኛ ክፍል ማስተማር ለሚጀምሩ ክልሎች በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ስርአተ-ትምህርት እየተዘጋጀላቸው ክልሎቹም ከራሳቸው የክልል ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ማስተካከያ እያደረጉ ትምህርቱን እየሰጡ ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የሚዘጋጀው ስርአተ-ትምህርት ትምህርቱን ከአምስተኛ ክፍል ማስተማር የሚጀምርን ክልል ያካተተ አይደለም። ትምህርቱን ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ መስጠትን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት፣
- የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋ፣ በአፍመፍቻ ቋንቋ፣ ትምህርትነት ሲማሩ የነበሩትና ከተለያየ የክፍል ደረጃ መማር የጀመሩ ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ ሁሉም በእኩል ደረጃ ላይ ይደርሳሉ/ይገኛሉ ተብሎ በመገመቱ ምክንያት በአንድ አይነት መጽሀፍ እንዲማሩ መደረጉ ትክክል መሆን አለመሆኑን መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት፣

- ትምህርት ሚኒስቴር ታህሳስ 2002 ዓ/ም (እ.ኤ.አ. ታህሳስ 2010) ባዘጋጀው የስርአተ-ትምህርት ትልመ ተግባር ላይ እንደቀረበው የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርነት ከ3ኛ-6ኛ ክፍል ለሚማሩት ተማሪዎች በሳምንት ሶስት ክፍለ ጊዜ፤ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ለሚማሩት ደግሞ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ እንዲማሩ የተመደበ ስለሆነ በክፍለ ጊዜ መለያየት ምክንያት ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት፣
- በአስረኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ላይ አማርኛ ቋንቋ ለሁሉም ክልል ተማሪዎች አንድ አይነት ፈተና በመዘጋጀቱ ትክክል መሆን አለመሆኑን ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት እና
- በየክልሉ ያሉ ተማሪዎችን ስንመለከት፤ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ በአማራው ክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደርና በድሬደዋ ከተማ መስተዳደር የሚገኙ ተማሪዎች አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ብቻ ሲማሩ በተቀሩት ክልሎች በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በሱማሊያ፣ በአፋር ክልል፣ በደቡብና በቤኒሻንጉል ግሙዝ ክልሎች ያሉት ተማሪዎች ሁለት የሁለተኛ ቋንቋዎችን በትምህርትነት እየተማሩ የሚገኙ በመሆናቸው ምክንያትና እነዚህም ምክንያቶች በክልሎች መካከል ልዩነት የሚፈጥሩ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይሄንን ጥናት ለማከናወን የመነሻ ሀሳብ ሆነዋል።

## 1.3 የጥናቱ አቢይ ዓላማ (General Objctive of the Study)

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ ልሳነ ብዙ የሆነ ህብረተሰብ በሚኖርባት ሃገራችን ኢትዮጵያ ተማሪዎች የጋራ መግባቢያ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ ከክልል፣ ከእድሜ፣ ከመኖሪያ ቦታና ከፆታ አንጻር ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎት እና ውጤት ምን እንደሚመስል፣ የተላውጦዎቹ የእርስ በእርስ ግንኙነትና በቋንቋው ትምህርት ላይ የሚኖራቸውን ተጽእኖ መመርመር ነው።

### 1.3.1 ዝርዝር ዓላማዎች (Specific objectives of the study)

1 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤትና በእድሜ መካከል ያለውን ዝምድና(ግንኙነት) ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር መፈተሽ፣

2. በየክልሉ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልሎች መካከል የአመለካከት ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር፣

3. በየክልሎቹ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልሎች መካከል የፍላጎት ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር፣

4. በየክልሉ ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በክልሎች መካከል የችሎታ የምዘና ውጤት ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር

5. እድሜ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ መኖር አለመኖሩን ማየት፣

6. የህብረ ብሄር ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ትምህርትን ከተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ መማር በመጀመራቸው ምክንያት በዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በተመሳሳይ የአመለካከት፣ የፍላጎት እና የውጤት ደረጃ ላይ መድረስ መቻላቸውን መፈተሽ፣

7. በገጠርና በከተማ ከሚኖሩ ተማሪዎች አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በተማሪዎች መካከል የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ልዩነት መኖሩን መፈተሽ፣

8. በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ባላቸው አመለካከት ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡትን ውጤት ፆታዊ ልዩነት መኖሩን መመርመር እና

9. ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ለሁሉም ለአንደኛና ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በአንድ አይነት ስርአተ-ትምህርት እንዲማሩ መደረጉ በየክልሉ ያለውን የተማሪዎች እውቀትና ችሎታን ከግምት ውስጥ አስገብቶ የቀረበ መሆኑን መፈተሽ ናቸው።

## 1.4 ጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ በዋናነት የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች ይመልሳል

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤትና እድሜ መካከል ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ምን ግንኙነት አለ?
2. ከእድሜ አንጻር የአማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በተማሪው ውጤት፣ አመለካከትና ፍላጎት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ይኖር ይሆን?
3. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ያላቸው አመለካከት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
4. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ይመስላል?
5. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት በመማር ሂደት ላይ በየክልሉ ከሚገኙ ተማሪዎች አንጻር ሲታይ የውጤት ልዩነት ይኖር ሆን?
6. የህብረ ብሄር ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ መማር በመጀመራቸው ምክንያት በዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ላይ ሲደርሱ የችሎታ ምዘና ውጤታቸው በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
7. ከወንድና ከሴት ተማሪዎች አንጻር ቋንቋን ለመማር ባለ ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የታን መሰረት ያደረገ ልዩነት ይኖር ይሆን?
8. በገጠርና በከተማ አካባቢ ከሚኖሩ ተማሪዎች አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በተማሪዎች ውጤት፣ አመለካከትና ፍላጎት ላይ የሚስተዋል ልዩነት፣ ተጽእኖና የተላውጦዎቹ የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን ይመስላል ?
9. አማርኛን በአንደኛና በሁለተኛ የቋንቋ ትምህርትነት በተለያየ የትምህርት ዝግጅትና ስርአት ሲማሩ ለነበሩ ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በአንድ አይነት የትምህርት ዝግጅትና ስርአተ-ትምህርት እንዲማሩ መደረጉ የተማሪዎችን የቀደምት እውቀትና ችሎታን ማዕከል አድርጎ የቀረበ ነው? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ ጥናት ነው።

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት(Significance of the Study)

በፌደራልና በሀገር ደረጃ (የብሄር ብሄረሰብ) የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሆኖ ለመስጠት ሲታሰብ በየክልሉ የሚገኙ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና የመማር ፍላጎት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አስቀድሞ ማወቅ አቢይ እና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ በፌዴራል ደረጃ የሀገሪቱ የመግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ይግባባበታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በትምህርት ቤቶችም አማርኛ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ይሰጣል፡፡ አንድን ትምህርት ለማስተማርም ሆነ ለመማር ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት በመምህሩ ዘንድም ሆነ በተማሪው ዘንድ ያለውን አመለካከትና ፍላጎት ከነ-ምክንያቱ ማወቅ መቻል በትምህርት የአሰጣጥ ስርአት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታትና ለማስተካከል ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንጻር ይሄ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. የዚህ ጥናት መከናወን ለቋንቋውና ለቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ አውጪዎች ያለውን የቋንቋ ትምህርት ጥቅል ፖሊሲን ለማሻሻል ወይም ለማስተካከል እና አዲስ የቋንቋ ፖሊሲ ለማውጣት የመነሻ ምክንያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

2. ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ያላቸውን የፍላጎት፣ የአመለካከት ደረጃና በትምህርቱ እያስመዘገቡ ያለው ውጤት ምን እንደሚመስል በማየትና በዙሪያው የሚስተዋሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣትና በማሳየት ለፖሊሲ አውጪዎችም ሆነ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ መፍትሄዎችና ማስተካከያዎች እንዲሰጡ ለማስቻል በመረጃነት ያገለግላል፡፡

3. በቋንቋ ትምህርት ወቅት በእድሜ፣ በአመለካከት እና በፍላጎት ልዩነት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳል፡፡

4. መምህራን የማስተማር ዘዴያቸውን ከተማሪዎች ፍላጎት፣ አመለካከትና ከአካባቢያዊ ሁኔታ አንጻር እንዲያስተካክሉና ካለው የክልል ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ልዩ እገዛን እንዲያደርጉ መረጃን ይጠቁማል፡፡

5. ከክልል፣ ከፆታ፣ ከእድሜ እና ከቦታ አንፃር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት ላይ የሚኖር ተጽእኖን በመለየት፤ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለተማሪዎች ልዩ እገዛና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል መረጃን ይጠቁማል::

6. ለመርሃ ትምህርትና የመርጃ መሳሪያ አዘጋጆች የሁሉንም የክልል ተማሪዎችን ያማከለ መርሀ ትምህርትና የመርጃ መሳሪያ እንዲያዘጋጁ የመነሻ ሃሳብን ይሰጣል::

7. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና አመለካከት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ስለሚለዩ ችግሮቹ የሚወገዱበትን መንገድ ያመለክታል።

8. ወደፊት በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኒዎች የጥናት አቅጣጫን ከማሳየቱ በተጨማሪ ለተለያዩ የጥናት መስኮች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

9. አማርኛ የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ሆኖ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ ወጥነቱን ጠብቆ በየትኛው የእድሜ ክልልና የትምህርት ደረጃ መጀመር እንዳለበት በቂ መረጃን ይሰጣል።

10. በዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ደረጃ እየተሰጠ ያለው የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ትምህርት በየክልሉ እየተማሩ ላሉ ተማሪዎች እንደየ ችሎታቸው ተመዝኖ ስለማይሰጥ በየክልሎቹ መካከል የሚስተዋለውን ልዩነት ለማጥበብና የመፍትሄ አማራጭን እንዲወሰድ አቅጣጫዎችን ያመላክታል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን(Delimitation of the Study)

ጥናቱ የሚከናወነው በኦሮሚያ ክልል፣ በአፋር ክልል፣ በትግራይ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ ሆኖ ዋና ትኩረቱ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ነው። ጥናቱ በዘጠነኛ ክፍል ላይ እንዲያተኩር የተደረገበት አቢይ ምክንያት አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ ክልሎች ከተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩ ስለሆነ ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በእኩል የክህሎትና የእውቀት ደረጃ ላይ ይገኛሉ በማለት በተመሳሳይ የመጻፍና

/የትምህርት ዝግጅት/ እንደማሩ በመደረጉ ምክንያት ተማሪዎቹ በእዚህ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙበትን የክህሎትና የእውቀት፣ የአመለካከትና የፍላጎት ልዩነትና አንድነትን ለማየት ምቹ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ካለው ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ ችግር ምክንያት በተለያዩ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉትን ተማሪዎችን ወስዶ ማጥናት ባለመቻሉ ምክንያት አጥኚው በተለያየ ክልልና አካባቢ ሁኔታ እንዲሁም ከተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ ሲማሩ የነበሩት ተማሪዎች 9ኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ ተመሳሳይ በሆነ አመለካከት፣ ፍላጎት እና የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ መድረስ መቻላቸውን ማየት የሚቻለው በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ ስለሆነ ለጥናቱ ምቹ በመሆኑ ነው።

ስለዚህ የተቀረውን የክፍል ደረጃ፣ በየክልሉ የሚዘጋጀውን ስርአተ ትምህርትንና መጻህፍትን መፈተሽን ወይንም በፌዴራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ለክልሎች የሚላከውን ስርአተ ትምህርት በተመለከተ፤ ክልሎች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የትምህርቱ ይዘትና መጠን ሳይለቅና ሳይቀይር እንዴት እየተጠቀሙበት እንዳሉ ማየትን አስመልክቶ በዚህ ጥናት የሚካተት አይደለም። በተጨማሪም የግል ትምህርት ቤቶች ካላቸው ልዩ ባህሪ አንጻር ይሄ ጥናት አይመለከትም።

በየክልሉ ያለውን የአንደኛ ደረጃ መምህራን (ከ3-8ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን) ስልጠናን በተመለከተም እጩ መምህራኑ እንዴት ተመልምለው እየሰለጠኑ እንዳሉና የስልጠናውን ይዘት ይሄ ጥናት በቀጥታ አይመለከትም። ለጥናቱ የሚሆን መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜም በመረጃ ሰጪነት የሁሉንም ክልል ተማሪዎች አያካትትም። ምክንያቱም ይሄ ጥናት በዚህ ደረጃ ላይ መጠናቱ የሌላኛውን ክልል ነባራዊ ሁኔታን ማሳየት የሚችል በመሆኑ ነው። ስለዚህ መረጃ የሚሰበሰበው የተወሰኑ ክልሎችን በናሙናነት በመምረጥ በክልሎቹ ከሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን ላይ ነው።

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማን በዚህ ጥናት ውስጥ እንዲገባ የተደረገበት አቢይ ምክንያት ክልሎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ ለትምህርቱ ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤት በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በማየት ሂደት ላይ ለንጽጽር እንዲያገለግል ተፈልጎ የቀረበ ነው፤ እንጂ የጥናቱ ዋና ክፍል ሆኖ የቀረበ አይደለም።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የህብረ ብሄረሰብ (Pluralistic Society) ምንነት

ህብረ ብሄረሰብ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ብዝሃነት ያላቸው ብሄረሰቦች በስነልሣን፣ በባህል፣ በእምነት እና በፖለቲካዊ አስተሣሠብ ልዩነት ኖሯቸው ነገር ግን በአንድ የመንግስት ወይም የኢኮኖሚ ሥርዓት ስር የሚገኙ ሆነው እኩል እውቅና ያላቸው ከሆነ በህብረ ብሄረሰብነት ይገለጻሉ፡፡ May (2008); Golden (1981)ን ጠቅሶ ህብረ ብሄረሰብ ማለት የተለያዩ ቡድኖች በቋንቋቸው፣ በእምነታቸው፣ በፖለቲካዊ አስተሣሠባቸውና ስርአታቸው እውቅና ያላቸው ወይም በልዩነት ውስጥ አንድነት ያላቸው ናቸው፡፡ Malesevic (2004) ህብረ ብሄረሰብ ማለት በጥልቀት ሲታይ በማህበረሠብ ውስጥ የተለያየ ገፅታ ያላቸው ጐሣዎች/ነገዶች በአንድ የፖለቲካ ጥላ ስር ወይም የተቋም ስርአት ስር በመገኘት ተከባብረውና ተቻችለው በጋራ የሚኖሩበት ሁኔታ ነው ይላሉ፡፡ ስለዚህ ህብረ ብሄረሰብ ሲባል በቋንቋ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ አመለካከት እና ተሣትፎ፣ በሃይማኖት፣ በትምህርትና ስልጠና፣ በስራ ሁኔታ በሁሉም ወይም በከፊል ልዩነት ኖሯቸውና የተከፋፈሉ ቡድኖች /ክፍሎች/ ሆነው፤ ነገር ግን የጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ በእኩልነት የሚስተናገዱ ሆኖ መገኘትን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህም ክፍሎች ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ አንድ የጋራ የሆነና የሚያስተሳስራቸው ነገር ካለ በህብረ ብሄረሰብነት ይገለፃሉ፡፡ የጋራ ጥላ ሲባል ጋራ የሆነ ሀገር፣ በጋራ የሆነ ቋንቋ፣ የጋራ የሆነ ኢኮኖሚ፣ የጋራ የሆነ ባህል፣ ጋራ የሆነ አስተዳደርና ማህበራዊ መስተጋብር ሊሆን ይችላል፡፡

Malesevic(2004) ህብረ ብሄረሰብ ሲባል ውስጣዊ አደረጃጀቱ ሲታይ የተለያየዩ ህብረተሰቦችን የያዘ ሆኖ እነሱም በልዩነታቸው እውቅና ተሰጥቷቸው በአንድ የጋራ ጥላ ሥር፣ የፖለቲካ ተቋም ወይም አስተዳደር ስር ሆነው በልዩነታቸው ተከባብረውና ተቻችለው የሚገኙ ጐሣዎች ወይም ብሄሮች ናቸው፡፡ ለምሣሌ ያህል የተለያየ እምነት ተከታይ፣ የተለያየ የአኗኗር ስርአትና የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት በተለያየ ቡድን የተከፋፈሉ ሆነው ልዩነታቸውን መሠረት በማድረግ እውቅና እና የእኩለነት መብት ያላቸው ከሆኑ ህብረ-ብሄረሰብ ይባላሉ፡፡ ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ገለፃ በመነሣት ህብረ ብሄረሰብ ማለት እኩል እውቅና የተሠጣቸው የተለያየ የቋንቋ ተናጋሪዎች በአንድ የጋራ ቋንቋ፣ አስተዳደር፣ ሀይማኖት

ጥላ ስር የሚገኝ ሆኖ መገኘትና ተከባብረው የሚኖሩ ህዝቦች ህብረ ብሄረሰብ ሊያሠኛቸው እንደሚያስችልም የምሁራኑ ሃሣብ ያስረዳል፡፡

በሌላ በኩል ለህብረ ብሄረሰብ መመስረት አብይና ቁልፍ ጉዳይ ነው፣ ተብሎ የሚነሳው ሐሳብ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይሄውም ከድህረ ቅኝ ግዛት አስተዳደር በኋላ ሁሉም ህብረተሠብና ማህበረሠብ ከውስጥ ገፅታቸው ሲታዩ ወይም ከመዋቅራዊ አደረጃጀታቸው አንፃር ሲታዩ ልዩነት ያላቸው ሆነው በአጠቃላይ ገፅታቸው ሲታዩ ደግሞ የጋራ የሆነ ባህሪ ያላቸው ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሚለያዩበት ባህሪ ያለአድልኦ እውቅና ተሰጥቷቸው በእኩልነት በሚስተናገዱበትና በአንድ የአስተዳደር ስርአት ስር መገኘትን የሚመለከት ሌላኛው ሀሳብ ነው፡፡ ስለዚህ የተለያየ ገጽታ ያላቸው ብሄር- ብሄረሰቦች ሆነው በአንድ በጋራ ጥላ ስር እውቅና ተሰጥቷቸው ያለ አድልኦ በእኩልነት የሚስተናገዱ ከሆነ ህብረ ብሄር ይባላሉ፡፡ በተጨማሪም ህብረ-ብሄር በሌላ ገጽታው ሲታይ ትናንሽ የጐሣ ክፍሎች የጋራ በሆነ በትልቅ የጐሣ ስርአት ሥር ታቅፈው ለእያንዳንዱ የጎሳ ክፍሎች እውቅና ተሰጥቷቸው በእኩልነት ያለልዩነት የሚስተናገዱበት ነው (Will, 1965)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ህብረ ብሄረሰብ ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ የጐሣዎችና ብሄረሰቦች በእምነት፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ አደረጃጀት ልዩነት ኖሯቸው፤ ልዩነታቸውን ይዘው፤ በአንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ስር እውቅና ተሰጥቷቸው ያለአድልኦ በእኩልነት የሚስተናገዱ ከሆነና እንደ ህብርነታቸው ካላቸው ገጽታ አንጻር ህብረ ብሄረሰብ፣ ህብረ እምነት፣ ህብረ ፖለቲካ፣ ወዘተ በማለት መጥራት እንደሚቻል ነው፡፡ ስለዚህ የተለያየ ገፅታ ያላቸው በእኩል ደረጃ የሚገኙ ከሆኑና በአንድ የጋራ ጥላ ስር/በልዩነት ውስጥ አንድ/ ሆነው እርስ በእርስ ተከባብረውና ተቻችለው የሚገኙ እና እኩል እውቅና ኖሯቸው ያለ አድሎ በእኩልነት የሚስተናገዱ ከሆነ በህብረ ብሄርነት መገለጽ ይችላሉ፡፡

## 2.2 ህብረ ብሄርነት ከልሣነ- ብዛህ (Linguistic Plurality) አንጻር ሲታይ

እንደ Coulmas (1997) አገላለፅ የልሳነ ብዛህ ብዙ ቋንቋን መናገር መቻልን የሚመለከት ነው፡፡ ልሳነብዛህ በግለሰብ፣ በብሄረሰብ ወይንም በሀገር ደረጃ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ህብረ-ልሳን ማለት የተለያዩ የቋንቋ ቡድኖች በአንድ ላይ መኖርና ቋንቋዎቹን በእኩልነት የመጠቀም፣ የመንከባከብ፣ የማሣደግ እና እውቅና የመስጠት ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል በቤልጅየም ፈረንሣይኛ በደቡባዊ ክፍል የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በጀርመን ደግሞ በሰሜን ምስራቅ ጀርመን ፈረንሣይኛ-ፍሌሚሽ የስራ ቋንቋ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በሃዋይ የሃዊኛ ቋንቋና የእንግሊዝኛ ቋንቋ በ1978 የሥራ ቋንቋዎች ሆነው ያገለግሉ ነበር፡፡ ዩናይትድ እስቴትም በተወሠኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች የልሣነ ብዙ ተግባራትን እያሣደገች ትገኛለች፡፡ በታሪኳ ውስጥም በተለያዩ ቦታዎች ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ ለምሣሌ ሎውሣና (Lousiana) በጣም ትልቋ የልሣነ ክልኤ የሥራ ቋንቋ ያላት እስቴት ነች፡፡ ፈረንሣይኛ ቋንቋንም የማሣደግና የመጠቀም ህግን አውጥታም ነበር፡፡ እንዲሁም በዩናይትድ እስቴት በ1968 የልሣነ ክልኤ ትምህርት በተወሠነ ደረጃ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በስተቀር ለሌሎቹ ተግባር ላይ ውሏል፡፡

Gray (1987) ምንም እንኳ ኘሮግራሙ ብዙ አስተዳራዊ መመሪያዎችና ደንቦች ቢኖሩትም ከስነ ትምህርት ማሻሻያነቱ አንፃር ሲታይ አንዳንድ ቋንቋዎች በሚኖራቸው ሽፋን የተወሠኑና ጥቂት አካባቢዎችን ከማማከላቸው ምክንያት የተወሰኑ ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የልሳነ ክልኤ ትምህርት ባህልን ከመጠበቅ አንፃር ፋይዳው የጐላ ነው፤ በማለት ማብራሪያ ያቀርባሉ(Coulmas, 1997)፡፡ በዋናነት በሀገር ደረጃ የጋራ መግባቢያ የሆነውን ቋንቋ በትምህርት እንዲሰጥ እያደረገ ያሉበት ሁኔታም ጠንካራ መሰረት ያለው ሆኖ ይገኛል፡፡

እንደ Wardhough(1992) አገላለፅ ህብረ ልሳናት ማለት ከሁለት ቋንቋዎች በላይ እውቅና ሲሠጥ ነው ይላሉ፡፡ እውቅናው ግን ሙሉ በሙሉ፣ ወይንም በከፊል ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ሁለትና በላይ የሆኑ ክፍሎችን የአኗኗር ሁኔታን መሠረት በማድረግ ከአንድ በላይ ቋንቋ በሀገር ደረጃና በህብረተሰብ ውስጥ አገልግሎት ላይ ሲውል ነው፡፡ ለምሣሌ ቤልጅየም፣ ካናዳ፣ ሲንጋፖር፣ ደቡብ አፍሪካ እና ኒውዘርላንድ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የፅሑፍና የሥራ ቋንቋ ያልሆነውን ሃገር በቀል ቋንቋ የስራና የፅሁፍ ቋንቋ እንዲሆን በማድረግ የቋንቋውን ደረጃ አሳድጎ ሁለትና ከዚያ በላይ የሥራ ቋንቋ እንዲኖር የሚያደረግ ሂደታዊ አደረጃጀት ነው፡፡

ለዚህም እንደ ምሣሌነት የሚጠቀሱ ቋንቋዎች ባህሣ በእንዶኔዥያ፣ ፎክፒስያንና ፖፑአ በኒውጊንና፣ ሄብሩ በእስራኤል፣ ታሉግ በፊሊፒን እና ኩፑአ በፔሩ በዚህ ሂደት እያደጉ ናቸው። በዚህም መሰረት በትምህርት ፖሊሰያቸው ውስጥ በማስገባት የቋንቋ ትምህርታቸውን እያቀዱ ቋንቋዎቹን በትምህርት አይነትነት እያስተማሩ ይገኛሉ።

Hoffman(1991) የቋንቋ እቀዳ ሂደት በውስጡ አራት አይነት ፍሬሃሣቦችን መሰረት አድርጎ የሚከናወን መሆኑን ይጠቅሣሉ። እነዛም ስነልሣንን መጠቀምና መያዝ፣ ልሣነ-ብዙነት፣ ሃገር አቀፋዊ ቋንቋን ማሣደግና፣ አለማቀፋዊ ቋንቋን ማሣደግ ናቸው ብለው ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ልሣነ ብዙነት ነው። ልሣነ ብዙነት በጥሬው ሲገለፅ የተለያዩ የቋንቋ ቡድኖች መኖርና የቋንቋ ተናጋሪዎቹ በራሳቸው ቋንቋ መተማመን ሲችሉና ሲገለገሉበት ነው። ከደረጃቸው አንፃር፣ ለስራ ከሚሠጡት ግልጋሎትና ከሚሠጡት ድጋፍ አንፃር፣ ለሌሎች ቋንቋ ከሚሠጥ ድጋፍ አንፃር ነው። ለምሣሌ ያህል በደቡብ አፍሪካ፣ በሲንጋፖር፣ በቤልጅየምና በፊንላድ ሁለትና ከሁለት በላይ የስራ ቋንቋ ተግባር ላይ የሚውልባቸው ሀገሮች ናቸው። እንዲሁም ሁለት ቋንቋ በእኩል ደረጃ የሚስተናገድባት ሀገር ካናዳም ተጠቃሽ ናት።

በካናዳ በእንግሊዝኛ ቋንቋና በፈረንሣይኛ ቋንቋ መካከል ያለው ግንኙነትና ተግባር አንድ አይነት ነው። በዚች ሀገር ሁለት ቋንቋ የሚናገሩ ህዝቦች እንዳሉባትና ሁለት የሥራ ቋንቋ ያላት ሃገር ናት። በቋንቋዎቹ መካከል ያለው አገልግሎትና ግንኙነትም ማዕከላዊነቱን የጠበቀ ነው፤ በማለት ይገልጻሉ። በሌላ በኩል ሲታዩ ደግሞ በካናዳ የቋንቋ ብዛትና ስርጭት ምን እንደሚመስል William(1984) ሲገልጹ ካናዳ ልሣነ ክልኤ ሃገር ናት ቢባልም ሀገር በቀል ሆነው የሚነገሩ ቋንቋዎች (ተወላጅ ቋንቋዎች) አስራ አንድ ናቸው ይላሉ። እነዚህንም ቋንቋዎች የሚናገሩ ቤተሠቦች እንዳሉ ነው የሚገለጸው። የቋንቋዎቹም ስም አልጐንቁኢዶን፣ አንታፖስኪአን፣ ሣሊሻን፣ ሲኦሉኣን፣ ትሊንግስት፣ ትስማሺያን፣ ኤክስም፣ አለኡት፣ ሃኢዳ፣ ኢሮጉአኡን፣ ኩቲአን እና ዋካሻም ናቸው።

በተጨማሪም ወደ ካናዳ ተሠደው የሄዱ ሌሎች የተለያዩ ቋንቋዎች እንዳሉም ይነገራል። ከዚህ አንፃር ብዙ ልሣናዊ ስርጭት በካናዳ ይገኛል። እያንዳንዱ ቋንቋዎች እርስ በእርሳቸው ንክኪ አላቸው። ይሁን እንጂ ካናዳ ልሣነ ብዙ ሃገር ስትሆን ከስራ ቋንቋ አንጻር የባለሁለት የሥራ ቋንቋ ሃገር ነች። ስለዚህ የቋንቋ እቀዳ ስርአቱ በሀገር ደረጃ ሲታይ ለእንግሊዘኛና ለፈረንሣይኛ ቋንቋ የእቅዱ ሂደት ተመሣሣይ እንደሆነ ያመለክታል።

ከላይ በተለያየ ቦታ ለማየት እንደተሞከረው ህብረ ልሣናት ሲባል ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድንና አሰራርን በመከተል ለሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ቋንቋዎች እኩል እውቅና የተሰጠ ከሆነ ነው። ካናዳን ብንወስድ በዚች ሀገር እንግሊዝኛና ፈረንሣይኛ እኩል እውቅና ስላላቸው ልሳነ ክልኤ አጠቃቀም የሚከናወንባት ሃገር ነች። ይህንንም በተመለከተ ከተለያዩ ሃገራት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃርም ሰፋ አድርጐ ማየት ይቻላል።

የሀገራችን ኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ የየክልሉ ቋንቋዎች ባሉበት የየክልሉ የስራ ቋንቋ እንዲሆኑና የአማርኛ ቋንቋ ከክልል ቋንቋነት በተጨማሪ የፌደራል የሥራ ቋንቋ እንዲሆን፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲያገለግል በትምህርትነት መሰጠት አለባቸው በሚል ተመርጠው በትምህርትነት እየተሰጡ ይገኛሉ። ስለዚህ ቋንቋዎቹ ከተመረጡበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እውቅና ተሰጥቷቸው አገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። ለቋንቋዎቹ በተሰጣቸው እውቅና መሰረት በትምህርት አይነትነት እንዲሰጡ ተወስኖ በስርአተ-ትምህርት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። ስለዚህ ሀገራችን የህብረ-ልሳን ሀገር መሆኗንና የትምህርት ስርአቱ ከዚህ አንጻር የተቃኘ መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

## 2.3 ህብረ ብሄርነት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሄረሠቦች ሃገር ስትሆን፣ ባለብዙ ቋንቋዎች፣ ባለብዙ እምነት፣ ባለብዙ ማህበረሠብ፣ ባለብዙ ጐሣ፣ ባለብዙ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ባለብዙ ፖለቲካዊ አስተዳደርና የአመለካከት ስብጥር ያለባት ሀገር ናት። በመሆኑም በኢትዮጵያ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ከሰኔ 24-28/83 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተካሄደው ጉባኤ ለሁለት አመታት የሚዘልቅ የሽግግር ወቅትን ሲያፀድቅ በአንቀፅ ሁለት ስር ብሄር ብሄረሠቦችና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሠን መብት፣ የራስን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ባህልና ታሪክን የማበልፀግ፣ በቋንቋ የመጠቀምና ቋንቋን የማሣደግ መብት ተካቷል። ለዚህም መሠረቱ ትምህርት ዋናው መሳሪያ በመሆኑ፤ ህዝቦች በራሣቸው ቋንቋ እንዲማሩ የተወካዮች ምክር ቤት፤ ብሄር ብሄረሠቦች በቋንቋቸው መማር እንዲችሉ፤ ትምህርት ስለሚሠጥባቸው ቋንቋዎች በሚመለከትም ከሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ጋር በማያያዝ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ሀገሪቱ አውጥታለች። በየአካባቢው የሚገኘው ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን፤ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ /በየቋንቋዎቹ/ ከ1ኛ-6ኛ በአፋጣኝ ትምህርት መስጠት

እንዲጀምሩ...ወዘተ የመሣሠሉት ድንጋጌዎች የሽግግር ወቅት የወጡ በመሆናቸው ተጠቃሽ ናቸው። በዚሁ መሠረት በአብዛኛው በሃገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ለብሄር- ብሄረሰቦች ከ1986 ሚያዝያ ወር ጀምሮ ዝግጅቱ እንዲጀምር ይፋ ተደርጎ የልሣነ ብዙ ትምህርት በሃገሪቱ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል።

የቋንቋ ፖሊሲ ለብቻው ባይወጣም ጥቅል የሆነ የቋንቋ ፖሊሲ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ አምስት ንኡስ አንቀጽ ሁለት ላይና በአንቀጽ ሠላሣ ዘጠኝ ንኡስ አንቀጽ ሁለት ላይ በድጋሚ የተረጋገጠ ሲሆን በተለይም በአንቀፅ 39 ቁጥር ሁለት ስር የሚከተለው ይገኝበታል። "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግና፣ ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው" ይላል።

የፊደላትንም አጠቃቀም በተመለከተ ብሔር ብሔረሠቦች የፈለጉትን ፊደል መርጠው የሚጠቀሙ ስለሆነ ለቋንቋዎቹ የፊደል ቀረፃ ተግባራትም ተከናውነዋል። በሌላ በኩል በሃገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ህዝቦች ከላይ ከቀረበው ፖሊሲ በመነሣት በእያንዳንዱ ብሄራዊ ክልል ውስጥ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ ቋንቋዎች ስራ ላይ ውለው የክልል የሥራ ቋንቋ ሆነዋል (Wondwosen & Bloor, 1996)።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎች የሥራ ቋንቋ ሆነው ስለሚያገለግሉና እያገለገሉ ስለሚገኙ ብዙ ቋንቋዎች ተግባር ላይ ውለዋል። በሌላ በኩልም ለእምነት እኩለነት እውቅና ስለተሰጠ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የአማርኛንና የግዕዝ ቋንቋን በጋራ የሚጠቀም ሲሆን የእስልምና እምነት ተከታይ ደግሞ የአረብኛ ቋንቋን በዋናነት የሚጠቀም ሲሆን ሀገሪቱ ከእምነትና ከቋንቋ አጠቃቀም አነፃርም ልሣነ ብዙ ሀገር ሆነች። በቋንቋ እቀዳው ላይም የልሣነ ብዙ የቋንቋ እቀዳን ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች(Wondwosn & Bloor, 1996)።

ይሁን እንጂ የጋራ የሆነ ቋንቋ አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ አማርኛ ቋንቋ ለሁሉም ብሄር/ብሄረሰብ የጋራ መግባቢያ እንዲሆንና የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ መሆን እንዳለበት በህገ መንግስቱ አንቀጽ አምስት ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ስለዚህ በኢትዮጵያ አማርኛ የጋራ ቋንቋ እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ ሁሉም ክልልሎች ቋንቋውን መልመድና መማር እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው።

ስለዚህ ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ስንመረምረው ለቋንቋ ትምህርትና ለቋንቋ ለመዳ አዎንታዊ የሆነ አመለካከትን የሚፈጥር ስርአት መኖሩን ያመለክታል። ይሄውም የራስን ቋንቋ ከማሳደግ ጎን ለጎን የጋራ የሆነውን ቋንቋ መማሩና ማወቁ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ነው፤ የሚያመለክተው። ሰፊ የእውቀት ስርጭት የሚገኘው ከሰፊ የቋንቋ ስርጭት ነው። ስለዚህ በሀገሪቱ ሰፊ የቋንቋ ስርጭት መኖሩ ሰፊ የሆነ የእውቀት ሽግግር መኖሩን ያመለክታል።

በጥቅሉ ህብረ ብሄርነት ከኢትዮጵያ አንጻር ሲታይ በየክልሉ የሚገኙ ብህር በሄረሰቦች ባሉበት ክልል ውስጥ ያላቸው ልዩነት እንዳለ ሆኖ በጋራ ሚያስተሳስራቸው ነገር አለ። ያም የጋራ ኢኮኖሚ፣ የጋራ የስራ ቋንቋና የጋራ አስተዳደር ያላቸው ሲሆን በልዩነታቸው ደግሞ ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩ ናቸው። በሀገር ደረጃም የተለያየ ክልላዊ አስተዳደርና ክልላዊ የስራ ቋንቋ ቢኖርም እነዚህ የተለያዩ ክልሎች በሀገር ደረጃ(በፌደራል መንግስት ደረጃ) ደግሞ የጋራ የሆነ የስራ ቋንቋ፣ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ ጥላ ስር ሆነው በልዩነታቸው ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖርባት ሀገር ስለሆነች ሀገራችን ኢትዮጵያ በህብረ- ብሄርነት የምትገለጽ ሃገር ነች።

## 2.4 የልሣነ-ብዛህነት እንደ ሀብት ወይስ እንደ ኪሳራ (Language Pluralism as an asset or as a Liability) ሲታይ

ልሣነ-ብዛህነትን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የሚቀርብ አዎንታዊና አሉታዊ አስተያየት አለ። ልሣነ-ብዛህነትን እንደ ኪሣራ የሚቆጥሩ ምሁራን እንዳሉ ሁሉ ጠቀሜታው የጐላና እንደ ከፍተኛ ሀብት የሚቆጥሩ ምሁራን በስፋት አሉ። Chia (2006) በሦስተኛው አለማት ያሉ ምሁራንንና በ1960ዎቹ አካባቢ ያሉትን ምሁራን በመጥቀስ ልሣነ ብዛህነት ለአንድ ሀገር ከፍተኛ ችግር ነው። በትክክሉ የአንድን ሃገር እድገት የሚያዘገይ በብሄራዊ አንድነት ላይ ችግር የሚፈጥርና የህዝቦችን አንድ መሆንና መዋሐድ ላይ ችግር እንደሚፈጥር ይገልፃሉ። በተለያዩ ሀገራትም ችግር ፈጥሮ እንደነበር በምሣሌነት የሚጠቅሷቸው ሃገራት አሉ። እንደ Fishman (1972፡ 387) አገላለፅ ልሣነ ብዙ በሆኑ ሃገሮች የፖለቲካ ውጥረቱ (Political Tension) ከፍተኛ እንደሆነ በማስመልከት በአንድ ወቅት በቤልጅየም የተከሰተውን በምሣሌነት ያቀርባሉ።

ቤልጅየም የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገርባት ሃገር ናት። በተለይ ሁለት የተለያዩ ትልልቅ ቋንቋዎችና በተናጋሪ ህዝብ ብዛታቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ቋንቋዎች አሉባት። አንደኛው ፍሎሚንግ ሲሆን ሁለተኛው ዋሉን ነው። ዋሉን ቋንቋ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ፣ ባህላዊ እድገትን፣ ፖለቲካን እና የፍሎሚንግ ቋንቋ ላይ ሳይቀር ተፅእኖ እያሣደረ የሚገኝ ቋንቋ ነው። ይሁን እንጂ የሁለቱ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአኗኗር ሁኔታ ሲታይ የተለያየ ነበር። በዚህ ሣቢያ ከጊዜ ወደጊዜ በሁለቱ ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ መካከል የፖለቲካ ውጥረትን እያስከተለ ሄደ። እ.ኤ.አ በ1960 ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ውጥረት እስከ ማስነሣት ደርሷል። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ውጥረቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስተካከለ በመሄድ የልሣነ ብዙ የሥራ ቋንቋ ሃገር መሆኗን ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ የምትግባባበት የጋራ የሆነ መግባቢያ ቋንቋ ከማስቀመጥ አላገዳትም።

እንዲሁም Chia (2006) በድጋሜ የተለያዩ የምሁራን ሀሳብን ሲገልፁ በሃገር በቀል ቋንቋ ውስጥ ልዩነት ካለ ብሄረሠቦች ለየብቻ እንዲሆኑና በሃገር ውስጥ የመከፋፈል እድል እንዲፈጠር ስለሚያደርግ የሀገር አንድነት እንዲዳከም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው ይላሉ። የብሄር አንድነት እንዳይኖር ከማድረጉም ባሻገር የብሔራዊ መተጋገዝን ያዳክማል። በልዩነት ውስጥ አደገኛ የሆነ ያለመቻቻል ስሜት እንዲኖር ምክንያት ነው። በሌላ በኩል ልሣነ ዋህድ መሆን ሃገራዊ አንድነትን ለመገንባት ከፍተኛ ሃይል ነው ይላሉ። በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች በጣም ሠፊ የሆነ የቋንቋ ስርጭት በመኖሩ የፖለቲካ ውጥረት እየተፈጠረ በኢኮኖሚው እድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ እንደሚገኝ የምሁራኑን ሀሳብ ያቀርባሉ።

አክለውም Chia (2006) ለምን እነዚህ ምሁራን ይህንን ጉዳይ በደንብ ማየት ተሣናቸው? ምንም እንኳ አንድ ቋንቋ የብሔራዊ ባንዲራ ነው ቢባልም፤ በአንድ ሃገር መለያ ምልክት መሆኑ አስቀድሞ የታወቀ ቢሆንም፤ የአንድነት ስሜትን የሚፈጥር ቢሆንም፤ የተለያዩ ብሔረሠቦችና የቋንቋ ቡድኖች የሆኑት በጋራ አስተሣሠባቸው እና ከመድረሻ ነጥቦቻቸው አንፃር ሲታዩ ደግሞ እነዚህን ወደ አንድ የፖለቲካ ጥላ ስር ማምጣት እንደሚቻል ሰፊ ማብራሪያ ይሠጣሉ። ለዚህም በምሣሌነት ኒዘርላንድን ይጠቅሣሉ።

በሌላ በኩል ባለአንድ ቋንቋ ሃገሮችና እንዲሁም አንድ ብሔራዊ ቋንቋ ብቻ ያላቸው ሃገሮች የቡርንዲ ብሔራዊ ቋንቋ ኪሩንዲ ነው። የሩዋንዳ ብሄራዊ ቋንቋ ኪንያሩዋንዳ እንዲሁም ሱማልያም ልሣነ ዋህድ ሃገር ስትሆን ሱማልኛ የብሄራዊ ቋንቋ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሃገራት ልሣነ ዋህድ የሆነ ፖለቲካን የሚያከናውኑ ሃገራት ሲሆኑ በብሔራዊ አንድነት ግንባታ

ወቅት አስቸጋሪና አስፈሪ ሁኔታዎች ገጥሟቸው ተስተውለዋል፡፡ ስለዚህ ስለ አንድ የጋራ ቋንቋ የሚያስማማው ጉዳይና ለብሔራዊ ግንባታ ከላይ የቀረበው መስፈርት አፈታሪክ ነው የሚሆነው፡፡ ለብሔራዊ ግንባታ እንደ ችግር የሚነሣው ጉዳይ በአንድ ሃገር ውስጥ ብዙ ቋንቋን እንደ ምክንያት ማንሣቱ ተገቢ አይደለም በማለት ይገልፃሉ፡፡ እንደውም ብዙ ቋንቋ መኖር የባለ ብዙ ባህል ባለቤት መሆን እንዲቻል ያደርጋል፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሀገር ደረጃም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ብዙ ቋንቋን መናገር መቻል የሚኖረው ፋይዳ ሰፊ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ቋንቋን መናገር ከብዙ ባህላዊ እሴቶች ጋር የእርስ በርስ መስተጋብር እንዲኖር ስለሚያደርግ ሰፊ እውቀትን መገብየት ያስችላል፡፡ ስለዚህ ብዙ ቋንቋን መናገር መቻል ጠቀሜታው ሰፊ እንደሆነ ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሁለትና ከዛ በላይ ቋንቋን ማወቅ/መናገር/ መቻል ከሌሎች ሀገሮች፣ ክልሎችና ማህበረሰቦች ጋር በቀላሉ መግባባት ያስችላል፣ ነገሮችን ከሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆነ አቅጣጫዎች አንፃር ማየት ያስችላል፣ አዕምሮ ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል ይላሉ፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ አንጻር ብዙ ቋንቋን መማር ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ነው፤ መረዳት የሚቻለው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያንም የባለብዙ ቋንቋ ሀገር ነች፡፡ ሀገሪቱ ለሁሉም ቋንቋዎች እኩል እውቅና በመስጠቷ በቋንቋ ተናጋሪ ብሄረሰቦች ዘንድ የጎላ የልዩነት ስሜት አይታይም የሚል እይታ አለ፡፡ እንደውም በሀገር ደረጃ ለመግባቢያ እንዲሆናቸው አማርኛን ለጋራ መግባቢያ ቋንቋነት በተወካዮቻቸው አማካኝነት መርጠው ከየክልሎቹ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር እየተገለገሉበት ይገኛሉ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ልሳነ ብዙነት ችግር አለመሆኑንና ጠቀሜታው ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ በተለያየ ቦታ በተገለጸው ሀሳብ መሰረት ሰፊ የእውቀት ስርጭት የሚገኘው ከሰፊ የቋንቋ ስርጭት እንደሆነ ነው፤ የቀረበው ሀሳብ የሚያስረዳው(Ediward, 1994; Chia, 2006 እና Wikiadia, 2009)፡፡

እንደ Campbll (2004) አገላለፅ ልሣነ ክልኤነት በተለያዩ ህብረተሰቦች መካከል ተግባቦትን ለማከናወን የቋንቋ ምርጫ እድልን ይሠጣል፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ህብረተሠቦችና ቤተሠብ ጋር ለመግባባት ሠፊ እድል ይሠጣል፡፡ ስለዚህ ልሣነ ክልኤ ከሆነ ቤተሠብ ወይም አካባቢ መወለድ ከሌሎች ሰዎች ጋር በነፃነት ለመግባባትና የጠበቀ ግንኙነት ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ባህሎችን ለማወቅና ለመረዳት ያግዛል፡፡ ይህንን ማለት ደግሞ የተለያዩ ክፍለ አለማትን እንደማወቅ ይቆጠራል፡፡ ብዙ ቋንቋን መቻል ስለ ቋንቋና ማህበረሠብ ጥሩ ግንዛቤ እና እይታ እንዲኖር ከማድረጉም በላይ የብዙ ህብረተሰን

ባህልና ስነ- ፅሑፍን ለማወቅ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋን የሚናገር ሰው ባህላዊ እሴቶችን በጥልቀት እንዲያስተውል እገዛ ያደርጋል፡፡ ሚስጥርን የመጠበቅም ሆነ የማወቅ እድሉ ሠፊ ነው፡፡

ልሣነ-ክልኤ የሆኑ ሰዎች ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰራዎችን ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ተግባብቶ ለመስራት ሰፊ እድል ይኖራቸዋል፡፡ ስለተለያዩ የቋንቋ ተናጋሪዎች ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖር ስለሚያደርግ ከማን ጋር ምን አይነት ቋንቋ መጠቀም እንዳለበት ለይቶ እንዲያውቅ ይረዳዋል፡፡ በተጨማሪ IQ (አይ ኪው) ፈተና በማዘጋጀት፣ ፈተናውን በተለያዩ ቋንቋዎች ለማዘጋጀትና ለመጠቀም ስለሚረዳ ጥልቅ ምርምርን ለማከናወን፣ ሰፊ ሀሣብ ለማሰባሰብና እና ያለ አስተርጓሚ መረጃን ከምንጩ መሠብሠብ እንዲቻል ሰፊ እድል እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ከትምህርታዊ ጠቀሜታ አንፃርም ልሣነ ክልኤ የሆነ ሰው ስርአተ ትምህርትን በማዘጋጀትም ሆነ የተዘጋጀ ስርአተ ትምህርት ለመገምገም ይረዳል፡፡ ከመማር ማስተማር አንጻርም እየተሰጠ ያለን ትምህርት በጥልቀት መማር እንዲቻል ስለሚያደርግ የልሳነ ክልኤነት ጠቀሜታ ሰፊ ነው(Ediward, 1994; Campbll, 2004; Chia, 2006 እና Wikiadia, 2009)፡፡

ልሳነ ክልኤነት ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም አንጻር ከፍ ያለ እድልን የሚፈጥር ነው፡፡ ብዙ ቋንቋ የሚችል ሰው በሚወጣ የስራ ማስታወቂያ ውስጥ ተቀጥሮ የመስራት እድሉ በጣም ሠፊ ስለሚሆን ስራን የማግኘት እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ አንጻር ብዙ ቋንቋን መማርና መልመዱ በሀገርም ደረጃ ሆነ በግለሰብ ደረጃ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ያረጋግጣል (Campbll, 2004 እና Chia, 2006)፡፡

## 2.5 የቋንቋ ምርጫ በልሳነ ብዙ ሀገር ውስጥ የሚከናወንበት ሂደት

የቋንቋ ምርጫ ሲነሳ ጉዳዩን ከሁለት አቅጣጫ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው ነዋሪው/ተናጋሪው ከሚኖርበት ነባራዊ ወይንም አካባቢ ሁኔታ አንፃር የሚመርጠው የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው መንግስታት ብሔራዊ ቋንቋ፣ "ኦፊሻል" ቋንቋ፣ የስራ፣ የትምህርትና የሚዲያ ቋንቋ ብሎም ከአንድ ቋንቋ ዘዬዎች መካከል አንዱን ለይተው ለመደበኛ ቋንቋነት የሚመርጡበት ሂደት ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን የሚከተሉ ሀገሮች ለነዚህ አገልግሎቶች መንግስታት ቋንቋን እንዲመርጡ ሲደረግ የሚመረጠው ቋንቋ የህብረተሰቡን ፍላጐትና ሀሳብን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ልሳነ ዋሀድ በሆኑ ሀገሮች ውስጥ ደግሞ

መንግስታት የሚጠበቅባቸው ኃላፊነት ከቋንቋው ዘዬዎች መካከል ለመደበኛነት በመምረጥ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የጋራ መገልገያ/መግባቢያ/ እንዲሆን ማድረግ ነው (Fasold 1984; Webb and Sure 2000)።

እንዲህ ያለው ልሳነ ብዙነት የሚዳብረው ቋንቋዎች ከሚያስገኙት ጠቀሜታና የአገልግሎት አስገዳጅነት አንጻር ነው ማለት ይቻላል (Webb and Sure, 2000)። Webb and Sure (2000) እንደሚያስረዱት እንዲህ ያለ ነባራዊ ሁኔታ በተለይ በአፍሪካ ሀገሮች የተለመደ ነው። አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ቢያንስ ለሦስት ቋንቋዎች ዕውቅና ሰጥተው አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋሉ።

በመንግስት በኩል የሚከናወነው ሌላኛው የቋንቋ ምርጫ አይነት በመንግስት ወይም መንግስት በሚያቋቁመው ቦርድ /ሌላ አይነት ተቋም ወይም ኮሚቴ/ አንድን ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል/ሉ የሚወሰንበት የቋንቋ ምርጫ ሂደት ነው።

በመሆኑም የቋንቋ ምርጫ የትኞዎቹ ቋንቋዎች ለመደበኛ ትምህርት መስጫ ያገለግላሉ? የትኞዎቹስ ለአስተዳደር፣ ለንግድ፣ ለሚዲያ፣ ለሲቪል ሰርቪስ፣ ለውትድርና ያገለግላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ በመንግስት /በመንግስት ስልጣን በተሰጠው ተቋም/ ምላሾችና ውሳኔዎች የሚሰጥበት ሂደት ነው(Fasold 1987; Webb and Sure, 2000)።

ልሳነ ብዙ በሆኑና ባላደጉ ሀገሮች በተለይም በአፍሪካ ሀገሮች በትምህርት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፣ በፓርላማ፣ በአስተዳደር፣ በንግድና ኢንዱስትሪ፣ በአብዛኞዎቹ ሚዲያዎች እየተሰራባቸው ያሉት የአውሮፓ ቋንቋዎች ናቸው (Webb and Sure, 2000 እና Mutasa, 2006)። እነዚህ ሀገሮች ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነፃ ቢወጡም ከቋንቋቸው ግን ገና ነፃ አልወጡም፤ ነፃ የሚወጡም አይመስሉም (Vinbe, 2006)።

በርግጥ አንዳንድ ሀገሮች በህገ መንግስታቸው እንኳን ሳይቀር ለሀገርኛ ቋንቋዎች እውቅና በመስጠት ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ ደንግገዋል። በዚህ ረገድ ታንዛኒያና ኬንያ ስዋሊህኛን ብሔራዊና "ኦፊሻል" /የወል ቋንቋ/ መግባቢያነት እንዲውል አውጀዋል። ኢትዮጵያም እንደዚሁ በህገ መንግስቷ ለሁሉም ቋንቋዎች የትምህርትና የየክልሉ መገልገያ ቋንቋ እንዲሆኑ እውቅና ሰጥታለች (Webb and Sure, 2000 and Vinbe, 2006)።

ከላይ ከቀረቡት ዝርዝር ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ምርጫ ብሔራዊ ቋንቋን፣ ኦፊሻል ቋንቋን /የስራ ቋንቋን/፣ ለሀገር፣ ለክልልና በየክልሎች ስር ለሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች እንዲያገለግል/ሉ ተገቢ መስፈርቶችን በመጠቀም የመምረጥ ተግባር ነው ማለት ይቻላል። የተመረጡ ቋንቋዎችን ከተመረጡበት አገልግሎት አንጻር ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ በማስገባት በትምህረት አይነትነት መስጠቱ ወሳኝ ጉዳይ ነው፤ በማለት ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ ።

## 2.6 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚመለከት የቀረበ አጭር ቅኝት

### 2.6.1 አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማርኛ የፌደራል ቋንቋ ሆኖ ስለተመረጠ ክልሎች ከክልሎች ጋር ወይም ከፌዴራል መንግስት ጋር፣ ብሄረሰብ ከብሔረሰብ ጋር በመግባባት ችግራቸውን መፍታት ይችሉ ዘንድ *አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ይህንን የጋራ መግባቢያ* ቋንቋ የሆነውን ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በትምህርት ቤት መማር እንዳለባቸው በትምህርት ፖሊሲው ላይ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሥርዓት ትምህርት ተቀርፆለት ትምህርቱ በመሰጠት ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ባወጣው መግለጫ መሠረት በቁጥር 2.2.1.2 ብሄር ብሄረሰቦች የአማርኛ ቋንቋን በመናገር ከፌዴራል መንግስትና ከክልል ማህበረሰብ ጋር መግባባት እንዲችሉ የህብረ-ብሄር ተማሪዎች ቋንቋውን መማር እንዳለባቸው ያስገነዝባል።

## 2.6.2 የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት ሲሰጥ ያለው አገልግሎት

የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ ለማወቅ በተለያዩ ጊዜያት የተሠሩ ሥራዎች፣ የቀረቡትን ሀሳቦችና መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል:: ደረጀ ተፈራ (1991)፣ Pubnkhourst(1976) እና የኢሕዲሪ የትምህርት ፖሊሲ ጥራዝ አንድ(1981 ዓ/ም) ላይ እንደሰፈረው ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን የተጀመረው 1900 ዓ.ም አካባቢ ነው:: አማርኛ ቋንቋ በዚህ ወቅት የመንግስትና ኦፊሴላዊ ቋንቋ ነበር:: ትምህርት በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚሰጥ ሲሆን አማርኛ፣ አረብኛ፣ ጣልያንኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጡ እንደነበር ተገልጾል::

በንጉስ ሀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስትም እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል:: ነገር ግን ጣልያን በ1928 ከመጣ በኃላ ከፋፍለህ ግዛው በሚለው እሳቤ ኢትዮጵያን በስድስት አስተዳደር ክልሎች በመከፋፈል ትግርኛ በኤራትራ አካባቢ፣ አማርኛ በአማራው አካባቢ፣ አማርኛና ኦሮሚኛ በአዲስ አበባ አካባቢ፣ ሱማሊኛ በሱማሌ አካባቢ፣ ሐረሪና ኦሮሚኛ በሐረርና ኦሮሚያ አካባቢ፣ ከፊቾ በደቡብ ምዕራብ ኦሮሚያና በሲዳማ አካባቢዎች በማስተማርያ ቋንቋነት እንደ ትምህርት አይነት ተሰጥተዋል:: ከጣልያን ወረራ በኃላ እስከ 1986 ዓ.ም ድረስም አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ስሰጥ ቆይቷል

በ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መተግበር እስከ ጀመረበት 1987 ዓ.ም ድረስ አማርኛ በመላው ሃገሪቱ ውስጥ ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች በትምህርትነት ይሰጥ እንደነበረ ይታወቃል:: የትምህርቱ ፖሊሲ በተግባር ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ግን ቋንቋው እንደ ትምህርት አይነት የመሰጠቱ ሁኔታ ከክልል ክልል ተለያይቷል::

በአማራው ክልል፣በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በድሬደዋ ካውንስል፣በቤኒሻንጉል ክልል፣በአፋር ክልል የአማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ-12ኛ ክፍል፣ እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመስጠት ላይም ነው:: እንዲሁም በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ የማስተማሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑት ከ1ኛ-12ኛ ክፍል እንደ አንድ የቋንቋ ትምህርት አይነት ይሰጣል::

በሌላ በኩል አማርኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆኑት ክልሎች በኦሮሚያ ክልል ከ5ኛ ክፍል፣ በትግራይና በሶማሊያ ክልል ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ በትምህርት አይነትነት የሚሰጥ ሲሆን፤ ለመሰናዶ ትምህርት ሲደርሱ ከክልሉ ቋንቋ ጋር እንደ አማራጭ

ሆኖ ይቀርባል:: በኦሮሚያ ክልል ደግሞ ትምህርቱ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነትነት መሰጠት የሚጀምረው ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ይዘልቃል:: ለመሰናዶ ተማሪዎች ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆኑ ክልሎችም ቋንቋው ከክልሉ ቋንቋ ጋር በአማራጭነት በማቅረብ ቋንቋውን የመረጡት ተማሪዎች ብቻ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይማሩታል።

የክፍለ ጊዜ ስርጭቱም በትምህርት የክፍል ደረጃና ከክልል ክልል የሚለያይ ሲሆን ከ3ኛ-8ኛ ክፍል ድረስ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት የተመደበለት ክፍለ ጊዜም በሳምንት ከ3-5 ክፍለ ጊዜን ይይዛል። ከ9ኛ-10ኛ ክፍል ደግሞ ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ በሳምንት ተመድቦለት እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ትምህርት ሚኒስቴር ታህሳስ 2002 ዓ/ም(እ.ኤ.አ ታህሳስ 2010) ባዘጋጀው የስርአተ-ትምህርት ትልመ ተግባር ላይ እንደቀረበው ደግሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ከ3ኛ-6ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በሳምንት ሶስት ክፍለ-ጊዜ የተመደበለት ሲሆን ከ7ኛ-10ኛ ክፍል ለሚማሩት ደግሞ በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ እንዲማሩ ተመድቧል። ከ11ኛ-12ኛ ላሉት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር በአማራጭነት የቀረበ ሲሆን ትምህርቱን ለመረጡት ተማሪዎች በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ እንዲማሩ ተመድቧል።

### 2.6.3 አማርኛ እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነት ያለው ሚና

ደረጀ (1991ዓ/ም)፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር (1994ዓ/ም)፣ ሙሉ እመቤት (198ዓ/ም9) እና የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጥራዝ አንድ (1981) መሠረት በኢትጵያ ውስጥ የዘመናዊ ትምህርት መስጠት የተጀመረው ከ1900 ዓ.ም አካባቢ ጀምሮ እንደነበረና በዚህ ወቅት የማስተማሪያ ቋንቋ የነበረው ፈረንሳይኛ ቋንቋ ነበር:: በኢጣልያን ወረራ ወቅት የነበረውን ደግሞ ከፋፍለህ ግዛ በሚለው መርህ መሰረት ለክፍፍሉ ዋነኛና መሠረታዊ መመዘኛው ቋንቋ ነበር። በ1928 ጀምሮ የኢጣልያን ገዥ በስድስት (6) አስተዳደር ክፍሎች በመከፋፈሉ ምክንያት አማርኛ ቋንቋ በአማራውና በአዲስ አበባ አካባቢ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ነበር። ጣልያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ ከወጣ ከ1931-1956 ዓ.ም በኃላ ባለው የቋንቋ ፖሊሲ መሠረት የአማርኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ቋንቋነት ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ተወስኖ ይሰጥ ነበር። ከ1958/9 ዓ.ም ጀምሮ አማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ-6ኛ ክፍሎች የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን

ተደርጓል፡፡ ይህም በ1986 ዓ.ም ወጣው የትምህርት ፖሊሲ መተግበር እስከ ጀመረበት 1987 ዓ.ም ድረስ በተግባር ላይ እየዋለ ይገኝ ነበር ፡፡

አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መተግበር ከጀመረበት 1987 ዓ.ም ጀምሮ ግን ቀድሞ የነበረው ሂደት ተለውጧል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 2 ላይ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ መብት አለው ይላል፡፡ በዚሁ መሰርት የኢፌድሪ መንግስት በ1986 ዓ.ም በሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ቋንቋን አስመልክቶ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን ማንነት መግለጫ የሆነውን ቋንቋቸውን ማሳደግ ስላለባቸው በራሳቸው ቋንቋ ዝግጅት እያደረጉ እንዲያስተምሩ በሚል በፖሊሲው ላይ በወጣው ድንጋጌ መሰረት ክልሎች የራሳቸውን ቋንቋ ለማስተማሪያነት እያዋሉ ይገኛሉ ፡፡

ይሁን እንጂ በተወሰኑት ክልሎች በአማራው፣ በቤኒሻንጉል ከ1ኛ-8ኛ ክፍል፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በድሬደዋና በአፋር ክልል ከ1ኛ-6ኛ ክፍል እና እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በሀረሪና በደቡብ ክልል በአንዳንድ ቦታዎች በክልሉ ቋንቋ ኢ-አፊፌት ስሆኑት አማርኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ቋንቋነት በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

## 2.7 የአማርኛ ቋንቋ ሚና በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ

የኢፌዲሪ መንግስት በ1986 ዓ.ም አገሪቱን የምትመራበትን የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ሲያወጣ የአማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀምጧል:: "ቋንቋና ትምህርት" በሚለው ርእስ ስር የሰፈሩትን ነጥቦች በቁጥር 3.5.2 ላይ ብሄር ብሄረሰቦች አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ በራሳቸው ቋንቋ ወይም በብሄራዊ ክልላዊ በሀገር ውስጥ ባላቸው የተናጋሪው ብዛትና ደረጃ መሠረት የሚመርጡት ቋንቋ ለማስተማሪያነት ከማገልገሉም በተጨማሪ በትምህርትነት ይሰጣል ይላል፡፡በሌላ በኩል በኢትጵያ ውስጥ የሚገኙት ክልሎችም ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪም ለጋራ መግባቢያ የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት እየተማሩ ይገኛሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ በቁጥር 3.5.3 ላይ የወጣው መመሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል፡፡ ትምህርቱ ቢሰጥም በየክሎሎች

ውስጥ ትምህርቱ የሚጀመረው ከተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ ነው፡፡ ቢሆንም በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አስገብተው እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት አንቀፆች ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች ስንመለከት ከሃሳቦቹ ከምናገኘው ነጥብ በመነሳት ክልሎች ለትምህርትነት ከሚመርጡት ቋንቋ በተጨማሪም ከክልል ውጪ መግባባት እንዲቻል ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል አንድ የጋራ ቋንቋ መማር እንደሚያስፈልጋቸው ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና የኦደቪዥዋል መመሪያ (1994ዓ/ም፣62-65) ባዘጋጀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጅና ፕሮግራሞች መጽሔት ላይም ቋንቋን በተመለከተ እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ይሄም አማርኛ ቋንቋ በሀገሪቱ ውስጥ የሁሉንም ብሄር ብሔረሰቦች በሀገር ውስጥ ሊያግባባ የሚችል ቋንቋ እንደሆነና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ለጋራ መግባቢያነት የተመረጠ ቋንቋ በመሆኑ በሀገሪቱ እንደ አንድ የትምህርት አይነት በትምህርትነት መሰጠት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡

በተጨማሪም "ፖሊሲው ህፃኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋው እንዲማር መብት ቢሰጠውም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን እንዲማር የሚያደረግ ነው፡፡" አማርኛ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት የወሰነና በህገ መንግስታቸው ውስጥም እንዲሰፍር ያደረገ በመሆኑ ተማሪው አማርኛ ቋንቋን የመማር ግዴታ እንዲኖርበት ማድረግ ትክክለኛ ነው (1994ዓ/ም፣65)፡፡ ይህም ቋንቋን እንዲማሩት ፖሊሲው የሚያስገድድ መሆኑን በአጽንኦት ያስረዳል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ በመነሳት በአሁኑ ጊዜ በየክልሉ ያሉት የትምህርት ባለሙያዎች በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አማርኛን እንደ አንድ ትምህርት በመውሰድ እንዲማሩት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በኦሮሚያ ክልልም ትምህርቱ ከአምስተኛ ክፍል ቢጀምርም በትምህርትነት በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርት አሰጣጡ የሚጀምርበት የክፍል ደረጃ ከክልል ክልል የተለያየና ወጥ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት እንዳይኖር አድርጎታል፡፡ ይሄ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ በክልሎች መካከል የቋንቋ ትምህርቱን በመማር ሂደት ላይ የሚስተዋለውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና በትምህርቱ የሚመዘገብ የውጤት ክፍተትን ማጥናትና መመልከት የግድ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 2.8 የአመለካከትና የፍላጎት የጥናት መስክ

አመለካከትና ፍላጎት በስፋት የሚጠኑበት የጥናት መስክ በሥነ-ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና(Educational psychology) ውስጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሥነ-ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና የሰውን መሠረታዊ ባህሪን መነሻ በማድረግ ሥነ-ትምህርት እንዴት ተግባር ላይ መዋል እንደሚችል እና የሥነ-ልቦና ክፍሎች በትምህርት ተግባር ላይ የሚውሉበትን መንገድ የሚያጠና የጥናት መስክ ነው፡፡ እንዲሁም እውቀት ከማህበራዊ መስተጋብርና ከመናበብ ሂደት የሚመጣ መሆኑን፣ የእውቀት መሳሪያዎችን፣ ዘዴዎችን፣ የጥናትና የምርምር መንገዶችን የሚያጠናና የሚያሳይ መስክ ነው፡

በተጨማሪም ስለ ሰዎች ስብዕና(Personality) በተመለከተ የልጆችን፣ የአዋቂዎችንና ተማሪዎችን፣ በትምህርት ቤት ውስጥ አና ውጪ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ ለመማር ማስተማሩ ሂደት መፋጠን ሲባል ልዩ ልዩ ጥናቶችን ያጠናል፣ ይመረምራል፣ ለችግሮቹም መፍትሔ ያፈላልጋል፡፡ በተጨማሪም ስለ ተፈጥሮአዊ፣ አካላዊና አእምሮአዊ እድገት፣ ማህበራዊ እድገት እና ለውጥ የአመለካከት፣ የፍላጎትና የንሺ ሁኔታዎችን፣ አእምሮአዊ እድገትንና የመማር ችሎታን፣ የክህሎትን፣ ትምህርቶችንና የመማር ሂደትን፣ የተለያዩ እደ-ጥበቦችን አስመልክቶ እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውሉ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከነመፍትሄዎቻቸው አጠቃሎ የሚይዝ የጥናት መስክ ስለሆነ ተላምጠዎቹ በዚህ ክፍል ስር በስፋት የሚገኙና የሚጠኑ ናቸው::

ከላይ በተገለጸው መሠረት ተማሪዎች በትምህርት ላይ የሚገጥማቸውን አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖች ምን እንደሆኑ በማጥናት የመማር ማስተማሩ ሂደት የተቃና እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል እንደ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ስሜት፣ ንሺ ወዘተ… ያሉት በአካባቢያዊ ማህበራዊ ስነ-ልቦናዊ ምክንያቶች በትምህርት ላይ የሚያሳድሩትን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖዎችን በሙሉ በማጥናትና የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ እንዴት መፍትሄ መስጠት እንደሚቻል የሚያሳይ የጥናት ክፍል መሆኑን የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ:: የቋንቋ ሊቃውንት የሆኑት Krashen (2009) እና Brown (2006) በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ አመለካከት፣ ዝንባሌ፣ ፍራቻ፣ ንሺና ፍላጎት በቋንቋ ትምህርትና ለመዳ ወቅት ያላቸውን ተጽእኖ ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ሊቃውንት ስነ-ልቦናዊ ተጽእኖ በቋንቋ ለመዳና ትምህርት ሂደት ወቅት የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ይህ ጥናት ስነ-ትምህርታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ስነ-ልሳናዊ መሰረት ያለው መሆኑን የሚጠቁም ሀሳብ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሥነ-ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን ለይቶ የሚያሳይ፣ በሰው ልጅ እና ሥነ-ትምህርት ዙሪያ ያለውን አጠቃላይ ገጽታን በማሳየት ምቹ የመማር ማስተማር ስርአትን የሚፈጥር የጥናት መስክ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ በትምህርት አይነትነት ሲሰጥ ከስነ-ትምህርታዊ ስነ-ልቦና የጥናት መስክ አንጻር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን በመለየት ለትምህርቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የግድ ስለሚል ስነ-ትምህርታዊና ስነ ልቦናዊ መሰረት የሚከናወን የጥናት መስክ ነው፡፡

በተጨማሪም በሚሰጠው ትምህርት ዙሪያ ከስነ-ልቦና ዘርፍ ውስጥ የሚካተቱ ተላውጦዎች የሆኑትን አመለካከትና ፍላጎት በትምህርቱና በሚመዘገበው ውጤት ላይ የሚኖር አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ምን እንደሆነና ያለውን የተጽእኖ መጠን፣ የተላውጦዎች አንድነትና ልዩነትን ከየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በማሳየት፤ የሚስተዋለውን የተጽእኖ መጠን ለማወቅ የሚከናወን ጥናት ስለሆነ ከስነ- ትምህርታዊ ስነ-ልቦና አንጻር ጥናቱን መቃኘቱ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ አመለካከት፣ ፍላጎትና የትምህርት ውጤት ከክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ያለቸውን ዝምድናና የሚገኙበትን ደረጃ ምን ላይ እንደሆነ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚመለስበት ስለሆነ ጥናቱን አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ይሄንን ርእሰ ጉዳይ በዚህ ላይ ማንሳት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም በርእሰ ጉዳዩ ላይ ከቀረበው ፍሬ ሀሳብ አንጻር ሲታይ ጥናቱ ስነ-ትምህርታዊና ስነ-ልቦናን መሰረት ያደረገ መሆኑን ለመጠቆም ሲባል የቀረበ ነው፡፡

## 2.9. የፍላጎትና የአመለካከት ምንነት

### 2.9.1. ፍላጎት ምንድነው?

የፍላጎት ምንነትን በተመለከተ የመስኩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ የሁሉም ሀሳብ ወደ አንድ ጎራ ሊካተት የሚችል ነው። Noll (1979); Craig (1979); Buglski (1971); እና Skinner 1985) ፍላጎት በስነ ልቦና የጥናት መስክ ውስጥ ከሚያጠና አካል ውስጥ አንዱ ሲሆን እንደ ንሺና አመለካከት ሁሉ በስነ ልቦና የጥናት መስክ ከሚተኮርባቸው ተላውጠዎች ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። Batz et al. (2010) አገላለጽ ፍላጎት ውስጣዊ ንሺ (Intrinsic motivation) ከሚለው ቃል ጋር አንድ እንደሆነና ሁለቱ የአቻነት ትርጉም እንዳላቸው ያስቀምጣሉ። Hamlin (1996) ፍላጎትን ሲገልፅ አንድ ድምፅ እንደተሰማ ማዳመጥ ይጀምራል። ከዚያም ስለ ጉዳዩ በማስተዋል ማሰብና የልብ ትርታ በፍጥነት እየመታ ማሰብን ያመጣል። በመጨረሻም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ከልብ ማዳመጥና የሚደመጠውንም የማስተዋል፣ ሙሉ በሙሉ በስሜት መዋጥና ስለ ጉዳዩ ሀሳብ ውስጥ የመግባት ተግባርን የሚመለከት ነው። ይህ ለማዳመጥ መነሳሳትና ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ የመከታተል ሂደት ፍላጎት ይባላል በማለት ይገልፃሉ።

Craing (1979) እና Turne (1997) ፍላጎት ማለት አንድ ግለሰብ ስሜቱንና ዝንባሌውን የሚገልፅበት መንገድ ነው። እንዲሁም የአንድን ነገር ምንነት ለማወቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከት የሚገፋፋ ሀይል ነው። ይህም አንድን ነገር ስንወደው ልንመርጠውና ልንተገብረው ወይም ስንጠላው እንዳይመረጥና እንዳንተገበር የሚያደርግ ንቃተ ህሊናዊ ስሜት ነው በማለት ይገልፃሉ። ብዙውን ጊዜ ፍላጎት ከአዎንታዊ አመለካከትና ንሺ የሚመጣ ነው።

Harlock (1972) ፍላጎት ማለት የስብእና አንዱ ክፍል እንደሆነና ወደ ተወሰነ ግብና አላማ፣ እንዲሁም ወደ ተግባር ሊመራን የሚችል ውስጣዊ ስሜት እንደሆነ፤ አንድ ነገር መርጦ ለመተግበር የሚያነሳሳ ሀይል ነው፤ በማለት ይገልፃሉ። GarrY (1970) ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ባልተለየ መልኩ ፍላጎት ወደ አንድ ተግባርና ግብ ሊያደርሰን የሚያስችል አዎንታዊ የሆነ ውስጣዊ ኃይል ነው፤ በማለት ይገልፃሉ። ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት ፍላጎት ከአንድ ከተወሰነ ነገር ጋር ተያይዞ ወደ ተግባርና እንቅስቃሴ የሚመራ አእምሮአዊ የሆነ የስሜት ክፍል ነው። ከላይ ከቀረበው ገለፃ አንፃር ፍላጎት አንድን ተግባር ለማከናወን ፈቃደኛ የመሆንና ያለመሆንን ምላሽ የሚሰጥበት ውስጣዊ ስሜት ነው ማለት ይቻላል።

Wilson (1971); Wat (1967)ን ጠቅሶ እንደገለፀው ፍላጎት አንድን ነገር ለማከናወንና ለመተግበር ትኩረት የሚሰጥበት፣ እንዲሁም አንድን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ውስጣዊ ግፊት፣ ዝንባሌ እና ስሜት ነው፡፡ አንድ ሰው አንድን ነገር ለማከናወን ትኩረት ሰጥቶና እራሱን እያዘጋጀ እያለ እንዳያከናውን ቢታቀብ የንዴትና የብስጭት ስሜትን ሊፈጥር የሚችል ኃይል ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል Skinner (1985); William James (1890)ን ጠቅሶ፤ ፍላጎት የታቀደን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወነን ተግባር መውደድና አለመውደዳችንን የሚያመለክት ውስጣዊ ንሺና ለተፈለገ ነገር ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ግፊት፣ ዝንባሌና ስሜት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Skinner (1985); Baridie (1946)ን ጠቅሰው፤ ፍላጎት ማለት በአንድ ነገር ለመሳብ (ለመማረክ) ወይም ለመገፋት ምክንያት የሚሆን ውስጣዊ ተግባር ነው፤ በማለት ይገልፃሉ፡፡ በአጠቃላይ ብዙ ጥናቶች እንደሚገልፁት ፍላጎት ማለት ከመውደድና ከመጥላት ጋር በተያያዘ መልኩ አንድን ነገር ለመምረጥ ወይም ላለመምረጥ ምክንያት ሊሆን የሚችል የስብዕና ክፍል ነው፡፡ ይህም አንድን ሁኔታ በመለማመድና ስለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ወደ ተግባር የሚያስገባ ስሜት ነው፡፡ ስለዚህ ፍላጎት ህያው የሆነ አንድን ነገር ጥቅሙንና አሰራሩን ለማወቅ የሚገፋፋ ሀይል ነው በማለት ሰፊ ማብራሪያ ያቀርባሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እንደምንረዳው ፍላጎት ማለት አንድን ተግባር ወይም ጉዳይን ለማከናወን የሚደረግ ውስጣዊ ተነሳሽነትን፤ መምረጥንና ያለመምረጥን የሚያመለክት የስብዕና ክፍል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ፍላጎትን ከተለያዩ ተግባራት አንፃር ስንመለከት ደግሞ የሰው ልጅ የተለያዩ ፍላጎቶች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የትምህርት ፍላጎት፡- አንድ ተማሪ ትምህርቱን ለመማር ያለውን ውስጣዊ ስሜት የሚያመለክት ነው (Skinner, 1985):: Hamilin (1996) የትምህርት ፍላጎትን ምሁሩ ሲገልፁ አንድ ተማሪ የትምህርትን አይነት ለማወቅና ለመማር የመፈለግ ሁኔታ ነው ይሉታል፡፡ ትምህርቱ ስለምንድነው የቀረበው፣ ምንን ለማከናወን ይረዳል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚከናወን ተግባርን መምረጥና ያለመምረጥን የሚያመለክት ተግባር ነው፡፡

ለ) የሥራ ፍላጎት፡- አንድ ሰው አንድን ስራ ለመስራት ያለው የሥራ ምርጫ ነው፡፡ የሥራ ምርጫም ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራን ይመርጣል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ ሰውን ያስከብራል ብሎ የሚያስበውን የሥራ ዓይነት

ይመርጣል። ለምሳሌ መምህር፣ ሀኪም፣ ነጋዴና ደላላ መሆንን የሚመርጡ ሰዎች አሉ። ስለዚህ ሰዎች ስራቸውን ሲመርጡ ካላቸው ውስጣዊ ፍላጎት አንፃር መሆኑን ያስገነዝባል።

ሐ) ግለሰባዊ ፍላጎት (Personal Interest)፡- የአንድን ግለሰብ የተወሰነ ነገርን ወይም ጉዳይን መምረጥ እና ማከናወን የሚያመለክት ሲሆን ግለሰቡ የሚያከናውነውን ተግባር መስራትን የሚያስወደድና አንድን ስራ የመምረጥ ሁኔታን ያጠቃልላል(Skinner, 1985)።

### 2.9.1.1. ፍላጎትና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት

Machky (1965) እና Schonell (1961) ፍላጎት በቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን ሚና ሲገልፁ የትምህርቱ ይዘት ምን ያህል ከተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት ጋር ይጣጣማል/አብሮ ይሄዳል? የሚለውን ለመወሰን ይጠቅማል ይላሉ። ምክንያቱም ተማሪው ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት ከሌለው የተዋጣለት ዘዴ እንኳን ቢኖር ኮርሱን ለማስተማር ምንም ላይፈይድ ይችላል። ተማሪው ቋንቋውን ለምን እንደሚፈልገው ወይም የትኛውን ክህሎት ለማዳበር እንደሚፈልግ ካላወቀ ለትምህርቱና ቋንቋው ስለሚነገርበት ሀገር ለማወቅ ባለው ፅኑ ጉጉት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል።

ተማሪው ለትምህርቱ ያለው የፍላጎት ደረጃ እንደየ ትምህርት አይነቱ ሊለያይ ይችላል። ምክንያቱም ንግግርን ለማለማመድ የምንገለገልበት ዘዴ ማንበብና መፃፍን ከምናስተምርበት ጋር አንድ ዓይነት አይደለምና። በመሆኑም የተማሪዎችን የፍላጎት ሁኔታ ለያይቶ መገመገም የግድ ያስፈልጋል። ይህንንም በተናጠል ስንመለከት የሚከተለውን ይመስላል።

#### 1. ማዳመጥና መናገር

በትምህርቱ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ሁነቶች (አውዶች) ተማሪው በእውነትም ይከሰታል ብሎ የሚያምናቸው ናቸው? ሁነቶቹን ተማሪው ከዚህ ቀደም ከሚያውቀውና ሊጠቅመው ከሚችል ነገር ከቤቱ፣ ከቤተሰቡ፣ ከሥራው፣ ከ ------------ ጋር አያይዞ ሊገልፃቸው ይችላል? ተማሪው ቋንቋውን ከሚማርበት ዓላማ ጋር ይዛመዳሉ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመሉ ለመመለስ ይረዳል።

## 2. ማንበብና መፃፍ

ለንባብ የሚቀርቡ ፅሁፎች የተማሪውን ፍላጎት ይጠብቃሉ/ ይመጥናሉ? ለተማሪው የስሜት እርከን ይቀርባሉን? ንባቡ የተማሪውን ስሜት ይበልጥ የሚያነሳሳ ከሆነ የተማሪውን ስሜት የመያዝ (የመግዛት) አቅሙ ከፍተኛ (ጥልቅ) ይሆናል። ለረጅም ጊዜም አይረሳውም፤ እንዲሁም ታሪኩንም ሆነ ታሪኩ የቀረበበትን ቋንቋ በቀላሉ (በፍጥነት) ያስታውሰዋል። ምክንያቱም በፅሁፍ ውስጥ የልብ ሰቀላ ሊኖር ይችላልና ነው።

ይሁን እንጂ ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የንባብ ዝንባሌ ላይኖራቸው ይችላል ወይም ማንበብ የሚፈልጉት ነገር የተለየ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል ወጣት ወንዶች ከልጃገረዶች የበለጠ አስጨናቂና የጀግንነት ታሪኮችን ማንበብ ይፈልጋሉ። ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ምናልባት እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተና መረጃ የሚሰጥን ፅሁፍ ማንበብ ይመርጡ ይሆናል። ስለዚህ ትምህርቱ የተማሪዎችን የፍላጎት ሰብጥር ሊያሟላ (ሊያመጣጥን) የሚችል ለማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪዎች ፍላጎት ሊታሰብበት የሚገባ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

Harmer (1991) አንድን ቋንቋ ለመማር የምንነሳው አላማን መሠረት አድርገን ነው። አላማ ደግሞ ለቋንቋው ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረን ያደርጋል። በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ፍላጎት እንዲኖር ምክንያታዊ የሆነ አላማ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ቋንቋ ከእለት ተእለት ተግባራችን ጋር የቀረበ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ቋንቋው በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሁሉ ጠቃሚ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ ቋንቋውን ለመማር በከፍተኛ ደረጃ ፍላጎት ያሳድራል።

በሌላ በኩል ለአንድ ቋንቋ ትኩረት ሰጥተን የምንናገረው፣ የምናዳምጠውና የምናጠናው፣ ለሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛው ከፍላጎት አንፃር ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር ነው። በመሆኑም አንድን ፅሁፍ የምናነበው ወይም ንግግር ከልብ የምናዳምጠው ለማንበብና ለማዳመጥ ፍላጎት ሲኖረን ነው።

ለምሳሌ አንድ መፅሔት የሚያነብ ሰው ከመፅሔቱ ውስጥ በቅድሚያ የሚመርጠው ርዕስ ጉዳይ ከፍላጎቱ ጋር ግንኙነት ያለውን ነው። አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ገጽ ካለው ርዕስ ጉዳይ ይልቅ፣ ብዙ ገፅ ያለውን ርዕስ ጉዳይ የምንመርጥበት ጊዜ አለ። መፅሐፍ አንባቢው ከቤተ መፃሕፍት ውስጥ የሚወደውን እና የሚፈልገውን መፅሐፍ መርጦ ያነባል። ምክንያቱም የሚወደውን ርዕስ ጉዳይ መምረጥ እንዳለበት አእምሮው ስለሚያስገድደው ነው።

በተመሳሳይ አንድ የሬዲዮ አድማጭም ለራሱ አስደሳችና አንቃቂ ነው ብሎ ያመነበትን መርጦ ያዳምጣል፡፡ ከዚህም እንደምንረዳው የምናዳምጠው ወይም የምንሰማውና የምናነበው ከፍላጎታቸው አንፃር ነው፡፡ ወይም ከሚሰጠን ደስታና ተዝናኖት አንፃር ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም አንድን ቋንቋ ለመማር ፍላጎት ሊኖረን ይገባል የሚባለው በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ማንበብ፣ ማዳመጥ፣ መማርና መፃፍ እንዲቻል ነው፡፡

የሁለተኛ ቋንቋን ለሚማር ተማሪ ለቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት እንዲኖረው ለማድረግ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚከናወን የቋንቋ ትምህርት ተማሪው ውስጣዊ ኀሺ እንዲኖረው ስለሚያደርግ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ ይሆናል በማለት ሊቃውንቱ ይገልፃሉ፡፡

### 2.9.1.2. የፍላጎት ጠቀሜታ

የተለያዩ ምሁራን እንደሚገልፁት አንድ አላማ ጥንካሬ እንዲኖረውና፣ ግቡን እንዲመታ ፍላጎት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ አንድን ተግባር የሚያከናውን አካል ለተግባሩ የፀና ፍላጎት ካለው ስራውን በወቅቱ አከናውኖ እንዲፈፅም ግፊት ያደርግበታል፡፡ አላማን መሰረት አድርጎ የሚከናወን ተግባር ከፍላጎት ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሙሉ ሀይልን ለመጠቀምና ተግባርን ለማከናወን ይረዳል (Schonell, 1970; Garry, 1970)::

Harmer (1991) እና Buglesk (1971) ሰዎች ለሚያከናውኑት ተግባር ወይም ጉዳይ ፍላጎት የሚኖራቸው ከሆነ ተግባሩን ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ ውስጣዊ ተነሳሽነትና ግፊት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ Schonell (1970) አንድ አንባቢ ለሚያነበው ምንባብ ከፍተኛ ፍላጎት ካለው በደንብ ስለሚያነበው የማንበቡ ሂደት ግብ መቺ ሊሆን ይችላል፡፡ ፍላጎት ማለት አንድን ተግባር ለሚከናወን ፈቃደኛና ዝግጁ መሆንን የሚመለከት ተግባር ነው፡፡

### 2.9.1.3. ፍላጎት በትምህርት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

ሊቃውንት በፍላጎትና ትምህርት አስመልክተው ያላቸው አመለካከት የተለያየ ነው፡፡ Buglsk (1971) ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖው ይገባል፡፡ ተማሪው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ካለው ትምህርቱን ከልብ ሊማር ይችላል፡፡ ለመማር ፍላጎት የሌለው ከሆነ ግን ትምህርቱን ፈፅሞ ሊማር አይችልም፡፡ ስለዚህ አንድን የትምህርት ዓይነት ለማስተማር በምንነሳበት ጊዜ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት የሚኖረው ፍላጎት አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ፍላጎት የሌለው ተማሪ ግን ትምህርቱን በተገቢው መንገድ መከታተል አይችልም፡፡ ስለዚህ የመማር ፍላጎት የሌለውን ተማሪ ማስተማር አስቸጋሪ እንደሆነ ነው የምሁራኑ ገለፃ የሚያስረዳው፡፡

ፍላጎት የሌለውን ተማሪ እንዴት ማወቅ ይቻላል የሚለውን Skinner (1959) ሲያብራሩ፤ ተማሪው የሚማረውን ትምህርት ከልብ የማይከታተል ከሆነ፣ ትምህርቱ ሲሰጥ ከልብ የማያዳምጥና በትክክል መረዳት የማይችል ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪው የመማር ፍላጎት የሌለው መሆኑን ያመለክታል ይላሉ፡፡ ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ምንም ፍላጎት የሌለው ከሆነ ደግሞ የመማር ማስተማሩ ተግባር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ለሚሰጠው ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ መምህራንም ሆኑ ማህበረሰቡ ተማሪዎችን ለትምህርታቸው ፍላጎት እንዲኖራቸው የሚረዳ ተግባርን መከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ አለበለዚያ ግን ለትምህርቱ ፍላጎት የሌለውን ተማሪ ማስተማሩ በክፍል ውስጥ የሌለ ተማሪን እንደ ማስተማር ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪው የመማር ፍላጎት (learning interest) ከሌለው የሚሰጠውን ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ መከታተል አይችልምና ነው፡፡

እንደ Schonell (1986) አገላለፅ ተማሪዎች ተምህርታቸውን በከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲማሩና ጉጉት (Curiosity) እንዲያድርባቸው፤ በቅድሚያ ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት ከሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ደግሞ ቀደም ብሎ ካላቸው እውቀት ጋር አያይዘውና አዋህደው እንዲገነዘቡትና በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ካላቸው እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በቀላሉ ሊረዱትና ሊያውቁት ከመቻላቸውም በላይ፤ የተማሩትን ለረጅም ጊዜ በአዕምሯቸው ይዘው እንዲቆዩ፣ በተማሩትና በሚያነቡት ርዕሰ ጉዳይ እንዲደሰቱ፤ ጥሩ ልምድና ተግባር እንዲኖራቸው፤ ውስጣዊ ንሺ ወይም ውሁዳዊ ንሺ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ፍላጎት በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወን ማንኛውም ተግባር ግብ መምታት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለዚህም የሚሰጠው የትምህርት ዓይነትም ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ተያያዥነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

Skinner (1989) እና Schon'ell (1961) ተማሪዎች እንደየ እድሜያቸው ፍላጎታቸውና ተግባራቸው ይለያያል ይላሉ፡፡ በዚህም መሠረት እድሜያቸውን መሠረት ያደረገ ትምህርት ከተግባርና ፍላጎታቸው ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት በአግባቡ ሊከናወን ይችላል፡፡ ሂደቱም ግብ መቺ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የአምስት አመትና የአስር ዓመት ተማሪ ያላቸው ፍላጎት የተለያየ ነው፡፡

ስለዚህም የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና ክንውኖችን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር በማቀናጀት የሚተገበሩ ከሆነ ተማሪዎቹ በሚሰጠው ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ ይሆናል፡፡ የመማር ሂደት ስኬታማ የሚሆነው ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣ በአስተውሎት መመርመርና መረዳት የሚቻለው ለትምህርቱ ፍላጎት ሲኖር ነው፡፡ ለትምህርቱ ጥሩ አመለካከት ያለው ተማሪ ደግሞ ጥሩ ፍላጎት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም የፍላጎትና የአመለካከት አዎንታዊ ቅንጅት ደግሞ የመማር ማስተማሩን ሂደት አስደሳችና ግብ መች ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የምሁራኑ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ፍላጎት ለትምህርት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያስገነዝባል፡፡ ተማሪው ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተልና በአግባቡ እንዲያከናውን ፍላጎት አንዱና መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም ያለፍላጎት የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ማካሄድም ሆነ ማሰብ አይቻልም፡፡ በስርአተ ትምህርቱ ላይ የተቀመጠው ግብ ከታሰበው ደረጃ መድረስ የማይቻል ይሆናል፡፡ ስለዚህ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅትም ሆነ በመማሪያ መፅሐፍ ዝግጅት ሂደት ላይ የተማሪዎቹ ፍላጎት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዘጋጅና በጉዳዩ ላይ ሊታሰብበት የሚገባ ነው፡፡

### 2.9.1.4. ፍላጎትን የማጥናት አስፈላጊነት

Harmer (1991) መምህራን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው አስቀድመው የተማሪዎቻቸውን ፍላጎታቸውን አውቀው በፍላጎታቸው መሰረት የሚሰጠውን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ስለሚረዳ የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማጥናትና መረዳት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ፍላጎት የንሺ. ዋና ክፍል ስለሆነ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ንሺ. እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሚረዳ ነው፡፡ Skinner (1989) እና Craig (1975) እንደሚሉትም ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው ትምህርት የየራሳቸው የሆነ ፍላጎት ስላላቸው፤ መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ትምህርቱም መቅረብ ያለበት የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት አድርጎ ሊሆን ይገባል፡፡ ፍላጎትን መሠረት ካላደረገ ግን ትምህርቱ ግቡን ሊመታ አይችልም (Gardner & masgort, 2003)፡፡ ይህንንም በተመለከተ ፍላጎት ያለው ተማሪ ያለ ምንም ንሺ. ጥሩ ውጤትን ሊያስመዘግብ ይችላል በማለት ሀሳቡን ያጠናክራሉ (Harlock, 2001; Gardner & masgort, 2003)፡፡ በአጠቃላይ የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቅ የማስተማር ዘዴን ለመወሰን፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት እና የተማሪዎቹን ማንነት ለማወቅ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

እንደ Callahan (1988); Buglski (1971) እና Garry (1970) ገለፃ ደግሞ፤ በክፍል ውስጥ የሚከናወነን ተግባር በብቃት ለማካሄድ፣ ከተማሪ ችሎታ፤ ተሰጥኦ፤ ዝንባሌ እና ግብ ጋር አብሮ የሚሄድን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ፍላጎትን ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ መምህሩም የመማር ማስተማሩ መቶት በትክክለኛው ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር መሄድ በሚችል መንገድ ማደራጀት አለበት፡፡ ለዚህም በተቻለ መጠን የተማሪዎችን ስብእና፤ ባህሪ እና የችሎታ ደረጃ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንንም መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ተቀራርቦ በመስራትና በአንዳንድ ጉዳዮች ላይም በመወያየት ማወቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በቃለ ምልልስ፣ በውይይት፤ በምልከታ የተማሪችን ባህርይ እና ፍላጎት ማጥናትና ማወቅ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ክንውኖችና መልመጃዎችን (ልምምዶችን) ተማሪዎቹ ሊወዷቸው ከሚችሉ ተግባራት ጋር አብሮ ለማዛመድ የሚረዱ የተለያዩ ስልቶችን ለመወሰን የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናቱ አስፈላጊ ነው፡፡

Skinner (1959) የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት ስለተማሪው ማንነት ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ፍላጎት አዎንታዊ ከሆነ ይህንኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ ጠብቆ ለማቆየት የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቁ ወሳኝ ነው፤ ይላል፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቁ ለሚቀርበው ትምህርት እንደ ዋና መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግላል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ የሥነ-ልቦና ሊቃውንት አገላለፅ ማንኛውም ሰው ራሱን ለትምህርት ካላዘጋጀ በስተቀር ትምህርቱን በትክክል መማር አይችልም፡፡ ስለዚህም በርካታ የሥነ ልቦና ሰዎች ተማሪዎች በትምህርታቸው የሚማሩበትን መንገድ ለማወቅና እንዲሁም ለማጠናከር ብዙ ጥናቶችን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ያለ ፍላጎት በአጋጣሚ የሚከናወን ትምህርት ግቡን አይመታም እና ነው፡፡ Gardner (2007) በመሆኑም የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት እና ጉጉት እንዲያድርባቸው ለማድረግ፤ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹ በትምህርቱ ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ወዘተ... ለማድረግ የተማሪቹን ፍላጎት ማጥናቱ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡

በHarmer (1981) አገላለፅም የተማሪዎችን ዳራ ማወቅ ተገቢ የሚሆነው የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀምና፤ ከተለያዩ የተማሪዎች ህይወት ገጠመኝ ጋር አያይዞ ለማቅረብ ስለሚጠቅም ነው፡፡ ከቋንቋ ትምህርት አንፃርም ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋን ለምን መማር እንደሚፈልጉና ቋንቋውንም ምን ያህል እንደሚወዱት ለማወቅ የተማሪዎችን የህይወት ዳራ ማወቅ አስፈላጊ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

ስለዚህም የተማሪዎችን ማንነት ለማወቅ የተማሪችን ታሪክ የሚገልፁ ጥያቄዎችን በማውጣት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ታሪክ የሚገልፁ ጥያቄዎችም እድሜ፣ ጾታ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ፣ የሥራ ሁኔታ፣ ንሽ/አመለካከት (motivation/Attitude) የትምህርት ዳራ፣ እውቀት፣ ፍላጎትና እምነት (interest and Believe) ምንነትን በመጠየቅ በሚቀርበው ምላሽ መሠረት ምን ዓይነት የማስተማሪያ መሳሪያ መምረጥ እንደሚያስፈልግ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በዚህ መንገድ የተማሪዎችን ታሪክ ለማወቅ የእነዚህን የመሳሪያዎች አይነትን በመጠቀም የተማሪዎቹን ትክክለኛ የሆነ ፍላጎታቸውን ለማወቅና ለመረዳት ይረዳል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪውን ማንነትና ፍላጎት ማወቅ የሚያስፈልገው ለተማሪው ምቹ የሆነ ትምህርት ለመስጠትና የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል ለመርዳት ነው፡፡ በአጠቃላይ የሁሉንም ሊቃውንት ገለፃ መሠረት በማድረግ

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው ተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ በተማሪዎች ዙሪያ ጥናት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

ስለዚህ ከላይ በቀረበው የምሁራን ገለፃ መሠረት የጥናቱ አስፈላጊነትና አብይ ጉዳይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የሚሰጠውን ክፍተት ለመሙላት የተማሪውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ለመጠቀም፣ የትምህርት ቅደችን ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር ለማቅረብ፣ በሀገሪቱ ለሚገኙ የተለያዩ የብሔር ብሄረሰብ ተማሪዎች እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ያታን እድሜንና አካባቢያዊ ሁኔታን መሠረት በማድረግ ትምህርቱን ያለምንም ችግር ለመስጠት ሲባል የፍላጎት ልዩነትን ማወቁ አስፈላጊና መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡

## 2.9.1.5. የተማሪዎችን ፍላጎት የማወቂያ ዘዴዎችና መንገዶች

እንደ Callahan (1988); Bugelski (1971) እና Gardiner (1985) የተማሪዎችን ማንነትና ፍላጎት ለማወቅ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ዘዴዎችም፣

1. በማህደራቸው ላይ የቀረቡትን ሪኮርድ ማየት፡- ከትምህርት ቤቱ ቢሮ፣ ከምክር አገልግሎትና ከትምህርት ክፍሉ የተማሪውን ማህደር በመጠየቅና በማየት የተማሪዎችን ማንነት ማወቅ ይቻላል፡፡

እንዲሁም መምህሩ በየጊዜው ስለተማሪው የመዘገበውን ታሪክ ከአስተዳደር፣ ከምክር አገልግሎት ሰጪዎች የተለያዩ መረጃዎችን በመውሰድ ስለተማሪው ትምህርታዊ ዳራ እና ማንነት ማወቅ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ማዕከላዊነቱን የጠበቀ ፈተና (Standardized test) አዘጋጅቶ በመፈተንና ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን በማየት የተማሪውን ማንነትና ፍላጎት ማወቅ ይቻላል፡፡

2. ምልከታ፡- ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ተግባራት በሜዳ ሲጫወቱ፣ እና በተለያዩ ቦታዎች የሚያከናወኑትን ተግባራት በማየት የተማሪዎችን ስብእናና የአቅም ደረጃቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡
3. በስብሰባ (Conference):- ከተማሪዎች ጋር የስብሰባ ውይይት በማከናወን የተማሪዎችን ፍላጎት ወይም ምኞት (Ambitions)፣ ተስፋ (Hopes) እና ሌሎች ነገሮችን ለማወቅ የሚሰጠውን ትምህርት ከነሱ ስብእና፣ ችሎታ እና ፍላጎት ጋር በሚሄድ መልኩ

በማዘጋጀት የተማሪውን ፍላጎት ማወቅ ይቻላል፡፡ በስብሰባ መልክ መረጃ በምንሰበስብበት ጊዜ ማከናወን የሚያስፈልጉ ተግባራት፡-

ሀ. ክፍት የሆነ ጥያቄ ብቻ በመጠየቅ (Ask open-ended questions) ተማሪዎች በነፃነት ውይይት እንዲያደርጉ በመፍቀድና በማበረታታት ምን እንደተናገሩ በመመዝገብ የሚከናወን ነው፡፡

ለ. ሞራላቸውን መጠበቅ፡- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚያቀርቡበት ሰዓት ባለመከልከል ምን ሀሳብና መልዕክት እንዳቀረቡ በመቀበል ያቀረቡትን ሀሳብ በአግባቡ በመመዝገብ ሞራላቸውን ማወቅ እና

ሐ. ከስብሰባ በኋላ አጠቃላይ የቀረበውን ሀሳብ በአግባቡ መመዝገብ ናቸው፡፡

4. ቤተሰባዊ ስብሰባ ማካሄድ (Parent conferences)፣ የቤተሰባዊ ስብሰባ በማድረግ ለተማሪዎቹ ብዙ መረጃዎችን መሰብሰብ ስለ ልጆቻቸው ብዙ መረጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህ ለቤተሰብ ጥያቄ በማቅረብ የሚመለሰውን መልስ በአግባቡ በመመዝገብ መረጃን መሰብሰብ ይቻላል፡፡

5. የራስ የህይወት ታሪክ (Auto-biographies)፡- የተለያዩ የህይወት ታሪክን የያዙ ደብዳቤዎች (ወረቀቶችን) በማንበብ በግለሰቡ (በተማሪው) ላይ የቀረቡ መረጃዎችን መመልከት ነው፡፡ የራስን ታሪክ አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

ሀ/ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትህን በጨረስክበት ጊዜ ምን ለመስራት አቅደሀል? ወይም አስበሃል?

ለ/ ሥራ አለህ? መልስህ አዎን ከሆነ ምን አይነት ሥራ ነው? ስራውን ትወደዋለህ?

ሐ/ ማንበብ ትወዳለህ? በአብዛኛው የትኛውን ክፍል ማንበብ ትወዳለህ?

መ/ የትርፍ ጊዜ ጊዜ ሰዓትህን ማሳለፊያ አለህ? የትርፍ ጊዜህን ለማሳለፍ የምትጠቀምበት ዘዴ ምንድን ነው?

6. በመጠይቅ፡- በመጠይቅ የሚቀርቡት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

ሀ) የፍላጎት ማወቅያ መጠይቆች (Interest finder)፤ፍላጎትን ለማወቅ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲባል ለምሳሌ ያህል የትኛውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም በይበልጥ ትወዳለህ? ስፖርት ትወዳለህ? የትኛውን የስፖርት ዓይነት ትወዳለህ? እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ የአንድን ግለሰብ እና የማህበረሰብ ፍላጎትን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን ዘርዘር አድርገን ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

1. ከጓደኛህ ጋር ካፍቴሪያ በምትሆኑበት ጊዜ አብዛኛውን ስለምን ጉዳይ ታወራላችሁ?
2. ማንበብ ትወዳለህ?
3. ምን ዓይነት ፅሁፍን በብዛት ታነባለህ?
4. በየቀኑ የሚወጡ ጋዜጦችን ታነባለህ?
5. የምታነብ ከሆነ ብዙውን ጊዜ የትኛውን ክፍል ታነባለህ?
6. የትኛው ፊልም የደስታ ስሜትን ይፈጥርልሀል?
7. ሁልጊዜ ቴሌቪዥን ትመለከታለህ?
8. አዎን የምትል ከሆነ የትኛውን ፕሮግራም በይበልጥ ትወደለህ? የመሳሰሉት ናቸው፡፡

Garediner(1985) ከላይ በቀረበው መልኩ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትን፣ አመለካከትን እና ንሺን የሚለካ የመመዘኛ መሳሪያ መጠይቅ አዘጋጅተዋል፡፡

ለ) የራስ ፍላጎትን አስመልክተው የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ በተራ ቁጥር አምስት ስር የቀረቡትን በሙሉ ይመለከታል፡፡ ስለዚህ በተራ ቁጥር አምስት ሥር ያሉት በዚህ ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ዘዴዎች በሙሉ የተማሪዎችን ፍላጎትና ማንነትን ለማወቅ የሚረዱ ዘዴዎች ሲሆኑ በርዕሰ ጉዳዩ መሰረት ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎትና ማንነት ማወቅ ይቻላል፤ በማለት ሊቃውንቱ በዝርዝር ያቀርባሉ፡፡

Skinner (1985) "የፍላጎት መስፈርት (መለኪያ)" በሚለው ርዕስ ውስጥ ፍላጎትን ለማወቅ የምንጠቀምበትን ስልትና ዘዴዎች ሲገልፁ ቃለ መጠይቅን በመጠቀም፣ ቡድን ተኮር ውይይትን በመጠቀም፣ ለጓደኞቻቸው ሪፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ እና የተለያዩ መጠይቆችን

በማዘጋጀትና በመጠየቅ በቂ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል። በዚሁ መሠረት ተከታታይ አሰሳ በማድረግና የጠበቀ ክትትል በማከናወን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስብእናን ማወቅ ይቻላል ሲሉ ይገልፃሉ።

### 2.9.1.6. የፍላጎት መመዘኛ (interest inventory)

Buross (1978) እና Craing (1979) የስብእና ክፍል እንደሆነና ከግለሰብ ዳራ፣ ገጠመኝ፣ ችሎታ ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ፍላጎትን እንዴት መለካት እንደሚቻል እንደሚከተለው ገለፃቸውን ያቀርባሉ።

የሰውን ፍላጎት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር ከፈተና እና ከስብእና መለኪያ (personality Inventory) ጋር ተመሳሳይነት አለው። በትምህርት ቤት የሚገኙ የምክር አገልግሎት ሰጪዎች ወይም የሥነ ልቦና ሊቃውንት የአንድን ሰው የሥራ ወይም የትምህርት ዓይነት ምርጫን ለማወቅ የሚጠቀሙበት የፍላጎትን ሥዕል ሊያሳይ የሚችል መመዘኛ ነው። መመዘኛውም የአንድ ሰው አንድን ጉዳይ ስለመውደድ /መምረጥ/ መፈለግ ወይም መጥላት/ አለመፈለግን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሚገኙ የተለያዩ የመልስ ውጤቶችን በመመዝገብና በማስላት ከስሌቱ በተገኘው ውጤት መሠረት ፍላጎት ይለካል።

የፍላጎት መመዘኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው በE.K Strong (1927 እና 1928) ሲሆን ይህም እስከ 1974 ድረስ በስፋት አገልግሏል። በመቀጠልም Cambell (1974) ለሴትና ለወንድ የሚሆን በሰባት አርእስተ ጉዳይ ላይ የቀረበ የፍላጎት መመዘኛ (ወደ 375 ጥያቄዎችን) አዘጋጅቷል። ርዕሰ ጉዳዮቹም፡-

1. ሥራን የሚመለከት
2. የትምህርት ዓላማ
3. ጨዋታ ወይም ደስታ
4. ተግባራትን
5. የሰው አይነቶች
6. ከሁለት በላይ ተግባራት ውስጥ አንዱን በመምረጥ እንደ ምርጫው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና
7. በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ መስማማትን አስመልክቶ የቀረቡ ናቸው (Craig, 1979)።

ከነዚህም ከ1-5 ያሉት የአንድን ሰው ግላዊ ምርጫ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው። በ6ኛው ተራ ቁጥር ሥር የሚካተቱት ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ አማራጮች ቀርበው በፍላጎት ቅደም ተከተል መሠረት ማስቀመጥን የሚመለከት ሲሆን በ7ኛው ተራ ቁጥር ሥር የሚካተቱት ጥያቄዎች ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ መስማማት ወይም አለመስማማትን በተመለከተ የቀረቡ የግል ገለፃዎች ናቸው። ለምሳሌ ያህል አዎን፣ አይደለም በማለት ለመመለስ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ ናቸው (Callahan, 1988; Craig, 1979)።

የግለ-ራስ መመዘኛ ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ ከፍላጎት፣ ከአጫጭር የህይወት ታሪኮች ጋር ተቀናጅተው የሚቀርቡና ከስድስት የተግባር ክፍሎች ጋር የተያያዙ ናቸው። ለምሳሌ ያህል እውናዊ (realistic)፣ ጥናታዊ (investigative)፣ ጥበባዊ(artistic)፣ ማህበራዊ(social)፣ ታታሪነት (enterprising) እና ተለምዶአዊ( conventional) ጋር የተያያዙ ናቸው። እንዲሁም 23 መሠረታዊ ፍላጎት (እርሻ፣ መካኒክስ፣ ጤና ሳይንስ፣ ማስተማር፣ ንግድ ወዘተ) እና 124 የሥራ መስኮችን (ጥበብ፣ ግብርና፣ ፖሊስ ፣ኃላፊ፣ የሥነ ልቦና ሊቃውንት፣ መምህር ወዘተ...) በተጨማሪ ከስራ ጋር የተያያዙ የትምህርት ዝንባሌ(orientation)፣ ስሜቱን አውስጦ የሚይዝ(introversion) ስሜቱን አውጥቶ ሚያሣይ(extroversion) በማካተት በሊስት የመቆጣጠሪያ ሰነድ (administrative indexes) ላይ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ ሆኖ የቀረበ ነው። እንዲሁም የመመዘኛ ጥያቄዎቹ ተገቢነት (validity) እና አስተማማኝነት (reliability) በትክክል የታየ መሆኑም ተገልያአል። የፈተናው አይነት ብዙ መልክ ቢኖረውም አስተማማኝነቱ በሚዛን (Scales) ላይ 0.80 ይሆናል። የሥራ ፍላጎትን አስመልክቶ የቀረበው ጥያቄ አስተማማኝነት ደግሞ በ0.60 እና 0.70 መካከል ላይ እንደሆነ ሊቃውንቱ ይገልጻሉ (Craig, 1979)።

### 2.9.1.7. የትምህርት ፍላጎት መመዘኛ ቅኝት (Vocational interest survey)

የትምህርት ዓይነትን በተመለከተ የሚቀርብ የፍላጎት መመዘኛ ከሌሎች የፍላጎት መመዘኛዎች በመጠኑም ቢሆን ይለያያል። ይሄም የተማሪዎች ውጤት የሚገለፀው እንደ ፍላጎት ሁሉ በፐርሰንታይል ሲሆን በእያንዳንዱ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ደግሞ የእያንዳንዱን ውጤት ወደ አማካኝ በመለወጥ በ "t" ቴስት ቀመር ልዩነቱን ማወቅ ይቻላል።

ሌላው ውጤት መለኪያ መሳሪያ በተማሪዎች የትምህርት ዝንባሌ ላይ ተመርኩዞ ፍላጎትን ሊለኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ትምህርቱ ያለውን የፍላጎት ደረጃ መመርመር ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በሁለተኛ ደረጃ ወይም በኮሌጅ ለሚሰጡ የትምህርት አይነቶች እንደ እርሻ፣ የኑሮ ዘዴ፣ እደ ጥበብ፣ ማህበራዊ ሳይንስ፣ ባዮሎጂካል ሳይንስ፣ ቋንቋ እና የመሳሰሉትን የትምህርት አይነቶች በተመለከተ ተማሪዎች ያላቸውን የፍላጎት ደረጃ በዚህ የፍላጎት መመዘኛ ማወቅ ይቻላል፡፡ ለእነዚህ የትምህርት ዓይነት የፍላጎት የመመዘኛ መስፈርቶችን በተለያየ መልኩ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ከመመዘኛዎቹ ውስጥም ባለሶስት፣ ባለ አምስትና ባለሰባት ስፍርታዊ መመዘኛ መስፈርትነት የሚጠቀሱ ናቸው (craing, 1979; gardner, 1985 and Cllahan, 1988)::

ባለ ሶስት ስፍርታዊ መመዘኛ የሚባለው ሦስት አማራጮችን የያዘ ሲሆን ባለ አምስት ስፍርታዊ መለኪያ የሚባለው ደግሞ አምስት አማራጮችን የያዘ ነው፡፡ ይሁንና የሰውን ፍላጎት ለመለካት በይበልጥ አመቺ የሆነው ባለ አምስቱ ስፍርታዊ መለኪያ እንደሆነ ከድረ-ገጽ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ እንደ Gardner (1985) ባለ ሰባት ስፍርታዊ የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ ጥያቄዎችን በተጨማሪነት አቅርበዋል፡፡ ከባለሶቱና ከባለ አምስቱ ስፍርታዊ የመለኪያ መሳሪያዎቹን በተመለከተ ከመለካት አንፃር ሲታይ ግን ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑንም ምሁራኑ ያስገነዝባሉ (Buros, 1959 and 1979; Gardner, 1985 and Mitcheil, 1985)::

## 2.9.1.8 በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

በTudor (1995) አገላለፅ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የተማሪው ነፃነት፣ የተማሪው ለአንድ ጉዳይ ያለው አመለካከት፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የተማሪው ነፃነት ስንል ተማሪው ከማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ በአንጻራዊነት ነፃ ሆኖ መገኘትን ያመለክታል፡፡ በዚህም ተማሪው በራሱ ፍላጎት የተመራ የሚማር ካልሆነ በትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው በማለት Tudor (1995); Noll (1979) and Schonell (1965) ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦችም ሆነ በተለያዩ ሊቃውንት በቀረበው ገለፃ መሠረት በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ተብለው የሚጠቀሱት 1ኛ) ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት 2ኛ) የማስተማሪያ ዘዴ 3ኛ) ተማሪው ለትምህርቱ ያለው አመላካከት 4ኛ) ተማሪው የሚገኝበት ሁኔታ (የተማሪው ጉብዝና፤ የሚኖርበት ማህበረሰብ፣ እድሜውና ጾታ ወዘተ)ና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህንም ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን፡፡

## 2.9.1.8.1 ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ግምት

Cronbach (1963) አመለካከት እንደ ማንኛውም የሰብእና ክፍሎች በትምህርት ሂደት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪው ለሚማረው የትምህርት አይነት ጥሩ አመለካከት ከሌለው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት አይኖረውም፡፡ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት ጥሩ የሆነ አመለካከት ካለው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ይኖረዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ካለው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት አይኖረውም በማለት ይገልፃሉ (Stern 1991; Gardner, 2006)፡፡

በሌላ በኩል ከድሬ ገፅ በተገኘው መረጃ መሠረት ብዙ ተማሪዎች የሂሳብ ትምህርትን ለመማር አዎንታዊ አመለካከት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ጥሩ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር አዎንታዊ ፍላጎት እንደሌላቸው ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድን ትምህርት የመማር ፍላጎት ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ተማሪዎች ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ናቸው (Harmer, 1991; Gardner, 2007 & Masgort, 2003)፡፡

በተመሳሳይም በአመለካከት አንድን የትምህርት አይነት በመማር ፍላጎት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ሲገልፁ፤ ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ጥሩ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል (Krashen, 1982 & 2009; Gardner & Masgort, 2003; Gardner, 2006; and Browen, 2007)፡፡ እንዲሁም አንድን ትምህርት ለመማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ለትምህርቱም ጥሩ የሆነ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል በማለት ይገልፃሉ (Spolsky, 1989; Skinner, 1985 buglisky, 1971)፡፡

ዲንቁሳ (1996ዓ/ም) ኢ-አፌፊትና አፊፊት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት አጥንተው፤ ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው አመልክተዋል። ይሄውም "አፌፊትም ሆነ ኢ-አፌፊት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚጠሉ አይደሉም።" ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል። ከዚህም እንደምንረዳው አዎንታዊ የሆነ አመላከት ከተማሪዎች የመማር ፍላጎት ጋር አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳለው፣ አመለካከት እና ፍላጎት እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊ መሆናቸውን በጥናቱ ላይ አስቀምጧል።

Hurlock (1972) ላይ እንደተመለከተው ደግሞ ተማሪዎች አንድን ትምህርት ምንም ጥቅም አይሰጥም ወይም ትምህርቱ ከባድ ነው የሚል አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን የመማር ፍላጎት አይኖራቸውም። ፍላጎታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖን ያሳድራልና። በተቃራኒው ተማሪዎቹ ትምህርቱ ጠቀሜታ አለው ብለው የሚገምቱ ከሆነና ስለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱንም ለመማር ፍላጎት ይኖራቸዋል (Harmer, 1991; Rubinsen, 2001; Gardner & masgort, 2003; Krashen, 2009; Gardner, 2007 and Browen, 2007) ከዚህ ሀሳብም መረዳት የሚቻለው ፍላጎትና አመለካከት አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ ትምህርቱን ለመማር አዎንታዊ ፍላጎት እንዲኖራቸው ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችል የተገለፀው መረጃ ያመለክታል።

### 2.9.8.1.2. የመምህሩ የማስተማር ዘዴ (Teaching method)

የማስተማር ዘዴ ለመማር ማስተማሩ ሂደት በጣም አስፈላጊና አቢይ ጉዳይ ነው። ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ጥሩ ፍላጎት እንዲኖራቸው ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል። Evans (1965) መምህሩ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሳደግ በመማር ማስተማር ላይ ከፍተኛ ሚንን ይጫወታል። በትምህርት ቤት ውስጥም በጣም አስፈላጊው ሰው ነው። ምክንያቱም መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት ለተማሪዎቹ ማነቃቂያ በመስጠት ለትምህርታቸው ንሺ እንዲኖር ያደርጋል። የተማሪዎቹ ስሜትም ወደ ሚሰጠው ትምህርት እንዲሆን በማድረግ ረገድ የመምህሩ የማስተማር ዘዴ ከፍተኛ የሆነ እገዛ ያደርጋል። ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ።

የሰው ልጅ አንድን ትህርት ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ካለው ተነሳሽነቱ ከመማር ፍላጎት የመጣ ነው፡፡ ፍላጎት ደግሞ የትምህርትን ሂደትና እንቅስቃሴን ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ትክክለኛ የማስተማሪያ መሳሪያን በመጠቀም ማስተማሩ እንደማነቃቂያ ሀይል ሆኖ ከማገልገሉም በተጨማሪ በተማሪዎችም ዘንድ የመማር ፍላጎትን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡ ስለዚህም መምህሩ የተማሪችን ስብእናና ፍላጎታቸውን ለይቶ በማወቅ ትክክለኛ የሆነ የማስተማር ዘዴን ከትክክለኛ የማስተማሪያ መሳሪያ ጋር አቀናጅቶ በመጠቀም ማስተማር አለበት፡፡ ይህ ተግባራዊ ከሆነ ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ወደ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት መሸጋገር ይቻላል፡፡

Wilson (1971) እንደሚገልፁት ደግሞ ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ፣ ለትምህርታቸው ፍላጎት እንዲኖራቸው የማስተማሩ ዘዴ ጥሩ እገዛ ያደርጋል፡፡ እየተሰጠ ባለ ትምህርት ዙሪያ የመማር ፍላጎት እንዲኖር የምንጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ነው፡፡ Harmer (1993) በተከናወነ ጥናታዊ ፅሁፍ በማስደገፍ እንደገለፁት የመማር ፍላጎት የሚመጣው ትምህርቱ የሚቀርብበት መንገድ የተስተካከለ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ የመማር ፍላጎትን ማምጣት፣ የሚቻለውና ስሜታዊ መቀስቀስ የሚቻለው ትምህርቱ ከቀስቃሽ ማበረታቻ ጋር ተያይዞ የሚሰጥ ከሆነ ነው፡፡ የተማሪውንም የመማር ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡

እንዲሁም Harmer (1991) በ1970 ባዘጋጁት ጽሁፋቸው ላይ የመምህሩ የማስተማር ዘዴና በተማሪዎች የመማር ፍላጎት መካከል ያለውን ግንኙነት ዘርዘር አድርገው ገልፀዋል፡፡ ጥናቱም የተካሄደው 12-17 እድሜ ባላቸው ተማሪዎች ላይ ሲሆን ተማሪዎች አንድን መምህር በጥሩ የትምህርት አቀራረቡ ጥሩ መምህር ሆኖ ሊመረጥ የሚችልበትን መስፈርት አስቀምጠዋል፡፡ ያም በሚከተለው መልክ ከተራ ቁጥር አንድ ጀምሮ እስከ ተራ ቁጥር አስር ድረስ ቀርቧል፡፡

1. ትምህርቱን በጣም ሳቢ፣ ማራኪና ተፈላጊ አድርጎ የሚያቀርብ
2. በጥሩ ንበት ማስተማር የሚችል
3. ግልፅ አድርጎ መግለፅ የሚችል
4. ቋንቋውን በጥሩ ደረጃ መናገር የሚችል
5. ለተማሪዎቹ ያለው አመለካከት በእኩል ደረጃ ከሆነ
6. ሁሉንም ተማሪ አሳታፊ የሚያደርግ

7. የችግር ፈቺነት ተግባርን የሚያከናውን

8. እንደ ተማሪው ባህሪና ልዩነት እገዛ የሚያደርግ

9. ተማሪዎቹ በተግባር እንዲሳተፉ የሚያደርግና

10. የመናገርና የመስማት ክሂልን የማስተማር ዘዴን ተግባር ላይ የሚያውል ናቸው፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ሀሳቦች መሠረት ከበጣም ከፍተኛ ጀምሮ በተዋረድ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ዝርዝር ተግባሮችን መምህሩ የሚያከናውን ከሆነ ተማሪዎቹ የትምህርት ፍላጎት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ ክፍሉን ሳቢ.ና ማራኪ. እንዲሆን ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሌላው በተራ ቁጥር 5-6 እና 9 ላይ የቀረቡት ተግባራት ደግሞ ተማሪዎችን በይበልጥ ተሳታፊ የሚያደርጉና በተማሪውና በመምህሩ የጋራ ግንኙነት ላይ ያተኩሩ ናቸው፡፡ በዝርዝሩ መሠረት ምንም ትምህርት ያስተምር የመምህሩ ተመራጭነትና ጥሩነት ከላ በመስፈርትነት በቀረበው ሀሳብ ላይ ለማስረዳት ተሞክሮአል፡፡

ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ለተማሪዎች ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ተጠይቀው ያቀረቡት ሀሳብና የአንድ መምህር ተመራጭነትና ብቃት በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀው፡፡

1. ለተማሪዎቹ ጥሩ ርህራሄ ሊያሳይ የሚችል
2. ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ የሚመለከት እና
3. በራስ የመተማመን መንፈስ ያለው ከሆነ ነው፡፡ እነዚህ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚፈለግ መምህር የሚመረጥበትና ክፍሉን ሳቢ.ና ማራኪ. (ተወዳጅ) ማድረግ የሚችል እንደሆነ ተገልፃል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው የመምህሩ የማስተማር ዘዴ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት ተፈላጊ.ና ተወዳጅ እንዲሆን የራሱ የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ነው፡፡ Turi (2003) ከላይ ቀረበውን ሀሳብ በማጠናከር በተማሪዎች የትምህርት ፈላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድረው የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴው ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም አንድ ትምህርት ሲ.ቀርብ በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ “አዝናኝ” አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ትምህርቱን በተማሪዎቹ ዘንድ ተፈላጊ.ና ተወዳጅ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ዓይነት የአቀራረብና የማስተማር ዘዴ የሚቀርብ ትምህርት ተማሪዎችን የሚያዝናና ስለሚሆን ሳይታወቃቸው ትምህርቱን ይማሩታል፡፡ በትምርቱም ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በጨዋታ መልክ የሚቀርብ ትምህርት አስደሳች ነው። ትምህርቱ በጨዋታና አዝናኝ በሆነ መልኩ የሚቀርብ ከሆነ ያለ መሰልቸት ብዙ መማር ይቻላል። የተንዛዛና አሰልቺ አይሆንም። ስለዚህም ይህ የማስተማር ስልት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ይጨምራል። McCombs (1997) Turdor (1996)ን ገለፃ መሠረት በማድረግ በተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከፍላጎታቸው ጋር በተገናኘ መልኩ መማር እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ በሚማሩት ትምህርት ስለሚደሰቱ፣ የመማር ፍላጎታቸውን ከፍ ያደርገዋል። በዚህ ዘዴ ትምህርቱ ከእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ስለሚሰጥ ከተለያየ አቅጣጫ ትምህርቱን ከፍላጎታቸው ጋር አጣጥመው ለመማር ይመቻቸዋል። የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንዲችሉም ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል። በአጠቃላይ ተማሪን ማዕከል ያደረገ ትምህርት፣ ተማሪዎቹ እንደየልምዳቸውና አስተሳሰባቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል። ይህም ተማሪዎቹ በከፍተኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት ለትምህርቱ እንዲነቃቁ የማድረግ ኃይል ስላለው፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፣ ውጤታማም ይሆናል።

በአጠቃላይ ከላይ የተለያዩ ሊቃውንት ባቀረቧቸው ገለፃ መሠረት የማስተማሪያ ዘዴውና የትምህርት አቀራረቡ ስልት በተማሪው ፍላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅታኖ እንደሚያሳድር መረዳት ይቻላል።

### 2.9.1.8.3 የመምህሩ ስብዕና

መምህሩ በመማር ማስተማር ሂደት እና ስኬት አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ቀደም ብሎ በቀረበው ርዕስ ላይ ተነስቷል። እዚህ ላይ ደግሞ የመምህሩ ስብዕና በማስተማሩ ሂደት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ማሳየት ነው። መምህሩ በተማሪው የስብዕና እና ባህሪና የመማር ፍላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል (Browen, 2007)።

Barnard (1972) እንደሚገልፁት የመምህሩ ስብእና በተማሪው የመማር ልምድና ፍላጎት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል ይላሉ። ይህም የመምህሩ የስብእና ባህሪይ ተማሪው በሚማረው የትምህርት ፍላጎት ላይ ከግምት ሊገባ በሚችል መልኩ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያስገነዝባሉ።

Evanse (1965) እንደሚሉት ደግሞ የአንድ መምህር አመለካከትና ተግባር የአምባገነንነትና የአመፀኝነትን ስሜት የሚያንፀባርቅ ከሆነ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂት ላይ ተፅእኖና ጫና ስለሚያሳድር በተማሪዎች ላይ የፍራቻ ስሜትን ያነግሳል። በትምህርታቸው በመማር ፍላጎታቸው ላይም አሉታዊ የሆነ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል በማለት ይገልፃሉ። በአንፃሩ ደግሞ መምህሩ የተማሪችን ስሜት የሚረዳና፣ ልዩ ድጋፍ የሚያደርግቸው ከሆነ በተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅነትን ያተርፋል። ተማሪዎቹ መምህሩን የሚወዱት ከሆነ ደግሞ የሚያስተምረውን ትምህርትም ሊወዱት ይችላሉ።

በዙሪያው የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ተማሪዎች መምህራቸውን የሚወዱ ከሆነ ለትምህርቱም አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ይኖራቸዋል። መምህራቸውን የማይወዱ ከሆነ ደግሞ በሚማሩት ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ለትምህርቱም አሉታዊ የሆነ አመለካከትና ፍላጎት ይኖራቸዋል።

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ አስመልክተው ማብራሪያ ሲሰጡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መምህሩን የሚጠሉት ከሆነ፤ በተለይም ተማሪዎቹ የኮሌጅ ተማሪዎች ከሆኑ፤ መምህሩን በመጥላታቸው ምክንያት የሚማሩትን ትምህርት በሚቀጥለው አመት ለመውሰድ ሲሉ ትምህርቱን ላይማሩት ይችላሉ። በአንፃሩ ግን መምህሩ ሰላማዊ ጠንካራና ከማንኛውም ኢ-ሥነ ምግባራዊና ተገቢ ካልሆነ ተግባር ቁጥብ ከሆነ በተማሪዎች ዘንድ መወደድንና ከበሬታን ስለሚያተርፍ የሚሰጠው ትምህርትም በተማሪዎቹ ዘንድ መምህሩም ተወዳጅና የተከበረ ይሆናሉ፤ በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ውጤታማና ስኬታማ ይሆናሉ፣ በማለት ይገልፃሉ (Barnard, 1972; Evanse, 1965)።

Harmer (1991) ተማሪዎች መምህራቸውን የሚወዱት ወይም የሚጠሉት ከሆነ በትምህርታቸው ንሺና ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ይላሉ። ለምሳ ያህል ሁለት መምህሮች በተመሳሳይ ዘዴ ተመሳሳይ ተማሪችን አስተምረው በሁለቱ መምህሮች የተማሩት ተማሪዎች በመሀከላቸው ሰፊ ልዩነት ያለው ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው መምህሩ እራሱ በትምህርቱ ላይ ራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው ነው። በአጠቃላይ ከላይ ሊቃውንቱ በገለፁት መሠረት የመምህሩ ስብእና በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖን እንደሚያሳድር ነው የምሁራኑ ገለፃ የሚያስረዳው።

### 2.9.1.8.4 ተማሪዎች ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ያላቸው ተነሳሽነት

እንደ Bugelsk (1971) እና Harmer (1991) አገላለፅ አንድ ተግባር ለሚከናወን የሚነሳ ግለሰብ ተግባሩን በቀላል ዘዴ ማከናወን እንዲችል በዙሪያ እውቀት ያስፈልገዋል። ስለዚህ ተግባሩን ለማከናወን ሊረዳው የማያስችል ትምህርትን ለመማር ከፍተና ፍላጎት ያድርበታል። ለምሳሌ ያህል መኪና የመንዳት ፍላጎት ያለው ሰው መኪናውን ለመንዳት የሚያስችል ትምህርት ለመማር ፍላጎት ያድርበታል።

በሌላ በኩልም አንድ ጉዳይ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን መንገድና የማግኛ ዘዴውን ለማወቅ ሲል በዙሪያው ዕውቀትን የሚሰጥ ትምህርት የመማር ፍላጎት ይኖረዋል። እንዲሁም የማንበብ ፍላጎት ያለው ግለሰብ ማንበብ እንዲችልና የማንበብ ችሎታ እንዲኖረው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ይኖረዋል።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎችና ሀሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው ለአንድ ተግባር የመነሳሳት ጉዳይ በዙሪያው የተለያዩ እወቀትንና ችሎታን ለማግኘት ሲባል አንድን ትምህርት የመማር ፍላጎት እንዲኖር ግፊት እንደሚያደርግ ያስገነዝባል። ስለዚህ ትምህርትን ለመማርና አንድን ተግባር ለማከናወን ተነሳሽነት መኖር ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነና የመማር ፍላጎትንም እንደሚጨምር ነው ሊቃውንቱ የሚያስረዱት(Harmer; 1991; Rubinsen, 2001; Gardner & Masgort, 2003; Gardner, 2007 and Browen, 2007)::

### 2.9.1.8.5 ተማሪው የሚገኝበት አውድና ማህበራዊ ጉዳይ

Tudor (1996) እና Spolisky (1989) በተማሪ ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩት ውስጥ አንደኛው ራሱ ተማሪው የሚገኝበት አውድና ነባራዊ ሁኔታ ነው። ያም ተማሪው ከተማሪው ጋር ያለው ግንኙነት ተማሪው ከተለያዩ የማህበረሰብ አካላትና ከቤተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት፣ የአካባቢ ሁኔታ፣ የቤተሰብ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች እና የተማሪው የንቃተ-ህሊና ደረጃ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገልፃሉ።

Schonell (1965) የማንበብና የመማር ፍላጎት በተለያዩ ምክንያቶች ተፅዕኖ ሊደርስበት ይችላል። ከነዚያም ውስጥ አንደኛው ምክንያት ከትምህርት ቤት ቁጥጥር ውጭ ያለ ነው። ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የመማር፣ የማንበብ ዝንባሌን እና ፍላጎትን ለማነሳሳት ከፍተኛ

ሚና አለው፤ በማለት በማንበብና በመማር ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩትን ጉዳዮች በሚከተለው መልኩ ያቀርባሉ።

እንደ Schonell (1965) ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

1. ቤተሰብ፡- የተማሪው ቤተሰብ ተማሪው በሚማረው ትምህርት ላይ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። እንዲሁም ለተማሪው የመማር ፍላጎት መሠረት ሲሆኑ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተፅእኖ ያሳድራል። በልጅነት ጊዜ ላይ የሚመጣ አመለካከት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት ቤተሰቦች ናቸው። ስለዚህ የልጅነት ጊዜ አመለካከት በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተፅዕኖን ያሳድራል።
2. የተማሪዎች የአእምሮ ችሎታና ንቃተ ህሊና፡- የተማሪው ንቃተ ህሊና የሚገኝበት ደረጃ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል።
3. በአእምሮአቸው በሳልና ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው። የመማርና የማንበብ ፍላጎት ከአእምሮ ብስለትና ንቃት ህሊና ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው።
4. በተፈጥሮ የሚመጣ የመማርና የማንበብ ፍላጎት፡- ተማሪዎች በተፈጥሮአቸው የማንበብና የመማር ፍላጎት ይኖራቸዋል። ስለዚህም አንድ ሰው በተፈጥሮው ለተለያዩ ትምህርቶች የተለያየ ችሎታና ፍላጎት ይኖረዋል ማለት ነው።
5. የማንበብና የመማር ፍላጎት፣ በየጊዜው በሚደረግ ጥረትና ልምምድ ተግባር ሊመጣ ይችላል። ተማሪው የሚያከናውነው የእለት ተእለት ልምምድና ተግባር በማከናወን በተማሪው የማንበብና የመማር ፍላጎት ላይ የራሱ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል።
6. አስፈላጊ የሆነውን ርእሰ ጉዳይ መርጦ የመማርና የማንበብ ፍላጎት የአንድን አስፈላጊ የሆነን ነገር ፍላጎት ይጨምራል (Harmer, 1989; Schonell, 1965)::

እንደ Tudor (1996) እና Craig (1979) አገላለፅ ደግሞ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተግባራትን በሚከተለው መልኩ ያቀርባሉ። እነዚያም ከተማሪዎቹ ጋር አብረዋቸው የሚማሩት ተማሪዎች ጎበዝ ከሆኑና ከጎበዞቹ ተማሪዎች ለመድረስ የሚጣጣሩ ከሆነ የመማር ፍላጎታቸው እየጨመረና እየዳበረ እንዲሄድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በተጨማሪም ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው የሚማማሩ ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በእምነት፣ በአመለካከትና፣ በጥቅም በአንድ ቦታ እንዲሰባሰቡ

ያደርጋቸዋል (Ball and Davitz, 1970)። እንደ ምሁራኑም ገለፃ በትምህርት ፍላጎት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አራት ሂደቶችን በሚከተለው መልኩ ያስቀምጣሉ።

1. የትብብር ሂደት፡- የስሜት ተመሳሳይነትን፣ የጋራ ስሜትንና ፍላጎትን በማሳደግ የጎላ ልዩነትን ማንበብን የሚመለከት ነው። ስለጋራ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ፍላጎትን ይጨምራል።
2. ውድድር፡- ግላዊ ስሜትን እና አመለካከትን የሚጨምር ሲሆን የጋራ አስተሳሰብ ስሜትን ይቀንሳል፤ ቀጥተኛ ተቃርኖን ይጨምራል፤ አንተ መጥፎ ነህ እኔ ጥሩ ነኝ ወደሚለው አዝማሚያ ይወስዳል። በውድድርም ላይ ከፍተኛ ወደ ሆነ አድሎአዊ ሁኔታ ይወስዳል። የአስታራቂነትን ተግባር ወደ እኩይ ተግባር ይቀይራል። የሰውን በጎ አድራጎትና ተግባራትን ከማሳደግ ይልቅ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል።
3. አንዱ ለሌላው ያለው አመለካከት
   ሀ. የመረዳዳት ሂደት፤- መተሳሰብን፣ መተማመንንና የሌላውን ስሜት ከመጠበቅ አንፃር ፈቃደኝነት እንዲኖር ያደርጋል።
   ለ. የውድድር ሂደት፡- ተማሪን ወደ ጥርጣሬ፣ የሌላ ሰው ስሜትን እና ፍላጎትን በመጫንና ከሌላ ሰው ለሚቀርብ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል።
4. የተግባር ዝንባሌ፡- የመረዳዳት ሂደትን ይጨምራል ያለመስማማትን ጉዳይ በጋራ በመሆን እንደ ጋራ ችግር በማየት በጋራ ሆነው እንዲፈቱ ያደርጋል። የሌላውን ሰላምና ስሜትን በመጠበቅ ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ የሚሆኑ ጉዳዮችን ወደ መፈለግ ተግባር ይመራል። የመረዳዳት፣ የመደገፍ፣ የመመካከር የመተጋገዝ ፍላጎትን ይጨምራል። ያለመግባባት ስሜትን ይቀንሳል። ብዙ ሀይል እንዲኖር ያደርጋል።

በአጠቃላይ ተማሪዎቹ የሚገኙበት መቸት ወይም አውድ፣ ተግባር፣ ማህበረሰብና ፖለቲካዊ ሁኔታ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ የራሱ አስተዋፅኦ እንዳለው ከላይ በዝርዝር የቀረበው ገለፃ ያለክታል።

### 2.9.2. አመለካከት(Attitude) ምንድነው?

እንደ ፍላጎት ሁሉ የአመለካከትን ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይግለጹታል። ይሁን እንጂ ሁሉም ምሁራን የጋራ የሚያደርግ ሀሳብ አላቸው። የስነ አእምሮ ሊቃውንት ቃሉን ከዝንባሌ፣ ከእይታ/አስተያየት አንፃር ይገለገሉበት እንደነበረ ነው የሚያስረዱት። Gerry(1970) አመለካከት አንድን ነገር የመውደድና የመጥላትን ወይም የመቅረብና መራቅን(approach-avoidance) አቅጣጫን የሚያመለክት ስሜት ነው ይላሉ። አመለካከት መላምታዊ ሆኖ በውስጡ ግምገማዊ እሳቤን የያዘ ሲሆን ስለ ክፍሎች ወይም ቡድኖች አሉታዊና አዎንታዊ የሆነ ስሜትን የያዘ የስብእና ክፍል ነው፤ በማለት ይገልጻሉ።

አመለካከት የተደራጀና ተከታታይነት ያለው ሰዎችን፣ ቡድኖችንና ማህበራዊ ጉዳዮችን ባጠቃላይ በአካባቢው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊ እና ባሕሪያዊ ክስተት እንደሆነ ይገልፃሉ (Lambert, 1969; Gagne,1977; Malim, and Birtch, 1998 እና Gardener,2006)። ከነዚህ ፍቺዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አመለካከት ከሰው ጋር አብሮ የሚወለድ ሳይሆን በእድገት ሂደት የምናዳብር የስብእና አንዱ ክፍል እንደሆነ kuppaswamy (1984) እና Aggarwa (1998) ያረጋግጣሉ። አመለካከት ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን ወዘተ የመውደድና የመጥላት፣ የመደገፍና የመንቀፍ፣ የመቅረብና የመራቅ...ዝንባሌ፣ ስሜት፣ ወይም እርምጃ ነው። ይሄም ባህሪ እራሳችንንና አካባቢያችንን ለይተን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ በአካባቢያዊ፣ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ......ተጽእኖ ምክንያት ቀስ በቀስ ከስብእናችን ጋር እየተዋሀደ የሚሄድ ወይም በውስጣችን በሂደት እየዳበረ የሚሄድ ነው።

### 2.9.2.1 አመለካከትን የማጥናት አስፈላጊነት

አዎንታዊ የሆነ አመለካከት በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቦታ፣ በማህበራዊ መስክ፣ በኢኮኖሚው መስክና በፖለቲካውም መስክ ሳይቀር ውጤታማ ተግባርን ለማከናወን ወሳኝ ነው፤ ከተባለ በሁሉም መስክ ያለውን የአመለካከት ሁኔታን ማጥናት ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል። ከመማር ማስተማር ሂደት አንጻር በBrown (2007) እና Gardner(2006) አገላለጽ ለአመለካከት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያስረዳሉ። ምክንያቱንም ሲገልጹ ተማሪው ለትምህርቱ ካለው ንሺ (motivation) እና በትምርቱ ከሚያስመዘግበው ውጤት ጋር በማያያዝ

ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ተማሪው አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለትምህርቱ የመማር ፍላጎት ወይም ንሺ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ለትምህርቱ ንሺ ያለው ተማሪ ደግሞ ውጤታማ ስለሚሆን አመለካከትን አስፈላጊ ከሚያደረጉት ነጥቦች ውስጥ አንዱ መሆኑን ነው ምሁራኑ የሚገልጹት(krashen,2009; Gardner,1985 and Brown,2007)፡፡

ስለዚህ ለምናከናውነው ተግባር አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ከሌለ የሚመዘገበው ውጤት ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለሥራ የሚኖረው ተነሳሽነት ዝቅተኛ እንዲሆን ስለሚያደርገው በመሆኑ ነው፡፡ ምሁራኑ እንደሚያስረዱት አመለካከት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ጫና መፍጠር ነው፡፡

ለተማሪዎች አንድን ትምህርት ማስተማር ከመጀመሩ አስቀድሞ የተማሪዎችን አመለካከት ማጥናትና መረዳትን ይጠይቃል ይላሉ(Skiner,1985; Spolsky, 1989; Harmer, 1991 and Brown, 2007):: Gardner (2006፣1985) በጥናታቸው ላይ እንዳሠፈሩት በአመለካከት ላይ የሚደረግ ጥናት ለማህበራዊ ሥነ-አእምሮ ግንባታ የመጀመሪያው የመሠረት ድንጋይ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ አመለካከት ከማህበራዊና ከሥነ-አእምሮ ሁኔታዎች የሚመጣ ስለሆነ በትምህርትና በሌሎች የተግባር መስኮች ዙሪያ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ አመለካከት የሚገኝበትን ሁኔታና አዎንታዊና አሉታዊ መንስኤዎቹን ወዘተ...ለማወቅ በጥናትና ምርምር ለይቶ በማጥናት በመማር ማስተማር ሂደት ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን መፍታቱ አስፈላጊነቱን ያጎላዋል፡፡

አዎንታዊ አመለካከት ያለው ተማሪ የሚሰጠውን ትምህርት ለመማር አዎንታዊ የሆነ ስሜት እንደሚያሳድር ሁሉ በተቃራኒው አሉታዊ አመለካከት ያለው ደግሞ አሉታዊ ተነሳሽነትና ፍላጎት እንደሚኖረው ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን ማንነት ለማወቅ የተማሪዎቹን ታሪክ ማወቁ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተማሪዎች ታሪክ ሲባል እድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ፣ የስራ ሁኔታ፣ ፍላጎትና እምነት፣ ስነልቦናዊ ሁኔታ፣ የትምህርት ዳራና ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ዙሪያ ያለው የእውቀት ደረጃና እውቀትን ማጥናት ማለት ነው፡፡ ከጥናቱ ውጤትም በመነሳት ምን አይነት የማስተማሪያ መሳሪያ መምረጥ እንደሚያስፈልግ ለመወሰንና አዘጋጅቶ ለማስተማር ይረዳል፡፡ በዚህ መንገድ የተማሪዎቹን ዳራ ማወቁ የተማሪዎቹን

ትክክለኛ የሆነ ፍላጎታቸውን ለመረዳትና በዙሪያው ለሚስተዋሉ ችግሮች ማስተካከያ ለመስጠት እንደሚረዳ ገለጻቸው ያስረዳል (Gardner and Masgort, 2003; Garry, 1970)::

በአጠቃላይ የተማሪውን ማንነትና ፍላጎት ማወቁ ተማሪው ለትምህርቱ ከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲኖረው ለማድረግና ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲባል አመለካከትን ማጥናት ወሳኝ ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል። እንዲሁም እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በተዋጣለት መንገድ ለመስጠትና ለማከናወን ከመርዳቱም በተጨማሪ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመጠቀም ሲባል የተማሪውን አመለካከት ማጥናቱ ወሳኝና አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸውን የአመለካከት ደረጃ ማጥናት የሚያስፈልግበት ምክንያት ለተለያዩ ተማሪዎች እንደየ ልዩነታቸውና ልዩ ባህሪያቸው አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን የምሁራኑ ገለጻ ያስረዳል(Gardner and Masgort, 2003; Garry, 1970)::

## 2.9.2.2 ለአመለካከት መፈጠርና መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች

አመለካከት ከባህሪ ለውጥ ውስጥ አንዱ ሲሆን ለውጡም ቀስበቀስ እየተለወጠና እየተፈጠረ የሚሄድ ነው። የሰውን ልጅ እድገት መሰረት በማድረግ የሚፈጠር አለበለዚያም በተወሰነ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚከሰት በቀጣይነት ያለ ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚከሰቱ ነባራዊ ሁኔታዎች አንጻር የሚመጣ ነው። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አመለካከት አካባቢያዊ ሁኔታን፣ የእድሜ ክልልን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ ሊፈጠር የሚችል የባህሪ ለውጥ እንደሆነ አመልክተዋል።

ለአመለካከት መፈጠር መነሻ የሚሆኑ ብዙ ነገሮችን ከላይ ለማየት ተሞክሯል። በተለይ እስከ ወጣትነት እድሜ ላሉት ልጆች ወላጆች፣ ማህበረሰብ፣ ከባህል፣ የእድሜ እኩዮችና መምህራን ለአመለካከት መፈጠር መነሻ ከሚሆኑት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Sills, 1968; Roger, and Houghton, 1995; Malim, and Birch, 1998)::

ወላጆች ልጆቻቸው ከተወለዱበት አንስቶ እራሣቸውን እስከሚችሉበት ድረስ ለአነጋገራቸው፣ ለፍቅርና ጥላቻቸው፣ በእምነታቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በአመጋገባቸውና ማህበራዊ ተራክቦዎች ከተለያየ የማህበረሠቡ አካላት ጋር ያላቸውን ተግባቦት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የበዐላት አካባበር፣

የሚከተሉአቸው ስነስርአቶች፣ ታሪክ የአስተሣሠብ ስሜቶችና ክንውኖች ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አነጋገርን የመጥላትና የመውደድ ዝንባሌን ወዘተ ከብጤዎች መኮረጅ የተለመዱና የወጣት ሰዎች ባህሪያት ናቸው፡፡ በመዝናናትም ሆነ ፍላጐታቸውን ለማሟላት ከእኩዮቻቸው ጋር በመሆን ነው፡፡ አብሮነት ደግሞ የፍላጐት፣ የእምነት፣ የአመለካከት፣ ወዘተ መጋራትን እንደሚያስከትል መገንዘብ እንችላለን፡፡ መምህራን ከዕውቀት አባትነት ባሻገር ተማሪዎች ጥሩ ስነምግባር እንዲኖራቸው፣ አገር ወዳድ እንዲሆኑ፣ ተፈጥሮ አድናቂና የጥሩ ተምሳሌት አርአያ እንዲሆኑ ወዘተ... ይቀርጿቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ከቤተሠብ አንስቶ አካባቢ፣ ህብረተሠብ፣ የእምነት ቦታ፣ ትምህርት ቤት፣ ጓደኛ፣ የእለት ተዕለት ገጠመኞች የአመለካከታችን የፍላጐታችን፣ የተነሣሽነታችን ምንጮች ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

Roger & Houghton (1995) እንደሚሉት አመለካከት በሂደት እየዳበረ ወይም ቀስ በቀስ እየተለወጠ ከሄደ ለውጥን የመቋቋም ሃይል ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ሁኔታዎች ለውጡን እንዲንቀበል የሚያደርጉበት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በሂደት እየዳበረንና እየተለወጠ የመጣን አመለካከት በቀላሉ መለወጥ አይቻልም፡፡ ይሁም ቀስ በቀስ ሂደታዊ በሆነ መልኩ ግን መቀየር ወይም ማስተካከል ይቻላል፡፡

አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል እንደሚችል ሰፊ ማብራሪያም የሚያቀርቡ ምሁራን አሉ፡፡ በነዚህም ምሁራን አተያይ አመለካከት ከከፍተኛ አዎንታዊነት ወደ አሉታዊነት፣ ከከፍተኛ አሉታዊነት ወደ አዎንታዊነት ሊለወጥ መቻሉን በግልፅ አስፍረዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜም አንዴ የዳበረን አመለካከት ለመለወጥ አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜም እንዳለ መሁራኑ ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቶቹንም ሲገልጹ አንደኛው አመለካከታችንን ወይንም እምነታችንን ሊለውጡ የሚችሉ ጉዳዮችን ካለማስተናገድ የሚመጣ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ማህበራዊና አካባቢያዊ ጫናን መሰረት በማድረግ ግለሰቡ ያንን ነገር ትክክል አለመሆኑን በማወቁ ምክንያት ከባህል ጋር ግጭት ይፈጥራል፡፡ የሄ ደግሞ አስቀድሞ ያለውን ግንዛቤ ይዞ ስሜቱን ሲያንጸባርቅ ይስተዋላል፡፡ ሶስተኛው ወቅታዊ ወይም ከዘመናዊነት አተያይና ትርጓሜ ጋር በማያያዝ በሚመጣ የግትርነት አስተሳሰብ ምክንያት የሚመጣ እንደሆነ የሚጠቀሱናቸው (Russcl in Skinner, 1989)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሶስት ነጥቦች አንጻር ግለሰብን፣ ማህበረሰብን፣ ቡድንን፣ ፓርቲን፣ የተለያየ ህብረተሠብ ክፍልን የመሳሰሉትን ክፍሎች አመለካከታቸውን ይዘው እንዲቆዩ ከሚያደርጉት ውስጥ በምክንያትነት የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው፣ ቡድን፣ ፓርቲ፣ ጐሣ፣ የህብረተሠብ ክፍል ወዘተ ቀደም ሲል የነበራቸውን አመለካከት ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ ወይም ከአዎንታዊ ወደ አሉታዊ ሊያስለውጡ የሚያስችሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ ጥናቶች ያረጋግጣሉ (Morgan, 1961; Smith, 1968; Royer, and Houghton, 1998)፡፡

ለአመለካከት መለወጥ ምክንያት ይሆናሉ ብለው ከሚጠቅሷቸው ነገሮች ውስጥ ትምህርት፣ ሚዲያዎች፣ ማህበራዊ መስተጋብር፣ ቅስቀሣ፣ ማስታወቂያ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ የቡድን አባላት ትስስር፣ የተለያዩ ሁኔታዎች፣ የመልዕክት አቀባይ ወይም ምንጭ፣ የመልዕክቱ ተቀባይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የፖለቲካ ሰዎች፣ የስነልቦና ሰዎች፣ ምሁራን፣ የፈጠራ ሰዎች፣ የተግባቦት ስልት፣ የንግግሩ ባለቤት፣ የተደራሲያን ባህሪ፣ የመልዕክቱ ባህሪ፣ መልዕክቱ የተላለፈበት አውድ፣ ወቅታዊ ሁኔታ፣ የግል ግንዛቤ፣ የንድፈ ሃሣብ ውሣኔን እና አገልግሎታዊ ንድፈሃሣብን ያካትታል (Ropger, and Hoaghton, 1995)፡፡

ከቀረበው ሀሳብ ማጠቃለል የሚቻለው አመለካከት አንዱ የባህሪ ክፍል ሲሆን ይሄም የባህሪ ክፍል በተለያዩ የሁኔታዎች አስገዳጅነት ምክንያት መለወጥ መቻሉን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ለአመለካከት መለወጥና መፈጠር በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ሰው የሚገኝበት ማህበራዊ አውድ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ትምህርታዊና አካባቢያዊ ለውጦችን መሰረት ያደረገ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.9.2.3 አመለካከት በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

Cronbach (1963) አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ለሁሉም የትምህርት አይነት በጣም አስፈላጊ ከሆኑት የስብእና ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ Gardner (1985) እና Masgort & Gardner(2003) ቋንቋን ለመማር ጥሩ የሆነ ግንዛቤና ስሜት ከሌለን በትህምርት ሂደት ላይ መልካም ፍላጐት አይኖርም፡፡ ፍላጐት ከሌለ ደግሞ ንሺ አይኖርም፡፡ ተማሪው ለሚማረው የሁለተኛ ቋንቋ ተምህርት አዎንታዊ አመለካከትና ተነሳሽነቱ ከሌለ ትምህርቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመከታተል አዳጋች ስለሚሆን ውጤታማ መሆን ላይ አሉታዊ ተጽእኖን ያሳድራል (Masgort, and Gardner, 2003)፡፡

Lightbown (2011) እንደ አጠቃላይ ሲታይ ማህበረሰባዊ ምክንያቶች በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ፣ ንሺና በትምህርቱ ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ Lightbown (2011) ተማሪው ለሚማረው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይገልፃሉ፡፡ ይህ ማለት ተማሪው በቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ካለው እንደ አፉ-ፈት ለመናገር ጥረት ስለሚያደርግ በድፍረት መናገር ይችላል፡፡ ከቋንቋ ተናጋሪዎቹ ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት ለመፍጠር ከፍተኛ የሆነ ፍላጐትን ያሳድራል (Celce-murcia, 1991; Stewart, 1968 እና Masgort, & Gardner,2003)፡፡

በተቃራኒው ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች አሉታዊ አመለካከት ያለው ከሆነ ቋንቋውን የመማር ፍላጐት እንዳይኖረው ከማድረግም አልፎ ትምህርቱ በሚሰጥበት ሰአትም ደስተኛ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪው የሚማረው እየተሰጠ የሚገኘውን የቋንቋ፣ ክህሎትና እውቀትን ብቻ ሣይሆን የቋንቋውን ተናጋሪ ባህል ጭምር ነው፡፡ Day and Bamford (1998) በበኩላቸው የሁለተኛ ቋንቋን መማር ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ከመማር በጣም የተለየ ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ የሚስተዋል ባህሪ ምክንያት የሚመጣ ነው፡፡

በመጀመሪያ ቋንቋና በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚታዩ ልዩነትን የሚያስከትሉ አራት ነገሮች እንዳሉ Spolsky (1969) ይጠቅሳሉ፡፡ እነሱም የማስተማር ዘዴ፣ ዕድሜ፣ ቅድመ ችሎታ እና አመለካከት ናቸው፡፡ ምሁሩም አክለው አንድን ቋንቋ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለበርካታ ሰዎች የአመለካከት መለወጥና አመለካከትን በተመለከተ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ የሆነ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች አሉ በማለት የሚከተሉትን ይጠቅሣሉ፡፡ እነሱም የተማሪው ጓደኞች፣ የተማሪው ወላጆች፣ መምህሩ፣ ተማሪው እራሱና ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ ይህ አባባል ከCelle-marcia (1991); Masgort & Gardner(2003) እና ከGardner (1985) ሃሣብ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ከሌለው ለትምህርቱ ንሺ ስለማይኖረው ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳባቸው በተጨማሪ ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩበት አውድ በአመለካከታቸው ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሣድር ይገልፃሉ(Spolsley, 1969 እና Masgort, & Gardner,2003)፡፡ የተማሪው ቋንቋን የሚማርበት አውድ ሲባል የማስተማር ዘዴው፣ የመርጃ መሣሪያው፣ የመምህሩ አቀራረብ፣ ትምህርቱ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ወይም ያለመሆኑ፤ ተማሪው ለትምህርቱ ጥሩ የሆነ እይታ ኖሮት የሚከታተልበትን መንገድ ያጠቃልላል፡፡ ስለዚህ የትምህርት አውድ በተማሪው አመለካከት ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖን ሊያሳድር ይችላል፡፡ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ካለ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችልና አሉታዊ ከሆነ ደግሞ በትምህርቱ ላይ ጫና እንደሚያሳድር ከላይ የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡

### 2.9.2.4 ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

ለአመለካከት መለወጥ መነሻ የሚሆኑ ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ በተለያዩ ቦታዎች ተጠቅሰዋል፡፡ ስለዚህ በጐ አመለካከትን ማዳበርና እንዲጐለብት ጥረት ማድረግ የመማር ማስተማሩ ትልቁ ግብ እንደሆነ ሁሉንም የሚያግባባ ነው፡፡ ነገር ግን የተፈለገው እቅድ ከዳር እንዳይደርስ ለአሉታዊ አመለካከት መፈጠር መንስኤ የሚሆኑት ደግሞ ለችግሩ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለይቶ ባለማወቅ የሚከሰት ነው፡፡ ለዚህ መፍትሔ ለመሻትም በአንድ የትምህርት አይነት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ነጥቦችን አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ እና በመተንተን ችግሮችን ለይቶ በማወቅ ማስተካከያ መስጠት ከተቻለ የመማር ማስተማር ተግባሩን ውጤታማ በማድረግ ረገድ ጠቃሚታው የጎላ ነው፡፡

ተማሪዎች በሚማሯቸው የትምህርት ዓይነቶች ላይ አዎንታዊ ወይንም አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚያደርጓቸው ብዙ ሁኔታዎች እንዳሉ ከገለጹ የስነልቦና ምሁራን መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው (Hurlock,1996; Harmu, 1983; Spolsky 1969 እና Morgan, 1969)፡፡ Hurlock (1996) በተለይ በተማሪዎች አመለካከት ላይ አሉታዊ ድባብ ከሚፈጥሩት ነገሮች ውስጥ የእኩዮች አመለካከት አንደኛው ይላሉ፡፡ እንደ Hurmer (1983) እና Hurlock (1996) አገላለፅ በወጣትነት እድሜ ተማሪዎች ከየትኛውም የህብረተሠብ ክፍል በበለጠ በእኩዮቻቸውና በጓደኞቻቸው ፍላጐት እንደሚመሩ ያስገነዝባል፡፡ ተማሪዎች ብዙውን

ጊዜ ከወላጆች በበለጠ በእኩዮች ሐሣብና ምርጫ የመመራት ሁኔታ ይስተዋልባቸዋል። ጓደኞቻቸው በክፍል ውስጥ የሚረብሹ፣ የቤት ሥራ የማይሠሩ፣ የማያጠኑ ከሆነ የእኩዮቻቸውን ዝንባሌ፣ ስሜትና አድራጐት ሊጋሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሰፊ ነው።

ሌላው ደግሞ ከወላጆች አመለካከት የሚመጣ ነው። ይኸውም ወላጅ ስለትምህርቱ ያለውን ግንዛቤ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል። ትምህርቱ በማህበራዊ ህይወት ላይ ያለው ሚና ምን እንደሆነ ያለቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ከሆነ፤ የሃገሪቱ ህግ ስለሚያስገድዳቸው ብቻ ልጆችን ወደ ት/ቤት የመላክ ሆኔታ ይስተዋላል። ይሄ ደግሞ በልጆቹ ላይ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት እንዲዳብር የሚረዳ አይደለም። ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ ማሣደር እንደሚችሉ እንደሚከተለው ያብራራሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ስነልቦናዊ እንቅስቃሴ ላይ የነቃ የተሣትፎ ጫና ወይም የደከመ የተሣትፎ ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ(Lambert and Klineberg, 1967; Gardner, 1975)።

በሌላ በኩልም የተማሪው የትምህረት ውጤት በተማሪው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ለምሣሌ በቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ ውጤት ካስመዘገበ የሚበረታታ ሲሆን፣ በየጊዜው ዝቅተኛ ውጤት የሚያገኝ ከሆነ ደግሞ ጥላቻን እያዳበረ ሊሄድ ይችላል። Hurlock (1996) የትምህርቱ ጠቀሜታ ወይም ትምህርቱ የሚሰጠው ፋይዳ፣ በመምህራን፣ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ ለትምህርት ፖሊሲው ካላቸው አመለካከት፣ በተጓዳኝ የአይነት ትምህርት ውጤታማ የመሆንና ያለመሆን የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል። እንዲሁም አንድ የቋንቋ ተማሪ በስነ-ፅሑፍ ክበብ በድራማ ክበብ በጋዜጠኝነት ወዘተ ውጤታማና ታዋቂ እየሆነ ከሄደ የቋንቋውን ትምህርት እየወደደው ሊሄድ ይችላል(ድንቁሳ፣ 1986 እና Hurlock 1996)።

በክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎች በቋንቋ አፈፊት ወይም አፈፊት ባይሆኑም በሁኔታዎች መመቻቸት የተነሳ በቋንቋው ጥሩ ተናጋሪ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለቋንቋው አፈፊት ወይም የቋንቋው ባለቤት ሆነው ቀበልኛ ተናጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህን ወቅት በተማሪዎች መካከል ብሽሽቅ ወይም ሌላም ፀያፍ ንግግር ካለ እነዚያ ተማሪዎች ከደረሰባቸው የማህበራዊ ቀውስ የተነሳ በቋንቋ ትምህርት ልዩ የሆነ አመለካከት እያዳበሩ ይመጣሉ።

### 2.9.2.5 የአመለካከት መመዘኛ/መለኪያ/ ፈተና (attitude inventory test)

የትምህርት አይነትን በተመለከተ የሚቀርብ የአመለካከት መመዘኛ ፈተና ልክ እንደ ፍላጎት፣ ንሺ፣ መመዘኛዎች ሁሉ ራሱን የቻለ መመዘኛ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ላይ ተመርኩዞ አመለካከትን ሊለኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በመጠየቅ ስለ ትምህርቱ ያላቸውን የአመለካከት ደረጃ መመርመር ነው፡፡ Gardner, (1985) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በማስመልከት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸውን የአመለካከት ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የአመለካከት መመዘኛ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡ የአመለካከት የመለኪያ መስፈርቱም በተለያየ መልኩ በማቅረብ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይሄውም ባለሶስት ስፍርታዊ የአመለካከት መለኪያ፣ ባለ አምስትና ባለሰባት ስፍርታዊ የአመለካከት መለኪያዎችን በማዘጋጀት በምሳሌነት አሳይቷል፡፡ ይሄም Craing (1979) and Cllahan (1988) እና ካዘጋጁት ጋር ተቃራራቢነት ያለው ነው፡፡

ባለ ሶስት ስፍርታዊ የሚባሉት ሶስት አማራጮችን የያዙ ሲሆን ባለ አምስት ስፍርታዊ መለኪያ የሚባሉት ደግሞ አምስት አማራጮችንና ባለ ሰባት አማራጮን የያዙ ናቸው፡፡ ይሁንና የሰውን አመለካከት ለመለካት በይበልጥ አመቺ የሚሆነው ባለ አምስቱ ስፍርታዊ መለኪያ እንደሆነ ከድረ-ገፅ የተገኘው መረጃ ያለክታል፡፡ ምክንያቱም ባለሰባቱ በተለያየ ደረጃ የመለካት አቅም ቢኖውም ለመረጃ ሰጪዎች አመቺ የሚሆነው ግን ባለ አምስቱ እንደሆነ በመስክ ጥናት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ከባለ ሶስቱ፣ ከባለ አምስቱና ባለሰባቱ ስፍራታዊ የአመለካከት መለኪያዎች አንፃር ያለው ልዩነት ሲታይ ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑን ምሁራኑ ያስገነዝባሉ (Buros, 1959 and 1979; Gardner, 1985; 2006 and Mitcheil, 1985)::

### 2.9.3 የፍላጎትና የአመለካከት ጥናት ለሥርዓተ ትምህርት ዝግት ወቅት ያለው ጠቀሜታ

መደበኛ የሆነ ትምህርት ስርዓተ-ትምህርት ተቀርጾለት የሚከናወን ነው፡፡ የትምህርቱ ዓላማም በዚሁ በስርዓተ ትምህርቱ ላይ የተቀመጠውን አላማ ከግብ ማድረስ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ትምህርቱ ከተማሪዎች አመለካከትና ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ መቅረብ ሲችል ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ስርዓተ-ትምህርት ሲቀረጽ ከተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከት ጋር ተጣጥሞ መዘጋጀት አለበት፡፡ የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ አመለካከትና ዝንባሌ ከግምት ውስጥ ያስገባ ስርዓተ

ትምህርት ደግሞ ግብ መቺ ይሆናል፡፡ የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ አመለካከትና ዝንባሌ ከግምት ውስጥ ያላስገባን ስርዓተ-ትምህርትን ከግብ ለማድረስ ያስቸግራል (Bickley 1990; Buglesky, 1971; Craing 1979; Skinner, 1985)::

Noll and Craing (1979) በስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪን አመለካከትና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተግባርን ማከናወን ለተግባሩ ግብ መምታት ዋናና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፤ ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት አስቀድሞ መለካቱና ማወቁ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የትምህርቱን አላማ ከተማሪዎች ዝንባሌ፣ አመለካከትና ስሜት ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ ያግዛል፡፡ በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪን ፍላጎትና አመለካከት ማወቁ የተለያዩ የትምህርት እቅዶችን ለመተግበር፣ ስርዓተ ትምህርትን ወደ ጥሩና ጠቃሚ ወደሆነ ደረጃ ለማሸጋገር /ለማሳደግ/፣ የፈተና ፕሮግራሞችን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አጣጥሞ ለማዘጋጀት፣ የተለያዩ የምርምር ፕሮግራሞችን ለማስተካከል ስለሚረዳ ጠቀሜታው ሰፊ ነው፡፡ በተጨማሪም ችግር ፈቺ የሆነ ምርምር ለማካሄድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ አንድን ስርዓተ ትምህርት ለማዘጋጀት ሲታሰብ የተማሪዎች ፍላጎትና አመለካከትን አጥንቶ ለዝግጅቱ በግብአትነት መጠቀም እንዲቻል ሁለቱን ተላውጦዎች በአንድ ላይ ማየት ያስፈላጋል(Noll and Craing, 1979)፡፡

Skinner (1985) በበኩሉ አንድ ስርዓተ ትምህርት ከመዘጋጀቱ በፊትም ሆነ ከተዘጋጀ በኋላ የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት ማወቅና ማጥናቱ መሰረታዊና አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህንንም ሀሳብ በመደገፍ Craig (1979) የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት ማጥናት በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ብቻ ሳይሆን በየጊዜው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይም ሆነ በየትምህርቱ ውስጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ ስለ ተማሪዎች ፍላጎት ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት የትምህርት ቤቶች አቢይ ተግባር መሆን አለበት ይላሉ፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት በተመለከተ ቀጣይነት ያለው ጥናትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል የሚል ሀሳብ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው አንድን ሥርዓተ-ትምህርት ለማዘጋጀት ሲታሰብ የተማሪዎች ፍላጎትና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አብሮ መታሰብ እንዳለበትና ሁለቱም ተላውጦዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መታየት ያለባቸው ተግባራት መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

## 2.10 ከጾታ አንጻር በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚስተዋል የፍላጎት ልዩነት

የተለያዩ ሰዎች ስለ አንድ ነገር የተለያየ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል። እንዲሁም በአንድ ተግባር/ጉዳይ/ ላይ የተለያዩ ሰዎች አንድ ዓይነት ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው ሰዎች ለአንድ ጉዳይ የጋራ ፍላጎት ሲኖራቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ሰዎች ለአንድ ጉዳይ የተለያየ ፍላጎትና ዝንባሌ እንዳላቸው ይገልጻሉ (Schonell, 1961 እና Robinson, 2001)።

የሰዎች ፍላጎት የተለያየ እንዲሆን የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚያም ውስጥ እድሜ፣ አካባቢያዊ ሁኔታና ፆታ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። Skinner (1985) በእድሜና በጾታ አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ ፍላጎቶችን Tyler (1955)ን ጠቅሰው ሲገልፁ አንድ ህፃን ልጅ መብራትን አትኩሮ ይመለከትና መብራቱን ለመንካት እንቅስቃሴ ያደርጋል። ይህ ተግባር ከፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው። ፍላጎቱም መብራቱን የመንካት ነው። እንዲሁም ከፍ ያሉ ልጆች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ሲኖራቸው፤ የወንድ ልጅ እድሜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር እንቅስቃሴው ይጨምራል። የሴት ልጅ እድሜ በጨመረ ቁጥር ደግሞ ይቀንሳል። እንዲሁም የልጆችን ፍላጎት በተለያየ ደረጃ መለካት እንደሚቻል ያመለክታል።

በሌላ በኩል Skinner (1985) የታይለርን ጥናት ጠቅሰው በ15 ልጆች ላይ ባካሄዱት ጥናት ከአምስት አመት ቆይታ በኋላ አራት የልጆች የፍላጎት አይነትን አግኝተዋል። 1ኛ/ ከቤት ውጭ የሚደረጉ ጨዋታዎችን 2ኛ/ የአሻንጉሊትና በግቢ ውስጥ የሚደረግ ጨዋታ 3ኛ/ የወረቀትና የእርሳስ ተግባር 4ኛ/ አዋቂን በሥራ ከመርዳት አንፃር በሴት ልጆችና በወንድ ልጆች መሀከል ልዩነት መኖሩን አረጋግጠዋል። ሴት ልጆች በአሻንጉሊት መጫወትና ግቢ ውስጥ የሚደረግ ጨዋታን ሲመርጡ፤ ወንድ ልጅ ደግሞ ከቤት ውጭ ያለውን ጨዋታና ተግባርን መምረጣቸውን አመላክቷል።

በተጨማሪም በተከናወነው ጥናት መሠረት የወንድና የሴት ተማሪዎች ፍላጎት ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ አጥንቷል። ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ መማርን የሚመርጡት የትምህርት ዘዴ በሚና መጫወት ሲከናወን ነው። በዚህ ደረጃ በሴትና በወንድ መካከል አንድን ነገር ለመውደድና ለመጥላት ልዩነት አለው። ልዩነቱም ከፆታ አንፃር በእድሜ ልዩነት የሚመጣ እንደሆነ ነው የሚገልፁት። በገለፃው መሠረት፤

- ተማሪዎቹ እያደጉ በሄዱ ቁጥር የተደራጁ ጨዋታዎችን የመጫወት ፍላጎታቸው እየጨመረ ይሄዳል፡፡
- ወንድና ሴት በተመሳሳይ እድሜ ደረጃ የባውሎጂካል ፍላጎታቸውን የተለያየ ነው፡፡
- ወንድ ልጆች ከ10-22 አመት የጋጥ-ወጥነት ተግባርን ለማከናወን ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ ልጃገረዶች ደግሞ በይበልጥ የጋጥ-ወጥነት (gangster) ስሜት የሚኖራቸው በ12ና በ13 አመት አካባቢ ነው፡፡
- ወንድ ልጆች ለፕሮፌሽን ስራዎችና ለቴክኒክ ትምህርቶች ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው፣ ሴት ልጆች ደግሞ የጥልፍ ስራ፣ የዲዛይን ስራዎች፣ የእደ ጥበብ ስራና ለስነ-ውበት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡
- ከስርዓተ ትምህርት ውስጥ ሥነ-ትምህርታዊ ፍላጎትን በተመለከተ (Curricular Interest) በተመለከተ የወንድ ልጆች ስነ ትምህርታዊ ፍላጎታቸው ሲታይ የተፈጥሮ ሳይንስንና የሂሳብና የፊዚክስ ትምህርት የመማር ፍላጎት አላቸው (Baram-tsabari et al, 2008: Jenkins, 2006; and Kessls, 2004)፡፡ ሴት ተማሪዎች ደግሞ የቋንቋ፣ የእደ ጥበብና የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን መማር ይፈልጋሉ፡፡ (Pintrich and Schunk 2002)፡፡

ከዚህ በላይ በቀረበው መሠረት የተማሪዎች ፍላጎት ከፆታና ከእድሜ አንፃር እንደሚለያይ ነው የሚገልፁት፡፡ በዚህ ረገድ ብዙ ሊቃውንት እንደሚገልፁት ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ከፆታ አንፃር ሲታይ ይለያያል፡፡ አማርኛም በሀገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚሰጥ ትምህርት ዓይነት አንዱ ሲሆን ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና አመለካከት ከሁለቱም ጾታዎች አንፃር ሲታይ ሊለያይ ይችላል እንደ ማለት ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ Hurlock (1980) እንደሚከተለው ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ወንዶች በክፍል ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ የምንባብን፣ የሥነ ጥበብንና፣ ማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዓይነቶች ደብዳቤ ነክ ጉዳዮችን፣ ቋንቋንና ሥነ-ፅሁፍን በትምህርት ቤት ውስጥ በሚማሩበት ጊዜ የሚሰጧቸው ዋጋ አነስተኛ ስለሆነ እነዚህን ትምህርቶችን የመማር ፍላጎታቸው አነስተኛ ነው፡፡ Hurlock (1980) እና Pintrich and Schunk (2002) በሌላ በኩል ለሴት ተማሪዎች ግን ከላይ የቀረቡት የትምህርት አይነቶች ተመራጭና ምቹ ናቸው፡፡ ሴቶች ለትምህርቶቹ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጧቸዋል፤ በማለት

ገልጸዋል፡፡ ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በተመለከተ Garrison (1965); Evans (1965) እና Skinner (1985) እንደሚገልጹት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል አንድን የትምህርት አይነት ለመማር የፍላጎት ልዩነት እንዳለ በመግለጽ፤ ሴት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸውና ወንድ ተማሪዎች ደግሞ ለተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርትና ለሂሳብ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል::

በተጨማሪም Bätz et al.(2010) የIPA (2003) ጠቅሶ በተከናወነ ጥናት በሂሳብ የትምህረት መስክ፣ በተፈትሮ ሣይንስ፣ በችግር ፈቺነት ዙሪ በጾታ መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ የጥናት ውጤት እንዳመለከተ ያቀርባሉ፡፡ ሌሎች አጥኚዎች ደግሞ በወንዶችና በሴቶች መካከል በተወሰነ ደረጃ ልዩነት መኖሩን አመልክተዋል(Bätz et al.,2010; Hanaa 2000; and Kaiser and Steisel 2000)፡፡ እንዲሁም Bätz et al.(2010) kassels (2004) ጠቅሶ ወንዶች በሂሳብ ነክ ትምህርቶችና ለፊዚክስ የትምህርት አይነት ከሴቶች በተሻለ መልኩ ከፍተኛ የመማር ፍላጎት እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ Pintrich and Schunk (2002) የትምህርት ሁኔታ ጾታን መሰረት በማድረግ ሲታይ ሴቶች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህረቱም ውጤማ ናቸው ይላሉ፡፡

ወንዶች ለፊዚክስ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ትምህርቱን ለመማር ይመርጡታል(Baram-Tsabari et al,2008; Jenkins, 2006; and kessls, 2004)፡፡ በዚህም ምክንያት ፊዚክስ የወንዶች ትምህርት ተብሎ ይታወቃል ይላሉ(Tsabari et al,2008; Jenkins, 2006; kessls, 2004)፡፡ በጀርመን ሀገር በተደረገ ጥናት ተማሪዎች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት የትምህርት አይነት ምርጫ በሚያከናውኑበት ወቅት የባውሎጂ ትምህርትን ለመማር የሚመርጡት በአብዛኛው ሴቶች ስለሆኑ የሴቶች ትምህርት ነው ይሉታል (Baram-Tasbari et al, 2008)፡፡ ሴቶች ለስነ-እንስሳ (zoology)ና ለስነ አትክልትና የአዝርእት ጥናት(botany) ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው(krombass, Urhahne and Harms,2008)፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በሴትና በወንድ መካከል የትምህርት ፍላጎት ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም እንደየ ትምህርት አይነቱ በሴቶችና በወንድ ተማሪዎች መካከል የውጤት ልዩነትም እንደየ ፍላጎታቸው ልዩነቱ ይስተዋላል ይላሉ፡፡ በተለይም በቋንቋ ትምህርት ከተፈጥሮ ሳይንስ ውስጥ የስነ-ህይወት(biology)፣ ስነ-እንስሳ(zoology)ና ስነ-አትክልትና የአዝርእት ጥናት(botany) የትምህርት አይነቶችን ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ ለመማር ፍላጎት ስላላቸው ትምህርቶቹን እንደሚመርጧቸው በውጪ ሀገራት የተደረገ ጥናት

ያመለክታል፡፡ Bätz et al.(2010) Gehlhaar et ai.(1999) ጠቅሰው ሴቶች ለእንስሳና የእንስሳትን ፓርክን ለመጎብኘት ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናታቸው ውጤት እንዳመለከተ ይገልጻሉ፡፡

በሀገራችን ከውጤት አንጻር በተደረገ ጥናት በተደረገ ጥናት ደግሞ ደሳለኝ (2004) በአማራ፣ በኦሮሚያ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ባከናወኑት ጥናት በሂሳብና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቶች ወንዶች ከሴቶች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበው መገኘታቸውን የጥናታቸው ውጤት ማሳቱን አመልክተዋል፡፡ USAID/Ethiopia(2004) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ባከናወነው ጥናት በንባብ ችሎታ፣ በእንግሊዘኛ ትምህርት ውጤትና በሂሳብ ትምህርት ውጤት ወንዶች ከሴቶች ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ደግሞ የኢትዮጵያን ከሌሎች ሀገራት ላይ ተከናውኖ ከተገኘ የጥናት ውጤት አንጻር ሲታይ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 2.11 የትምህርት ውጤት (Academic Achivment)

በBicke (1990) አገላለፅ የትምህርት ውጤት ማለት አንድን የትምህርት ዓይነት በዓላማው መሠረት አስተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለተማሪዎች በማስተማር ትምህርቱ ከተላለፈ በኋላ ዓላማው ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነና በተማሪዎች ላይ የመጣውን የባህሪ ለውጥ አስመልክቶ የሚገኝ ውጤት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ በKuhle (1968) አገላለፅ ደግሞ የትምህርት ውጤት ማለት አላማን መሠረት ያደረገ ትምህርት ለተማሪዎች ካስተማሩና ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ በተማሪዎች ላይ የመጣው የባህሪይ ለውጥ ልኬት ነው፡፡ ስለዚህ የትምህርት ውጤት ማለት የባህሪ ለውጥ ሂደት ነው፤ በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከላይ በቀረበው ገለፃ መሠረት የሁሉም ምሁራን አንድ ዓይነት ሲሆን ገለፃቸው የትምህርት ውጤት ማለት አንድ ትምህርት ተከናውኖ በተማሪው ላይ የመጣው የባህሪ ለውጥ በፈተና ተለክቶ የሚገኝ እንደሆነ የቀረበ ነው፡፡

የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት መለካት የሚያስፈልግበት አቢይ ምክንያት መምህሩም ሆነ የሚመለከተው አካል ቀጣይ እቅዱን ለማቀድ ይረዳዋል፣ ተማሪዎቹ ያሉበትን ደረጃ ለማየት ይጠቅማል፡፡ ተማሪዎቹ ምን እንደሚፈልጉ፣ ትምህርቱን በምን ሁኔታ ማሻሻል እንደሚቻልና ምን መሰራት እንዳለበት ለመወሰን ያስፈልጋል፡፡ በትምህረቱ ላይ ያለውን ጥንካሬና ድክመት

ለመመርመር ይረዳል፡፡ መስፈርቶችን ለማውጣት ያገለግላል (Lambert, 2000):: ስለዚህ በየክልሉ የሚሰጠውን የትምህርትን ውጤት ማየቱ በክልል ተማሪዎች ደረጃ ያለውን የልዩነት ደረጃን ወይም የልዩነቱን ስፋትና ጥበት በመለየት ክፍተቶችን በማስተካከል ወደ ተመሳሳይ ችሎታና የእውቀት ደረጃ ለማምጣት የሚቻልበትን አማራጭ ለመወሰን ያግዛል፡፡

## 2.11.1 በትምህርት ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

Hancock (2004) እና Garry (1970) በተማሪ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች ውስጥ የንሺ ሁኔታ አንደኛው ምክንያት ነው፡፡ ንሺ በተማሪ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችለው፤ ተማሪው በክፍል ውስጥ ያለው ንሺ ከትምህርቱ አላማ ጋር እንደየአስፈላጊነቱ ተጣጥሞ ባለመቅረቡ የሚመጣ ነው፡፡ Skinner (1985); Lewis (1936 & 1942)ን ጠቅሶ የተማሪዎች ባህሪይ፣ ስብእና፣ ተግባርና የአካባቢ ሁኔታ ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዮችም በተማሪው ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ በሚያሳድሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሳቢያ በትምህርት ውጤትም ላይ አሉታዊና አዎንታዊ የሆነ ተፅዕኖን ሊሳድሩ ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ (Grdner, & Masgort 2003; krashen 2009; Grdner, 1995 እና 2006)፡፡

### 2.11.1.1. ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት

Rubinson (2001) Grdner (1995)ን ጠቅሶ እንደገለፀው እና በGarry (1970) አገላለፅ መሠረት ሶስት የንሺ ባህሪያት እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ እነሱም የግል ጥረት፣ የመንፈስ ጠንካራነትና ፍላጎት የማሳደር ሀይል ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስቱ ተላውጦዎች የሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱን ለመማርና ለትምህርቱ ተነሳሽ እንዲሆን ሀይል ይሰጡታል፡፡ ንሺ ውጤትን በማስመዝገብ ዙሪያም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው (Masgort, & Gardner, 2003 and Gardner, 2006):: ከተማሪው የመማር ስልት ጋርም ጠንካራ ሆነ ቁርኝት አለው፡፡ የትምህርት ስልት ደግሞ አንድን እየተከናወነ ያለን ትምህርት በቀላሉ መረዳት እንዲቻል የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ስለዚህ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ ጥሩ የትምህርት ስልትን በመጠቀም ትምህርቱን ይማራል፡፡ ስለዚህም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይም ለትምህርቱ ትኩረት ለመስጠት ይረዳል፡፡

ንሺ. ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የተለያዩ ችግሮችን በመቋቋም ከፍተኛ ውጤትን ለማስመዝገብ ይረዳል በማለት ይገልፃለሉ። ተማሪዎች በትምህርት ውጤታቸው ዝቅ እንዲሉ ወይንም ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ንሺ. ያለው ተማሪ ከሌሎቹ ተማሪች በተለየ መልኩ ስኬታማ ይሆናል። ንሺ. ውስጣዊ ሂደት ሲሆን አንድን ተግባርና ትምህርት በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ ውስጣዊ ሀይል ነው። ስለዚህም ንሺ. ካለ እየተካሄደ ባለ ትምህርት ውጤታማ ይሆናል። ምንም ንሺ. ከሌለው ተማሪ ይልቅ በጣም የተነሳሺነት ያለው ተማሪ ረጅም የሆነ ግብን ለማሳካትና ለማከናወን ይችላል። ስለዚህ አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን ለመልመድ፣ ለማወቅና ተምሮ ውጤት ለማስመዝገብ ተነሳሽነት አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

Masgort & Gardner (2003) heckhause (1991)ን ጠቅሶ እና Gardner (2006) ንሺ. ወደ ግብ የሚያደርስ ባህሪ እንደሆነ ገልፀዋል። ተነሳሽ ሰው ሀይሉንና ያለውን ጉልበት በስፋት ይጠቀማል፣ አንድን ተግባር በንቃት ይከታተላል፣ ግብ አለው፣ ዝንባሌው የሰፋ፣ ፍላጎቱ ምኞቱ ከፍተኛ ተስፋ ያለውና በሚሰራው ስራም ይደሰታል። ከልብ በመነቃቃት ትክክለኛ ያልሆነውን በመጣል የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሞ ስኬታማ ይሆናል። በዚህም ሳቢያ ጥሩ ውጤትን ያስመዘግባል። ስለዚህም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ተማሪው ንሺ. ካለው በተለይ ውስጣዊ ወይም ውህዳዊ ንሺ. (Intigrative motivation) ካለው በትምህርቱ ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል።

Brown (1993) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ሲማሩ ከፍላጎታቸው ጋር አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት ካለው ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ከፍተኛ ንሺ. እንዲኖራቸው ያደርጋል። ንሺ. ደግሞ እንደሚታወቀው ከተማሪዎች ውስጣዊና ውጫዊ ዝንባሌ (Interinsic and exterincic orientation) የሚመጣ እንደሆነ ይገልፃሉ። በአጠቃላይ ንሺ. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ተላውጦ ሲሆን ውስጣዊ ንሺ. ከውጫዊ ንሺ. በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው በማለት የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ።

### 2.11.1.2. የማስተማር ዘዴ

እንደ McCombs (1997) አስተያት ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ዘዴ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከመርዳቱም በተጨማሪ በሥርዓተ ትምህርት ዝግጁት ሂደት ውስጥም ወደ ግብ የሚያደርስ መንገድን እንዲከተሉ ይረዳል በማለት ሲገልፁ፤ ተማሪን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ዘዴ ተማሪው ለትምህርቱ ንሺ እንዲኖረው ስለሚያደርግ ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይረዳል በማለት ይገልፃሉ፡፡

Tsui (2003) በተግባቦት ዘዴ የሁለተኛ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎቹ ንሺ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ እርስ በርሳቸው በነፃነት ስለሚማማሩ በትምህርታቸውም የመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በተለይ ተማሪቹ ሲማሩ በጨዋታ በቀልድ መልክ እየተዝናኑ ቢማሩ ይመረጣል፡፡ በዚህ ሂደት የሚማሩ ከሆነ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ስለሚኖራቸው ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤትን ማስመዝገብ ይችላሉ በማለት ገለፃቸውን ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የመማር ማስተማር ዘዴ በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው ያስረዳል፡፡ ስለዚህ በጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ የተማረ ተማሪ ጥሩ ውጤት እንደሚያስመዘግብ ነው ከቀረበው ገለፃ መረዳት የሚቻለው፡፡

## 2.12 በአመለካከት በፍላጎትና በትምህርት ውጤት መካከል ያለ ዝምድና

በተማሪዎች ውጤትና ተማሪዎቹ ለአንድ ትምህርት ባላቸው ፍላጎት መካከል ያለውን ዝምድናን ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ በመስኩ ሊቃውንት የቀረበው ሀሳብ እንደሚያመለክተው አጥጋቢ ውጤት ካለፍላጎት፣ ንሺና ዝንባሌ በስተቀር ማስመዝገብ እንደማይቻል ያስረዳል (Grary, 1970; Ivans 1965 and Bugleski, 1971)፡፡

ከላ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ Hurlock (1980) እንደገለፁት ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ፍላጎት ከሌላቸው ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ይኸውም ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና ትምህርቱን ለማጥናት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ይሆናል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Hurlock በ(1972) በፃፉት ፅሁፍ ላይ ሲገለፁ አንድ ሰው ለአንድ ትምህርት አነስተኛ ፍላጎት ካለው የሚያስዘግበው ውጤትም በጣም ዝቅተኛ ይሆናል የሚል ነው፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች ለአንድ የትምህርት አይነትና አነስተኛ ፍላጎትና ዝንባሌ ካላቸው ተማሪዎቹ በትምህርታቸው የሚያስመዘግቡት ውጤትም አነስተኛና ከተፈለገው በታች ይሆናል። በተጨማሪም ለሚማሩት የትምህርት ዓይነት የሚመድቡለት የጥናት ጊዜም በጣም አነስተኛ እንደሚሆን ያስረዳሉ (Garry, 1970)።

Gardner (2006) እና Masgort & Gardner (2003) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትና በአመለካከት (Attitude)፣ ውህዳዊ ንሺ (Integrative motivation)፣ ውህዳዊነት (Integratveness)፣ ንሺ (motivation)ና ውህዳዊ ዝንባሌ (Integrative orientation) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ የትኛው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፤ በተላውጦዎች መካከል ያለው ዝምድና ምን እንደሚመስል ጥናት አከናውነው፤ የተገኘው ውጤት ሁሉም ተላውጦዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው፣ ንሺ ደግሞ ከአራቱ ተላውጦ በበለጠ ሁኔታ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለውና ከእድሜና ከቦታ አንፃር የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ግንኙነት እንደሌለው በጥናታቸው አመልክተዋል።

ከውጤቱም በመነሳት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት፤ ውጤት ለማስመዝገብ ንሺ አቢይና መሠረታዊ ተላውጦ እንደሆነና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ዘንድ ንሺ እንዲኖራቸው አድርጎ ማስተማር ያስፈልጋል በማለት ሀሳባቸውን ያቀርባሉ።

ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሠረት Harmer (1991) እንደገለፁት ፍላጎት የንሺ አቢይ ክፍል ነው ይላሉ። ከዚህ ገለፃቸው መረዳት እንደሚቻለው ከላይ Masgort & Gardner (2003) ካቀረቡት ውጤት አንፃር ስንመለከት ፍላጎት ከውጤት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳናል።

Gidi (1990); Herbert (1965)ን ጠቅሶ በፍላጎትና በውጤት መሀከል ከፍተኛ የሆነ የቅርብ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸዋል። እንዲሁም Silberman (1992); Schifel (1988)ን ጠቅሶ እንደገለፀው ለመጀመሪያ ጊዜም ሆነ ለመጨረሻ ጊዜ ለትክክለኛ ተግባር ፍላጎትና ንሺ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ፍላጎት ትኩረታችንን ትክክለኛ ወደ ሆነ ተግባር እንድናተኩር ይረዳናል። ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ፍላጎት ካላቸው ትርጉም ወዳለው ተግባር ይመራቸዋል። እንዲሁም በትምህርቱ የተማሩትን ርዕሰ ጉዳይ በተማሪዎቹ ሳይረሳ ለረጅም ጊዜ በአእምሮ ውስጥ እንዲቆይ (ወደ ረጅም ተውስታ እንዲቀየር) ማድረግ ከመቻሉም በተጨማሪ እውቀትን በስፋት ለመገብየት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

አንድን ተግባር ለማከናወን መነቃቃትን ስለሚያመጣ ስሜ ወደ ሆነ ተግባርና ስራ ይመራናል፤ በማለት ይገልፃሉ። ከላይ በቀረበው ሀሳብ ላይ በመስማማት ፍላጎት ለአንድ ተግባር ስኬታማነትና ለትምህርት ሂደት መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ የራሳቸውን ገለፃ መሠረት አድርገው ስሜ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ውጤትና ፍላጎትም ተያያዥ ጉዳዮች እንደሆኑ ይገልፃሉ (Masgort, & Gardner, 2003; Spolsky, 1989; Hudsoin, 1980; Mackey, 1965; Gardner, 1968 Bugelsk, 1971):: Gidi (1990) ከላይ የቀረበውን ሀሳብ በመደገፍ ሲገልፁ፤ መምህር ትምህርት በሚያስተምርበት ጊዜ የሚሰጠውን ትምህርት ከተማሪዎች የአእምሮ ችሎታና ፍላጎት ጋር በማገናዘብ አጣጥሞ ማቅረብ እንደሚስፈልግ ያስገነዝባሉ።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ፍላጎት ለውጤታማ ተግባር መሠረት እንደሆነና ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትጋት እንዲማሩ ስለሚያደርግ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ ስለሚረዳ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

## 2.13 የአመለካከት፣ የፍላጎት፣ የንሺ እና የስኬት ተያዥነት

በእያንዳንዱ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አራቱም የስብእና አላባውያን ሲሆኑ እርስ በእርሳቸው ግንኙነት ያላቸው ናቸው። አመለካከት ለአንድ ርእሰ ጉዳይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ግንዛቤን ይዞ መገኘትን የሚመለከት ሲሆን፤ ይሄም ደግሞ ከፍላጎትና ከንሺ አስቀድሞ የሚመጣ በመለሆኑ ለተላውጦዎቹ መነሻ የሆነ የስብእና ክፍል ነው። አመለካከት እንደ ፍላጐትና ንሺ ሁሉ በግለሰብ ባህሪ ላይ ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችልና ፍላጎት ደገሞ ከውስጣዊ ንሺ ጋር አንድ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። ስለዚህ የአንድን የትምህርት መርሃ ግብር ከግብ ለማድረስ በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ንሺ፣ ስኬት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ በማጥናት፣ በዙሪያው የሚስተዋሉ ችግሮችን አስቀድሞ በመፍታትና ያልተፈቱ አሉታዊ ጎኖችንም ከግምት ውስጥ በማስገባት መርሀ ግብሩ መቀረጽ አለበት።

በሌላ በኩል በSpolsky (1998) እና Masgoret & gardner (2003) አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ንሺ እና ስኬት ተያያዥነት ያላቸውና በተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚያደረርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ ይጠቁማሉ። በተለይ ውስጣዊ

ንሺና /Integrative Motivation/ ፍላጎት ለስኬት ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በሰፊው ያብራራሉ (Gardner, 1968)።

ከላይ ከቀረቡት የመንደርደሪያ ሃሳቦች መሰረት አመለካከት፣ ፍላጐት፣ ንሺና ስኬት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የእርስ በእርስ የተያያዥነት ያላቸውና የተሰናሰሉ በመሆናቸው እያንዳቸው እርስ በእርሳቸው ተጽእኖ ከመደራረጋቸውም አልፎ በትምህርት ውጤት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ የቀረበው ሀሳብ ያመለክታል። ስለዚህ አራቱንም ተላውጦዎች በትምህርት ውጤት ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ በተናጠል ማጥናት ሳይሆን በአንድ ላይ ማጥናቱ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ያሳያል።

## 2.14 እድሜና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት

የሥነ-ትምህርትና የስነ-ልቦና ባለሙያዎች መደበኛ ትምህርት ለማከናወን እድሜ ከግምት ውስጥ መግባት ካለባቸው ተላውጦዎች መካከል አንደኛው እንደሆነ ይገልፃሉ። የሁለተኛ ቋንቋን ከመልመድና ከመማር ረገድም እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ።

ይሁን እንጂ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የሚቀርቡ ፅንስ ሐሳቦች እጅግ አከራካሪና አወዛጋቢ ጉዳይ በመሆናቸው እና በምሁራኑ ዘንድም የተለያየ እይታና ግንዛቤ በመኖሩ ምክንያት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን እና እድሜን በማስመልከት የተለያዩ ምርምሮች የተከናወኑ መሆናቸውን ይገልጻሉ። እስካሁንም ድረስ በመስኩ ዙሪያ ያሉት አከራካሪ ሀሳቦች በትክክሉ መፍታትና ምላሽ መስጠት አልተቻለም። ሆኖም ግን እድሜ በተማሪዎች አመለካከት፣ንሺና ፍላጎት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው የተለያዩ የጥናት ውጤትን በአስረጂነት በማቅረብ Setrn (1991) ይገልጻሉ።

በFeer Man (1991:207) አገላለፅ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ከእድሜ አንፃር ትምህርቱን ይበልጥ ለማከናወን ወሳኝ የእድሜ ክልል አለው። ያም የእድሜ ክልል ከተወለደ አንድ አመት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘጠነኛ ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ስለዚህ አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን መማር መጀመር ያለበት የእድሜ ክልል የአንደኛ ደረጃን ትምህርቱን መማር ከሚጀምርበት የእድሜ ደረጃ ላይ መሆን

እንዳለበትና ይህም ጊዜ ወሳኝ የእድሜ ክልል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ወሳኝ ነው፤ የተባለበት ምክንያት ተማሪ ሁሉን ነገር ለማወቅ ከሚኖረው ፍላጎት በመነሳት ለሚማረው ትምህርት ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖረዋል በማለት Stern(1991) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ደግሞ ቋንቋን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር አንድ ያደርገዋል፡፡

William(1984) እና Krashen(1982) ብዙ ምሁራን እና የመስኩ ሰዎች የሚቀበሉትና የሚያምኑበት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ልጆች ወይም ታዳጊዎች ከአዋቂዎች በተሻለ ሁኔታ መማር እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡ ይህንንም በአንድ ወቅት በተደረገ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የጥናቱም ውጤት እንደሚያሳየው በስደት በሌላ ሐገር በሚኖሩ\ ቤተሰቦች ላይ በተደረገው ጥናት ታዳጊዎቹ ከአዋቂዎቹ በተለየ ሁኔታ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን ተምረው ከመጀመሪያ የቋንቋው ተናጋሪዎች ባልተናነሰ ሁኔታ ለመናገር ችለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አዋቂዎች የውጭ ዜጋ መሆናቸውን የሚገልፅ የሌላ ቋንቋ ዱካ በሁለተኛ ቋንቋው ላይ እያሳረፉ የሚናገሩ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤቱ እንዳመለከተ ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን አሜሪካ በተደረገ ጥናት (Ramis,1974) እና በምዕራብ ጀርመን (Dlein,1979) በተገኘ የጥናት ውጤት ወጣት ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋን ተምረው ከፍተኛ ችሎታ ማስመዝገብ መቻላቸውን እንዳረጋገጡ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ገለጻ አንፃር ሲታይ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ የሆነ ጊዜና የእድሜ ክልል መኖሩን፣ አእምሮ እንደልብ የሚታዘዝበት፣ የቋንቋው ትምህርት ሂደት ተፈጥሮአዊ ባህሪን የሚከተልበት፣ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በቀላሉ መማር የሚቻልበት የእድሜ ክልል እንዳለና ያም ከመጀመሪያዎቹ አመታት እስከ አቅመ አዳምና አቅመ ህይዋን( puberty) ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሆነ የጥናታቸው ውጤት ማሳየቱን ይጠቅሳሉ፡፡ ይህም እድሜ ክልል ከጉልማሳ እድሜ አስቀድሞ ባለው ዓመታት በመሆኑ ተፈጥሮአዊ የቋንቋ የመማር ወቅት ይባላል፡፡

ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማርን Browen (2005); Stern (1970: 57-58) ጠቅሶ ሲገልፅ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት የአፍ መፍቻ ቋንቋ የለመዳ ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የሚከናወን እንደሆነ ነው፤ የሚገልፁት፡፡ ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማር የሚባለውም፡-

1. በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ያልተቋረጠ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ልክ ህፃናት የእናታቸውን ድምፅ በመስማት እንደሚለማመዱት፣

2. የቋንቋ ትምህርቱ ከሌላ የመኮረጅ ሂደት ነው። ልክ ህፃናት የእናታቸውን ድምፅ ሰምተው በመኮረጅ እንደሚናገሩት፣
3. ህፃናት የሚለማመዱበትን መንገድ በቋንቋ ትምህርት ላይ ማዋል፣
4. የልምምዱ ሂደትም የሚጀምረው ተለያይተው ካሉ ድምፆች በመጀመር ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ከዛም አረፍተ ነገርና ውስብስብ ወደ ሆነ መዋቅር የመሄድ ሂደትን በመከተል ነው። ይህ ሂደት ተፈጥሮአዊ ቅድመ ተከተል ይባላል ።
5. የህፃናት የቋንቋ እድገትን ስንመለከት መጀመሪያ ማዳመጥ ከዛም መናገር ነው። ይህ ትክክለኛው ቅድመ ተከተል ነው።
6. ትንንሽ ልጆች ያዳምጣሉ ከዛም ይናገራሉ። ማንበብና መፃፍ በአእምሮአቸው አይኖርም። ማንበብና ማፃፍ በከፍተኛ የቋንቋ እድገት ደረጃ ላይ የሚመጣ ነው ይሉታል።
7. ልጅ ቋንቋን ሲለምድ ማንም ሰው አይተረጉምለትም። ቋንቋን መማር ከተፈለገ ትርጉም አያስፈልግም።
8. ትንንሽ ልጆች መደበኛ የሰዋሰው ስርዓትን ሳይማሩ በቀላሉ ቋንቋን ይጠቀማሉ። እንደነዚህ የመሳሰሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማር ሂደት ይባላል።

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት የዚህን አካሄድ ስርዓትን መከተል ተፈጥሮአዊ የቋንቋ ትምህርት ጋር ይገናኛል። ይህም የሚከናወነው ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት እስከ አቅመ አዳምና አቅመ ህይዋን አቅራቢያ ድረስ ባለው ዓመታት ውስጥ እንደሆነ ነው የሚገልፀው። ስለዚህ በዚህ ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ሁኔታ መማር የሚቻልበት ወቅት ነው ብለው ምሁራን ይናገራሉ።

Cook (2001:133) ልጆች የመጀመሪያ ቋንቋቸውን ከ2-10 ዓመት ድረስ በደንብ ጠንቅቀው ያውቃሉ። የተለያዩ ምርምሮችም እንደሚያስረዱት እድሜ አዎንታዊ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው ነው። ስለዚህ ተማሪዎች ጥሩ ንበት እንዲኖራቸው ከተፈለገ በልጅነታቸው ቋንቋውን መማር አለባቸው የሚለውን ሀሳብ በጽሁፋቸው ውስጥ የተጠና ጥናትን ጠቅሰው አቅርበዋል።

የሥነ ህይወት ባለሞያዎችና አጥኝዎች ዘንድም የሁለተኛ ቋንቋን ከመማር አንፃር ሰዎች ቋንቋን ለመማር የሚያስችል የአእምሮ ክፍል አላቸው። ያም የአእምሮ ክፍል ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ነገር ግን እድሜ እየጨመረ ሲሄድ የአእምሮ ክፍሉ እየተለወጠና

እየተቀየረ ይሄዳል። ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በመማር ሂደት ላይ ውጤታማ የሚኮነው ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት እስከ አቅመ አዳምና አቅመ ህይዋን(puberty) ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ እንደሆነ ይገልፃሉ።

Webb (2000) እና Little wood (1984) እድሜ እየጨመረ ሲሄድ የሰው ልጅ አእምሮ፣ አካል፣ አስተሳሰብ፣ አንድን ተግባር የማከናወን ሁኔታ፣ ስሜት፣ አመለካከትና የንሽ ሁኔታዎች እየተለወጡ ይሄዳሉ በማለት ይገልፃሉ። Stern (1991) ይሄን ሀሳብ በተመለከተ በአነስተኛ እድሜ ደረጃ የሚገኙ ልጆች ለሚማሩት ትምህርት ውስጣዊ ተነሳሽነት እንደሚኖራቸውና እድሜያቸው ወደ ጎልማሳነት እየተጠጋ ሲሄድ በይበልጥ ወደ ውጫዊ ተነሳሺነት እየተለወጠ እንደሚሄድ ከመግለጻቸው በተጨማሪም ከተማሪው አመለካከት አካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽእኖ ሳቢያ እየተለወጠ እንደሚሄድ ይገልጻሉ።

የኒውሮሎጂካል ጥናትና ምርምር እንደሚያሳየው ደግሞ እንደ አካላዊ እድገት ሁሉ የተለያዩ የአእምሮ ክፍሎች በተለያዩ የተግባራት አይነት ላይ የሥራ ክፍፍል ያደርጋሉ። በክፍፍሉም መሰረት ሰው ከልጅነት እድሜው በኂላ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚቆጣጠረው የአእምሮ ክፍል ከቀኝ ወደ ግራ ክፍል እንደሚዞር በምርምራቸው እንዳረጋገጡ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ በቀኝና በግራ የአእምሮ ክፍሎች መካከል የሚከናወነው የሥራ ክፍፍል የሚጠናቀቀው ደግሞ እስከ 16 ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

በእድሜያቸው ከአቅመ አዳምና ህይዋን በኂላ ያሉ አዋቂ ሰዎች የሁለተኛ ቋንቋቸውን እንደ ተወላጅ ቋንቋ መናገር የማይችሉበትና የንበት ችግር ከሚያጋጥምበት ምክንያት ውስጥ አንዱ እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ድምፆችን ለማውጣት የሚረዱ ጡንቻዎች ታዛዥነታቸው እየቀነሰ ስለሚሄድ ነው ይላሉ። በሌላ በኩልም ድምፆችን ለማውጣት የሚረዱ ጡንቻዎችና የአእምሮ ክፍሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የድምጾች አወጣጥ ስርአት ስለሚገሩና ስለሚታነፁ የታለመውን የቋንቋ ድምፆች ለመጥራት አዲስ ስለሚሆንባቸው በጡንቻዎቹና በአእምሮ ክፍሎቹ ትእዛዝ አማካኝነት ለመጥራት የመቸገር ጉዳይ ይከሰታል በማለት ይገልፃሉ።

Brown (2005) እና Stern (1983) የጂን ፒያጀን የእንቴሌክቹዋል የእድገት ደረጃን በመጥቀስ ለቋንቋ ትምህርት፣ ለቋንቋ ለመዳ ወሳኝ የእድሜ ደረጃ እና ተማሪው በስፋትና በጥልቀት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በይበልጥ የሚማረውና የሚለምደው በኮንክሪት ኦፐሬሽናል ወቅት ላይ ነው ይላሉ። ይህም ከሰባት ዓመት እስከ አስራ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፤

በማለት የጀን ፒያጀን ትወራ ይገልፃሉ፡፡ ይህ የጀን ፒያጀ አባባል ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም ቋንቋን ይበልጥ መማር የሚቻለው ከጉርምስና እድሜ አስቀድሞ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ከሚለው ሀሳብ ጋር አብሮ ሊጠቃለል የሚችል ነው፡፡ ይህም ቋንቋን መማር የሚቻለው ከመጀመሪያዎቹ አመታት እስከ አቅመ አዳምና አቅመ ሀይዋን ከሚለው ትወራና ከወሳኝ የቋንቋ ለመዳና የትምህርት የእድሜ ክልል መላምት /Critical Period Hypothesis/ ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡

Stern (1991) እና Cook (2001) በእድሜና በቋንቋ ትምህርተ ላይ የሚደረግ የጥናት ውጤት አሻሚ ስለሆነ ትክክለኛ ከሆነ ድምዳሜ ላይ መድረስ አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ትምህርት መሰረት የሚያደርገው ከስነ-ትምህርታዊና ከስነ-ልቦና ሂደቶች በተሻለ መልኩ ከስነ-ከማህበራዊ ግዳዮች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መጀመር ያለበት ማህበራዊ ተግባራትን ማከናወን በሚጀምርበት የእድሜ ክልል አንስቶ መሆን እንዳለበት የመስኩ ምሁራን እንደሚገልጹ ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ ጊዜ ከጉርምስና/ኮረዳነት ደረጃ(Adolescent) አስቀድሞ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ይሉና እንደምክንያት የሚያቀርቡትም ከጉርምስና አካባቢ ቀደም ብሎ አእምሮው የተጐዳ ሰው የቀዶ ጥገና ህክምና ከተደረገለት በኋላ ቀድሞ የነበረውን የቋንቋ ችሎታን እንደገና የማስታወስና መልሶ የመልመድ ሁኔታ ሲታይበት ከአቅመ አዳምና ከአቅመ ሀይዋን በኋላ የአእምሮ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ግን ከቀዶ ጥገና በኋላ አብዛኛውን ጊዜ እንደገና የማስታወስ ተግባርን እንደማያከናውኑ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከአቅመ አዳምና አቅመ ሀይዋን ጊዜ ቀድሞ መሰጠቱ አስፈላጊና ወሳኝ ጊዜ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ከአቅመ አዳምና አቅመ ሀይዋን እድሜ አስቀድሞ ትምህርቱ መስጠት እንዳለበት ነው ጥናቱ የሚያመለክተው፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከጉርምስና በኋላ አእምሮ እየዳበረ የሚሄድበት ወቅት ስለሆነ ለቋንቋ ትምህርት በተለይ ለሰዋስው በጣም ወሳኝ ጊዜ ነው፤ በሚል ሐሳብ ላይ እየተደረሰ መጣ፡፡ ወጣቶችና ጐልማሶች በቋንቋ ትምህርት ላይ ፈጣኖች ናቸው፡፡ ነገር ግን ታዳጊ ልጆች በሂደት ከፍተኛ የቋንቋ ትምህርት ደረጃ ላይ የመድረስ እድላቸው ከጐልማሶች ይሻላል በማለት ቀደም ብሎ ወደቀረበው ሀሳብ ይመጣሉ፡፡

በልጅነት የአድሜ ክልል ውስጥ ካሉት ይልቅ አዋቂዎች ቋንቋን ሲማሩ ይበልጥ ፈጣን መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን ከልጅነት ጀምሮ የቋንቋውን ትምህርት መማር የሚጀምሩት ደግሞ በጊዜ ሂደት በቋንቋው ክህሎትና አውቀት ከመጨረሻው ጣሪያ የመድረስ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው የሚገልጹት፡፡ ሆኖም ግን የቋንቋ ትምህርት በልጅነት የአድሜ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ቋንቋን መማር የጀመሩ ተማሪዎች በአዋቂ እድሜ ክልል ውስጥ ከጀመሩት በተሻለ ከፍተኛ ወደሆነ የቋንቋ ችሎታ ላይ መድረስ እንደሚችሉ ጥናቶች እያረጋገጡ መጡ፡፡ ይሄ መሆኑ ደግሞ ለቋንቋ ትምህርት በቂ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ያመለክታል፡፡ የጥናቱም ውጤት አዋቂ ሰዎች ለቋንቋ ትምህርቱ በቂ ጊዜ ካላቸውና የቋንቋን በይበልጥ መማር ይቻላሉ ወደሚለው ማጠቃለያም ተደርሷል፡፡ ሆኖም ግን በልጅነት የአድሜ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ቋነቋን መማር የጀመሩት ቋንቋውን ተምረው ከመጨረሻው ጣሪያ መድረስ እንደሚችሉ ነው የሁሉም ጥናት የሚያመለክተው (Lightbown 2011)፡፡

William 1984) እና Steren (1991) የቋንቋ ትምህረት ጥናት ሰው-ሰራሽ(አርቲፊሻል) በሆነ አካባቢ ላይ የተመሰረተና ትክክለኛ ባልሆነ የቤተ-ሙከራ(የላብራቶሪ) ውጤት ላይ ያላተኮረ ነው ይላሉ፡፡ በአዋቂ፣ በታዳጊዎች እና በልጅነት የእድሜ ክልል የሚከናወን የቋንቋ ትምህርት ጥናት የተወሳሰበ የሚያደርገው በዙሪያው በጣም ብዙ ተለውጦዎች ስላሉ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ተላውጦዎችም በተለይ ልጆች ከአዋቂዎች በተለየ መልኩ ቋንቋን ለመማር ጥሩ አጋጣሚ ስለሚኖራቸው ነው፡፡ ይሄውም ልጆች ብዙ ጊዜ ስላላቸው፣ ትኩረት የመስጠት ጉዳይ፣ የአመለካከት ጉዳይ፣ ለተግባቦት ፍላጐት መኖርና፣ ቋንቋውን ለመለማመድ ብዙ ጊዜ የመጠቀም እድል መኖር፣ የተነሳሽነት፣ የፍላጎት ሁኔታዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡

በሌላ በኩል ልጆች ከወጣቶችና ከአዋቂዎች በበለጠ ሁኔታ ሁለተኛ ቋንቋቸውን መማር ይችላሉ የሚለው ሃሳብ አያስኬድም የሚለውን የሚያራምዱት ደግሞ በሁሉም የእድሜ ደረጃ እኩል የመማር እድልና አጋጣሚ አለ፡፡ የእድሜ ልዩነት የቋንቋ ትምህርት ልዩነትን አያመጣም የሚሉ ናቸው፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ በሆላንድ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ይህንን ጥናት ያከናወኑት ካዝሪን እና ማሪን (1978) የእንግሊዘኛ ተናገሪ ተማሪዎች የደችን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ አወቂዎቹ ከታናናሾቻቸው የበለጠ መማር እንደቻሉ ጥናቱ ያስረዳል፡፡

Stern (1991) Fatman (1975)ን ጠቅሰው ሲገልፁ ፋትማን ባደረገው ጥናት መሰረት ከአስራ አንድ እስከ አስራ አምስት እድሜ ያላቸው ተማሪዎች /ልጆች/ የእንግሊዝኛ ቋንቋን ሲማሩ ከስድስት እስከ አስር ዓመት የእድሜ ክልል ካሉት ተማሪዎች በፈጠነ ሁኔታ በሁለተኛ ቋንቋ

ትምህርት ወቅት በሰዋሰው ትምህርት በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ታዳጊዎቹና አነስ ያለ እድሜ ያላቸው ደግሞ በንበት በእድሜ ከፍ ካሉት በልጠው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተ ገልጸዋል ፡፡

William (1984) ደግሞ ወጣቶችና አዋቂዎች እንዲሁም በእድሜ ከፍ ያሉት አነስተኛ እድሜ ካላቸው በበለጠ መልኩ ፈጣን እንደሆኑ በመግለጽ ከጉርምስና እድሜ ክልል በፊት ያሉት ግን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በንበት(pronounciation) ብቻ ከአዋቂዎች በልጠው ተገኝተዋል ይላሉ፡፡ Mclauphlin (1987) በእድሜ ከፍ ያሉ ሰዎች ለቋንቋ ትምህርታቸው ትኩረት በመስጠት ረገድ የተሻሉ በመሆናቸው ከታለመለት ግብ ፈጥነው ይደረሳሉ፡፡ በስነ-ድምጸ-ልሳን ደረጃ ግን በእድሜ አነስ ያሉት የተሻሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ Oyama (1987) በአነስተኛ የእድሜ ደረጃ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር የጀመሩ ተማሪዎች የድምጽ አወጣጣቸው እንደ አፈፈት ይሆናል በማለት ሲገልጹ Snow (1978) በኒዘርላንድ ባደረገው ጥናት መሠረት እድሜና የቋንቋ የትምህርትን አስመልክቶ ከደረሰበት ውጤት በመነሳት የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርቧል፡፡

1. በሁሉም እድሜ ክልል የሁለተኛ ቋንቋን በትምህርት ማሻሻል የሚቻል መሆኑን
2. አዋቂ ተማሪዎች ከታናናሾቻቸው በላቀ መልኩ በምዕላድ፣ በአገባብ፣ በቃላትና በተግባቦት ችሎታቸው በልጠው መገኘታቸውን
3. አዋቂዎችና በእድሜ ከፍ ያሉት በቃላት እውቀታቸው በእድሜ ከሚያንሱት በልጠው መገኘታቸውን ያረጋገጡ መሆኑን ሲገልፁ
4. በጣም አነስተኛ ልዩነት የታየው በልጅነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ቋንቋ መማር የጀመሩት ተማሪዎች በንበት ከአዋቂዎች ተሽለው መገኘታቸውንና ይህም በጣም ትንሽ ልዩነት ያሳየ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

Cook, V. (2001) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በማስመልከት ወሳኝ የሆነው ጊዜ መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ ያልተመለሰ ነው፡፡ በሌላ አባባል በእድሜና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል ያለው አከራካሪ ጉዳይ በትክክሉ መልስ አላገኘም፡፡ ስለዚህ በአዋቂዎች፣ በወጣቶችና በታዳጊ ልጆች መካከል ሲደረግ የነበረው ንፅፅር አርቴፊሻል ነው፡፡ ወሳኝ የእድሜ ክልል የተባለው በውል አልታወቀም፡፡ ከዚህ ለማየት የተቻለው በትምህርት ሥርአት ውስጥ በየትኛው የእድሜ ክልል የቋንቋ ትምህረት መጀመር እንዳለበት ቁርጥ ያለ መልስ የለም የሚሉ አካላት እንዳሉ

ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦች በመነሳት የሚከተሉትን ነጥቦች ማስቀመጥ ይቻላል።

1. የቋንቋ ትምህርት በተለያየ የእድሜ ክልል ማከናወን እንደሚቻል ጥናቱ ያስረዳል። ከልጅነት እስከ ከፍተኛ እድሜ ደረጃ ድረስ ቋንቋን መማር እንዲሚቻል ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር ወሳኝ የሆነ የቋንቋ ለመዳ የእድሜ ክልል አለ የሚለውን ማስቀመጥ ይከብዳል የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራል።

2. በተወሰነ የእድሜ ክልል የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት አዋቂዎች፣ ታዳጊዎች፣ የተለያየ የመማረ ስልትን እንደሚጠቀሙ ለማየት የተሞከረ ሲሆን፣ ነገር ግን እያንዳንዱ የእድሜ ክልል የራሱ የሆነ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤትን አሳይቷል። ይህ ደግሞ የዚህ እድሜ ክልል ወሳኝ ነው የሚለውን ሐሳብ ለመናገር አያስደፍርም።
3. ቋንቋን መማር ልክ እንደ ሌሎቹ ክፍሎችና አውቀቶች /ትምህርቶች/ አንድና ወጥ የሆነ አካሄድ አለመኖር የታየ ሲሆን እንደየ እድሜ ክልሉ የሚለያይ መሆኑን ለማየት ተሞክሯል።
4. ለውጥና እድገት ደረጃ ልዩነቱን የሚያሳይ ግልፅ ሆኖ የቀረበ ልዩነት የለም።
5. በእያንዳንዱ የእድገት ደረጃና እድሜ በሂደት በቋንቋ ትምህርት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል ያመለክታል።
6. የትኛው የእድሜ ደረጃ በቋንቋ ትምህረት ወሳኝ መሆኑን ለመወሰንና ትክክለኛ ሐሳብ ላይ ለመድረስ በስነ-ልቦናዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ በጥናት የተደገፈ ሥራ በማየት በጥናቱ የተወሰነ ግንዛቤ ተወስዷል።

በየትኛው እድሜ ክልል ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ይበልጥ ሊማሩ ይችላሉ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ባይገኝም በልጅነት የአድሜ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ቋነቋን መማር የጀመሩ በጊዜ ሂደት በቋንቋ ትምህርቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚችሉ ሁሉንም አጥኚዎች ያግባባል። በተለያየ የእድሜ ክልል ቋንቋን የመማር ፍላጎት፣ የአመለካከትና የንሺ ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ የተለያየ የማስተማር ዘዴን በመከተል ሁለተኛ ቋንቋን ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ የመሁራኑ ሀሳብ ያስረዳል። ይሄንን በተመለከተ Cook (2001) እንደየ እድሜ ክልሉ አመቺ የሆነ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነም ያስገነዝባሉ። ይሁን እንጂ ከላይ በቀረበው መሰረት ትምህርቱን ማልዶ የጀመረና ጊዜ ወስዶ እተማረ ያለው

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በሂደት በቋንቋ ትምህርቱ ከተፈለገው ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል ሁሉንም ምሁራን የሚያስማማ ነው(Stern, 1991; Cook, 2001 እና Lightbown, 2011)።

## 2.15 ማህበራዊ-ትምህርት ሞዴል(Socio-Educational model)

በዚህ ጽሁፍ የጋርድነር የማህበራዊ ስነ-ትምህርታዊ ሞዴል(Socio-Educational model) ከሚከናወነው ጥናት ጋር በማስተያየት የቀረበ ነው። የማህበራዊ-ትምህርታዊ ሞዴል መሰረት ሰው በሚኖረው ተነሳሽነት/ንሺ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የሚቃኝ ነው። ተነሳሽነት/ንሺ ማለት የአንድ ቋንቋ ለማጆች /ተማሪዎች/ ቋንቋን መማራቸው አላማቸውን ከማሳካት አንጻር ያላቸውን እሳቤ ወይም አመለካከት መሰረት በማድረግ የቀረበ ዝርዝር ጉዳይ ነው። ተነሣሽነት በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንደተገለጸው በሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ይከፈላል። ይሄውም ውህዳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Integretive Motivation) እና ቁሳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Instrumental motivation) በመባል ነው። ውህዳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Integretive Motivation) ይህ አይነቱ በቋንቋ ለመዳ ሂደት ተማሪው ለሚማረው ወይንም ለሚለምደው ቋንቋ ያለውን አዎንታዊ አመለካከትና ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር እራሱን ለማዋሀድ ያለውን ፍላጎት የሚመለከት ነው። በሌላ በኩል ቁሳዊ ተነሳሽነት/ንሺ (Instrumental motivation) የሚባለው ደግሞ አንድ የቋንቋ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋውን ለመልመዱ ወይም ለመማሩ ምክንያት የሚያደርገውን ማህበራዊ ወይንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ነው። ይሄ የሚያሳየው ቋንቋን መማር ያለብን ለምንፈልጋቸው ጉዳዮች ማሳኪያ ወይም መከወኛ ተብሎ ለመዳውን/ትምህርቱን ለማከናወን ሲቻል እንደሆነ በGardner (2006) ሀሳብ ላይም በስፋት ቀርቧል።

በሁለቱም የተነሳሽነት ክፍሎች በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳና በትምህርቱ መካካል ያለውን ትስስር በሚመለከት በውጪው ሀገር የተለያዩ ጥናቶች ተከናውነዋል። በመሆኑም ለመማር ያለ ተነሳሽነት ያለውን ሚና/ተጽዕኖ/ በሚመለከት ጃፓኖች እንግሊዘኛን እንደ ውጪ ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል በዘርፉ ጥናት ተከናውኗል።

በLarson Freeman እና long (1994) እንዳቀረቡት የጋርድነርን ማህበራዊ-ትምህርታዊ ሞዴል መሰረት በማድረግ ለመማር ባለ ተነሣሽነት ዙሪያ ትኩረት እንዲያደርግ ያነሳሳው (Mowrer, 1950) እንደሆነ በመግለጽ ይሄውም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ የተሰራው ስራ ከፍተኛ

ተጽእኖ ስላሳደረበት እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ሞዴል መሰርት የሚያደርገው የአንድ ህጻን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ስኬታማ እንዲሆን ከሚያደርጉት ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ቤተሰቦቹ ሲሆኑ ቀጥሎም በአካባቢው የሚገኙ የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና ወይም ተቀባይነትን ለማግኘት ካለው ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው። ከዚህ አንጻር አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ያለው ተነሳሽነት ለስኬታማ የቋንቋ ለመዳ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች ወይንም በቋንቋ ለመዳ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች ውስጥ የተማሪው ቤተሰብና ማህበራዊ አውድ መሆኑን በዋናነት ሊሰመርበት እንደሚገባ ነው የቀረበው። ምክንያቱም ለመማር ያለ ተነሳሽነት ብቻውን ለቋንቋው ለመዳ ምክንያት አይደለምና ነው።

በGardner (1982) የማህበራዊ ትምህርት ሞዴል በሁለተኛ ቋንቋው ለመዳ እርስ በእርሳቸው የሚመጋገቡ (የማይነጣጠሉ) የተለያዩ ምክንያቶች ተለይተው ቀርበዋል። በዘርፉ ከተከናወኑ ጥናቶች በተለይ የጋርድነር ሞዴሎች ትኩርት የሚያደርጉት የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ከተፈጥሮአዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታ ይልቅ የተደራጀ መደበኛ የክፍል ውስጥ መማር ማስተማርን የሚመለከቱ ሲሆን ሥራዎቹ መሰረት የሚያደርጉትም የውጪ ቋንቋን መማር ላይ ነው። የጋርድነር ሞዴል አራት የሁለተኛ ቋንቋ ከመማር ጋር እርስ በርሳቸው ትስስር ያላቸው ናቸው፤ ብሎ ያቀረባቸው፡-

1. ማህበራዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች፣
2. የግለሰቦች የመማር ችሎታ ልዩነት፣
3. ትምህርቱ የሚከናወንበት አውድ እና
4. ቋንቋን መማር የሚያመጣው ውጤት ናቸው(Gardner,1982)።

ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ሁኔታ ግለሰቡ ወይንም የቋንቋው ተማሪ የሚኖርበትን ከባቢያዊ ሁኔታ የሚመለከት ነው። ይህም ሁኔታ የአንድ ማህበረሰብ አባላት ሌላው ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ ያላቸው እምነትና አመለካከት ቋንቋውን በብቃት በመማርና ባለመማር መካከል ያለውን ልዩነት ይወስናል የሚል ነው። ይህም በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ እና መማር ላይ ጉልህ የሆነ ተፅእኖ እንዳለ ያመለክታል። ለምሳሌ ያህል አህዳዊ የሆነ ባህላዊ አካባቢ ባለበት እና አብዛኛው ማህበረሰቧ ሌላ ቋንቋን መማር አያስፈልግም በማለትና፤ ይልቁንም አናሳ ቡድኖች ከአብዛኛው የቋንቋ ተናጋሪ ጋር መዋሃድ እና የበላይነት የያዘውን የሀገሪቱን ቋንቋ መማር አለባቸው ብለው

የሚያምኑ ህዝቦች ያሏትን እንግሊዝን ወስዶ ማየት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ሌሎች የአሃዳዊ ባህል የበላይነት የሰፈነባቸውን የአለም ሃገሮችን በመውሰድ ብዙ ማለት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ካናዳ ባሉ ልሳነ-ክልኤነት እና ባህለ-ክልኤነት በአብዛኛው ማህበረሰብ ተፈላጊነት ባለባቸውና ማህበረሰቡ ልሳነ-ክልኤ እና ባህለ-ክልኤ እንደሆኑ በሚበረታቱባቸው ሌሎች ሃገሮች ልሳነ-ክልኤነት እና ባህለ-ክልኤነትን በተመለከተ ካላቸው አመለካከትና ልምድ ጋር ለቋንቋውና ለባህሉ ካላቸው አመለካከት ጋር ተዳምረው ግለሰቡ ለሚማረው ቋንቋ ያለውን መሠረታዊ አመለካከት ይወስናሉ(Ellies,1997)፡፡ ሁለተኛው ደረጃ የጋርድነር ሞዴል ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን አራቱን ግለሰባዊ ልዩነቶች ያስተዋውቃል፡፡ እነዚህም፡-

1. አዕምሮአዊ ብቃት/ጉብዝና/ (Intelligence)
2. ቋንቋን የመማር ችሎታ/ክህሎት/ (Language aptitude)
3. ተነሳሽነት
4. ሁኔታዊ ፍራቻ (Situational-anxiety) ናቸው ብለው Ellies(1997) Giles Comland(1991)ን ጠቅሶ ሀሳቡን በምክንያትነት ያቀርባል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ጋር በጥብቅ የሚተሳሰሩና በቀጣዩ የጋርድነር ክፍል የሚታየው ሌላኛው ወሳኝ ሁኔታ ደግሞ ትምህርቱ የሚካሄድበት አውድ ወይም መቼት ሲሆን ለዚህም ተከታዮቹ ሁለት አይነት አውዶች ተለይተው ቀርበዋል፡፡

1. በክፍል ውስጥ የሚካሄድ መደበኛ ትምህርትና
2. በኢ-መደበኛ ወይም ተፈጥሮአዊ አከባቢ የሚካሄድ የቋንቋ ለመዳ ናቸው፡፡

የቋንቋ ትምህርቱ እንደሚካሄድበት አውዳዊ ሁኔታ የግለሰቦች የመማር ችሎታ ልዩነትን በተመለከተ የቀረቡት ምክንያቶች ወይም ተለዋዋጮች የሚያሳድሩት ተጽእኖም ይለያያል፡፡ ለምሳሌ፡- በመደበኛ ሁኔታ በሚካሄድ የመማር ማስተማር ላይ የተማሪው ችሎታ ወይም ጉብዝና እና የቋንቋ እውቀት ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን በኢ-መደበኛ ወይም ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ደግሞ የተማሪው ጉብዝናም ሆነ እውቀት የሚኖራቸው ተጽእኖ እምብዛም ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁኔታዊ ፍራቻ(Situational anxiety) እና ተነሳሽነትን በምናይበት ጊዜ በኢ-መደበኛ የመማር አውዶች ላይ የሚኖራቸው ተፅእኖ እኩል ወይም ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል፡፡

የመጨረሻው የጋርድነር ሞዴል ደረጃ የመማር ልምድ በሥነ-ልሳናዊና ኢ-ስነልሳናዊ ብቃት ላይ የሚኖረውን ሚና የሚመለከት ነው። ስነ-ልሳናዊ ብቃት ሲባል የተማሪውን ትክክለኛ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት የሚመለከት ነው። ተማሪው በትምህርቱ ያመጣቸው የፈተና ውጤቶች እና አጠቃላይ የቋንቋ ብቃት ፈተናዎች ላይ ያስመዘገባቸውን ውጤቶች የሚያጠቃልል ነው። በሌላ በኩል ኢ-ስነ-ልሳናዊ ውጤቶች ደግሞ ግለሰቡ ለሚማረው ቋንቋና ተናጋሪ ማህረሰብ ባህላዊ እሴቶች ያለውን አመለካከት የሚያሳይ ነው። Ellies (1997) ግለሰቦች ለሚማሩት ቋንቋ ስነ-ልሳናዊና ኢ-ስነ-ልሳናዊ ውጤቶችን (ጠቀሜታዎች) በጎ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት ሲኖራቸው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ከፍተኛ ውጤት(ስኬት) ያስመዘግባሉ! የመማር ብቃታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል ይላሉ።

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በቀረበው ሀሳብ መሰረት ማህበራዊ ትምህርት ሞዴል ቋንቋውን ለመማር ያለ ተነሳሽነት የሚከተሉትን ሶስት ክፍሎችን ያካትታል። የመጀመሪያው ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት (ተነሳሽነት) ያሳየው ግለሰብ ቋንቋውን ለመማር የሚያጠፋው ጊዜና ጥረትን የሚመለከት ነው። ሁለተኛው ቋንቋውን በመማሩ ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብ /ውጤትን/ ሚመለከት ሲሆን ሶስተኛው ቋንቋውን ለመማር ተነሳሽነት ያሳያው ግለሰብ ቋንቋውን ለመማር በፍቅር የሚሠራቸው መልመጃዎች(tasks) በሙሉ በፍላጎት መሆን ወይም አለመሆኑ የሚኖረውን ተጽእኖ የሚመለከት ነው።

ፍላጎት ቋንቋውን ለመማር ያለውን ሚና በተመለከተም ውህዳዊ መነሳሳት(integrative motivation). ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ግብሩ ከተማሪው ልምድ(orientation) ጋር ትስስር ያለው መሆኑን ነው። ይህም ማለት ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለውን በጎ አመለካከትና ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ራሱን ለማዋሃድ ያለውን ፍላጎት ያመለክታል። ሶስተኛው ቋንቋን ለመማር ውህዳዊ መነሳሳት ያለው ሰው ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ለማወሃድና ራሱን ለማሳወቅ ከፍተኛ ፍላጎት አለው ይህም ለመማር ያሉት አጋጣሚዎች ሁሉ በቅንነት በትክክል ወደመመርመሩ ይሸጋገራል፤ በማለት Hashi (2001) ሀሳባቸውን ያቀርባሉ።

በሌላ በኩልም ቁሳዊ መነሳሳት (Instrumental motivation) በተመለከተ Hudson (2000) እንዳቀረቡት በሁለተኛ ቋንቋ ጥናት ተማሪው በተጨባጭ ሊያገኛቸው ወይም ሊተገብራቸው የሚፈለጋቸውን ጉዳዮች አስመልክቶ የሚያሳያቸውን ባህርያት የሚመለከት ነው። ቁሳዊ

ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን በማወቁ ወይም በመማሩ የሚያገኙቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቹን የሚመለከት ነው።

ሌላው የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የሚያነሳሳው ጉዳይ ተማሪው ቋንቋን በሚማርበት ወቅት ያጋጠሙትን አስቸጋሪ የሚመስሉ (አስቸጋሪ በሆኑ) ሙከራዎች አልፎ እና ለመማር አስቸጋሪ የሆኑትን ችግሮች በመወጣቱ ለራሱ የሚኖረው ስሜት ወይም እችላለሁ (ተወጣሁት) ብሎ የመደሰት ስሜት ቋንቋን በተሻለ ትጋትና ፍላጎት ለመማር ምክንያት ይሆናል። የሁለተኛ ቋንቋን በመማር በሚገኝ ለውጥ ምክንያት የሚኖር መነሳሳት በተመለከተ በተለየ የሁለተኛ ቋንቋ ልማጆች (ተማሪዎች) የበለጠ የሚገፋፉት ቋንቋውን በመማራቸው የሚመጣውን ጥቅም በማሰብ ነው። ቋንቋውን መማር የሚፈልጉት ራሳቸውን ለማሻሻል፣ አልያም ቋንቋን በመማራቸው የህይወት ምዕራፋቸው ላይ የሚያመጣውን ለውጥ በማሰብ ነው የሚል የጥናት ውጤቶች ላይም ቀርቧል።

በዚህ ጥናት ላይ የጋርድነር ትምህርታዊ-ማህበራዊ ሞዴል እንደ ጥናቱ ባህሪ አብሮ የሚሄደውን ወስዶ በመጠቀም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጠዎችን የሚለይ ጥናት ተከናውኗል። አካባቢያዊ አውድን መሰረት በማድረግ በገጠር ተማሪዎችና በከተማ ተማሪዎች መካከል ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በቋንቋ ትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤትን መመርመር የዚህ ጥናት ዋነኛ ስራ ነው።

### 2.15.1 ለሁለተኛ ቋንቋን ትምህርት ፆንሺነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች

1) **የቋንቋ ደረጃ** (Lauguage level):- የውህዳዊ ንሺ ንዑስ መዋቅር (integrative motivational sub system)" ቁሳዊ ንሺ ንዑስ መዋቅር(Instrumental motivational Sub system)
2. **የተማሪው ደረጃ** (learner level):- ስኬታማ የመሆን ፍላጎት፣ በራስ መተማመን፣ ስለ ራስ ያለ የብቃት ስሜት(self-efficacy)፣ ማህበራዊ ተቀባይነት፣ ቋንቋን የመናገር ፍርሃት (Languages anxiey) ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ያለ አመለካከት (አልችልም ብሎ ማሰብ)፣ ለቋንቋ ትምህርት ያለ ተለምዶአዊ አመለካከት

3. የመማር አጋጣሚና ትምህርቱ የሚካሄድበት ደረጃ፡- ኮርስ ተኮር የሆነ መነሳሳት ወይም ከትምህርት አይነት አንጻር ትምህርቱን ለመማር የሚኖር ፍላጎት(Interest)፤ ቋንቋውን መቻልና መማሩ ከሚሠጠው ጥቅም፣ ውስጣዊ እርካታ፣ መምህር ተኮር መነሳሳት አይነቶች፣ ለቋንቋው ያለን ፍቅር፣ የስልጣን አይነት (authority type)፣ ራስን ከቋንቋ ተናጋሪው ማህበረሰብ ጋር በቀጥታ ለማዋሃድ ያለ ፍላጎት፣ ቡድን ተኮር መነሳሳት፣ ለአለማችን ያለን እሳቤዎች፣ ባህላዊ ሁኔታ፣ የማበራታቻ ስርዓት፣ ቡድናዊ ጥምረት (ውህደት)፣ የክፍል ውስጥ መዋቅራዊ ግብ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ንሺነት በምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 2.15.2 በማህበረሰብ-ትምህርታዊ ሞዴል ላይ የሚቀርቡ አስተያየቶች

ለበርካታ አመታት የማህበራዊ ትምህርት ሞዴልን በተመለከተ ለሁለት ጉዳዮች ሲባል ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን ይሄውም ንሺ ከቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና ውህዳዊ መነሳሳትን ለመመርመር ሲባልና የጋርድነር ሞዴሉ መዋቅራዊ ቅርጽን(Structure) ለአመታት ማጥናቱ ላይ ትችት ቀርቧል፡፡ ከመነሻው በAu(1988) እና Oller (1981) የጋርድነርን ጭብጥ ሀሳብ (concept) እና ለሞዴሉ ጭብጥ የተሰጠውን ተግባራዊ ብያኔ (operational definition) አመለካከት እና ፍላጎት በቋንቋ የምዘና ውጤት ላይ የሚያሳርፈውን ተፅእኖ አስመለክቶ ያቀረቧቸው ሃሳቦች ወጥነት የጎደላቸው ናቸው የሚል አስተያየት ቀርቦበታል፡፡

## 2.16 በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዙሪያ የተደረጉ ተዛማጅ ጥናቶች

አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋው ወይም ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማየት አጥኚው በ1997ዓ/ም ካከናወነው ጥናት በስተቀር ሌላ ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም በገጠርና በከተማ፣ በክልሎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ጥናትም አልተከናወነም፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተገለጸው ዓመተ ምህረት በት/ቤቶች መካከል ያለውን ልዩነት ማየትና እንዲሁም በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለውን ግኝኙነት ለማየት ከተከናወነ ጥናት በስተቀር ሌላ ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ

ትምህርታቸው ያላቸውን አመለካከት በተናጠል የተጠኑ ሁለት የማስተርስና ሦስት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን መመልከት የተቻለ ሲሆን እያንዳንዱ ጥናት ከነ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ብርሀኑ ገብረማርያም በ1976 ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ ሲባል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቃ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የቀረበ ጥናት ተከናውኗል፡፡

ይህ ጥናት በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ሆኖ ተማሪዎች በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት በንጽጽር ያለው የልዩነት ደረጃ ለማየት ሲባል የሚከናወን ጥናት ሲሆን ትኩረቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚስተዋልን አመለካከት የሚዳስስ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት ሲታይ አብዛኛው ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ የእንግሊዘኛ ቋንቋን እንደሚመርጡና የአማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን እንደሚፈልጉ ከሴቶች ይልቅ ወንዶች አማርኛ ቋንቋን እንደሚመርጡ በጥናት ግኝታቸው ላይ አቅርበዋል፡፡ ይሄም ጥናት ከእንግሊዘኛ ቋንቋ አንጻር የታየ እንጂ በተናጠል ይሄንን ያህል ነው የሚል አይደለም፡፡ የአጠናኑ ዘዴና  የመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ጥርት ባለ መልኩ ትንታኔ የተሰጠበት አይደለም፡፡

ታሪኩ ፋንታዬ 1988 ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ተቋም አማርኛን በማስተማር ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ‹‹የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከትን ለማወቅ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ የታሪኩ ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ዘንድ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው? ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተላውጠዎችን መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱም ግኝት የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆችና የተማሪዎች  እኩዮች ለአማርኛ ቋንቋና ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ነው በጥናታቸው ላይ ያቀረቡት፡፡ ይሄም አጥኚው ከደረሰበት የጥናት ውጤት በስተቀር ጥናቱ ውስጥ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጠዎችን ለማየት የተደረገ ጥናት ነው ከሚለው ሀሳብ ጋር ተያይዞ ተጽእኖ ስላሳደሩት ተላወጦዎች በግልጽ የተሰበሰበ መረጃና የተገኘ ውጤት የለም፡፡

አበበ ሽፈራው 1990 ዓ/ም  በኮተቤ የመምህራን ካሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኢጁኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ ‹‹አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በሰበታ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል፡፡ የአበበ መላምት በየትምህርት ቤቱ የሚገኙት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱት ለአማርኛ አዎንታዊ አመለካከት የላቸውም›› የሚለውን መፈተሽ ነበር፡፡ ግኝቱ እንድሚያስረዳው ተተኳሪ ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ፣ በቋንቋው ትምህርት፣ በቋንቋው ተናጋሪ ጥሩ አመለካከት የላቸውም በሚል ውጤት ላይ የደረሰበት ነው፡፡

ዳንኤል መኮንን1992 ዓ/ም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኢዱኬሽነ ዲግሪ ማሟያ ‹‹በሀይዲኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በሆሣዕና ከተማ ባሉ የሁለተኛ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት›› በሚል  የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በሆሣዕና ከተማ በሚገኙ ሁለት ከፍትኛ ት/ቤት ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አፋቸውን በሀዲኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለቋንቋውና፣ ለቋንቋው ትምህርት፣ ለቋንቋው ተናጋሪ ወዘተ አዎንታዊ አመለካከት አለ በሚል ውጤት ላይ ደርሷል፡፡

ድንቁሣ 1996 ዓ/ም ‹‹ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት መፈተሽና›› በአዲስ አበባ መስተዳደር የአማርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት በኦሮምኛና ብሔራዊ ክልል ኢ-አፈ ፈት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች›› በሚል ርዕስ ጥናት አከናውኗል፡፡

የጥናቱ ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ከአማርኛ በተሻለ ሁኔታ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን እንደሚወዱ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አስበልጠው የሚወዱም አሉ በሚል የጥናቱን ውጤት አቅርቧል፡፡ አብዛኛዎቹ ለቋንቋው አፈ-ፈት የሆኑትም ሆነ ኢ-አፈፈት የአማርኛ ተናጋሪዎችንም ሆነ ቋንቋውን የሚጠሉ አይደሉም የሚል አስተያየት መሰል ውጤት አቅርቧል፡፡ ይሄ ውጤት ከአበበ ሽፈራው1990 ዓ/ም የጥናት ውጤት በተለየ መልኩ በአወንታዊ ጎኑ የቀረበ ነው፡፡ የቋንቋውን ውጤት በተመለከተም ለተማሪዎቹ እንደማይከብዳቸው ጥናቱ ያመለክታል በሚል ውጤቱን አቅርቧል፡፡ ነገር ግን ስለመክበድና አለመክበዱ ጉዳይ አጥኚው በፈተና የመዘነበት

መመዘኛ ስለሌለው ማጠቃለያ ደረጃ ላይ የተደረሰበት መንገድ በግልጽ አለመቅረቡን ለመመልከት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል በተማሪዎችም፣ በወላጆች፣ በእኩዮች፣ በህብረተሰቡ እና በመገናኛ ብዙሀን አካባቢ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ስለቋንቋው የተሳሳተ ግንዛቤ አልፎ አልፎ ይንጸባረቃል የሚል ውጤትም ቀርቧል፡፡ አንዳንድ ብሄር ብሄረሰብም፤ እንዲሁም ክልሎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ በጎ አመለካከት የላቸውም የሚል ውጤት ቀርቧል፡፡ ነገር ግን ክልሎች፣ ብሄር ብሄረሰቦች እና የመገናኛ ብዙሀን በጎ አመለካከት የሌላቸው መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ መረጃና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አለመኖሩን መመልከት የተቻለ በመሆኑ የጥናቱ ውጤት ወደ ግል አስተያየት እንዲያዘነብል አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ሲተያይ ከጥናቶቹ ጋር ይህን ያህል የቀረበ ግንኙነት የላቸውም፡፡ አመለካከትን በተመለከተ በተወሰነ ደረጃ ተቀራራቢ ቢመስልም በጥናቶቹ ላይ ከቀረበው ውጤት፣ ከመረጃ አተናተን ዘዴውና ከጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ጋር ሲነጻጸር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ስለዚህ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ከዚህ የጥናት መሰረታዊ ነጥብ አንጻር የተለየ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ባለመከናወኑ ይሄን ጥናት በማከናወን በዙሪያው በየሚከሰቱ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ዘዴ(Methodology of study)

በዚህ ክፍል ውስጥ አጠቃላይ የጥናቱ አተገባበር የሚታይበት ነው፡፡ ይሄውም የጥናቱ አይነት፣ የጥናቱ አካላይ እንዴት እንደተወሰነ ለጥናቱ የሚወሰዱ ቦታዎችና የቦታዎቹ አመራረጥ፣ መረጃ ሠጪዎች እንዴት እንደተመረጡ የሚብራራበት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና የመሳሪያዎቹ አዘገጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የተሰበሰበው መረጃ እንዴት እንደተተነተነ በዝርዝር ቀርቦ ከውጤትና ከመፍትሄ ሀሳብ ላይ እንደተደረሰ በሚያሳይ መልኩ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## 3.1 በየደረጃው የሚገኙ የጥናቱ አካላዮች አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለው ፈርጀ ብዙ/ባለብዙ ደረጃ/ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ (Multistage Sampling) የሚባለው ዘዴ ነው፡፡ ይሄ ዘዴ የክልል ወይም የቡድን ንሞና (Area or Cluster Sampling) ዘዴ ተቀጽላ ነው፡፡ ስለዚህ በቡድንም ሆነ በተናጠል እንደ አስፈላጊነቱ አራት ወይም ከዚያ በላይ ደረጃዎችን በመከተል ናሙናዎችን ለመምረጥ ስለሚያስችል ይሄ ዘዴ ለዚህ ጥናትም ይበልጥ አመቺ በመሆኑ ተመርጧል፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ የተወሰደው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሰባት ደረጃዎችን ተከትሎ የተከናወነ ነው፡፡ ደረጃውም የሚከተለውን ሂደት ይመስላ፡፡

ክልል→ ዞን →ትምህርት ቤት→የክፍል ደረጃ → ክፍል →ተማሪ→ ናሙና

ከላይ በቀረበው ተግባር መሰረት ጥናቱ የሚከናወነው በሀገር ደረጃ ሆኖ ክልሎች ምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ክልሎችም ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ትግራይ እና ክልል 14(አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር) ናቸው፡፡ ክልል 14(አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር) በጥናቱ ውስጥ እንዲካተት የተፈለገበት ምክንያት ከሌሎች ክልሎች ጋር ያለውን የልዩነት ደረጃ በንጽጽር ለማመሳከርያነት ለመጠቀም ሲባል ነው፡፡ ከኦሮሚያ ክልል፣ ከአፋር ክልል፣ ከትግራይ ክልል ሁለት ሁለት ዞኖችና እና ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውስጥ ሁለት ክፍለ ከተሞች በእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በዞኖቹና በክፍለ ከተሞቹ

ውስጥ ካሉ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በዞን ደረጃ ሁለት ትምህርት ቤቶችን በክልል ደረጃ በድምሩ አራት ትምህርት ቤቶችን በእድል ሰጪ ናሙና ዘዴን በመጠቀም በደረጃው ያሉ ናሙናዎችን በመምረጥ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

## 3.2 የዞኖችን አመራረጥ ዘዴ

ጥናቱ የሚከናወነው ከላይ በተገለጹት አራት ክልሎች ላይ ነው፡፡ በየክልሎቹ የሚገኙትን የዞኖች ዝርዝር በቅደም ተከተል በመመዝገብ የእጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ከየክልሉ ሁለት ሁለት ዞኖች  በድምሩ ስምንት ዞኖች ተመርጠዋል፡፡ ዞኖቹ የተመረጡበት የናሙና አወሳሰድ ዘዴም በየክልሎቹ ያሉ ዞኖችን በፊደላት ቅደም ተከትል መሰረት ከተመዘገቡ በኋላ ከእድል ሰጪ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ውስጥ ቀላል የእጣ ንሞና ዘዴን በመጠቀም በእጣ የማውጣት ዘዴ አማካኝነት ዞኖቹ ተመርጠዋል፡፡

የእጣ አወጣጡ ሂደት ለጥናቱ ከተመረጡት ክልሎች ውስጥ በየክልሎቹ የሚገኙትን ዞኖች በሙሉ  ለብቻ ለብቻ የመመዝገብ ተግባር ተከናውኖ፤ ከዛም እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች በዞኖቹ ቁጥር ልክ በማዘጋጀት በወረቀቶቹ ላይ በየክልሉ ሁለት ወረቀቶች ላይ “ተመርጧል” የሚል በመጻፍና በተቀሩት ላይ ደግሞ “አልተመረጠም” የሚል በመጻፍ ወረቀቶቹ ተጠቅልለው በተመዘገቡት ዞኖች በቅደም ተከተል መሰረት ዞኖችን በመጥራት የተፈለገው የናሙና ቁጥር (ሁለቱ ተመርጠዋል የሚሉት ወረቀቶች) እስከሚወጣበት ድረስ የእጣ ማውጣቱ ተግባር ቀጥሎ “ተመርጧል” የሚሉት ሁለቱ እጣዎች እንደወጡ እጣውን በማቆም በእጣው የተመረጡት ዞኖች ለጥናቱ ተወስደዋል፡፡ ይህም የተደረገበት አቢይ ምክንያት ለሁሉም ዞኖች እኩል እድል ለመስጠት ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ለሙከራ ጥናቱ በክልል ደረጃ አንድ ዞን በድምሩ 4 ዞኖች ተመርጠው  ጥናቱ የተከናወነ ሲሆን ለዋናው ጥናት በክልል ደረጃ ሁለት ሁለት ዞኖች በሀገር ደረጃ በድምሩ 8 ዞኖች ተመርጠውዋል፡፡ የሙከራ ጥናቱን ጨምሮ በአጠቃላይ 12 ዞኖች ተመርጠው ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

ለሙከራ ጥናቱ ከየክልሎቹ የተመረጡት ዞኖች ከአዲስ አበባ ከ10 ዞን(ክፍለ ከተማ) ውስጥ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ከኦሮሚያ ከ18 ዞን ውስጥ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ከአፋር ክልል ከ5 ዞን ውስጥ ዞን አራትን፣ ከትግራይ ከ7 ዞን ውስጥ ትግራይ ማእከላዊ ዞንን አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠው የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ ለዋና ጥናቱ መሰረት ተጥሏል። አጥኚው አመቺ የናሙና (Conveniece sampling) አመራረጥ ዘዴን የተጠቀመበት አቢይ ምክንያት ከቅርበት ያገኛቸውንና እንዲሁም ሁለት ድንበርተኛ የሆኑ ክልሎችንና ዞኖችን በመጠቀም ከነዚህ ውስጥ ለሙከራ ጥናቱ ይበቃል ተብሎ በተወሰነው የቁጥር መጠን መሰረት ትምህርት ቤቶችን መርጦ በትምህርት ቤቶቹ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናቱን ማከናወን ተችሏል። የሙከራ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ለዋናው ጥናት የሚያስፈልጉ ዞኖችንና ትምህት ቤቶችን ለመወሰን ተችሏል።

ለዋናው ጥናት የተመረጡ ዞኖች ከአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማና ጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ ከኦሮሚያ ክልል ጂማ ዞንና ምእራብ ሸዋ ዞን፣ ከአፋር ክልል ዞን አንድና ዞን ሶስት፣ ከትግራይ መቀሌ ዞንና ደቡባዊ ምእራብ ትግራይ ዞን ለጥናቱ ተመረጠዋል። የሙከራ ጥናቱን ጨምሮ በድምሩ12 ዞኖች ለጥናቱ ተመርጠው ጥናቱ ተከናውኗል።

## 3.3 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ዘዴ

ከላይ በተራ ቁጥር 3.2 ላይ በቀረበው ተግባር መሰረት የዞኖች መረጣ ተከናውኖ እንደተጠናቀቀ በየክልሉ ካሉት ዞኖቹ ውስጥ ትምህርት ቤቶችን ወደ መምረጥ ተግባር ተገብቷል። ትምህርት ቤቶችም የተመረጡበት የናሙና አመራረጥ ዘዴም የሚከተለውን ይመስላል። በእያንዳንዱ ዞን ውስጥ የሚገኙ ከዘጠኝ እስከ አስረኛ ክፍል ከሚያስተምሩ የመንግስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በሙሉ በመመዝገብ እንደ መረጃው አስፈላጊነት ከየዞኑ ሁለት ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ከእድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ውስጥ ቀላል የእጣ ንሞናን በመጠቀምና እጣ የማውጣት(Lottery Method) ዘዴ መሰረት ትምህርት ቤቶቹ ተመርጠዋል። የእጣ አወጣጡ ለጥናቱ ከተመረጡት ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን በሙሉ በስማቸው ፊደል ቅደም ተከተል መሰረት ተመዝግበዋል። ከዛም በእያንደንዱ ዞን የሚገኙ የትምህርት ቤቶች ቁጥር ልክ እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን

ወረቀቶች በማዘጋጀት በወረቀቶቹ ላይ በያንዳንዱ ዞን ሁለት ሁለት ወረቀቶች ላይ "ተመርጧል" የሚል በመጻፍና በተቀሩት ላይ ደግሞ "አልተመረጠም" የሚል በመጻፍ ወረቀቶቹ ተጠቅልለው በእጣ ማውጫ እቃ ውስጥ በማስቀመጥና እቃውን በመወዝወዝ ትምህርት ቤቶቹ የተመዘገቡበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ በመጥራት የተፈለገው የናሙና ቁጥር (ከእያንዳንዱ ዞን ሁለት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል የሚሉት ወረቀቶች) እስከሚወጣበት ድረስ እጣውን የማውጣቱ ተግባር ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ከእያንዳንዱ ዞን ሁለት ሁለት ትምህርት ቤቶችን በክልል ደረጃ አራት አራት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡

ትምህርት ቤቶቹ በእጣ የማውጣት ዘዴ የተመረጡበት ምክንያት ለሁሉም ት/ቤቶች እኩል እድል ለመስጠት ታስቦ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከትግራይ ወልደ ንጉስ፣ አዴ ጉዶም፣ ጥላሁን ይግዛው፣ መሆኒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ ከኦሮሚያ ክልል አሲንዳቦ፣ ሰርቦ፣ ጥቁር እንጪኒ እና ጉደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ ከአፋር ክልል ሰመራ፣ ሎጊያ፣ ገዋኔና መልካ ሳዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ ከአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ፣ ድል በር፣ ኒውኤራና ደብረ ሰላም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡

ለዚህ ለዋና ጥናቱ የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ተጨማሪ ግብአት ሆኖ ያገለገለው የሙከራ ጥናቱ ሲሆን ይሄውም ከየክልሉ አንድ አንድ ዞን በመምረጥ የናሙና ጥናቱን በማከናወን በተገኘ መረጃ መሰረት ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ቤተልሄም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ለቅድመ ሙከራ ጥናቱ ተመርጦ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያን መፈተሽ ተችሏል፡፡ ከዛም ለሙከራ ጥናቱ የተመረጡት ዞኖች ከትግራይ ማእከላዊ ዞን ከአቢያዲ ራስ አሉላ አባነጋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ደገምንና ኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ከአፋር ክልል ከዞን አራት ከልዋን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠው የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ ለዋና ጥናቱ መሰረት የሆኑትን በግብአትነት በመጠቀም ነው፡፡

## 3.4 ለሙከራና ለዋናው ጥናት የክፍሎች አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ክፍል ውስጥ ከላይ በተከናወነው የናሙና አመራረጥ ዘዴ መሰረት የዞኖች አመራረጥ ተግባር ተከናውኖ እንደተጠናቀቀ በየክልሉ ካሉት ዞኖች ውስጥ ትምህርት ቤቶችን የመምረጥ ተግባር ተከናውኗል፡፡ ለሙከራውና ለዋናው ጥናት ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተመረጡ ናሙና ክፍሎችና የክፍሎች ብዛቶች በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተው መልኩ ቀርቧል፡፡

### 3.4.1 ለሙከራ ጥናት የክፍሎች አመራረጥ ዘዴ

ለሙራ ጥናቱ ከዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ከ4-5 የሚደርሱ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ የክፍሎቹም አመራረጥ ከእድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ውስጥ ቀላል የእጣ ንሞናን በመጠቀም እጣ የማውጣት (Lottery system) ዘዴ መሰረት ነው፡፡ የእጣ አወጣጡ ለጥናቱ ከተመረጡት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ የሚገኙ ክፍሎችን በሙሉ በፊደል ተራ ቁጥራቸው መሰረት ተመዝግበዋል፡፡ ከዛም እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች በክፍሎቹ ቁጥር ልክ በማዘጋጀት በወረቀቶቹ ላይ በትምህርት ቤት እንደ ክፍሎቹ ብዛት በ4 ወይም በ5 ወረቀቶች ላይ "ተመርጧል" የሚል በመጻፍና በተቀሩት ላይ ደግሞ "አልተመረጠም" የሚል በመጻፍ ወረቀቶቹ ተጠቅልለው በእጣ ማውጫ እቃ ውስጥ በማስቀመጥና በመወዝወዝ ትምህርት ቤቶቹ የተመዘገቡበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ በመጥራት የተፈለገው የናሙና ቁጥር (ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አምስት ወይም ስድስት ክፍሎች ተመርጠዋል የሚሉት ወረቀቶች) እስከሚወጡበት ድረስ የእጣ ማውጣቱ ተግባር ተከናውኗል፡፡

*ለቅድመ ሙከራ ጥናቱ ከአዲስ አበባ ከቤተልሄም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች እጣ በማውጣት የናሙና አወሳሰድ ዘዴን ተጠቅሞ በመምረጥ ቅድመ ሙከራ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡ ለየሙከራ ጥናቱ ከተመረጡት ዞኖች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ከደገም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3 ክፍሎችንና ኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3 ክፍሎችን፣ ከትግራይ ማእከላዊ ዞን ከአቢያዲ ራስ አሉላ አባነጋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ 5 ክፍሎች፣ ከአፋር ክልል በዞን አራት ከሚገኘው የከልዋን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 4 ክፍሎቸ በእጣ ማውጣት የናሙና ዘዴ በመጠቀም*

*በድምሩ 20 ክፍሎች ተመርጠው የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ በተገኘው በቂ የመረጃና ግብአት ግብአት ማግኘት ተችሏል፡፡*

*ሰንጠረዥ አንድ ሀ ፤ ከክልል አንጻር የት/ቤቶችና የተመረጡ ክፍሎች ብዛት*

| ተ.ቁ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | አዲስ አበባ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ተቅላላ |
| 2 | ከልዋን | 4 | ራስ አሉላ አባነጋ | 5 | ከኤጀሬና ከደገም | 6 | ቤተልሄም | 5 | 20 |

## 3.4.2 ለዋና ጥናቱ የተመረጡ ክፍሎች ብዛት

የከሙከራ ጥናቱን በተጨማሪ ግብአትነት በመጠቀም ለዋናው ጥናት ከዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ከ5-6 የሚደርሱ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ የክፍሎቹም አመራረጥ ከእድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ውስጥ ቀላል የእጣ ንሞናን በመጠቀም እጣ የማውጣት (Lottery system) ዘዴ መሰረት ነው፡፡ የእጣ አወጣጡ ለጥናቱ ከተመረጡት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ የሚገኙ ክፍሎችን በሙሉ በፊደል ተራ ቁጥራቸው መሰረት ተመዝግበዋል፡፡ ከዛም እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች በክፍሎቹ ቁጥር ልክ በማዘጋጀት በወረቀቶቹ ላይ በትምህርት ቤት እንደ ክፍሎቹ ብዛት በ5 ወይም በ6 ወረቀቶች ላይ "ተመርጧል" የሚል በመጻፍና በተቀሩት ላይ ደግሞ "አልተመረጠም" የሚል በመጻፍ ወረቀቶቹ ተጠቅልለው በእጣ ማውጫ እቃ ውስጥ በማስቀመጥና በመወዝወዝ ትምህርት ቤቶቹ የተመዘገቡበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ በመጥራት የተፈለገው የናሙና ቁጥር (ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አምስት ወይም ስድስት ክፍሎች ተመርጠዋል የሚሉት ወረቀቶች) እስከሚወጡበት ድረስ የእጣ ማውጣቱ ተግባር ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ከእያንዳንዱ ዞን ከአስር ያላነሱ ክፍሎችን በክልል ደረጃ ከሃያ የማያንሱ በሀገር ደረጃ ከ78 ያላነሱ ክፍሎች ተመርጠዋል፡፡ ከሙከራ ጥናቱ ጋር በአጠቃላይ 96 ክፍሎች ተመርጠው ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

ክፍሎቹም በእጣ የማውጣት ዘዴ የተመረጡበት ምክንያት ለሁሉም ክፍሎች እኩል እድል ለመስጠት ታስቦ ነው። በዚሁ መሰረት ከትግራይ ወልደ ንጉስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ አዴ ጉዶም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ ጥላሁን ይግዛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ መሆኒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ እጣ በማውጣት የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። ከኦሮሚያ ክልል አሲንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ ከሶኮሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ ከሰርቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎችን፣ ከጥቁር እንጪኒ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች እና ጉደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች እጣ በማውጣት የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። ከአፋር ክልል ከሰመራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 4 ክፍሎች፣ ከሎጊያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ ከገዋኔ 4 ክፍሎችና ከመልካ ሳዲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶት 5 ክፍሎች እጣ በማውጣት የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል። ከአዲስ አበባ ከጥቁር አንበሳ 5 ክፍሎች፣ ከድል በር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎች፣ ከደብረ ሰላም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5 ክፍሎችና ከኒውኤራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 5 ክፍሎች እጣ በማውጣት የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል።

ሰንጠረዥ አንድ ለ ፤ ከክልል አንጻር የት/ቤቶችና የተመረጡ ክፍሎች ብዛት

| ተ.ቁ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | አዲስ አበባ | | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | ት/ቤት | የክፍል ብዛት | |
| 2 | ሰመራ | 4 | አዴ ጉዶመ | 5 | አሲንዳቦ | 5 | ጥቁር አንበሳ | 5 | 19 |
| 3 | ሎጊያ | 5 | ጥላሁን ይግዛው | 5 | ሰርቦና ሶኮሩ | 5 | ድል በር | 5 | 20 |
| 4 | ገዋኔ | 4 | ወ/ሰንበት | 5 | ጉደር | 5 | ኒውኤራ | 5 | 19 |
| 5 | መልካ ሰዲና አዋሽ አርባ | 5 | መኮኒ | 5 | ጥቁር እንጪኒ | 5 | ደብረ-ሰላም | 5 | 20 |
| ድምር | 18 | | 20 | | 20 | | 20 | | 78 |

ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተመረጠው የክፍል ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል ነው፡፡ የክፍል ደረጃውም ምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም የተመረጠ ነው፡፡ ዘጠነኛ ክፍል በምክንያታዊ አመራረጥ ዘዴ የተመረጠበት አቢይ ምክንያትም የየክልሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ከተለያየ የክፍል ደረጃ ላይ መማር በመጀመራቸውና ከክልል ክልል የተለያየ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት በመኖሩ ምክንያት እነዚህ በልዩነት ቋንቋውን ሲማሩ የነበሩ 9ኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ ተመሳሳይ የአመለካከት፣ የፍላጎት እና የውጤት ደረጃ ላይ መድረስ ይችላሉ ተብሎ በተመሳሳይ መርሀ ትምህርትና መጽሀፍ እንዲማሩ መደረጉ ተማሪዎቹ በእኩል የችሎታ ደረጃ ላይ መገኘት ይችሉ እንደሆን በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ መፈተሹ ምቹ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህ የተመረጡት ክፍሎች በሙሉ በዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው፡፡

## 3.5 የተጠኚ ተማሪዎች የናሙና አወሳሰድ ዘዴ(Sampling Method)

የናሙና አወሳሰድን በተመለከተ ውስብስብ የእጣ ንሞናን በመጠቀም ናሙናዎችን ለመምረጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከውስብስብ የእጣ ንሞና ውስጥም የተራዘመ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን መጠቀም ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን የተራዘመ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ አድካሚና ጊዜን የሚወስድ ቢሆንም ከክልል፣ ከዞን፣ ከትምህርት ቤት፣ ከክፍል ደረጃ፣ ከቋንቋው ሁኔታ አንጻር ለናሙናነት የሚመረጡት ናሙናዎች ወካይነታቸው ከፍ እንዲል በማሰብ ነው፡፡ በዚህም የናሙና አይነት በርካታ የእጣ ናሙና ዘዴዎችን ለመጠቀም ተችሏል፡፡

ስለዚህም ከክልል እስከ ጥናቱ አባላት ድረስ የተከናወነው የናሙና አመራረጥ በተቻለ መጠን ማእከላዊነቱን ጠብቆ በእድል ሰጪ ንሞና መሰረት የተከናወነ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አጥኝው በዚህ ዘዴ በርካታ እድል ሰጪ የንሞና ዘዴን ለመጠቀም የተገደደበት አቢይ ምክንያት ለሁሉም ተጠኝዎች እኩል ዕድል ለመስጠትና የሚሰበሰበው መረጃ ትክክለኛ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ ከክፍል ተማሪዎች በሚመረጡበት ጊዜም በአማርኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎችን ከክፍል ውስጥ በማስወጣት በቋንቋው ኢ-አፈ-ፈት ከሆኑት ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ ተማሪዎቹ በሚመረጡበት ጊዜ ከጾታ፣ ከመኖሪያ ቦታ(ገጠርን ወይንም ከተማን) አንጻር ለብቻ ለብቻ በመመደብ ስብጥራዊ ወካይነታቸውን በጠበቀ መልኩ የተማሪዎችን ስም በፊደል ቅደም ተከተል

መሰረት ከተመዘገበ በኋላ የስርአታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተጠኚ ተማሪዎቹ ከየክፍሉ ተመርጠዋል።

### 3.5.1 በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ መረጃ ሰጪዎች ብዛት (population of the study)

አንድን ጥናት ለማከናወን ምን ያህል የናሙና ብዛት ያስፈልጋል? ለሚለው ጥያቄ የናሙናውን ቁጥር የሚወስነው የጥናቱ አይነት፣ የምርምሩ ስልት፣ የገንዘብ ሁኔታ፣ የጥናቱ አካላይ ብዛት፣ የጥናቱ አስፈላጊነት የመሳሰሉት በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ ተጠኝዎች ብዛትን ይወስናሉ። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚመረጡ የተጠኚዎች ብዛት የጥናቱን አላማ፣ ያለውን የገንዘብ ችግርና አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የናሙና ብዛቱ ተወስኗል። ይሄም ሲባል የተመረጠው የናሙና ብዛት ትንሽ ነው፤ ማለት ሳይሆን ከምርምር ስልትና ከጥናቱ አስፈላጊነት አንጻር በተቻለ መጠን ተገቢውን ውክልና ሊሰጡ የሚችሉ ተጠኝዎች ተመርጠዋል።

በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ ተጠኝዎችን በተመለከተ ያለው(2009) ምርምሩ ተዛምዷዊና ጥናቱ በርካታ አካላይን ያቀፈ ከሆነ በጥናቱ ውስጥ መታቀፍ የሚገባቸው የጥናቱ አካላይ ቁጥር ከ30 የናሙና ብዛት ማነስ የለባቸውም ይላሉ። በጥናቱ ሁለት የሚወዳደሩ ቡድኖችን ለማጥናት ከሆነ በእያንዳንዱ ቡድን የሚሳተፍ የናሙና አባላት ብዛት ከመቶ ባያንሱ ይመረጣል። ተመራማሪው በርካታ ነጻ ተለዋዋጮችን ለማጥናትና ጥናቱ የሚካሔድባቸው ቡድኖች ብዛት ከሁለት በላይ የሚከፈሉ ከሆነ በእያንዳንዱ ንኡስ ቡድን ውስጥ የሚካተቱ የናሙና ብዛት ከ20-50 እንዲሆኑ ይጠበቃል(Macmillan and schumacher, 2006 እና ያለው እንዳወቀ 2009)።

በሌላ በኩልም ገንዘብ የናሙና መጠኑን የሚወስነው አንዱ ክፍል ነው። ጥናቱን ለማከናወን የሚበቃ በቂ ገንዘብ ካለ በርካታ ቁጥር ያለው ናሙና መጠቀሙ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ገንዘብ ከሌለ ግን አቅም የሚችለውን ያህል ናሙና ወስዶ ጥናቱን ማካሔድ ነው። ስለዚህ ገንዘብ ከሌለ ምርምር አይካሄድም ማለት አይደለም በማለት ምሁራኑ ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚጠኑት ተለዋዋጮች ብዛት ያላቸው ስለሆነና የናሙናዎቹ ብዛት ሲከፋፈል

እንዳያንስ አጥኚው በተቻለ መጠን የናሙናውን ብዛት ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡ ስለዚህም በዋናነት የጥናቱን ትክክለኝነት ለመጨመር ሲባል የናሙናው መጠን ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት በጥናቱ ላይ የሚሳተፉት የጥናቱ አካላዮችን በተመለከተ በክልል ደረጃ የሚመረጡት ተጠኚዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ባሕሪ ስላላቸው ከየክልሉ ስፋት አንጻር በርካታ ቁጥር ያለው ተጠኚ(መረጃ ሰጪ) መውሰዱ አስፈላጊ ሆኖ ባይገኝም ነገር ግን ያንን ለመጠበቅ በተወሰነ ደረጃ ጥረት ተደርጓል፡፡ በየክልሉ ካለው የተማሪ ብዛት አንጻር ሙሉ በሙሉ በመቶኛ ተሰልቶ ያለመውሰዱ በጥናቱ ላይ የሚያስከትለው የጎላ ችግር ባለመኖሩ ነው፡፡ በMacmillan and schumacher (2006) እና ያለው እንዳወቀ (2009) አገላለጽ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ናሙናዎች አስር ሰዎችም ተወሰደ፣ ከመቶ ሰዎችም የሚገኘው መረጃ ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለዚህ ከአስር ሰዎች መረጃ ወስዶ ትንታኔ መስጠት ይቻላል ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለጥናቱ ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች አንጻር በየክፍሉ ካለው የተማሪ ስብጥር አንጻር ናሙናዎቹ ተመርጠዋል፡፡

የናሙና አመራረጡም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ ከተመረጡ በኋላ በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚገኙ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ሴክሽኖችን በቁጥራቸው መሰረት በመመዝገብ በእጣ ማውጣት ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ከዛም በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የተማሪዎች ብዛት በአማካኝ 60 አካባቢ ስለሆነ ከብዛታቸው አንጻር በማስላት ናሙናዎችን መምረጥ ተችሏል፡፡ ይሄውም በተመረጠው ክፍል እየተማሩ ከሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ ፆታዊና አካባቢያዊ ስብጥርን በመጠበቅ ከተለዩ በኋላ 17 በመቶ የሚሆንት ስርአታዊ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ ስለዚህ በናሙና አወሳሰድ በኩል የሚስተዋለውን ችግር በዚህ አግባብ ለመቅረፍ ተሞክሯል፡፡

ከዚህም አንጻር በክልሎቹ በራሳቸው ውስጥ ካለው ተመሳሳይ ባሕርይ አንጻር በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ የተጠኚዎች(የመረጃ ምንጮች) ብዛትና የጥናቱ አካላዮች ከዚህ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የተመረጡ ናቸው፡፡ ለምሣሌ በየክልሉ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለማየት ያህል የየክልሉ ስርአተ ትምህርት አዘገጃጀት፣ የስራ ቋንቋ ሁኔታ፣ የመምህራን አሰለጣጠን ሁኔታ፣ የክፍለ ጊዜ አመዳደብ ሁኔታና የመጻህፍት አዘገጃጀት ሁኔታ የአንዱ ክልል ከራሱ ዞኖችና ትምህርት ቤቶች አንጻር ሲታይ ተመሳሳይና ልዩነት የሌለው ነው፡፡ ልዩነት የሚኖረው ከክልሉ ውጪ ካሉ ትምህርት ቤቶችና ዞኖች አንጻር ሲታይ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ የናሙና ቁጥርን ለመወሰን የተቻለው ካለው የባህሪ ተመሳስሎና ልዩነት በመነሳት ነው፡፡ ለምሳሌ በትልቅ ድስት

የተፈላ ወጥም ሆነ በትንሽ ድስት የተፈላ ወጥን ለመቅመስ ከተፈለገ የሁለቱንም ድስቶች ውስጥ ያለውን ወጥ በደንብ አማስሎ ከተዋሀደ በኋላ በማማሲያ ጫፍ ነካ ተደርጎ ቢቀመስ የትልቁም ሆነ የትንሹ ድስት ወጥ ውክልናው ተመሳሳይ ነው(ያለው እንዳወቀ 2009)፡፡ ይህም ማለት ከትልቁ ድስት የተቀመሰው ውክልናው ትልቁን ድስት ነው፡፡ እንደዚሁም ከትንሹ ድስት የተቀመሰው ውክልናው ትንሹን ድስት ነው፡፡ የግድ ከትልቁ ድስት ብዙ ወይም ከትንሹ ድስት ደግሞ ትንሽ ወስዶ መቅመስን አይጠይቅም፡፡ ከዚህ አንጻር ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ከየክልሉ የሚወሰደው ናሙና በተቻለ መጠን ወደ እኩል ደረጃ ወይም ተቀራራቢ ቁጥር ቢኖራቸው በጥናቱ ላጥ የሚያመጣው የጎላ ችግር ባለመኖሩ የናሙና አወሳሰዱን ተገቢ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ለሙከራ ጥናቱና ለዋናው ጥናት የተመረጡ ናሙና መረጃ ሰጪዎች የሚከተለውን ይመስላል፡፡

#### 3.5.1.1 ለሙከራ ጥናቱ የተመረጡ መረጃ ሰጪዎች

ከላይ በ3.6 ተራ ቁጥር ላይ በቀረበው ዝርዝር ሁኔታ መሰረት በማበልጸጊያ ጥናቱ ወቅት ከየክልሉ አንድ አንድ ዞን በመምረጥ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡ ከተመረጡት ዞኖች ውስጥም ከትግራይ ማእከላዊ ዞን ከአቢያዲ ራስ አሉላ አባነጋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩ 74 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ከኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ደገምንና ኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚማሩ 90 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን፣ ከአፋር ክልል ዞን አራት ከልዋን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚማሩ 65 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በድምሩ 229 ተማሪዎች አመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠው ከነዚህ ውስጥም ትክክለኛ መረጃ በሰጡት 222 ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ ለዋና ጥናቱ በግብአትነት ያገለገለ መረጃ ማግኘት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ከአዲስ አበባ ቤተልሄም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለቅድመ ሙከራ ጥናቱ 50 ተማሪዎችን በመጠቀም የመጠይቆችንና የፈተናውን ደረጃ አስተማማኝነትና ተገቢነትን ለመለካት ያገለገለ ስለሆነ በሙከራ ጥናቱ ወቅት ከአዲስ አበባ ተጨማሪ መረጃ መውሰድ አላስፈለገም፡፡ ስለዚህ በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛትና ክልላዊ ስብጥር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሰንጠረዥ ሁለት፤ ከክልሎች አንጻር የሙከራ ጥናቱ የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛት

| ፆታ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ወንድ | 33 | 50.8 | 37 | 50 | 46 | 51 | 116 | 50.5 |
| ሴት | 32 | 49.2 | 37 | 50 | 44 | 49. | 113 | 49.5 |
| ድምር | 65 | 100 | 74 | 100 | 90 | 100 | 229 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዥ ሁለት ላይ የቀረበው ከየክልሎቹ የተወሰዱ መረጃ ሠጪ ተማሪዎች ከተወሰዱበት ክልልና ጾታ አንጻር የናሙና ብዛትንና ለዋናው ጥናቱ በግብአትነት ያገለገሉትን የሚያሳይ ነው፡፡

በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች አካባቢያዊ ስብጥር ሲታይ ደግሞ ከገጠር መጥተው ትምህርታቸውን ከሚማሩት ተማሪዎች ተመርጠው መረጃን በትክክል የሞሉት 113 ሲሆኑ የከተማ ተማሪዎች ደግሞ 109 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 222 ተማሪዎች ተመርጠው የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ ለዋና ጥናቱ በግብአትነት አገልግሏል፡፡ ከአካባቢያዊ የስብጥር ሁኔታ አንጻር በናሙናነት የተመረጡ የተጠኚ ተማሪዎችን በተመለከተ ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሶስት ፤ ለሙከራ ጥናቱ አካባቢ ስብጥርን መሰረት በማድረግ በናሙናነት የተመረጡ መረጃ ሰጪ ተማሪዎች

| አካባቢያዊ ሁኔታ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ገጠር | 27 | 48.6 | 35 | 46.8 | 51 | 58.6 | 113 | 50.9 |
| ከተማ | 37 | 57.8 | 37 | 51.4 | 35 | 41.4 | 109 | 49.1 |
| ድምር | 64 | 100 | 72 | 100 | 86 | 100 | 222 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ እንደቀረበው ለሙከራ ጥናቱ ከየክልሉ በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች ብዛትን የሚያሳይ ሲሆን ቁጥሩ የተለያየ መጠን እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ዞኖቹ ከተመረጡት ትምህርት ቤት ውስጥ በየክፍሉ ከሚገኙ የተማሪዎች ብዛት አንጻር ተመጣጣኝነቱን በጠበቀ መልኩ በመመረጡ ነው፡፡ ከላይ በተገለጸው መሰረት ለናሙና ጥናቱ መረጃ ሰጪዎች ተመርጠው የሙከራ ጥናቱ ተከናውኖ የተገኘው መረጃ ለዋናው ጥናት በግብአትነት አገልግሏል፡፡

ከላይ ለቀረበው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ መሰረት የሆነውና በግብአትነት ያገለገለው የቅድመ ሙከራ ጥናቱ ወቅት የተከናወነው የመረጃ ፍተሻ ተግባር ነው፡፡ ይሄውም በቅድመ ሙከራ ጥናቱ ወቅት ከአዲስ አበባ ቤተልሄም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 50 ተማሪዎችን በመጠቀም የናሙና መጠኑን ለመወሰንና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለመፈተሸ መሰረት ሆኖ አገልግሏል፡፡

### 3.5.1.2 የዋና ጥናቱ ናሙና መረጃ ሰጪዎች

ከላይ በ3.6 ተራ ቁጥር ላይ በቀረበው ዝርዝር ሁኔታ መሰረት በዋናው ጥናት ውስጥ እንዲካተቱ የተመረጡት መረጃ ሰጪዎች ጥናቱ ከሚከናወንባቸው ክልሎች ውስጥ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲሆን ይህም ከየክልሉ እንደ መረጃው አስፈላጊነት አራት አራት ትምህርት ቤቶች በእድል ሰጪ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ውስጥ እጣ የማውጣት ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ ስብጥራዊ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን በመጠቀም ከትግራይ ክልል ወንድ 98 ሴት 100 በደምሩ 198 ተማሪዎች፣ ከኦሮሚያ ወንድ 100 ሴት 100 በደምሩ 200 ተማሪዎች፣ ከአፋር ክልል ወንድ 96 ሴት 96 በደምሩ 192 እና ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ወንድ 103 ሴት 77 በደምሩ 200 ተማሪዎች በአጠቃላይ ከሁሉም ክልሎች የተመረጡ ተማሪዎች ድምር 790 ሲሆኑ እነዚህም ተማሪዎች በእድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ጾታዊ ተዋጽኦን በተመለከተ ስብጥራቸውን ጠብቆ 393 ሴት እና 397 ወንድ ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆን ባጠቃላይ 790 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡

ሰንጠረዥ አራት ፤ ለዋና ጥናቱ በናሙናነት የተወሰዱ የተማሪዎች ብዛትና ክልላዊ ስብጥር

| ፆታ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | አዲስ አበባ | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ወንድ | 96 | 50 | 98 | 49.5 | 100 | 50 | 100 | 50 | 397 | 50.25 |
| ሴት | 96 | 50 | 100 | 50.5 | 100 | 50 | 100 | 50 | 393 | 49.75 |
| ድምር | 192 | 100 | 198 | 100 | 200 | 100 | 200 | 100 | 790 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ አራት ላይ የቀረበው ከየክልሎቹ የተወሰዱ መረጃ ሰጪ ተማሪዎችን በተመለከተ ከክልልና ከጾታ አንጻርና ከናሙና ብዛት አንጻር የተወሰደን የናሙና መጠንን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም የተመረጡ ተማሪዎችን በተመለከተ ጾታዊ ስብጥራቸውን ከመጠበቅ ጎን ለጎን የከተማና የገጠር ስብጥራቸውም(stratum) እንዲጠበቅ ለማድረግ ከየክልሉ አዲስ አበባን ሳይጨምር ከአፋር ክልል 81 ተማሪ የገጠር እና 111 ተማሪ የከተማ፣ ከኦሮሚያ ክልል 107 ተማሪ የገጠር እና 93 ተማሪ የከተማ እና ከትግራይ ክልል 92 ተማሪ የገጠር እና 106 ተማሪ የከተማ እንዲሆን በድምሩ 280 ተማሪ ከገጠር እና 310 ተማሪ ከከተማ በማድረግ ተመርጠዋል። ይሄንን ሲባል የተመረጡ ተማሪዎች ቁጥር እንደ ተማሪዎቹ ልዩ ባህርይ ብዛት አንጻር ስብጥራቸውን እንዲጠብቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

ሰንጠረዥ አምስት፤ ለዋና ጥናቱ ተጠኝዎች የተወሰዱበት የቦታ ወይም የአካባቢ ስብጥር

| አካባቢ ያዊ ሁኔታ | አፋር | | ትግራይ | | ኦሮሚያ | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ገጠር | 81 | 42.2 | 92 | 46.47 | 107 | 53.5 | 280 | 47.46 |
| ከተማ | 111 | 57.8 | 106 | 53.53 | 93 | 46.5 | 310 | 52.54 |
| ድምር | 192 | 100 | 198 | 100 | 200 | 100 | 590 | 100 |

ከላይ ከሰንጠረዥ አምስት ላይ መመልከት እንደሚቻለው አዲስ አበባን ሳይጨምር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ከሚያስተምሩ በሶስቱ ክልሎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በናሙናነት የተወሰዱ የገጠርና የከተማ ተማሪዎች የናሙና ብዛትን የሚያሳይ ነው፡፡

## 3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

### 3.6.1. የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን በተመለከተ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይሄውም የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለት አይነት አዘገጃጀትን ተከትሎ የቀረበ ነው፡፡ አንደኛው አይነት የጽሁፍ መጠይቅ ዝግ ጥያቄ ሲሆን እሱም ባለ አምስት የደረጃ ድልድል መለኪያ መስፈርት (five point Likert Rating scale) የተዘጋጀ ነው፡፡ ይሄም የመጠይቅ አይነት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርትና ለቋንቋው ያላቸውን ፍላጎትና አመለካከትን ለመለካት የሚያገለግል ነው፡፡ መጠይቁም ሲሞላ መላሾቹ ከቀረቡላቸው አማራጮች መካከል የነሱን ሀሳብና እምነት ሊያመለክት ወይም ሊወክል ይችላል ያሉትን በመምረጥ እንዲመልሱ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

ውስን የጽሁፍ መጠይቅ አዘገጃጀትን በተመለከተ ባለሶስት፣ ባለአምስትና ባለሰባት ስፍርታዊ መመዘኛዎችን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ባለ ሶስት ስፍርታዊ የሚባሉት ሶስት አማራጮችን የያዙ ሲሆን ባለአምስት ስፍርታዊ መለኪያዎች የሚባሉት አምስት አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ ባለሰባት ስፍርታዊ የሚባሉት ደግሞ ሰባት አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ ይሁንና ፍላጎትንና

አመለካከትን ለመለካት በይበልጥ አመቺ የሚሆነው ባለአምስቱ ስፍርታዊ መለኪያ እንደሆነ ከድረ-ገጽ የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡ እንደ Gardner,(1985) ባለሰባት ስፍርታዊ የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ ጥያቄዎችን በተጨማሪነት አቅርበዋል፡፡ ከባለሶስቱና ከባለ አምስቱ ስፍርታዊ መለኪያዎች የፍላጎትና የአመለካከትን ተላውጦዎችን ከመለካት አንጻር ሲታይ ግን ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑንም ከሀሳባቸው ጋር አያይዘው ምሁራኑ ያስገነዝባሉ(Buros, 1959 and 1979; Gardner,1985 and Mitcheil,1985):: Careswell(2012) ባለ አምስት ስፍርታዊ መለኪያን መሰረት በማድረግ አጠቃቀሙ ምን እንደሚመስል በምሳሌነት አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ለፍላጎትና ለአመለካከት መለኪያነት እንዲያገለግል ባለ አምስት ስፍርታዊ መመዘኛ መለኪያን በማዘጋጀት መረጃን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ አዘገጃጀቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

I. ባለ አምስት ስፍርታዊ አዎንታዊ የፍላጎት መለኪያ(መመዘኛ)

1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር እወዳለሁ፡፡

| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |

2. የአማኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር ያስደስተኛል፡፡

| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |

በምሳሌ ሁለት ላይ የቀረቡት ባለ አምስት ስፍርታዊ የፍላጎት መለኪያ ሲሆን አዎንታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ለአማራጮቹ የቁጥር አሰጣጡ ከአምስት ጀምሮ በቅደም ተከተል እስከ አንድ ድረስ ይሆናል፡፡ አሉታዊ ጥያቄ ከሆነ ደግሞ ከአንድ ጀምሮ እስከ አምስት ደረስ ይሆናል፡፡

ምሳሌ 2 . ባለ አምስት ስፍርታዊ አሉታዊ የፍላጎት መለኪያ

1. የአማኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር አልፈልግም ፡፡

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |

2. የአማኛ ቋንቋ ትምህርትን በክፍለ ጊዜ ተገኝቼ ባልማር እመርጣለሁ ፡፡

1 2 3 4 5

በጣም እስማማለሁ እስማማለሁ አልወሰንኩም አልስማማም ፈጽሞ አልስማማም

II. ባለ አምስት ስፍርታዊ የአመለካከት መለኪያ(መመዘኛ)

ለምሳሌ አዎንታዊ ጥያቄዎች

1. አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የህብረ ብሄር ቋንቋ ስለሆነ በትምህርትነት መሰጠት አለበት ፡፡

5 4 3 2 1

በጣም እስማማለሁ እስማማለሁ አልወሰንኩም አልስማማም ፈጽሞ አልስማማም

2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ ትምህርት ነው፡፡

5 4 3 2 1

በጣም እስማማለሁ እስማማለሁ አልወሰንኩም አልስማማም ፈጽሞ አልስማማም

ለምሳሌ አሉታዊ የአመለካከት ጥቂዎች

1. አማርኛ ቋንቋ ለእኔ የተንዛዛና አሰልቺ ትምህርት ነው፡፡

1 2 3 4 5

በጣም እስማማለሁ እስማማለሁ አልወሰንኩም አልስማማም ፈጽሞ አልስማማም

2. አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የህብረ ብሄር ቋንቋ ሆኖ በትምህርትነት መሰጠት የለበትም

1 2 3 4 5

በጣም እስማማለሁ እስማማለሁ አልወሰንኩም አልስማማም ፈጽሞ አልስማማም

በሁለተኛ ደረጃ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ አዘገጃጀት ደግሞ ልቅ /ነጻ/ ጥያቄ ሲሆን መላሾቹ ነጻ ሆነው በተነሳው ጥያቄ ላይ የራሳቸውን አመለካከት፣ ፍላጎትና አስተሳሰብን እንዲገልጹ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹም መጠይቁን እንደ ጥያቄው ሁኔታ በመመሪያው መሰረት እየሞሉ ወይም መልስ እንዲሰጡ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የጽሁፍ መጠይቆቹም ሲዘጋጁ ሌሎች ሊቃውንቶች ያዘገጁትን የአመለካከትና የፍላጎት መለኪያ

መጠይቆችን በማየት፣ የተለያዩ ድርሳናትን በማንበብና ቀደም ብሎ ለተመሳሳይ ጥናት ተዘጋጅተው ያሉ መጠይቆች ላይ ማስተካከያ በማድረግና አንዳንዶቹንም ለጥናቱ እንደ አመቺነታቸው በቀጥታ በመውሰድ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ስለዚህም የአመለካከትንና የፍላጎት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቅ በሚዘጋጁበት ወቅት በአሁኑ ሰአት በስራ ላይ እየዋለ ያለውን ለዚህ ጥናት አመቺ እንዲሆን አድርጎ በማሻሻልና እንዳለ በመውሰድ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ አንጻር የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ መጠይቆች ሲዘጋጁ የBuros (1959); Carig (1979); Mitcheil (1985) እና Callahan (1988) ለአመለካከትና ለፍላጎት መለኪያነት ሲባል የተዘጋጀ የመመዘኛ የጽሁፍ መጠይቅ አዘገጃጀታቸው እንዴት እንደሆነ በማየት ለሙከራ ጥናቱ በግብአትነት ለመጠቀም ተችሏል፡፡ ይሄም ለዚህ ጥናት የሚዘጋጀው የፍላጎትና የአመለካከት የመመዘኛ መጠይቅ ምን መሆን እንዳለበት ለመወሰን ምሁራኑ ያቀረቧቸውን ንድፈ-ሀሳቦች መሰረት በማድረግ ለማዘጋጀት ተችሏል:: በተለይም ቋንቋን በሚመለከት የGardner (1985) የመመዘኛ ጥያቄዎችን ለጥናቱ አስፈላጊ በመሆናቸው የተወሰኑትን እንዳሉ በመውሰድና የተወሰኑትን ደግሞ ከጥናቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በማስተካከል ተዘጋጅቷል፡፡

መጠይቁ የተዘጋጀው በአማርኛና በኦሮሚኛ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት በተደረገ የቅድመ ሙከራ ጥናት በኦሮሚያ፣ በአፋርና በትግራይ ክልል ለሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ የተዘጋጀውን መጠይቅ ተልኮላቸው በአፋርና በትግራይ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ የተዘጋጀውን መጠይቅ አንብበው ለመረዳት ሲችሉ ነገር ግን በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች አንብበው ለመረዳት ቀርቶ ለማንበብም እንኳን ሲቸገሩ ተስተውለዋል፡፡ ስለዚህ ከመጠይቁ አላማ አንጻር ተማሪዎቹ መልስ በሚሠጡበት ጊዜ ጽሁፉን በደንብ አንብበውና ተረድተው መሆን ስላለበት ለኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መጠይቁን በኦሮሚኛ ቋንቋ ማዘጋጀትን የግድ ብሏል፡፡ ስለዚህም የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ መጠይቁ በኦሮሚኛ ቋንቋ ተዘጋጅቷል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁን የተቀባይነት ደረጃ ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሚያስተምሩ የስነልቦና ሊቃውንት ለሆኑት ሁለት ምሁራንና እንዲሁም ለቋንቋ ሊቃውንት ለሆኑት ሁለት ምሁራን በማሳየት ዳግም በማስተካከል የተቀባይነት ወይም ተገቢነት ደረጃውን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡

የጽሁፍ መጠይቅ መመዘኛ አስተማማኝ የሚሆንበትን ደረጃና የትክክለኛነት ደረጃን በተመለከተ ያለው እንዳወቀ (2001) እንዳቀረበው ተመራማሪው የሚያጠናው ባህሪ ተጠኚዎች ለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አመለካከት፣ ዝንባሌና ፍላጎትን የመሳሰሉትን የስብእና(personality) ነክ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የሚገኘው የአስተማማኝነት መጠን ቢያንስ እስከ 0.65 ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ይላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተመራማሪው የሚያጠናው ነገር አዕምሮአዊ(Cognitive) ከሆነና የተጠኚውን የመማር ችሎታና ወይም እውቀት ለመለካትና አጥኚው ለተጠኚዎች ምልመላና ድልደላ ለመስጠት ወይም ሌሎች ጠቃሚ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ከሆነ የመለኪያ አስተማማኝነት ከ0.90 ማነስ የለበትም ይላል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ተመራማሪዎች በሚገኘው ጥናት መረጃ ላይ ተመርኩዞ ውሳኔ ለመስጠት፣ ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ካልሆነና የመለኪያው አገልግሎት ሰብእና ነክ ባህሪያትን ለመለካት ከሆነ የአስተማማኝነት መጠን እስከ 0.55 ዝቅ ቢል ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ለአእምሮአዊ መለኪያነት የሚያገለግል ከሆነ ደግሞ እስከ 0.70 ዝቅ ቢልም ብዙም ችግር የለውም በማለት ያቀርባሉ፡፡ Craig (1979) የስራ ፍላጎትን ለመለካት የሚቀርብ የጽሁፍ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃ የሚያሳየው ውጤት በ0.60 እና 0.70 መካከል ላይ የሚገኝ ከሆነ መጠይቁ አስተማማኝ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የተዘጋጀው የአመለካከትና የፍላጎት መለኪያ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃ ኩደር ሪቻረድሰንና የጉት ማንን ስልት-ትወራ ሂሳባዊ ቀመርን በመጠቀም ተሰልቶ ሲታይ የአስተማማኝነት ደረጃው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሰንጠረዥ ስድስት ፤ የአመለካከትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቆች የአስተማማኝነት ደረጃ በክሮምባክ አልፋ**

| የተዘጋጀበት ቋንቋ | የመመዘኛ መሳሪያዎች | የጥያቄዎች ብዛት | ክሮምባክ አልፋ |
|---|---|---|---|
| አማርኛ | የፍላጎት | 18 | .83 |
| | የአመለካከት | 16 | .82 |
| ኦሮሚኛ | የፍላጎት | 18 | .81 |
| | የአመለካከት | 16 | .80 |

ከላይ በሰንጠረዥ ስድስት ላይ ማየት እንደሚቻለው የፍላጎት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃ 0.826 ሲሆን፤ የአመለካከት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቁ የአስተማማኝነት ደረጃው ደግሞ 0.818 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ ምሁራን ከቀረበው ገለጻ አንጻር ሲታይ ለዚህ ጥናት የተዘጋጀው የአመለካከትና የፍላጎት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቅ በከፍተኛ ደረጃ አስተማማኝ መሆኑን የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ ያረጋግጣል፡፡

የተዘጋጀው የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋና በኦሮሚኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ነው፡፡ በሁለቱም ቋንቋ የተዘጋጀው መጠይቅ የትርጉም ልዩነት እንዳያመጣ በማሰብ በአማርኛ የተዘጋጀውን ወደ ኦሮሚኛ እና በኦሮሚኛ የተዘጋጀውን ደግሞ ወደ አማርኛ ዳግም በመተርጎምና በማስተርጎም የማመሳከርና የማስተካከል ስራ ተሰርቷል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ቋንቋዎች በተዘጋጁ መጠይቆች መካከል ምንም የትርጉም ልዩነት እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በናሙና ጥናቱ ወቅትም በኦሮሚኛ የተዘገጀውን መጠይቅ የአስተማማኝ ደረጃን በኩደር ሪቻርድ ሰን 20 እና 21 ቀመር መሰረት በማስላት የፍላጎት መለኪያው ውጤት 0.812 የመጣ ሲሆን፤ የአመለካከት መለኪያ ጥያቄው ደግሞ .803 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሄም በአማርኛ ከተዘጋጀው መጠይቅ ጋር ሲነጻጸር ጉልህ የሆነ ወይም ትርጉም ያለው ልዩነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ለአመለካከትና ለፍላጎት መለኪያነት የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ ውስጣዊ አስተማማኝነትን (Internal Consistacy of the reliability) በተመለከተ የክሮንባች አልፋም (Crombach Alpha) ሆነ በኩደር ሪቻርድ ሰን 20 እና 21 የአስተማማኝ መለኪያ ቀመር መሰረት የተገኘው ውጤት .803 አስከ .826 ባለው መጠን ስፋት ውስጥ መሆኑ በቅድመ ሙከራ ጥናቱና ከሙከራ ጥናቱ በኂላ በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ የፍላጎትና የአመለካከት መመዘኛ የጽሁፍ መጠይቆች ከመስፈርት ተኮርና ከቲዎሪ ተኮር ትክክለኝነት አንጻር ትክክኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 3.6.2 ቡድን ተኮር ውይይት

ይሄም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በተቻለ መጠን ተገቢነቱን እና ትክክለኛነቱን የጠበቀ የመወያያ ርእሰ ጉዳዮችን 13 የሚሆኑ መነሻ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብለው ለተመረጡት ወይም ለተጋበዙት መምህራንና ተማሪዎች በማቅረብ ከነሱ ጋር

ውይይት በማድረግ መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ ነው፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ወቅትም ከ5-8 የሚደርሱ ተሳታፊዎችን በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን በመጋበዝ ውይይቱ ተከናውኗል፡፡ ይሄንን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት መሰብሰብ ያልተቻለውን መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል ተግባር ላይ የዋለ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አማካኝነት በውይይቱ ላይ እንዲሳተፉ የተመረጡት መረጃ ሰጪ ተወያዮች አመራረጥን በተመለከተ በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ርዕሳነ መምህራንን፣ የትምህርት ክፍል ተጠሪዎችን፣ ከሶስት ያላነሱ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችንና ትምህርቱን እያስተማሩ ያሉ መምህራንን ግኝታዊ(Convenience) የናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል፡፡ ለውይይቱ የተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ከትግራይ ክልል መምህራንና ተማሪዎች መምህራን 12 ተማሪዎች 6 በድምሩ 18 ከሚሆኑ፣ ከኦሮሚያ 12 መምህራን ተማሪዎች 8 በድምሩ 20 ስልሳ ከሚሆኑ ከአፋር ክልል 11 መምህራን 6 ተማሪዎች በድምሩ 17 ከሚሆኑ መረጃ ሠጪዎች አጠቃላይ ድምር 55 ተመርጠው ባሉበት ትምህርት ቤት በሚደረግ ውይይት ላይ እንዲገኙ በመጋበዝ ውይይቱ ተከናውኖ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይሄም ተግባር የተከናወነው ለመወያያ የተዘጋጀውን ርዕስ ጉዳይ ለተወያዮቹ በማቅረብና ተወያዮቹ ያለምንም ገደብ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ያነሷቸውን ርዕሰጉዳዮችና የደረሱበትን የጋራ ሀሳብ በመመዝገብ ነው፡፡ የውይይቱ ርእሰ ጉዳይም በውስጡ ያካተታቸው ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው ተሳትፎና የሚያስመዘግቡት ውጤት፣ ለቋንቋውና ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና ቋንቋውን ለመናገርና ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል፣ በክፍለ ጊዜው ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎና የተማሪዎች በክፍለ ጊዜው የመገኘት ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከተወያዮቹ ጋር የሃሳብ ተራክቦ በማድረግ መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ ነው፡፡ በተለይም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለውን የውጤት፣ የአመለካከትና የፍላጎት ልዩነትን በተመለከተ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ልዩነት ካለም በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እየተጠቀሙበት ያለውን ዘዴና የመጣውን ለውጥ አስመልክቶ በቂ የሆነ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በአጠቃላይ ይሄንን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን በመጠቀም በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ለመሰብሰብ አዳጋች የሆነውን ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በተለይም ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ የሚሳዩትን ተሳትፎና ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ውጭ

ያለውን ነባራዊ ሁኔታን በተመለከተ ከመምህራንና ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውሎ ተፈላጊ የሚባል መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ ነው::

### 3.6.3. የችሎታ መመዘኛ ፈተና

የተማሪዎች የትምህርት ምዘና ውጤት ለመለካት ሲባል የሚሰበሰበው መረጃ ስምንተኛ ክፍልን ያጠናቀቀና ዘጠነኛ ክፍል የደረሰ ተማሪ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ሊኖረው የሚገባውን መሰረታዊ ችሎታና እውቀትን መለካት የሚችልና ደረጃውን የጠበቀ ፈተና ተዘጋጅቶ የተማሪዎችን ችሎታ መመዘን ተችሏል። ፈተናው ሲዘጋጅም በየደርጃው ያለውን የሀገሪቱን ስርአተ ትምህርት መሰረት ያደረገ ሆኖ ቢያንስ አንድ ዘጠነኛ ክፍል የደረሰ ተማሪ ሊያውቅ ይገባል ተብሎ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረበውን አላማ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

ፈተናው በውስጡ ሶስት የፈተና አቀራረብ አይነቶችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የችሎታ መመዘኛ ፈተናው ሲዘጋጅም Weeden (2002) እና Race (2005) ባቀረቡት ሀሳብ መሰረት ለተማሪዎች የሚዘጋጁ የምዘና ፈተና አይነቶች ያሉባቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በማየትና ከግምት ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። የምዘና ፈተናው አቀራረብም ምርጫ፣ አጭር መልስ ስጡ የሚልና በራስ አባባል ግለጹና ጻፉ በሚል መልኩ የቀረበ ነው።

የምዘና ፈተናው ከይዘት አንጻር ሲታይ ይዘት ተኮር ትክክለኝነትን (content validity) ከግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀ ነው። በይዘቱም ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ሰዋስውን፣ ቃላትን፣ ድርሰትንና አንብቦ መረዳትን የሚመለከቱ ሲሆኑ ከ6ኛ-8ኛ ክፍል ያለውን የትምህርት ይዘትና አላማን መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹን በማመጣጠን ለማዘጋጀት ተችሏል። በተጨማሪም የምክንያትና ውጤት ጥያቄዎችን እና የሀቅና የአስተያየት ጥያቄዎችንም ለማካተት ተችሏል። ስለዚህ ፈተናው በዋናነት የአንብቦ መረዳት ክሂልን፣ የጽህፈት ክሂልን፣ የቃላትንና የሰዋስው እውቀትን የሚጠይቅ ነው። የጥያቄዎቹም ቁጥር 32 ሲሆን ከላይ በቀረበው የይዘት አይነት ማዕከላዊነቱን ለመጠበቅ ጥረት ተደርጓል። ከላይ በተገለጸው መሰረት የችሎታ ምዘና ፈተና ይዘቶችን ለማመጣጠን በየደረጃው ያለውን ስርአተ ትምህርት መሰረት ያደረገ ሆኖ ለትምህርቱ የተመደበ የክፍለ ጊዜ ብዛትና የይዘት መጠን በመቶኛ በማስላት የጥያቄውን ብዛት በማስላት ተዘጋጅቷል።

ሰንጠረዥ ሰባት፤ የፈተና ዓይነት ዝርዝር

| ተራ ቁ. | የትምህርት ይዘት | የጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ሰዋስው | 10 |
| 2 | ቃላት | 8 (ምሳሌያዊ አነጋገርና ፈሊጥ በውስጡ ይዟል) |
| 3 | አንብቦ መረዳት | 5 |
| 4 | የጽህፈት | 5 |
| 5 | አስተያትና ህቅ | 4 |
| | ድምር | 32 |

ከላይ በሰንጠረዡ ሰባት ላይ ማየት እንደሚቻለው በፈተና ይዘትነት የቀረቡትን የምዘና ፈተና አይነቶችን ለማሳየት ያህል በቁጥር ተገልጾ ይቅረብ እንጂ በአንዱ ርእሰ ጉዳይ ውስጥ የሚገኝ የጥያቄ ይዘት የሌላኛውን ርእሰ ጉዳይ ይዘት እንዲያካትት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰዋስዋዊ ስርአቱን አስተካክለህ/ሽ ጻፍ/ጻፊ የሚለው ጥያቄ በሚዘጋጅበት ጊዜ ጥያቄዎቹ በዋናነት ሰዋስውንና የቃላት እውቀትን የሚጠይቁ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ የጽህፈትንና የንግግርን ችሎታን መመዘን የሚችሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት የተዘጋጀው ፈተና የማዳመጥ ክሂልን የሚጠይቅ ጥያቄ ማካተት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን የመናገርን ክሂል የሚመዝን ጥያቄ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ከ10 ጥያቄዎች በላይ በውስጡ ይዞ ይገኛል፡፡

ፈተናውን ለማዘጋጀት በመሰረትነት መጠቀም የተቻለው ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውን ስርአተ ትምህርት ነው፡፡ ዘጠነኛ ክፍል የደረሰ ተማሪ ቢያንስ ሊያውቃቸው ይገባል ተብሎ የሚታሰበውን መሰረታዊ ጉዳይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የማዳመጥ ክሂልንና በተወሰነ ደረጃ የመናገርን ክሂልን ለመመዘን ተብሎ ለብቻው የችሎታ መመዘኛ ፈተና ማዘጋጀት ያልተቻለው ፈተናውን ከማዘጋጀትና ከመፈተን አንጻር ጊዜንና ከፍተኛ ወጪና የሰው ሀይል ስለሚፈልግ የመመዘኛ ፈተናውን በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሞ ጥናቱን ለማከናወን አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የምዘና ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ውስጥ

ያለመካተታቸው በጥናቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የለም። ምክንያቱም በሌሎቹ ላይ የሚታየው የምዘና ውጤት በነዚህም የክህሎት ትምህርት ውጤት ላይ ሊንጸባረቅ ይችላልና ነው።

ፈተናው ሲዘጋጅ ከመለካትና ከመመዘን (Measurement and evaluation) አንጻር የ linn (2000)ን ውስንና ልቅ የፈተና አወጣጥ ጽንሰ ሀሳብን እንደተጨማሪ ግብአትነት በመጠቀም እያንዳንዱ ጥያቄና በጥያቄዎቹ ስር የሚገኙ አማራጮች ምን መምሰል እንዳለባቸው በማየትና ከዚህ አንጻር ተዘጋጅቶ ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት ታይቷል። በተዘጋጀው ፈተና ውስጥ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ፈተናው ከተከናወነ በኋላም ምን ያህል ተገቢና የመመዘን ብቃት (የመለካትና የመመዘን ችሎታ) ያላቸው መሆናቸውን በሂሳባዊ ስሌት በማስላት ጥሩ ፈተናና ጥሩ የፈተና አማራጮች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ዳግም መስተካከል ባለባቸው ጥያቄዎች ላይም የማስተካከል ስራ ተሰርቷል። በተለይም ክፍተት ያለባቸውን የጥያቄዎችን አማራጮች(distractor) በመለየት በፈተናው የጥያቄዎቹ አማራጮች ላይም ማስተካከያ ተደርጓል።

በተጨማሪም የፈተናውን ተገቢነትና ትክክለኝነት ለማወቅ ከሶስት ክልሎች (ከትግራይ፣ ከአፋር፣ ከኦሮሚያ) በቋንቋው ትምህርት በቂ ግንዛቤ ያላቸውንና በደረጃው ቢያንስ አምስት አመት የማስተማር ልምድ ያላቸውን ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በግኝታዊ(Convenience) የናሙና ዘዴ በመምረጥ የተዘጋጀውን ፈተና ከተገቢነት አንጻር እንዲመለከቱት በመስጠት ከመምህራኑ ተጨማሪ አስተያየት ተሰብስቧል። የመምህራኑ አመራረጥም የአገልግሎት ዘመናቸውን መሰረት በማድረግ አምስት አመትና ከዚያ በላይ እያስተማሩ ያሉና የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ የሆኑ ናቸው። መምህራኑ ፈተናውን አይተው አስተያየት እንዲሰጡ ለማድረግ የተመረጡበት ዋናው ምክንያት በመስኩ እያስተማሩ ካለው ልምድ በመነሳት ከተገቢነት አንጻር ለፈተናው ጥሩ አስተያየትና ግብአት ይሰጣሉ ተብሎ በመገመቱ ነው። በመምህራኑ ከተሰጠው አስተያየት በመነሳትም በፈተናው ላይ ዳግም የማስተካከል ስራ ተሰርቷል። ስለዚህ የፈተናውን ግልብ ትክክለኝነት (Face validity) ለማረጋገጥ ተችሏል።

የምዘና ፈተናውን መደበኛነት ለማየት ደረጃውን የጠበቀ ፈተና የማዘጋጀት ልምድ ላላቸው ለከፍተኛ ተቋም መምህራን በማሳየት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የምዘና ጥያቄውን ዳግመኛ

በማስተካከል የተቀባይነት ደረጃውን የማሳደግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ሃገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ፈተናውን ከተገቢነትና ከይዘት አንጻር እንዲያዩት በመስጠት ተገቢነቱን በድጋሚ እንዲታይ ተደርጎ የተሰጠ አስተያየትን በማካተትና እንዲሁም በጥናቱ ማበልጸጊያ ጊዜ የተሰጠውን ግብአት በማካተት የመጨረሻ ማስተካከያ ተደርጎ የምዘና ፈተናው ተዘጋጅቷል:: በተደረገው ማስተካከያ መሰረት ቀደም ብሎ የተዘጋጀው የምዘና ፈተና ጥያቄ 56 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በትክክሉ መስፈርቶቹን ያሟሉ 32 ጥያቄች የተመረጡ ሲሆን የተቀሩት ጥያቄዎች እንዲቀሩ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ በፈተናዎቹ ላይ ማስተካከያ ተደርጎ ከላይ በሰንጠረዥ ሰባት ላይ በቀረበው ዝርዝር ሁኔታ መሰረት የምዘና ፈተናው ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ ውሏል፡፡

የፈተናውን የአስተማማኝነት ደረጃን ለማወቅ ደግሞ ተማሪዎቹ በመመሪያው መሰረት ፈተናውን ከተፈተኑ በኂላ በማረም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጠው መልስ በመነሳት ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት 20%ቱን ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት 20% የሚሆነውን በSPSS የመረጃ ማስፈሪያ ፕሮግራም ላይ በማስፈር ትንታኔ ተሰጥቶ ታይቷል፡፡ የአስተማማኝነት ደረጃውን ለመለካት በፈተናው ውጤት መሰረት በSPSS የመረጃ ማስፈሪያ ፕሮግራም ላይ በሚሰፍርበት ወቅት እያንዳንዱ ተማሪዎች የሰጡትን መልስ መሰረት በማድረግ በትክክል የተመለሱትን ጥያቄዎችና በስህተትነት የተመለሱትን ጥያቄዎች በመመዝገብና የምዝገባው ሂደት እንዳበቃ በKuder Richardson 20 የአስተማማኝነት መለኪያ ሂሳባዊ ስሌት መሰረት የአስተማማኝነት ደረጃው ተሰልቷል፡፡ በስሌቱ መሰረት የተገኘው የክሮምባክ አልፋ ውጤት 0.852 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ከተገኘው የክሮምባክ አልፋ ውጤት በመነሳት የተዘጋጀው ፈተና አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል:: Craig (1979) የፈተና አይነት ብዙ መልክ ቢኖረውም አስተማማኝነቱ የሚዛን(Scales) ላይ 0.80 ከሆነ በከፍተኛ ደረጃ ላይ አስተማማኝ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ያለው እንዳወቀ (2001ዓ/ም) ለአእምሮአዊ ችሎታ ለመለኪያነት የሚያገለግል ፈተና የአስተማማኝነት ደረጃው እስከ 0.70 ዝቅ ቢል ብዙም ችግር የለውም በማለት ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ለዚህ ጥናት የተዘገጋጀው የፈተና የአስተማማኝነት ደረጃው በመስኩ ምሁራን ከቀረበው የአስተማማኝነት ደረጃ አንጻር ሲታይ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በተጨማሪም እያንዳንዱ ጥያቄዎችን በተመለከተ በጥያቄዎቹና በፈተናው አማራጮቹ ላይ ትንተና(item analysis) በማከናወን የክብደት ደረጃቸውን፣ ጎበዙን ከሰነፍ የመለየት የመለየት

አቅም እና የመልስ አማራጮች ብቁ መሆናቸውን አስመልክቶ ትንታኔ ተከናውኗል፡፡ ከትንታኔውም በመነሳት በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ዜሮ የመለየት አቅም እና ነጋቲቭ የመለየት አቅም(Discrimination power) ያላቸው ጥያቄዎች፣ በጣም ቀላል የሆኑ ጥያቄዎች፣ ችግር ያለባቸው የጥያቄ አማራጮች በቅድመ ሙከራ ጥናቱ ላይና በሙከራ ጥናቱ ወቅት ተለይተው ተወግደዋል፡፡

በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተዘጋጀውን የችሎታ ምዘና ፈተና ተቀባይነትና አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላና በጥናት ማበልጸግያ ወቅት በተሰጠ አስተያየት መሰረት የመጨረሻ ማስተካከያ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚያም በናሙናነት ለተመረጡት ለእያንዳንዱ ተማሪ በማቅረብ ከአመለካከትና ከፍላጎት መለኪያ መጠይቅ ጋር በተያያዘ መልኩ ኮድ ሰጥቶ በመመዝገብ ለናሙና ተማሪዎቹ በመስጠትና በመመሪያው መሰረት ፈተናውንና የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ከዚያም ፈተናውን በኮዱ መሰረት በመሰብሰብና በማረም የተገኘውን ውጤት ለሂሳብ ስሌት በሚያመች መልኩ ወደ መቶኛ ተለውጦ ተመዝግቧል፡፡

## 3.7 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ጥናቱ አይነታዊና አሀዛዊ የረጃ አሰባሰብ ዘዴን የተጠቀመ ጥናት ስለሆነ በቡድን ተኮር ውይይትና በልቅ የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ በገለጻ አማካኝነት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይሄም መረጃ መሰብሰብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የተሰበሰቡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመልክ በመልካቸው የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላም ሆነ በሚሰበሰብበት ጊዜ አስፈላጊ ያልሆኑ መረጃዎች እንዲቀሩ በማድረግ የተሰበሰበውን መረጃ እንደ መረጃው ባህሪና አይነት ወደ ፊትና ወደ ኋላ በመመላለስ ተራክቦአዊ በሆነ መንገድ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በዝግ የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና በችሎታ ምዘና ፈተና አማካኝነት የተሰበሰበ መረጃን በተመለከተ ደግሞ ለእያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅና ፈተና በተሰጠ የመለያ ኮድ መሰረት በSPSS ሶፍት ዌር ላይ ተመዝግቦ አሀዛዊ የሆነ ዘዴን በመጠቀም ትንታኔው ተከናውኗል፡፡

Careswell (2012) እና DÖrnyes (2007) አሀዛዊና አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በአንድ ላይ መጠቀምን በተመለከተ ሲገልጹ ሁለቱን ዘዴዎች በማቀላቀል(በመቀየጥ) መጠቀም ባለብዙ የጥናት ዘዴን ለመፈተሽ ወይም የአጠናን ዘዴዎችን ለማመሳከር ከመርዳቱም በተጨማሪ ጥልቅ የሆነ ጥናት ለማከናወን ይረዳል ይላሉ። ስለዚህ ቅይጥ የመረጃ አተናተን ዘዴን ተጠቅሞ መረጃን መተንተን ጠቀሜታው የጎላ መሆኑንና ውጤታማ ዘዴ እንደሆነ በጽሁፋቸው ላይ አስፍረዋል። ስለዚህ አይነታዊና አሀዛዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በአንድ ላይ ተጠቅሞ መረጃን መተንተን ቅይጥ ሞዴል በመባል እንደሚታወቅና በአሁኑ ሰአት በሰፊው ተቀባይነት ያገኘና አገልግሎት ላይ እየዋለ የመጣ ዘዴ መሆኑን ሰፊ ማብራሪያ አቅርበዋል።

በተጨማሪ DÖrnyes (2007) Onwueegbuzie & Leech (2005) እና Sandelworski (2003)ን ጠቅሶ ቅይጥ መረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም መረጃን መተንተን ሙሉ በሙሉ ከታለመው ግብ ለመድረስ ይረዳል። ቅይጥ ዘዴን(Mixed method) መጠቀም የጥናቱን ውጤት ከተለያየ አቅጣጫ በማየት ውስብስብ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን ለመረዳት እና ለመፈተሽ እንደሚጠቅም በመግለጽ፤ ቅይጥ ዘዴ በርካታ ጠቀሜታ እንዳለው በመረጃ ላይ የተደገፈ ማብራሪያ አቅርበዋል።

ስለዚህ ከተሰበሰበው መረጃና ከጥናቱ ባህሪ አንጻር በዚህም ጥናት በልቅ ወይም በነጻ የጽሁፍ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰበ መረጃን አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ በመጠቀም ትንታኔ የተሰጠ ሲሆን፤ በውስን የጽሁፍ መጠይቅና በፈተና የተሰበሰበ መረጃን አሀዛዊ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ትንታኔ ተሰጥቷል። በመጨረሻም ተመሳሳይ ርእሰ ጉዳዮች የሆኑትን ወደ አንድ ወገን በማምጣትና በማነጻጸር በአንድ ላይ (Concurrently) በማድረግና በተናጠላዊ (Separately) ጭምር ዳግም ትንታኔ ተሰጥቷል። ቅደም ተከተሉን በተመለከተ መጀመሪያ አሀዛዊውን በመቀጠል አይነታዊውን በማስከተልና ከዚያም በአንድ ላይ በማጣመር ትንታኔው በተወሰኑት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ ሆኗል። በተወሰኑት ርእሰ ጉዳዮች ላይም እንደ አስፈላጊነቱ አሀዛዊው በተናጠል የቀረበበትም ሁኔታ ይገኛል።

ስለዚህ ከየክልሉ ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋውና ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ሲባል በጽሁፍ መጠይቅና በፈተና አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ኮድ እየተሰጠው ለብቻ ለብቻ ተመዝግቦ ቀርቧል። ከዚያም የውጤት፣ የአመለካከትና የፍላጎትና የእድሜ መረጃዎችን

በተሰጣቸው ኮድ መሰረት በማስተያየት በSPSS ሶፍት ዌር/የመመዝገቢያ ሺት/ ላይ ሰፍሮና ተመዝግቦ እንዳበቃ በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ (Pearson correlation) መሰረት በፍላጎት በአመለካከትና በውጤት መካከል ያለው የግንኙነት ደረጃ ታይቷል::

የግንኙነት ልኬትን መሰረት በማድረግ DÖrnyes (2007) እና Careswell (2012) እንደሚሉት ተመራማሪዎች የግንኙነት ጥናትን ሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ተላውጦዎች መካከል ያለን ተጽእኖና ግንኙነትን ለመለካት የሚከናወን የጥናት ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ጥናትም በአራት ተላውጦዎች መካከል ያለን ግንኙነት ለማየት ሲባል አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይሄውም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በፍላጎት፣ በአመለካከት፣ በውጤትና በእድሜ መካከል ያለን ግንኙነትና በመካከላቸው የሚስተዋልን የተጽእኖ መጠንና የተጽእኖውን አቅጣጫ ለማየት ሲባል ዘዴው አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎቹ አጠቃላይ የፍላጎት፣ የአመለካከት፣ የውጤት ግንኙነት በተገኘው የሂሳባዊ ቀመር/ስሌት/ መሰረት በሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ በገለጻ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡

በእድሜ፣ በፆታ፣ በክልሎች፣ በትምህርት ቤቶች እና በቦታ(በገጠርና በከተማ) መካከል ያለውን የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነትን ለማየት በየተላውጦው አይነት በተገኘው ውጤት መሰረት የአማካኝና የመደበኛ ልዩነት ውጤት ለብቻ ለብቻ ተሰልቶ ቀርቧል:: ከዚያም ተማሪው ከሚኖርበት አካባቢ፣ ከእድሜ፣ ከክልል፣ ከፆታ እና ከትምህርት ቤት አንጻር ያለውን የአማካኝ ውጤት ልዩነትን(Leveneis test for equality of variances) ለማወቅ በ"ቲ" ቴስት ቀመር መሰረት ለማየት ተችሏል፡፡ የ"ቲ" ቴስቱ ውጤቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም የጉልህነት ደረጃን ለማረጋገጥ 0.05 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆንና በተጠኝዎቹ የአስተማማኝ የደረጃ ነጻነት (degree of Freedom) መሰረት በማድረግ ከቀረበው ሰንጠረዥ ላይ በማየት በተላውጦዎቹ የአማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና እርግጠኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከሁለት ተላውጦዎች በላይ የሆኑትን በሚመለከት የጉልህነት ደረጃን በማስተካከል በ"ቲ" ቴስት ቀመር መሰረት ደጋግሞ በማየትና ልዩነትን በማወዳደር መመልከት የሚቻል ቢሆንም ይበልጥ ምቹ የሆነው ዘዴ የነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ (one way anova) ስለሆነ ከሁለት ተላውጦዎች በላይ የሆኑትን በዚህ ስሌት መሰረት በማወዳደር ለማየት ተችሏል፡፡ በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ(one way anova) የተገኘው ውጤት ምክንያታዊና አስተማማኝ ወይም ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ 0.05 ባለሁለት ጫፍ የጉልህነት ደረጃ ላይ በማየት በተላውጦዎቹ

የአማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና እርግጠኛ መሆኑን ለማት ተችሏል፡፡ የማረጋገጥ ሁኔታው በእያንዳንዱ ክልል መካከል ያለውን ልዩነት መሰረት በማድረግ ዝርዝርና ጥልቅ ትንተና ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ረድፍ የሚገኙትንና በልዩነት ደረጃ ላይ የሚገኙትን በሰንጠረዠ ላይ በማስቀመጥ ለፖሊሲ አውጪዎች በሚጠቅም መልኩ ውጤቱ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡትን የመረጃ አተናተን ዘዴና ስልቶችን በመጠቀም ከጥናቱ ውጤት ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚያም የተገኘው የውጤት በሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ከሌሎች የጥናት ስራዎች ጋር በማስተያየት ዝርዝር ትንታኔና ገለጻ ተሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያና መደምደሚያ ቀርቦ ውጤቱን መሰረት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ/አስተያት/ ቀርቧል፡፡

## 3.8 ከመረጃ ሰጪዎች የተሰበሰበ መረጃን ማጣራት

ወደ መረጃ ትንታኔ ከመገባቱ በፊት በተማሪዎች ተሞልቶ የተሰበሰበውን መጠይቅ በሙሉ በተሰጠው ኮድ መሰረት አንድ ባንድ አንስቶ በማየት መጠይቆቹ በትክክል መሞላታቸውን እና ሁሉም ጥያቄዎች በአግባቡ መመለሳቸውን የማየትና የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይሄም ሲከናወን በመጠይቁ ውስጥ ለማመሳከሪያነት (For Triangulatoin) በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ የማመሳከር ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህም ሲባል ከቀረበው ጥያቄ ውስጥ ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ያህል ለፍላጎት መመዘኛነት የቀረበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ "የአማርኛን ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ሲያልፈኝ ቅር ይለኛል፡፡" ለሚለው ሀሳብ "በጣም እስማማለሁ" ብሎ የመለሰ ተማሪ በሌላውና በተቃራኒው ለቀረበው ጥያቄ "የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት መማር አልፈልግም፡፡" በማለት ለቀረበ ጥያቄ "በጣም አልስማማም" ብሎ ከመለሰ የሰጠው መልስ ወጥነት አለው፡፡ ስለዚህ መጠይቁ ትክክለኛ ሆኖ ይመረጣል፡፡ ለሁለተኛው ጥያቄ ተማሪው የሰጠው መልስ በጣም እስማማለሁ በማለት የመለሰ ከሆነ ግን የተሰጠው መልስ ወጥነት የሌለውና በጥናቱ ትክክለኝነት ላይ ችግር የሚፈጥር ስለሆነ እንደዚህ አይነቱ መጠይቅ ለጥናቱ ስለማያስፈልግ ከነፈተናው ጭምር የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ አንጻር

የሁሉንም የመረጃ ሰጪ አካላት መጠይቆችን ከትክክለኝነት አንጻር ትክክለኛ መረጃ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል።

በሙከራ ጥናቱ ላይ ከአፋር ክልል በአራት ተማሪዎች የተመለሱ መጠይቆች፣ ከትግራይ ክልል በሶስት ተማሪዎች የተመለሱ መጠይቆች፣ ከኦሮሚያ ክልል በአራት ተማሪዎች የተመለሱ መጠይቆች እና ከአዲስ አበባ በአምስት ተማሪዎች የተመለሱ መጠይቆች የተሟላ መልስ ያልተሰጠባቸው ሆነው ስለተገኙ ከችሎታ ምዘና ፈተናዎቹ ጭምር ከዋናው ጥናት እንዳይገቡ በመወሰን ተወግደዋል። የማበልጸጊያ ጥናቱ ለዋና ጥናት መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ብዛት ያለው ስህተት እንዳይፈጠርና ጥንቃቄ እንዲደረግ ፍንጭ በማመላከት ረድቷል። ስለዚህ ለዋናው ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅት ብዛት ያለው የመጠይቅ አሞላል ስህተት አልተከሰተም ማለት ይቻላል። በተጨማሪም የየትምህርት ቤቱ አስተዳደርና መምህራን ባደረጉት ከፍተኛ እገዛ ምክንያት በተቻለ መጠን የተበላሸ መጠይቅ እንዳይኖር ከፍተኛ ጥረት በመደረጉ የጎላ ችግር አልተስተዋለም። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ከሁሉም ክልሎች የ16 ተማሪዎች መጠይቅ ባግባቡ ባለመሞላቱ ከተማሪዎቹ የፈተና ወረቀት ጭምር ከጥናቱ ውጪ እንዲሆን ተደርጓል። የተወገደው መጠይቅና ፈተናም ከ2.02 በመቶኛ ላይ ያረፈ ስለሆነ በጣም ጥቂት የሚባል ነው።

ስለዚህ የተበላሸ መጠይቅና የተወገደ የችሎታ መመዘኛ ፈተና ወረቀት ከ2.5 በመቶ ያነሰ በመሆኑ መወገድ ያለበት ትክክለኛ ያልሆነ መረጃን የመለየቱ ስራ ከተጠናቀቀና መወገድ ያለበት ከተወገደ በኋላ የተሰበሰበውን ሰፊ የሆነ ጥሬ መረጃ ለትንታኔ እንዲያመች በአይነት በአይነቱ ኮድ በመስጠት የማስተካከል ስራ ተሰርቷል። ከዛም መረጃው በአይነት በአይነቱ በተሰጠው ኮድ መሰረት በSPSS የመረጃ ማስፈሪያ ፕሮግራም (Sofetewer) ወይም የኮድ ሽት ላይ በጥንቃቄ የማስፈር ተግባር ተከናውኗል። በSPSS ላይ ሲሞላ የአሞላልና የኮድ አሰጣጥ ሂደቱ ስህተት እንዳይኖር ለማድረግ በትክክል መሞላቱን በድጋሜ ክለሳ በማድረግ የመረጃ አሞላል ስህተት እንዳይኖር ዳግም የማጣራት ስራ ተከናውኗል። ከዛም መረጃዎች ለአሀዛዊ ስሌት ወይም ትንታኔ ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ ወደ መረጃ ትንታኔ ተገብቷል።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃዎች ትንታኔና ግኝት/ውጤት

### 4.1 የመረጃ ትንታኔ አጠቃላይ መግለጫ

በርዕሱ እንደተገለጸው በዚህ ክፍል ውስጥ የሚታየው ርእሰ ጉዳይ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይሄውም በማበልጸጊያ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበ መረጃ፣ መረጃ ትንታኔ በዝርዝር የቀረበበት ክፍል አንደኛው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከዋናው ጥናት ጋር በተያያዘ መልኩ የመረጃ ትንታኔውና የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ ይህውም ጥናቱ የተከናወነው በአራት ክልሎች ላይ ማለትም በአፋር፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ላይ ሲሆን ለሙከራና ለዋናው ጥናት የተሰበሰበ መረጃን በማስመልከት መረጃው የተሰበሰበበትን ሂደትን፣ በተሰበሰበ መረጃ ላይ የተደረገ ትንታኔና የትንታኔው ውጤት የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ የሙከራ ጥናቱን መሰረት በማድረግ የተከናወነ የመረጃ ትንታኔን በተመለከተ በዚህ ክፍል የመጀመሪያ ገጾች ላይ ቀርቧል፡፡ ከትንታኔውም በመነሳት ለዋናው ጥናት በግብአትነት ያገለገሉ ርእሰ ጉዳዮች በዝርዝር የቀረበበትና ከትንታኔው ውጤት በመነሳት ለዋናው ጥናት ፍንጭ አመላካች መንገዶችና መረጃዎች በአጭሩ የቀረበበት የመጀመሪያው ክፍል ሲሆን በሁለተኛው ደግሞ በጣም ሰፊው ክፍል ነው፡፡ ይሄውም ለዋናው ጥናት የተሰበሰበ የመረጃ የአሰባሰብ ሂደትን በተመለከተ፣ በመረጃው ላይ የተሰጠ ትንታኔ፣ ከመረጃ ትንታኔው በመነሳት የተደረሰበት የጥናት ውጤት/ግኝትን/ በተመለከተ በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱንም ርእሰ ጉዳዮችን በተመለከተ በቅደም ተከተላቸው መሰረት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

### 4.2 የሙከራ ጥናቱ የመረጃ ትንታኔ

#### 4.2.1 ለሙከራ ጥናቱ የተሰበሰበ መረጃና የመረጃ ምንጮች

ለሙከራ ጥናቱ የተበተኑ የጽሁፍ መጠይቆች/የፍላጎት መመዘኛና የአመለካከት መመዘኛ/ እና የችሎታ ምዘና ፈተናን በተመለከተ ከመረጃ ሰጪዎች እንዴት እንደተሰበሰበ በዝርዝር የቀረበበት ነው፡፡ በሙከራ ጥናቱ ወቅት መረጃ የሰጡ የመረጃ ምንጮች በሚከተለው መሰረት

ቀርበዋል፡፡ በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተመለሰ(የተሰበሰበ) መረጃን በተመለከተ ከሶስት ክልሎች (ከአፋር፣ ከኦሮሚያና ከትግራይ ክልል) ለአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፌፌት ከሆኑት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች 113 ሴትና 116 ወንድ በድምሩ 229 ተማሪዎች ተመርጠው የተዘጋጀውን ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅን በመስጠት መጠይቁን እንዲሞሉና ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጎ በትክክል መረጃውን ሞልተው የመለሱ 110 ሴትና 112 ወንድ በድምሩ 222 ተማሪዎች ናቸው፡፡ በትክክሉ ተሞልቶ የተመለሰው የመረጃ መሰብሰቢያ መጤቅና ፈተና ከ95 ከመቶ በላይ ስለሆነ የተቀረውን በቡድን ተኮር ውይይቱ በተሰበሰበ መረጃ ማሟላት ስለሚቻል በተሰበሰበው የሙከራ ጥናት መረጃ ላይ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

በተጨማሪም ከትግራይ ክልል መምህራንና ተማሪዎች መምህራን 5 ተማሪዎች 4 በድምሩ 9 ከሚሆኑ፣ ከኦሮሚያ 6 መምህራን ተማሪዎች 5 በድምሩ 11 ስልሳ ከሚሆኑ ከአፋር ክልል መምህራን 4 ተማሪዎች 4 በድምሩ 8 ከሚሆኑ መረጃ ሠጪዎች በቡድን ተኮር ውይይት አማካንኝት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ ከተሰበሰቡበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች አንጻር በአይነት በአይነታቸው ከተደራጁ በኋላ ከእያንዳንዱ ክልል የተሰበሰበው መረጃ በተናጠል እና በአንድ ላይ በማቀናጀት ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ዝርዝር ትንታኔው በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ለዋናው ጥናት ግብአት ሆኖ አገልግሏል፡፡ ማጠናከሪያ የሚሆን መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡

### 4.2.2 በሙከራ ጥናቱ ላይ የየክልሉ የተማሪዎች የእድሜ ሁኔታ

ከየክልሉ ለሙከራ ጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች የእድሜ ሁኔታን የሚያሳይ ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ስምንት፤ ለሙከራ ጥናቱ ከየክልሉ የተመረጡ ተማሪዎች እድሜ

| እድሜ | አፋር | | ኦሮሚያ | | ትግራይ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% |
| 15≤ | 5 | 7.812 | 13 | 15.116 | 1 | 1.388 |
| 16 | 12 | 18.75 | 16 | 18.604 | 22 | 30.55 |
| 17 | 23 | 35.94 | 26 | 30.23 | 22 | 30.55 |
| 18 | 15 | 23.44 | 24 | 27.907 | 25 | 34.72 |
| 19 | 5 | 7.812 | 4 | 4.65 | 2 | 2.778 |
| 20≥ | 3 | 4.687 | 3 | 3.488 | 0 | 0 |
| ድምር | 64 | 100% | 86 | 100% | 72 | 100% |

ከላይ ከሰንጠረዥ ስምንት ላይ ማየት እንደሚቻለው የየክልሎቹ ተማሪዎች የእድሜ ስብጥር ከ70 በመቶ የሚሆኑት ከ16-18 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን በሰንጠረዡ ላይ የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የሶስቱም ክልል ተማሪዎች የእድሜ ስብጥር በተመሳሳይ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

### 4.2.3 በሙከራ ጥናቱ ላይ የተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣ የትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና እድሜ መካከል ያለ የግንኙነት ደረጃ

በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የሚኖር ግንኙነትን ወይም ዝምድናን ለማየት ሲባል በተሰበሰበው መረጃ ላይ የተከናወነ ትንተናና ገለጻ የሚቀርብበት ክፍል ነው፡፡ በተላውጦዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም ዝምድና ለማየት ሲባል ተግባር ላይ የዋለው የስሌት ቀመር ፒርሰን ያዘጋጀው የግንኙነት መለኪያ ቀመር ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የህብረ ብሔር ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ

ቋንቋ ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና ታይቷል፡፡ ዝምድናውም በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ በሚከተለው መልኩ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ፤** በሙከራ ጥናቱ ወቅት የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ግንኙነትን የሚያሳይ

| ተለዋዋጭ | ፍላጎት | አመለካከት | ውጤት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | 1 | | | |
| አመለካከት | .685** | 1 | | |
| P | .000 | | | |
| ውጤት | .772** | .734** | 1 | |
| P | .000 | .000 | | |
| ዕድሜ | -.039 | -.061 | -.073 | 1 |
| P | .563 | .368 | .278 | |

**. ግንኙነቱ በባለ ሁለት ጫፍ 0.01 ደረጃ ላይ

*. ግንኙነቱ በባለ ሁለት ጫፍ 0.05 ደረጃ ላይ

ከላይ በሰንጠረዥ ዘጠኝ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የህብረ ብሄር ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነትን ወይም ዝምድናን የሚያሳይ የግንኙነት ልኬት ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ በሰንጠረዥ ላይ በቀረበው መሰረት በፍላጎት፣ በአመለካከትና በውጤት መካከል የቀረበው የግንኙነት ደረጃና ውጤት በባለ ሁለት ጫፍ የአስተማማኝነት ፍተሻ ላይና በጉልህነት ደረጃ ማሳያ በ0.05 ላይ ሲታይ ሶስቱም ተላወጦዎች በከፍተኛ ደርጃ አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸውና ውጤቱ አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከእድሜ አንጻር ከአዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ በሚመዘገብ ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ በ0.05 ላይ ሲታይ አስተማማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

## 4.2.4 በሙከራ ጥናቱ በክልሎች፣ መካከል ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

### 4.2.4.1. በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት

በየክልሉ የሚገኙ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል ለማወቅ በፍላጎት መመዘኛ ቴስት መሰረት ከየክልሉ ተማሪዎች የተገኘው የአማካኝ ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ የተስተዋለው የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ለመመልከት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ አስር፤ በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር የሚስተዋል የፍላጎት ልዩነት

| ተላውጦ | ክልል | የተጠኝዎች ቁጥር | አማካኝ ውጤት | መደበኛ ልይት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ቴስት ውጤት | የአስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | አፋር | 64 | 82.00 | 13.68 | 91 | 6.43 | P=.000 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 69.81 | 7.47 | | | |
| ፍላጎት | አፋር | 64 | 82,00 | 13.68 | 123 | 4.02 | P=.000 |
| | ትግራይ | 72 | 73.23 | 11.36 | | | |
| ፍላጎት | ትግራይ | 72 | 73.23 | 11.36 | 119 | 2.19 | P=0.03 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 69.81 | 7.47 | | | |

የአስተማማኝ ደረጃ $P \leq 0.05$

ከላይ በሰንጠረገዡ እንደቀረበው በኦሮሚያና በአፋር ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የፍላጎት አማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ በአፋርና በኦሮሚያ መካከል ያለው 6.43 ሲሆን በትግራይና በአፋር ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የፍላጎት አማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ"

ዋጋ 4.43 ነው፡፡ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የፍላጎት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 2.19 ነው፡፡ በቀረበው ቅደም ተከተል መሰረት የ P ዋጋ.000፣ .000 እና 0.03 ነው፡፡ ስለዚህ የ P ዋጋ 0.05 ስለሚያንስ በክልሎቹ መካከል ያለው ልዩነቱ የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎችና መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ግማሽ በግማሽ የሚሆኑ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን በውይይቱ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡ አንደኛው የራስን ቋንቋ ለማሳደግ ሲባል ሌላን ቋንቋ መማሩ ጠቀሜታ የለውም በሚል ምክንያት፣ ሁለተኛው ቋንቋውን ለመማር ፊደል መቁጠር የሚጀመረው ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነና በዛ ደረጃ ላይ ፊደል መቁጠር መጀመሩ አሰልቺና አስቸጋሪ ስለሚሆን የሚል ግምት በመኖሩ፣ ትምህርቱን መማር ያለመፈለግ እንደሆነ፣ ሌላኛው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማርኛ ቋንቋን በደንብ ስለማይችሉት ክፍለ ጊዜውን ለኦረምኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀማቸው ምክንያት በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ያሳደረ እንደሆነ ከውይይቱ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

## 4.2.4.2 በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት ያለ የአመለካከት ልዩነት

ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት በክልል ተማሪዎች መካከል የጎላ ልዩነት አለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ለማረጋገጥ የየክልሉን ተማሪዎች የአመለካከት አማካኝ ውጤትን በማነጻጸር የውጤቱን ልዩነት በ "ቲ" ቴስት ቀመር መሰረት በማስላት የልዩነት ደረጃው ታይቷል፡፡ ልዩነቱም ምክንታዊ መሆኑን አለመሆኑን ከተገኘው የ"ቲ" ቴስት ውጤት በመነሳት ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ለጥያቄው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

ሰንጠረዥ አስራ አንድ፤ በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት ያለ የአመለካከት ልዩነት

| ተላውጦ | ክልል | የተጠኝ ዎች ቁጥር | አማካኝ ውጤት | መደበኛ ልይት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ቴስት ውጤት | የአስተማማ ኝነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አመለካከት | አፋር | 64 | 52.00 | 7.93 | 130 | 4.16 | P=.000 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 46.70 | 7.39 | | | |
| አመለካከት | አፋር | 64 | 52.00 | 7.93 | 130 | 2.09 | P=.000 |
| | ትግራይ | 72 | 49.20 | 7.61 | | | |
| አመለካከት | ትግራይ | 72 | 49.20 | 7.61 | 149 | 2.08 | P=0.04 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 46.70 | 7.39 | | | |

የአስተማማኝ ደረጃ $P \leq 0.05$

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ እንደቀረበው በኦሮሚያና በአፋር ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የአመለካከት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 4.16 ነው፡፡ በአፋር በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የአመለካከት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 2.09 ሲሆን በኦሮሚያና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የአመለካከት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በ "ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ "ቲ" ዋጋ 2.08 ነው፡፡ የተገኘው የ P ዋጋ በቅደምተከተላቸው መሰረት .000፣ .000 እና 0.04 ይህም የትግራይ ክልል ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን ትምህርት ለመማር ያላቸው አመለካከት ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ የጎላ መሆኑን የተገኘው የቲ ቴስት ውጤት አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የP ዋጋ 0.05 ስለሚያንስ በክልሎቹ መካከል ያለው ልዩነቱ የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ በአመለካከት መመዘኛ ከተሰበሰበሰው መረጃና በቡድን ተኮር ውይይት ላይ ከቀረበው መረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻለው የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ከትግራይና ከአፋር ክልል ተማሪዎች ያነሰ መሆኑን የሙከራ ይናቱ አሳይቷል፡፡

### 4.2.4.3 በሙከራ ጥናቱ በክልል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ያለ ልዩነት

በየክልሉ የሚገኙ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል ለማወቅ በፍላጎት መመዘኛ ቴስት መሰረት ከየክልሉ ተማሪዎች የተገኘው የትምህርት ውጤት መካከል የተስተዋለው ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ መሰረት ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ ሁለት ፤ በሙከራ ጥናቱ ላይ በክልል ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርት ውጤት የተስተዋለ ልዩነት**

| ተላውጠ | ክልል | የተጠኚዎች ቁጥር | አማካኝ ውጤት | የነጻነት ደረጃ | የ "ቲ" ቴስት ውጤት | የአስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | አፋር | 64 | 68.10 | 100 | 7.52 | P=.000 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 53.50 | | | |
| ውጤት | አፋር | 64 | 68.10 | 124 | 4.48 | P=.000 |
| | ትግራይ | 72 | 55.00 | | | |
| ውጤት | ትግራይ | 72 | 55.00 | 130 | 2.95 | P=.004 |
| | ኦሮሚያ | 84 | 53.50 | | | |

የአስተማማኝ ደረጃ $P \leq 0.05$

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ እንደቀረበው በኦሮሚያና በአፋር ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የትምህርት ውጤት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በቲ ቴስት ሲሰላ የተገኘው

የቲ ዋጋ 7.52 ሲሆን በ100 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት፤ ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ 1.90 ነው፡፡ የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ ማለትም 7.52 ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋው ከ1.90 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡት የችሎታ ምዘና ውጤቱ በሂሳባዊ ቀመሩ የተገኘው ስሌት ሲታይ የጎላ ልዩነትን አሳይቷል፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው የአፋር ክልል ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውንና በሁለቱ ክልል ተማሪዎች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን የሙከራ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ 12 ላይ እንደቀረበው በትግራይና በአፋር ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የውጤት የአማካኝ ልዩነትን ለመወሰን በቲ ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የቲ ዋጋ 4.484 ሲሆን በ124 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ 2.13 ነው፡፡ የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ ማለትም 4.48 ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋው ከ2.13 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ በአፋርና በትግራይ ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡት የችሎታ ምዘና ውጤቱ በሂሳባዊ ቀመሩ ተሰልቶ ነየተገኘው ስሌት ሲታይ የጎላ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው የአፋር ክልል ተማሪዎች ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በህብረ ብሄር የቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘገቡ በመካከላቸው ሰፊ የሆነ የውጤት ልዩነት መኖሩን የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡

በኦሮሚያና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የአማከይ ውጤት ልዩነትን ለመወሰን በቲ ቴስት ዋጋ ተሰልቶ የተገኘው የቲ ዋጋ 2.95 ሲሆን በ130 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ 1.61 ነው፡፡ የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ ማለትም 2.95 ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋው ከ1.61 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የቲ ቴስት ዋጋ በልጦ ስለተገኝ በኦሮሚያና በትግራይ ተማሪዎች መካከል የህበብረ ብሄር የቋንቋ ትምህርት ውጤት ሲታይ የትግራይ ክልል ከኦሮሚያ ክልል በልጦ ተገኝቷል፡፡ በቲ ቴስቱ ላይ ሲታይም ልዩነቱ የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የትግራይ ክልል ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ በሆነው ትምህርት ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር የጎላ ልዩነት እንዳለው ከተገኘው የቲ ቴስት ውጤት ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በጥናቱ የተገኘው ውጤት ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ባላቸው አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን ከሙከራ ጥናቱ መመልከት ተችሏል። ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውና ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ በተቃራኒው ዝቅተኛ ፍላጎትና አሉታዊ አመለካከት ያላቸው በትምህርቱ ዝቅተኛ ውጤት እያስመዘገቡ መሆኑን የማበልጸጊያ ጥናቱ አመልክቷል። የአፋር ክልል ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ ትግራይ ክልል ከኦሮሚያ ክልል አንጻር ሲታይ ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እና ትምህርቱን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በሶስቱም ተላውጦዎች ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ መሰረት ከዚህ ከማበልጸጊያ ጥናት መነሻነት ለዋናው ጥናት የመከተለው ዝርዝር ሀሳብ በግብአትነት ተገኝቷል።

## 4.2. 5 ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ግብአትና ለዋና ጥናቱ የተደረገ ማስተካከያ

- ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀው የአመለካከትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅና የውጤት መመዘኛ ፈተና አስተማማኝ መሆናቸውን በሙከራ ጥናቱ ማረጋገጥ ስለተቻለ ትርጉም ያለው ተጨማሪ ማስተካከያ ሳያስፈልግ ወደ ዋናው ጥናት መሄድ እንደሚቻል ጥናቱ አመልክቶ ለዋናው ጥናት የቅደም ተከተል ችግሮችንና ድርብ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ማስተካያ መደረግ እንዳለበት በማበልጸጊያ ጥናቱ ላይ በተሰጠ ሙያዊ አስተያየት መሰረት ማስተካከያ ተደርጎ ለዋናው ጥናት መረጃ ተሰብስቧል። ስለዚህ የተዘጋጀው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተደጋጋሚ ተፈትሸው ትክክለኛና አስተማማኝ እንደሆኑ በማበልጸጊያ ጥናቱ ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል።

- በየትምህርት ቤት የቋንቋ መምህራን ትምህርቱን በሚያስተምሩበት ወቅት አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ክልላዊ ችግሮች ካሉ እንዲገልጹ በማድረግ ከዚህ ከተሰበሰበው መረጃ በበለጠ መልኩ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ የሙከራ ጥናቱ አመልክቶ ከተወሰኑ የክልል ናሙና ተማሪዎች ጋርና መምህራን ጋር ጠለቅ ያለ የቡድን ተኮር ውይይት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጥናቱ አመልክቶ በቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ለመሰበሰብ ተችሏል፡፡

- ከየክልሉ ሁለት ሁለት ዞኖችን ከተመረጡ በኂላ ከዞኖች ውስጥ አራት አራት ት/ቤቶችን በመምርጥ መረጃ መሰብሰብ በሚል ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ነገር ግን በየክልሉ ባሉ ዞኖች የሚገኙ ተማሪዎች ብዛትና በየት/ቤቱ ያሉ የሴክሽን ብዛት በኦሮሚያ፤ በትግራይ፤ በአዲስ አበባ ያለው ተቀራራቢ ሲሆን በአፋር ያለው ግን ከሌሎቹ ከአንድ ሶስተኛ እስከ አንድ አራተኛ ያንሳል፡፡ ስለዚህ የናሙና አወሳሰድ ሁኔታን በተመለከተ ከተማሪዎች ቁጥር አኳያ መውሰድ ታስቦ ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ተቀራራቢ ስለሆነና ከየክልሉ የተመረጡ ክፍሎች እኩል እንዲሆኑ በማድረግ ከየክፍሎቹ ተመጣጣኝ ናሙና ወስዶ ማጥናት እንደሚቻልና ምንም ችግር ሊያስከትል እንደማይችል የሙከራ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ስለዚህ የናሙና አወሳሰዱ መጠን የግድ ከክልል ተማሪዎች ብዛት አንጻር መወሰዱ ጠቀሜታ ቢኖረውም ከየክልሉ የሚወሰዱ ናሙና ተጠኚዎች ከየክልሉ ወካይ የሆኑ ናሙናዎች መምረጥ ከተቻለ እኩል የሆነ ናሙና መጠቀም እንደሚቻል ከሙከራ ጥናቱ የተገኘ ግብአት ነው፡፡ ይሄንን ሲባል ክልላዊ ወካይነት እንዲኖራቸው አካባቢያዊና ጾታዊ ስብጥራቸውን የግድ በመጠበቅ በአንድ በክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎችን ቁጥርን መሰረት በማድረግ የመረጃ ሰጪ ብዛትን መወሰን እንደሚያስፈልግ ከሙከራ ጥናቱ ግንዛቤ ማግኘት በመቻሉ ለዋናው ጥናት በግብአትነት ለመጠቀም ተችሏል፡፡

- በገጠር ተማሪዎች እና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለን የተላውጦ ልዩነት ማየት አስፈላጊ መሆኑን የሙከራ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ የናሙና አወሳሰዱ ዘዴ ያንን ታሳቢ ያደረገ መሆን እንዳለበት አቅጣጫ አመልክቶ ጥናቱን ከዚህ አንጻር መመልከቱ አንደኛው የጥናቱ አካል እንዲሆን ተድርጓል፡፡

- በአማርኛ የተዘጋጀውን መጠይቅ መፈተሸን በተመለከተ ለትግራይ፣ ለአዲስ አበባ፣ ለአፋር ተማሪዎች በአማርኛ የቀረበውን መጠየቅ በአግባቡ የሚረዱት መሆኑንና ለኦሮሚያ ክልል ግን በኦሮሚኛ ተተርጉሞ መጠይቁ ለተማሪዎች መቅረብ እንዳለበት በተደረገ ቅድመ ናሙና ጥናት ለማየት በመቻሉ መጠይቁ በኦሮሚኛ ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

- በክልሎች መካከል ያለው የቋንቋ ትምህርት ውጤት ከፍተኛ ክፍተት ያለበት መሆኑንና ችግሩ ምን እንደሆነ በጥልቀት ማየት እንደሚያስፈልግ የተወሰነ አቅጣጫ አመላክቶ በዋና ጥናት በስፋት ማየት እንደሚያስፈልግ በመታየቱ በተገኘው ግብአት መሰረት ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

- ጥናቱን በመጀመሪያው ዝክረ ተግባር ላይ የቀረበው 7-9 ክፍል ያሉ ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ነበር፡፡ ይሄ ደግሞ ከጊዜ እንዲሁም ከገንዘብ አንጻር አስቸጋሪ መሆኑን የሙከራ ጥናቱ በመማመላከቱ ጥናቱን በዘጠነኛ ክፍል ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ማጥናት እንደሚያስፈልግ ፍንጭ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ለዋና ጥናት በመረጃ ሰጪነት የተያዘው የመረጃ ሰጪ ብዛት 1600 ሲሆን በሙከራ ጥናቱ ወቅት በውጫዊና ውስጣዊ ፈታኞች በተሰጠው አስተያየት መሰረት በመረጃ ሰጪ ቁጥር ላይ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡

- ትምህርቱ ለህብረ ብሄር ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋነት ሲሰጥ የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የፍላጎት ዳሰሳ አለመከናወኑን በተደረገው ዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ ስለተቻለ ይሄንን ጥናት ማከናወን አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ከሙከራ ጥናቱ ለማረጋገጥ መቻሉ የጥናቱን አስፈላጊነትን አሳይቷል፡፡ ስለዚህ በጥናቱ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ ከክልሎች አንጻር ቀደም ብሎ ምንም ጥናት አለመከናወኑን ለማረጋጋጥ ተችሏል፡፡

- የጥናቱ ውጤት ተጨማሪ የክለሳ ድርሳናትን ክለሳ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ፍንጭ ስለሰጠ ወቅታዊ በሆነ ጉዳይ ዙሪያ ተጨማሪ ክለሳ ድርሳናትን በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፡፡

- የሙከራ ጥናቱን ሁኔታ አጥኚውን በገመገሙት ምሁራን በኩል በተሰጠ አስተያየት መሰረት የሰንጠረዥ አጠቃቀምን አስመልክቶ በአሁኑ ወቅት አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለውን የሰንጠረዥ አጠቃቀም እስታንዳርድ መሰረት ለመጠቀም ተችሏል፡፡

- ከእድሜ አንጻር የተሰበሰበው መረጃ በቂ እንዳልሆነና የሚቀር ነገር ያለ ከመሆኑም በተጨማሪ በዘጠነኛ ክፍል ላይ ብቻ ተመስረቶ በተሰበሰበ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ውጤቱ ይሄ ነው ማለት አስቸጋሪ ስለሚሆን ሌላ አማራጭ ዘዴ እንደሚያስፈልግ የጠቆመ ቢሆንም የተማሪዎችን ቁጥር በዛ አድረጎ ማየትን እንደሌላ አማራጭ መመልከት እንደሚቻል ከውሳኔ ላይ ተደርሶ ከዚህ አንጻር በዋናው ጥናት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ስለዚህ አጥኚው ካለበት የፋይናንስ ችግር ምክንያት ይሄንን አማራጭ ቢጠቀምም ወደፊት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በየደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን ወስዶ በጥልቀት ማጥናት እንደሚያስፈልግ የሙከራ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

## 4.3 የዋና ጥናት የመረጃ ትንታኔ

### 4.3.1 ለዋና ጥናቱ የተሰበሰበ መረጃ

ለዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የጥናቱ ተላውጦዎችም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በመማር ረገድ የተማሪዎች ፍላጎት፣ አመለካከት፣ የችሎታ ምዘና ውጤት፣ እድሜ፣ ፆታ፣ አካባቢያዊ ሁኔታ/ገጠር ወይም ከተማ/ና ክልሎች ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹ ተላውጦዎችን መሰረት በማድረግ ለዋናው ጥናት የተበተኑ የጽሁፍ መጠይቆችን /የፍላጎት መመዘኛና የአመለካከት መመዘኛ/ እና የችሎታ ምዘና ፈተናን በተመለከተ ከመረጃ ሰጪዎች ምን ያህሉ በትክክሉ ተሞልቶ እንደተሰበሰበ በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት የተሰበሰበ መረጃን በተመለከተ የችሎታ መመዘኛ ፈተናውን የተፈተኑና የጽሁፍ መጠይቁን በትክክል ሞልተው የመለሱ ተማሪዎች ክልላዊ ስብጥር ሲታይ በአፋር ክልል ለ96 ሴትና ለ96 ወንድ ተማሪዎች በድምሩ ለ192 ተሪዎች ፈተናውንና መጠይቁን ሰርተው መልሰዋል፡፡ በትግራይ ክልል ለ98 ሴትና ለ100 ወንድ በድምሩ ለ198 ተማሪዎች የተሰጠ ፈተናና መጠይቅ ሞልቶ መልሰዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ለ100 ሴትና ለ100 ወንድ በድምሩ ከ200 ተማሪዎች የተሰጠ ፈተናና መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለ97 ሴትና ለ103 ወንድ በድምሩ ከ200 ተማሪዎች የተሰጠ ፈተናና መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ በአጠቃላይ የወንድ 397 እና የሴት 393 በድምሩ የ790 ተማሪዎች ፈተናና

የጽሑፍ መጠይቆች በትክክሉ ተሞልተው ተመልሰዋል። ይሄንን በተመለከተ ከላይ በጥናቱ ዘዴ ውስጥ ከቀረበው ሰንጠረዥ ሁለትና አራት ላይ ማየት ይቻላል።

በተጨማሪም ከመምህራን፣ ከርእሳነ መምህራንና ከተማሪዎች በቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ተሰብስቧል። ከትግራይ ክልል መምህራንና ተማሪዎች መምህራን 12 ተማሪዎች 6 በድምሩ 18 ከሚሆኑ፣ ከኦሮሚያ 12 መምህራን ተማሪዎች 8 በድምሩ 20 ስልሳ ከሚሆኑ ከአፋር ክልል 11 መምህራን 6 ተማሪዎች በድምሩ 17 ከሚሆኑ መረጃ ሠጪዎች አጠቃላይ ድምር 59 ተመርጠው በቡድን ተኮር ውይይት አማካንኝት መረጃ ተሰብስቧል። የተሰበሰበው መረጃ ከተሰበሰቡበት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች አንጻር በአይነት በአይነታቸው ከተደራጁ በኋላ ከእያንዳንዱ ክልል የተሰበሰበው መረጃ በተናጠል እና በአንድ ላይ በማቀናጀት ትንታኔ ተሰጥቶበታል። በዚሁ መሰረት ዝርዝር ትንታኔው በሚከተለው መልኩ ቀርቧል። ከተማሪዎች የተሰጠ ፈተናና የተሞላ የጽሁፍ መጠይቅ 99 በመቶ የሚሆነው በትክክል የተሞላ ስለሆነና የተቀረውንም በቡድን ተኮር ውይይትቱ ከተሰበሰበው መረጃ ማሟላት የሚቻል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደ መረጃ ትንታኔው ተግባር ተገብቷል።

## 4.3.2 ለዋና ጥናቱ መረጃ የሰጡ የክልሉ ተማሪዎች የእድሜ ሁኔታ

ከየክልሉ ለዋና ጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች የእድሜ ሁኔታን የሚያሳይ ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አስራ ሶስት ፡ የየክልሉን ተማሪዎች የእድሜ ደረጃን የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ

| እድሜ | አፋር | | ኦሮሚያ | | ትግራይ | | አዲስ አበባ | | ጠቅላላ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% | ቁጥር | በ% |
| 15≤ | 18 | 9.4 | 41 | 20.5 | 3 | 1.5 | 183 | 91.5 | 250 | 31 |
| 16 | 36 | 18.8 | 38 | 19 | 63 | 31.8 | 12 | 6 | 146 | 18.9 |
| 17 | 69 | 35.9 | 55 | 27.5 | 61 | 31.3 | 4 | 2 | 190 | 24.1 |
| 18 | 48 | 25 | 51 | 25.5 | 65 | 32.8 | 1 | .5 | 164 | 20.75 |
| 19 | 15 | 7.8 | 9 | 4.5 | 5 | 2.5 | - | - | 29 | 3.7 |
| 20≥ | 5 | 2.60 | 6 | 3 | 1 | 0.5 | - | - | 16 | 2.02 |
| ድምር | 192 | 100 | 200 | 100 | 198 | 100 | 200 | 100 | 790 | 100 |

ከላይ ከሰንጠረዥ 13 ላይ ማየት እንደሚቻለው የየክልሎቹ ተማሪዎች የእድሜ ደረጃ ሲታይ ከ62.6 በመቶ የሚሆኑት ከ16-18 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው ከአዲስ አበባን ሳይጨምር የሶስቱን ክልል ተማሪዎች የእድሜ ስብጥር ሲታይ ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ ተማሪዎች ግን 91.5 በመቶ የሚሆሙት 15≤ ስለሆነ ተማሪዎቹ ትምህርት የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች ማልደው መሆኑን የቀረበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ተማሪዎች እድሜ ዝቅ ብሎ መገኘቱ በጥናቱ ሂደት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የለውም፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ዋና ትኩረት ትምህርቱን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩት ክልሎች ላይ ስለሆነና በነዚህ ክልሎች መካከል ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት ጊዜ መለያየት ካልሆነ በስተቀር ከተማሪዎቹ የእድሜ ደረጃ አንጻር የጎላ ልዩነት ባለመኖሩ ምክንያት ወደ ትንታኔ ተገብቷል፡፡

### 4.3.3 በተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣ ፍላጎት፣ አመለካከትና በእድሜ መካከል ያለ የግንኙነት/የዝምድና/ ደረጃ

በዚህ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የሚኖር ግንኙነትን ወይም ዝምድናን ለማየት ሲባል በተሰበሰበው መረጃ ላይ የተከናወነ ትንተናና ገለጻ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ በተላውጦዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም ዝምድናን ለማየት ተግባር ላይ የዋለው የስሌት ቀመር የፒርሰን የግንኙነት መለኪያ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የህብረ ብሔር ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና በችሎታ ምዘና ውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና በተሰበሰበው መረጃ ላይ ትንታኔ በማድረግ ታይቷል፡፡ ከመረጃ ትንታኔው የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ በተላውጦዎቹ መካከል ያለው ዝምድና በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አስራ አራት፤ በተማሪዎች የትምህርት ውጤት፣ ፍላጎት፣ አመለካከትና በእድሜ መካከል ያለ ግንኙነት

| ተ.ቁ | ተላውጦ | ፍላጎት | አመለካከት | ውጤት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፍላጎት | 1 | | | |
| | (P) | | | | |
| 2 | አመለካከት | .637 | 1 | | |
| | (P) | .000 | | | |
| 3 | ውጤት | .739** | .703** | 1 | |
| | (P) | .000 | .000 | | |
| 4 | እድሜ | -.179* | -.285** | -.385** | |
| | (P) | .02 | .000 | .000 | 1 |

የመረጃ ሰጪዎች ቁጥር = 590 (የአፋር፣ የትግራይና የኦሮሚያ ተማሪች

**. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ0.01 ላይ

*. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ 0.05 ላይ

ከላይ በሰንጠረዥ 14 ላይ እንደቀረበው በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣

ፍላጎት፣ እድሜና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ያለው ግንኙነት/ዝምድና/ የሚያሳይ የግንኙነት ልኬት ውጤት ነው፡፡

በሰንጠረዡ ላይ የቀረበውን ትንታኔ ስንመለከት በፍላጎት፣ በአመለካከትና በውጤት መካከል የተስተዋለ የግንኙነት ደረጃና ውጤት በባለ ሁለት ጫፍ የአስተማማኝነት ፍተሻ ላይና በጉልህነት ደረጃ ማሳያ በ0.01 ላይ ሲታይ በፍላጎት፣ አመለካከትና ውጤት መካከል አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው የቀረበው የመረጃ ትንታኔ ውጤት አመልክቷል፡፡ ይሄውም በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ ቀመር መሰረት የተገኘው የግንኙነት ልኬት በዝርዝር ሲታይ ፍላጎት ከአመለካከት ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የp ዋጋ 0.000 ላይ ሆኖ .637** ነው፡፡ ፍላጎት ከውጤት ጋር ያለው የግንኙነትና መጠን የp ዋጋ 0.000 ላይ ሆኖ .739** ነው፡፡ አመለካከት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የp ዋጋ 0.000 ላይ ሆኖ .703** ሲሆን የቋንቋ የትምህርቱን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የp ዋጋ 0.000 ላይ ሆኖ 0.637** ነው፡፡ የp ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ከ0.05 እና0.01 ያነሰ ስለሆነ(0.000<0.05 እና 0፣000<0.01) የተገኘው የግንኙነት ውጤት ጉልህና ስተማማኝ ነው፡፡

ስለዚህ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ማረጋገጥ እንደሚቻለው አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ እንደሆነ ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ የተገኘው ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በተላውጦዎቹ መካከል ያለው የግንኙነት መጠን ከGardner(2006) እና Masgort and Gardner(2003) ካደረጉት የጥናት ግኝት አንጻር ሲታይ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በተመሳሳይ ሁኔታ አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

ከዚህ ማረጋገጥ ሚቻለው ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት አዎንታዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ይሄም አዎንታዊ አመለካከት ሲጨምር ለትምህርቱ ያለ ፍላጎትና የችሎታ ምዘና ውጤ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚጨምር ከተደረገው የመረጃ ትንታኔው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከእድሜ አንጻር ሲታይ ደግሞ እድሜ ከፍላጎት፣ ከአመለካከትና ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት በባለ ሁለት ጫፍ የአስተማማኝነት ፍተሻ ላይና በስህተት ይሁንታ ደረጃ ማሳያ በ0.05 ላይ ሲታይ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ሲታይ ፍላጎት የp ዋጋ .02 ላይ -.179* ሲሆን

ከአመለካከትና ከውጤት ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የp ዋጋ 0.000 ላይ -.285** እና -.303** ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እድሜን በተመለከተ ከተደረገው የመረጃ ትንታኔ ማረጋገጥ የሚቻለው እድሜ ከአመለካከት፣ ከውጤትና ትምህርቱን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃ ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት አረጋግጧል፡፡ የግኝኙነትና የተጽእኖው አቅጣጫ ሲታይ ደግሞ ከሶስቱም ተላወጦዎች ጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ መሆኑን ከመረጃ ትንታኔው የተገኘው ውጤት አሳይቷል፡፡ ይሄም Cook(2001: 133) እና Feer-man (1991፡ 207) አገላለጽ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት ታዳጊዎች ከአዋቂዎች በተሻለ ሁኔታ መማር የሚችሉ ስለሆነ፤ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር መጀመር ያለበት የዕድሜ ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን መማር በሚጀምርበት የዕድሜ ክልል ላይ መሆን አለበት በማለት የገለጹትን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ከእድሜ ጋር ተያይዞ በተገኘውን ውጤት መሰረት ለግንኙነት ደረጃው የሚሰጠው ትርጓሜ የተማሪዎች እድሜ ከትምህር ውጤት፣ አመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር ያለው ዝምድና አሉታዊ ነው፤ ማለት ደግሞ ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት አድሜ እየጨመረ ሲሄድ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህቱ የሚመዘገብ ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ከትንታኔው የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ከአንደኛ የክፍል ደረጃ ወይም ከአነስተኛ የእድሜ ደረጃ ቋንቋውን መማር የጀመሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ በአንጻሩ ደግሞ ትምህርቱን ከፍ ካለ የክፍል ደረጃ ወይም ከፍ ካለ የእድሜ ደረጃ ላይ መማር የጀመሩ ተማሪዎች ውጤታቸው ዝቅ ማለቱን የቀረበው የመረጃ ትንታኔ አረጋግጧል፡፡ ይሄውም የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋን ከመማር አንጻር እድሜ ሲጨምር ለትምህርቱ ያለ አመለካከት ፍላጎትና ውጤት ላይ ያለው ተጽእኖ አሉታዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የተገኘው ውጤት ከየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በተናጠል ሲታይ ደግሞ እንደሚከተለውን ይመስላል፡፡

### 4.3.3.1 ከአፋር ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በአፋር ክልል ተማሪዎች ዘንድ ያለ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና የውጤት ግንኙነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ሰፍሮ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ አስራ አምስት፤ ከአፋር ተመሪዎች የአመለከካት፣የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነት**

| ተላውጦ | ፍላጎት | አመለካከት | ውጤት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | 1 | .556** | .663** | 0.004 |
| (P) | | .000 | .000 | .956 |
| አመለካከት | | 1 | .765** | -.119 |
| (P) | | | .000 | .101 |
| ውጤት | | | 1 | -.095 |
| (P) | | | | .191 |
| እድሜ | | | | 1 |
| (P) | | | | |

የመረጃ ሰጪዎች ቁጥር = 198

**. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ0.01 ላይ

ከላይ በሰንጠረዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና ውጤት ከአፋር ክልል ተማሪዎች አንጻር ሲታይ ፍላጎት፣ አመለካከትና ውጤት መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዳለቸው የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ ያሳያል። ይሄውም በጉልህነት ደረጃ 0.01 ላይ ሲታይ የተገኘው የP ዋጋ በሶስቱም የተላውጦ .000 ስለሆነ ከስህተት ይሁንታው መፈተሻ ከ0.01 ያነሰ ነው። ስለዚህ P≤0.01 ወይም.000≤0.01 ስለሆነ በሶስቱ ተላውጦዎች መካከል የጎላና ከፍተኛ ግንኙነት መኖሩን ያረጋግጣል።

በስሌቱ መሰረት ከአፋር ክልል ተማሪዎች አንጻር የተገኘው የግንኙነት መጠንን በተመለከተ ፍላጎት ከአመለካከት ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃ የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .556** ነው። ፍላጎት ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና በትንታኔው መሰረት የተገኘው የልኬት ውጤት

ወይም ደረጃ የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .663** ነው፡፡ ፍላጎት ከእድሜ ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የP ዋጋ .956 ላይ ሆኖ .004 ነው፡፡ አመለካከት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን የግንኙነት ደረጃ በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .745** ነው፡፡ አመለካከት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .101 ላይ ሆኖ -.119 ነው፡፡ ውጤት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .191 ላይ ሆኖ -.095 ነው፡፡

ስለዚህ ከተገኘው የመረጃ ትናታኔ ውጤት ማረጋገጥ የሚቻለው በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ መሆኑንና አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ከእድሜ ጋር ተያይዞ እድሜ ከመማር ፍላጎት፣ ከአመለካከትና ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ሲታይ የተገኘው የP ዋጋ ከ0.05 (P>0.05) ይበልጣል፡፡ ይሄውም እድሜ ከፍላጎት፣ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኝነት በቅደም ተከተል ሲታይ የ p መጠን ወይን ዋጋ 0.956፣ 0.101፣ 0.191 ነው፡፡ ስለዚህ P > 0.05 ስለሆነ በአፋር ክልል እድሜ ከፍላጎት፣ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግኘኑነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ የአፋር ክልል በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ መሆኑንና አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት እድሜ ከአመለካከት፣ ከፍላጎትና ከውጤት ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት አረጋግጧል፡፡

### 4.3.3.2 ከኦሮሚያ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ዘንድ ያለ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና የውጤት ግንኙነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አስራ ስድስት፤ ከኦሮሚያ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የእድሜና የውጤት ግንኙነት

| ተላውጦ | ፍላጎት | አመለካከት | ውጤት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | 1. | .476** | .609** | -.185* |
| (P) | | .000 | .000 | .009 |
| አመለካከት | | 1. | .625** | -.200** |
| (P) | | | .000 | .004 |
| ውጤት | | | 1. | -.369** |
| (P) | | | | .000 |
| እድሜ | | | | 1. |

የመረጃ ሰጪዎች ቁጥር = 200

**. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ0.01 ላይ

*. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ 0.05 ላይ

ከላይ በሰንጠረዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና በውጤት መካከል ያለው የግንኙነት ደረጃ ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች አንጻር ሲታይ አራቱም ተላውጦዎች የጠበቀ የእርስ በእርስ ግንኙነት አላቸው። በስሌቱ መሰረት የተገኘው የግንኙነት መጠን ሲታይ ፍላጎት ከአመለካከት ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .476** ነው። ፍላጎት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና ዝምድና በትንታኔው መሰረት የተገኘው የልኬት ውጤት ወይም መጠን የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .609** ሆኖ ተገኝቷል። ፍላጎት

ከእድሜ ጋር ያለው የግንኙነት መጠን የP ዋጋ .009 ላይ ሆኖ -.185* ነው፡፡ አመለካከት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ .625** ነው፡፡ አመለካከት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .004 ላይ ሆኖ -.200** ነው፡፡ ውጤት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት የP ዋጋ .000 ላይ ሆኖ -.369** ነው፡፡ ይሄም በጉልህነት ደረጃ /በስህተት ይሁንታ ደረጃ/ 0.01 ላይ ሲታይ የተገኘው P ዋጋ በአራቱም ተላውጦዎች ከ0.01($P<0.01$) ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ $P<0.05$ ወይም $P<0.01$ ($0.000<0.05$ ወይም $000<0.01$) ስለሆነ የተገኘው የግንኙነት ደረጃ በአራቱም በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት በተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ከተገኘው ውጤት ማረጋገጥ እንደሚቻለው በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ መሆኑንና አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ እንደሆነ ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ የተገኘው የሂሳብ ስሌት ውጤት አስተማማኝ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል ከእድሜ ጋር ተያይዞ እድሜ ከመማር ፍላጎት፣ ከአመለካከትና ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ሲታይ የተገኘው የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታ(የጉልህነት ደረጃ) 0.05 ያንሳል ($P<0.05$)፡፡ ይሄውም እድሜ ከፍላጎት፣አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት በቅደም ተከተል ሲታይ የp መጠን በቅደም ተከተላቸው መሰረት ሲታይ 0.009፣ 0.004፣ 0.000 ነው፡፡ ይሄም ከስህተት ይሁንታው መጠን (ከጉልህነት የመፈተሻ ደረጃው) ከ0.05 እና ከ0.01 ያንሳል($P< 0.05$ እና $P<0.01$)፡፡ ስለዚህ በኦሮሚያ ክልል እድሜ ከፍላጎት፣ ከአመለካከት እና ከውጤት ጋር ያለው ግኙነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌቱ መሰረት ሲታይ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ጉልህ መሆኑንና የግንኙነት አቅጣጫው አሉታዊ መሆኑን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ እድሜ ከአመለካከት፣ ከፍላጎትና ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ጉልህ ሲሆን ግኙነቱ አሉታዊ ነው፡፡

ይሄም ማለት በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን እየተማሩ ያሉት ተማሪዎች በእድሜ ከፍ ብለው የሚገኙት ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑንና እድሜ ሲጨምር በተወሰነ ደረጃ ውጤት እንደሚቀንስ የመረጃ ትንታኔው ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በሌላ አገላለጽ በኦረሚያ ክልል የተማሪዎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ከትንታኔው የተገኘው ውጤት ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.3.3 ከትግራይ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በትግራይ ክልል ተማሪዎች ዘንድ ያለ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና የውጤት ግንኙነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ሰፍሮ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አስራ ሰባት፤ ከትግራይ ተማሪዎች አንጻር የአመለከካት፣ የፍላጎት፣ የውጤትና የእድሜ ግንኙነት

| ተላውጦ | ፍላጎት | አመለካከት | ውጤት | እድሜ |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | 1. | .769** | .734** | -.347** |
| (P) | | .000 | .000 | .009 |
| አመለካከት | | 1 | .676** | -.209** |
| (P) | | | .000 | .003 |
| ውጤት | | | 1 | -.337** |
| (P) | | | | .000 |
| እድሜ | | | | 1 |
| (P) | | | | |

የመረጃ ሰጪዎች ቁጥር = 200

**. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ0.01 ላይ

*. በባለሁለት ጫፍ የግንኙነት ደረጃ አስተማማኝነት በ 0.05 ላይ

ከላይ በሰንጠረዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ እድሜና ውጤት ከትግራይ ክልል ተማሪ አንጻር ሲታይ አራቱም ተላውጦዎች የጠበቀ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይሄውም በስህተት ይሁንታ ደረጃ 0.01 አንጻር ሲታይ የተገኘው የP ዋጋ በአራቱም የተላውጦ ከ0.01 ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ P≤0.01 ወይም.000≤0.01 ስለሆነ በአራቱም ተላውጦዎች መካከል የጎላ ግንኙነት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

በስሌቱ መሰረት ከትግራይ ክልል ተማሪዎች አንጻር የተገኘው የግንኙነት መጠን በዝርዝር ሲታይ ፍላጎት ከአመለካከት ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃ .769** ነው፡፡ ፍላጎት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና ዝምድና በትንታኔው መሰረት የተገኘው የልኬት ውጤት ወይም መጠን .734** ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ፍላጎት ከእድሜ ጋር ያለው የግንኙነት ደረጃ -.347** ነው፡፡

አመለካከት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን የግንኙነት መጠን በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት .676** ነው፡፡ አመለካከት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት ደረጃ በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው መጠን -.209** ነው፡፡ የትምህርት ውጤት ከእድሜ ጋር ያለውን የግንኙነት ደረጃ ሲታይ በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት -.337** ነው፡፡

ከተገኘው ውጤት ማረጋገጥ እንደሚቻለው በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት መካከል ያለው ግንኙነት አዎንታዊ መሆኑንና አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ከእድሜ ጋር ተያይዞ ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ እድሜ ከመማር ፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ሲታይ የተገኘው የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታ 0.05 እና 0.01 ያንሳል (P<0.05 እና P<0.01)፡፡ ይሄውም እድሜ ከፍላጎት፣ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኝነት በቅደም ተከተል ሲታይ የ p መጠን/ዋገ/ 0.000፣ 0.03፣ 0.000 ነው፡፡ ይሄም ከስህተት ይሁንታ መጠን 0.05 እና 0.01 ያንሳል(P< 0.05 እና P< 0.01)፡፡ ስለዚህ እንደ ኦሮሚያ ክልል ሁሉ በትግራይም እድሜ

ከፍላጎት፣ ከአመለካከት እና ከውጤት ጋር ያላቸው ግንኙነት ጉልህና አሉታዊ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ የተገኘ የግንኙነት ደረጃ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው፡፡

ስለዚህ በትግራይ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት እድሜ ከአመለካከት፣ ከፍላጎትና ከውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ጉልህ ሲሆን ግንኙነቱ አሉታዊ ነው፡፡ ይሄም ማለት በትግራይ ክልል ትምህርቱን እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች በእድሜ ከፍ ሲሉ አዎንታዊ አመለካከት፣ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ የሚመዘገብ ውጤት እንደሚቀንስ ከመረጃ ትንታኔ የተገኘው ውጤት ያረጋግጣል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 4.3.3.1፣ 4.3.3.2 እና 4.3.3.3 ላይ እንደቀረበው ከእድሜ አንጻር በኦሮሚያ ክልል ላይና በትግራይ ክልል ላይ የተደረገው የመረጃ ትንታኔ እንደሚያመለክተው ትምህርቱን እየተማሩ ያሉት ተማሪዎች በእድሜ ከፍ ያሉት ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑንና እድሜ ሲጨምር ውጤት እንደሚቀንስ የመረጃ ትንታኔው ውጤት አረጋግጧል፡፡ በሌላ አገላለጽ የኦሮሚያና ትግራይ ክልል የተማሪዎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ከመረጃ ትንታኔው የተገኘ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

ትምህርቱን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ሲማሩ በነበሩት የአፋር ክልል ተማሪዎች ላይ ደግሞ እድሜ በቋንቋ ትምህርቱ ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ ውጤት ላይ ምንም ተጽእኖ እንደሌለው አመልክቷል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪው ትምህርቱን ማልዶ ከአንደኛ ክፍል መማር የሚጀምሩ ከሆነ እድሜ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የጎላ ተጽእኖ እንደማይኖረው /እንደሌለው/ ያመለክታል፡፡

Skinner (1989) እና Schon'ell (1961) ተማሪዎች እንደየ እድሜያቸው ፍላጎታቸውና ተግባራቸው ይለያያል፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች እድሜያቸውን መሰረት ያደረገ ትምህርት ከተግባርና ከፍላጎታቸው ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ ሊሆን ይችላል፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል አምስት አመት እድሜና አስር አመት እድሜ ባለው ተማሪ መካከል ያላው የፍላጎት እና የአመለካከት ሁኔታ የተለያየ ነው፤በማለት

ከእድሜ አንጻር ያላቸውን ልዩነት አስመልክተውም ሰፊ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ አንድን ትምህርት የመማር ማስተማር ተግባር ከተማሪው እድሜ ጋር የተገናዘበ መሆን እንዳለበት የምሁራኑ ሀሳብ ያስረዳል፡፡

ከዚህ አንጻር ክልሎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለተማሪዎቻቸው ሲያስተምሩ እድሜን ከግምት ውስጥ አስገብተው ነው ወይ? ተብሎ ሲጠየቅ ምላሹ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይሄውም ክልሎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲያስተምሩ እድሜን ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት በተሰበሰበው መረጃ መሰረትም በአፋር ክልል ትምህርቱ የሚጀምረው ከአንደኛ ክፍል ሆኖ የተማሪው እድሜ አማከይ በ8 አመት ደረጃ ላይ ነው፡፡ በትግራይ ክልል ትምህርቱ የሚጀምረው ከሶስተኛ ክፍል ሆኖ የተማሪው እድሜ አማካይ ከ10 አመት ደረጃ ላይ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል የተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት ክፍል ከአምስተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ሲሆን እድሜያቸው በአማካይ 12 አመት ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ከኦሮሚያ ክልል በተሰበሰበው የቡድን ተኮር ውይይት መረጃ መሰረት ከ5ኛ ክፍልና በ12 አመት የእድሜ ደረጃ ላይ ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምረውም በፊደል ቆጠራ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ በዚህን የክፍል ደረጃ እንደገና ወደ ፊደል ቆጠራ ሲገቡ በላያቸው ላይ የሚያሳድረው ስነ-ልቦናዊ ስሜት አሉታዊ መሆኑን ከቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ይሄውም በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ሀሳብ ሲገልጹ፤ የህጻንነት ስሜት እንደሚሰማቸውና እንደገና ወደ እታች እንደተመለሱ አድርገው እንደሚቆጥሩት ነው ያስረዱት፡፡ በፊደል ቆጠራው የመማር ማስተማር ሂደት ላይም በተማሪዎቹና በመምህሩ የመማር ማስተማር ተግባር ላይ የመሰላቸት ሁኔታ እንደሚታይባቸው ከክልሉ ተማሪዎችና መምህራን የተሰበሰበው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ አንጻር በተከናወነው የቡድን ተኮር ውይይት መሰረት የተገኘው መረጃ በSkinner (1989) እና Schon'ell (1961) ከቀረቡት ሀሳብ ጋር አንድ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ተማሪዎች እንደየ እድሜያቸው ፍላጎታቸውና ተግባራቸው ይለያያል ይላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተማሪዎችን እድሜ መሰረት ያደረገ ትምህርት ከተግባርና ከፍላጎታቸው ጋር በማቀናጀት የሚሰጥ ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይችላል፡፡ ከላይ በቀረበው ምሁራን ሀሳብ መሰረት

የአምስትና የአስር አመት ተማሪዎች ያላቸው ፍላጎት የተለያየ መሆኑንና የቋንቋ ትምህርቱን ማልዶ መስጠት እንዳለበት ከቀረበው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የመረጃ ትንታኔው ያረጋግጣል፡፡ ይሄንን በተመለከተ Lightbown (2011) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በቋንቋ ትምህርቱ አላማና ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡ የቋንቋ ትምህርቱ አላማ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ የአፊ-ፊትነትን ችሎታ ያህል እንዲኖረው ከተፈለገ በተቻለ መጠን ትምህርቱን ማልዶ መጀመር አለበት በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ በቀረበው ገለጻ በተመሳሳይ ሁኔታ ለንጽጽር እንዲሆን ከጂማ ዞን የቡድን ተኮር ውይይት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የኦሮሚኛን ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ከአምስተኛ ክፍል መማር የጀመሩ ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እየተሰጠ ካለው ባልተለየ መልኩ የቁቤን ፊደል ቆጠራ ከአምስተኛ ክፍል መማር በመጀመራቸው ምክንያት ፊደል በመለየት ሂደት ላይ ፊደል ቆጠራውን ተማሪዎቹ እንደሚሠላቹና እንደገና ወደ እታች እንደተመለሱ አድርገው እራሳቸውን እንደሚቆጥሩ ነው የሰጡት መረጃ የሚያረጋግጠው፡፡ በተጨማሪም ኦሮሚኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ከአምስተኛ ክፍል ጀምረው መማር የጀመሩት ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ተምረው ከመጡት አፊ-ፊት ተማሪዎች ጋር አብሮ ለመሄድ እንደሚቸገሩና ቋንቋውን በመልመድ ሂደት ላይ እየተቸገሩ መሆናቸውን ከጂማ ዞን ትቤ/ቶችና ከጂማ ከተማ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተሰበሰበው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ በዚህ የተነሳ በጂማ ከተማ እየኖሩ ኦሮሚኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ተምረው እያሉ የኦሮሚኛ ቋንቋን በደንብ መናገር የማይችሉ ተማሪዎች በርካታ መሆናቸውን ከቡድን ተኮር ውይይቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

Stern (1991) ላይ ከቀረበው ውስጥ ማልዶ ትምህርትን መማር መጀመርን አስመልክቶ በተገኘው ልምድ መሰረት በልጅነት አንድን የትምህርት አይነት መማር የጀመረ ተማሪ በትምህርቱ ውጤታማ ከመሆኑም በተጨማሪ ለትምህርቱ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖር ያደርጋል የሚል ሀሳብ ይገኝበታል፡፡ ከዚህ አንጻር በኦሮሚያ ክልል እድሜን በተመለከተ የተገኘው ውጤት ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከአምስተኛ የክፍል ደረጃ የሚጀምር ስለሆነ የተጀመረበትን የእድሜ ደረጃ ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ክልል እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ትምህርቱን ለመማር ያለው ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከትና ውጤት እንዲቀንስ ያደረገው ትምህርቱ መስጠት የሚጀምርበት የክፍል ደረጃ ከፍ በማለቱ እንደሆነ አንደኛው ምክንያት መሆኑን በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰበው መረጃ

ያመለክታል። በተመሳሳይ ሁኔታም በትግራይ ክልል ትምህርቱን ከሶስተኛ የክፍል ደረጃ የሚጀምር ስለሆነ የተጀመረበትን የእድሜ ደረጃ ከፍ እንዲል ያደርገዋል። በዚህም ክልል የእድሜ ልዩነት በመኖሩ ምክንያት በቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ነው ጥናቱ ውጤት መለከተው።

በኦሮሚያ ትምህርቱ የሚጀምርበት የክፍል ደረጃው ከፍ ማለቱ ተማሪው ትምህርቱን መማር ከጀመረበት የእድሜ ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች በአራት አመት የዘገየ መሆኑ፣ በትግራይ ደግሞ ከሌሎቹ ክልሎች በሁለት አመት የዘገየ መሆኑ ደግሞ እድሜ ከፍላጎት፣ ከአመለካከት እና ከውጤት ጋር ያላቸው የግንኙነት ደረጃ አሉታዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የበኩሉ አስተዋጽኦ እንዳለው ያመለክታል። ስለዚህ ከእድሜ ጋር ተያይዞ ከተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ውስጥ አንደኛው ትምህርቱን ማልዶ ካለመጀመር የመጣ እንደሆነ ይጠቁማል።

በአጠቃላይ ከላይ በሠንጠረዥ 14፣ 15፣ 16፣ እና 17 ላይ ከተደረገው ትንታኔ ማረጋገጥ የሚቻለው በፍላጎት፣ በአመለካከትና በውጤት መካከል ያለው የግንኙነት ደረጃ አዎንታዊና ጉልህና ከፍተኛ ግንኑነት ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል። ይሄውም አንደኛው ተለዋዋጭ በመጠን ሲጨምር ሌላኛውም ተለዋዋጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እየጨመረ የሚሄድ እንደሆነ ወይም አንደኛው ሲቀንስ ሌላኛውም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀንስ ያረጋግጣል። ስለዚህ የተገኘው ውጤት Gardner እና Masgoret (2003) ካከናወኑት የጥናት ውጤት ጋር አንድ ከመሆኑም በተጨማሪ በምሁራኑ የተገኘው የጥናት ውጤት በዚህም ሀገር መስራት እንደሚችል ከተሰበሰበው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል።

ከእድሜ አንጻር ያለው ግንኙነት ሲታይ በተወሰነ ደረጃ የእድሜ ልዩነት ባላቸው ተማሪዎች ላይ በተደረገ ጥናት መሰረት የተገኘው ውጤት እድሜ ሲጨምር ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ መሆኑን ጥናቱ ይጠቁማል። ይሄም ማለት እድሜ እየጨመረ ሲሄድ አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚመዘገብ ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ነው፣ የጥናቱ ውጤት ያረጋገጠው።

እድሜን መሰረት አድርጎ በበርካታ ምሁራን ዘንድ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው ቋንቋን ለመማር የእድሜ ገደብ እንደሌለ ገልጸው ነገር ግን ማልዶ የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርትን መማር የጀመረ ተማሪ ዘግይቶ ከጀመረው ይልቅ በቋንቋው ችሎታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚደርስ


መሆኑን የተገኘው የጥናት ውጤት ያረጋግጣል፡፡ Setern (1991) አገላለጽም የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርትን ማልዶ መማር የጀመረ ተማሪ ለትምህርቱ በቂ ጊዜን ስለሚያገኝ በትምህርቱ ውጤታማ እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡

እንደ Cook (2001: 133) Webb (2000) እና Feer-man (1991፡ 207) አገላለጽ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክያቱም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በዝቅተኛ የእድሜ ደረጃ ላይ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱን መማር የጀመሩ ተማሪዎች ዘግይተው ከጀመሩት /በከፍተኛ እድሜ ደረጃ ላይ ከጀመሩት/ በተሻለ ሁኔታ በቋንቋው ትምህርት እውቀትና ችሎታቸው ከፍተኛ ከሚባለው ደረጃ መድረስ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር መጀመር ያለበት የዕድሜ ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን መማር በሚጀምርበት የዕድሜ ክልል ላይ መሆን አለበት በማለት ይገልጻሉ፡፡ በልጅነት እድሜ ሁለተኛ ቋንቋን መማር የጀመረ ተማሪ ዘግይቶ ከጀመረው በተሻለ ሁኔት በሂደት በቋንቋው በከፍተኛ የችሎታ ደረጃ ላይ መድረስ ስለሚችል ትምህርቱን ማልዶ መጀመር እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ ይሄ ሀሳብ ሐሳብ ደግሞ በዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

Lightbown(2011) አገላለጽም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በቋንቋ ትምህርቱ አላማና ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል ይሉና፤ የቋንቋ ትምህርቱ አላማ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ የአፉ-ፈትነት ችሎታን ያህል ብቃት እንዲኖረው ከተፈለገ በተቻለ መጠን ትምህርቱን ማልዶ መጀመር ይጠበቅበታል፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህና ከላይ ከቀረበው ሀሳብ አንጻር የክልል ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን በየትኛው የክፍል ደረጃ ላይ መማር መጀመር አለባቸው? የሚለውን ጥያቂ ይመልሳል፡፡

በተጨማሪም የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በትምህርትነት ለመስጠት መጀመር ያለበትን የክፍል ደረጃን በተመለከተ ለየክልሉ ተማሪዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ መሰረት የተገኘው መረጃ በሚከተለው ባር ግራፍ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ባርግራፍ አንድ፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መጀመር ያለበትን ደረጃ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽን የሚያሳይ ባር ግራፍ




ከላይ በባርግራፉ ላይ ማየት እንደሚቻለው 76 በመቶ የሚሆኑት በቁጥር 600 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠትና መማር መጀመር ያለበት የክፍል ደረጃ ከአንደኛ የክፍል ደረጃ ላይ መሆን እንዳለበት፣ 9.2 በመቶ የሚሆኑት በቁጥር 73 ተማሪዎች ደግሞ ከሶስተኛ የክፍል ደረጃ መጀመር እንዳለበት እና 7.3 በመቶ የሚሆኑት በቁጥር 58 ተማሪዎች ደግሞ ከአምስተኛ የክፍል ደረጃ መጀመር እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ 7.5 በመቶ የሚሆኑት በቁጥር 58 ተማሪዎች ከመዋእለ ህጻናት ደረጀ መጀመር አለበት በማለት ምላሽ የሰጡ ናቸው፡፡

መረጃ ሰጪዎቹ ምክንያታቸውን እንዲገልጹ በተጠየቁት መሰረት ከአንደኛ የክፍል ደረጃ ላይ ጀምሮ ትምህርቱ መሰጠት እንዳለበት ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ቋንቋውን ይበልጥ ለመማርና ቋንቋውን በዚህ ደረጃ መጀመሩ የትምህርቱን ጫና ይቀንሳል፡፡ ቋንቋውን በፍጥነት ለመማርም የሚረዳ ነው፣ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከሶስተኛና ከአምስተኛ ክፍል ደረጃ መጀመር አለበት በማለት ምላሽ የሰጡት ደግሞ የራሳቸውን ቋንቋ ለማሳደግ ስለሚጠቅም ነው የሚል ምላሽ ነው የሰጡት፡፡

በዚህ ሀሳብ ዙሪያ ማለትም ከአንደኛ ክፍል የሁለተኛ ቋንቋን መማር መጀመር በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል የሚል ጥናትም ሆነ ጽሁፍ ላይ የሰፈረ ካለ ለማየት ተፈልጎ በዙሪያው የተሰራ ስራም ሆነ ሀሳብ እምብዛም ማግኘት ባይቻልም ነገር ግን Lightbown(2011) ላይ በቀረበው በሀሳብ መሰረት አንድኛው የቋንቋ ትምህርት በሌላኛው የቋንቋ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር የቀረበ ሀሳብ ይገኝበታል፡፡ ይሁን እንጂ በቀረበው ሀሳብ መሰረት የትኛው ቋንቋ በየትኛው ቋንቋ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር /የአፍ መፍቻው ቋንቋ ወይስ አለለም አቀፉ ቋንቋ ወይስ የህብረብሄሩ ቋንቋ/ በግልጽ የሚያሳይ ሀሳብ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አልቀረበም፡፡ ነገር ግን ትምህርቱ ከአንደኛ ክፍል መጀመር አለበት የሚለውን ሀሳብ በተመለከተ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የተማሪዎቹ ስሜት Cook(2001:133) እና Feer-man(1991፡ 207) ሌሎችም በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ በምሁራኑ ከቀረበው ሀሳብ ጋር የሚሄድ ሲሆን የጥናቱ ውጤትም በዋናነት ከዚህ ሀሳብ ጋር አንድ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በተጨማሪም Stern (1991) ተማሪዎች ትምህርታቸውን ይበልጥ እንዲማሩ ንሺ አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሄውም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት መማር በሚጀምሩበት ወቅት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሥራ መሰራት አለበት፡፡ ይሄንን ሲባል ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ንሺ እንዲኖራቸው ማድረግ ግን አይቻልም፡፡ ለዚህ በምክንያትነት ከሚቀርቡት ውስጥ አንደኛው የእድሜ ተጽእኖ ነው፡፡ እድሜ በተማሪዎች ንሺ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ተላውጦዎች ውስጥ አንደኛው ነው፡፡ ይሄውም ተማሪዎች እድሜ በተለያዩ የእርከን ደረጃ ይገኛል፡፡ በህጻንነት ደረጃ በአዶለሰንት፣ በወጣትነት፣ በመጀመሪያ ጎልማሳ፣ በመካከለኛ ጎልማሳ፣ በመጨረሻ ጎልማሳ ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር Stern (1991) ማብራሪያ ሲሰጡ ከማንኛውም በተለየ መልኩ ሕፃናት ተማሪዎች አንድን ነገር ለማወቅ በጣም ጉጉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለአንድ ነገር ትኩረት ሰጥቶ ተመስጦ ከመከታተልና ከማስታወስ አንጻር ሲታይ ደግሞ ችሎታቸው ከጎልማሶች ያነሰ ነው፡፡ ልጆች የመምህራንን አድናቆትን እና ክትትልን ይፈልጋሉ፡፡ በመምህሩ አድናቆትን የሚያገኙትን ተግባር እንደ ዋና ምክንያት ይመለከቱታል፡፡ በልጅነት የእድሜ ደረጃ ውስጣዊ ንሺ ከፍተኛ ነው፡፡ ይሄም ከንሺ በተለየ መልኩ በመምህሩ አመለካከትና ባሕርይ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ውስጣዊ ንሺ የሚቀንስ ሲሆን ውጫዊ ንሺ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ጥናቶችን አጣቅሰው ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ሲባል አንድ ተማሪ ቋንቋን የሚማረው ከሚያገኘው ጥቅም አንጻር ነው፤ በማለት ጥናቶችን በማጣቀስ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ(Gardner 1984)፡፡ ከዚህ

አንጻር የትግራይ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች አንጻር ሲታይ በ2 አመት ዘግይተው ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች አንጻር ሲታይ ከሶስተኛ ክፍል ጀምረው ከሚሩት በ2 እና ከአንደኛ ክፍል ጀምረው ከሚሩት በ4 አመት ዘግይተው ነው፡፡ የተማሪዎች እድሜ ሲጨምር ደግሞ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሳሺነት ውጫዊ (instrumental) እየሆነ የሚሄድ መሆኑን ከላይ የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ይህን ማለት ደግሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ጥቅም ይሰጠኛል በሚል እንደሚሆን ነው፤ በምሁሩ የቀረበው ሀሳብ የሚያስረዳው፡፡

በሌላ በኩል ከተሰበሰበው የመረጃ ትንታኔ ውጤት መሰረት የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው የችሎታ ምዘና ውጤት፣ አዎንታዊ አመለካከትና ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ሲታይ ከሌሎች ክልሎች በጣም አንሶ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለኦሮሚያ ክልል ምንም ጥቅም የለውም (ጥቅም አይሰጥም) የሚል ግንዛቤ በተማሪዎቹ ዘንድ ያለ መሆኑን በውይይቱ ላይ የቀረበው የተማሪዎች ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወጪ ሌላ ቋንቋን መማርም ሆነ መናገር እንደማይፈልጉ በተወሰኑ ተወያዮች የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ከዚህ አንጻር በክልሉ ተማሪዎች በኩል ያለው ውጫዊ ተነሳሽነትም ዝቀተኛ መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በኦሮሚያ ክልል የተማሪዎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ውስጣዊ ተነሳሽነትና ውጫዊ ተነሳሺነት እየቀነሰ እንደሚሄድ Stern (1991) ካቀረቡት ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በጥናቱ ከተገኘው የትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

Feer-man(1991) አገላለፅ ለመማር በጣም ወሳኝና መሠረታዊ ወቅት አለው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ የሚጀምረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን መማር በሚጀምርበት ወቅት ነው፣ የሚል ሀሳብ በጽሁፋቸው ውስጥ አስቀምጠዋል፡፡ በዚህ ወቅት የሁለተኛ ቋንቋን መማር የሚጀምር ተማሪ ልክ እንደ መጀመሪያው ቋንቋ /አፍ መፍቻ ቋንቋ/ ሊናገረውና ሊያጎለብተው ስለሚችል የቋንቋ ትምህርቱን ማልዶ መጀመሩ ጠቀሜታው ሰፊ ነው፡፡

Stern (1983) ከተማሪዎች ባህርይ አንፃር ብዙ ጥናት ላይ ከሚቀርቡት መካከል አንደኛው እድሜ ነው። የእድሜና የብስለት ደረጃ በአእምሮ ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ በቋንቋ ትምህርት ላይም የራሱ የሆነ ተጽእኖ ይኖረዋል ይላሉ።

ከዚህ አንጻር ከሶስቱ ክልሎች (ከአፋር፣ከትግራይ፣ ከኦሮሚያ) አንጻር እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ሲታይ የአፋር ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤትጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ ቢሆንም ግንኙነቱ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት የክፍል ደረጃ ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤትጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ ሆኖ ግንኙነቱ ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል።

የትግራይ ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት የክፍል ደረጃ ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ በአፋር ክልል እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤትጋር ግንኙነት የሌለ ሲሆን በኦሮሚያና በትግራይ ግን እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር አሉታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያመለክታል። ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ ሲጨምር ለትምህርቱ ያላቸው በጎ አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

### 4.3.4 በክልሎች፣ በፆታና በመኖሪያ አካባቢ መካከል ያለው የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

በዚህ ርእስ ጉዳይ ስር በራቱም ክልሎች መካከል የሚስተዋል የአመለካከት፣ ፍላጎትና የውጤት የአማካይ ልዩነት በባለ አንድ ገጽታየንጽጽር ትንተና (one way anova) አማካኝነት ሚስተዋል ልዩነት የሚታይበት ክፍል ነው። እንዲሁም ከጾታ አንጻር በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ያለውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ልዩነት መኖሩንን በ "t" ቴስት ልዩነት ንጽጽር ትንተና መሰረት የሁሉንም ክልሎች በአንድ ላይ እና በተናጠል አማካይ ልዩነቱና ደረጃው

አስተማማኝና ጉልህ መሆኑ የሚታይበት ክፍል ነው። በተጨማሪም ከመኖሪያ ሁኔታ አንጻር በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ልዩነትን መኖሩን ለማየት ሲባል አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ሶስት ክልሎችን አፋር፣ ትግራይና ኦሮሚያን ክልሎች በአንድ ላይ እና በተናጠል አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ "ቲ" ቴስት መሰረት በማስላት የሚታይበት ክፍል ነው። ስለዚህ የመረጃ ትንታኔው እያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ቀርቦ የልዩነቶችን ደረጃ ለማየት ተችሏል።

## 4.3.4.1. በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋውን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት

በየክልሉ የሚገኙ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል ለማወቅ የፍላጎት የአማካይ ውጤት ንጽጽር ትንተና መሰረት ከየክልሉ ተማሪዎች የተገኘው የአማካይ ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አስራ ስምንት፤ በክልሎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት የአማካይ ልዩነትን የሚያሳይ መደበኛ የሂሳባዊ ስሌት ትንተና ውጤት

| ተላውጠ | ክልል | የመረጃ ሰጪ ብዛት (N) | አማ ካኝ ውጤት($\bar{x}$) | መ/ልይት (S.d) | 95% የአማካይ ልዩነት የአስተማማኝነት ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ፍላጎት | አፋር | 192 | 81.78 | 13.40 | 79.88 | 83.69 |
| | ኦሮሚያ | 200 | 64.04 | 6.80 | 63.09 | 64.98 |
| | ትግራይ | 198 | 71.17 | 10.90 | 69.64 | 72.70 |
| | አዲስ አበባ | 200 | 74.94 | 11.95 | 73.27 | 76.60 |
| | አጠቃላይ | 790 | 72.89 | 12.72 | 72.01 | 73.78 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው የፍላጎት መመዘኛ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥራቸው 790 ነው። የአጠቃላዩ አማካይ ውጤት 72.89 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 12.72 ነው። በተናጠል ሲታይ የየክልሎቹ አማካኝ ውጤት የአፋር ክልል 81.78፣

የኦሮሚያ 64.03፣ የትግራይ 71.16 እና አዲስ አበባ 74.94 ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር የአፋር ክልል ከአራቱ ክልሎች የአማካይ ውጤቱ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነው። አማካይ ውጤቱ በተዋረድ ሲታይ አፋር > አዲስ አበባ> ትግራይ >ኦሮሚያ መሆኑን ያመለክታል። የአራቱም ክልሎች በአንድ ላይ መደበኛ ልይታቸው ሲታይ አጠቃላዩ 12.72 ነው። በተናጠል የየክልሎቹ ሲታይ የአፋር፣ የአዲስ አበባ፣ የትግራይ እና የኦሮሚያ በቅደም ተከተላቸው መሰረት 13.40፣ 11.95፣ 10.90 እና 6.80 ሲሆን ከአራቱ ከፍተኛ ልዩነት ያለው የአፋር ክልል ተማሪዎች ላይ ነው።

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 18 ላይ በቀረበው የአማካይና መደበኛ ልይት ስሌት መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በአጭር የንጽጽር ትንተና መግለጫ መሰረት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ትናታኔ ተሰጥቶበታል።

**ሰንጠረዥ አስራ ዘጠኝ፤ በክልል ተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋል የፍላጎት ልይት ትንተና አጭር መግለጫ**

| ጥገኛ ተላውጠ | የልነት ምንጭ | ያጠቃላይ ካሬ | የደርጃ ነትነጻ | አማካይ ካሬ | የ (F) ዋጋ | (P) ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | በቡድን መካከል | 32302.83 | 3 | 10767.611 | 88.77 | .000 |
| | በቡድን ውስጥ | 95340.66 | 786 | 221.23 | | |
| | ጠቅላላ | 127643.49 | 789 | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ $P \leq 0.05$ የP ዋጋ = .000 ነው። ስለዚህ $0.000 \leq 0.05$

ከላይ በሰንጠረዥ 19 ላይ ማየት እንደሚቻለው የተገኘው የ F ዋጋ ትርጉም በ3 ጠሪና 786 ቆጣሪ የነጻነት ደረጃ 0.05 ላይና በ0.01 የጉልህነት ደረጃና ባለሁለት ጫፍ የ F ሰንጠረዥ ዋጋ 3.83 እና 5.15 ነው። ይሄም(3, 786, $\alpha$=0.05) =3.83 እና(3, 786, $\alpha$=0.01) = 5.15 ነው። የተገኘው ውጤት የ F ዋጋ በ $\alpha$=0.05 ላይም ሆነ በ0.01 ላይ ሲታይ P=.000 ሆኖ የF ዋጋ

88.77 ስለሆነ ከ F የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር ከ3.83 እና ከ5.15 ሲወዳደር ሁለቱንም በከፍተኛ ደረጃ ይበልጣል። ስለዚህ በክልል የተማሪዎች መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለው የፍላጎት ልዩነት የጎላ መሆኑን የተገኘው ውጤት ያረጋግጣል። ልዩነቱን በዝርዝር ለማየት በልዩነት ትንተና መሰረት ሲታይ የተገኘው የአማካኝ ውጤት ልዩነት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሀያ ፡ በክልል ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት የልይይት ትንተና ዝርዝር መግለጫ

ባለብዙ ቡድን ንጽጽር

| ጥገኛ ተላውጠ | (I)ክልል | (J)ክልል | የአማካይ ልዩነት(I-J) | (P) ደረጃ | 95% ጉልህነት ደረጃ ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | አፋር | ኦሮሚያ | 17.75* | .000 | 14.89 | 20.62 |
| | | ትግራይ | 10.62* | .000 | 7.75 | 13.49 |
| | | አዲስ አበባ | 6.85* | .000 | 3.99 | 9.72 |
| | ትግራይ | ከኦሮሚያ | 7.13* | .000 | 4.29 | 9.97 |
| | አዲስ አበባ | ከኦሮሚያ | 10.90* | .000 | 8.06 | 13.74 |
| | | ከትግራይ | 3.77* | .004 | 0.93 | 6.61 |

*. የአማካኝ ልዩነት የአስተማማኝነት ድረጃ 0.05 ላይ ነው።

ከላይ በሰንጠረዥ 20 ላይ ማየት እንደሚቻለው በአፋርና በኦሮሚያ መካከል ያለው የአማካይ ልዩነት ሲታይ አፋር ከኦሮሚያ በ17.75* በልጦ ተገኝቷል። በአፋርና በትግራይ መካከል ያለው የአማካኝ ልዩነት ሲታይ አፋር ከትግራይ በ10.62* በልጦ ተገኝቷል። በአፋርና በአዲስ አበባ መካከል ያለው የአማካይ ልዩነት ሲታይ አፋር ከአዲስ አበባ በ6.85* በልጦ ተገኝቷል። አዲስ አበባ ከኦሮሚያና ከትግራይ ጋር ሲነጻጸር ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በቅደም ተከተላቸው መሰረት አዲስ አበባ 10.90* እና 3.77*በልጦ ተገኝቷል። ትግራይ ከኦሮሚያ በ7.132*በልጦ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር በክልሎች መካከል ቋንቋውን ለመማር የፍላጎት መለያየት መኖሩን

ለማየት የተቻለ ሲሆን የተገኘው የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .000 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 17.75* ነው። ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው። ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P= 0.000 ስለሆነ (.000 < 0.01) የአማካኝ ውጤት ልዩነቱ 17.75* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ ሲሆን የአፋር ክልል ከኦሮሚያ ክልል በ17.75*በልጦ ተግኝቷል። ብልጫውም በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው።

በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .000 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 10.62* ነው። ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው። ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P= 0.000 ላይ ሆኖ የተገኘው ልዩነት 10.62* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ ሲሆን የአፋር ክልልና ከትግራይ ክልል በ10.62* በልጦ በመገኘቱ የተገኘው ልዩነት በተደረገ ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑ ተረጋግጧል።

በአፋርና በክልል 14 ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .000 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 6.85* ነው። ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰኝጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው። ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P= 0.000 ሆኖ P<0.01 (.000 < 0.01) ስለሆነ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 6.85* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአፋር ክልልና በክልል 14 ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ

ሲሆን የአፋር ክልል ከክልል 14 በ6.85* በልጦ በመገኘቱ የተገኘው ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በትግራይና በኦሮሚያ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .000 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 7.13* ነው፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P=0.000 ሆኖ P<0.01 (.000 < 0.01) ስለሆነ የአማካኝ ውጤት ልዩነቱ 7.13* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ ሲሆን የትግራይና ከኦሮሚያ ክልል በ7.13*በልጦ በመገኘቱ የተገኘው ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .000 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 10.90* ነው፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P=0.000 ስለሆነ .000 < 0.01 ስለሆነ የአማካኝ ውጤት ልዩነቱ 10.90* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ ሲሆን የክልል 14 ከኦሮሚያ ክልል በ10.90* በልጦ በመገኘቱ የተገኘው ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአዲስ አበባና በትግራይ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የውጤት ልዩነት ሲታይ የ P ደረጃ P= .004 ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ 3.77*ነው፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 እና ከ0.01 ካነሰና የአማካኝ ውጤቱ ልዩነት በጉልህነት ደረጃ በ0.01 ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው P= 0.004 ስለሆነ .004 < 0.01 ስለሆነ የአማካኝ ውጤት ልዩነቱ 3.77* ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአዲስ አበባና በትግራይ ክልል

ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሰፊ ሲሆን ልዩነቱ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል።

ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ትንታኔ ማየት እንደሚቻለው በአራቱ ክልሎች መካከል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱን ለመማር ያለው የፍላጎት ደረጃ ሰፊ ልዩነት ያለው ሲሆን በብልጫ ቅደም ተከተል ሲታይ አፋር >አዲስ አበባ> ትግራይ> ኦሮሚያ ሆኖ መገኘቱን የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል። በክልሎች መካከል የሚስተዋል ተመሳስሎና ልዩነትን በግልጽ ለማየት የፍላጎት የአማካይ ውጤት የስብስብ ደረጃው የሚያርፍበትን ቦታ ለማየት ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

ሰንጠረዥ ሀያ አንድ ፤ በቋንቋ ትምህርት ፍላጎት በተመሳሳይ የስብስብ ረድፍ ላይ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ

| | | | የስብስብ ሁኔታ α=.05(Subset for alpha = .05) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጥገኛ ተላውጦ | ክልል | ብዛት “N” | 1 | 2 | 3 | 4 |
| | ኦሮሚያ | 200 | 64.35 | | | |
| | ትግራይ | 198 | | 71.17 | | |
| ፍላጎት | አዲስ አበባ | 200 | | | 74.94 | |
| | አፋር | 192 | | | | 81.78 |
| | P | | 1 | 1 | 1 | 1 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው የአራቱም አማካኝ ውጤቶች በ α=0.05 የስህተት ይሁንታ መጠን ላይ ሲታይ ሁሉም በተለያየ ረድፍ ወይም የስብስብ ደረጃ ላይ እንጂ በተመሳሳይ ረድፍ ላይ አልተገኙም። ይሄም ማለት በአራቱም ክልሎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና ከፍተኛ ሆኖ መገኘቱን የሚያረጋግጥ እንጂ ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም በአንድ የስብስብ መስመር ውስጥ የሚገኙ ሆነው አልተገኘም። ስለዚህ በክልል ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የሆነውን የጋራ ቋንቋን በትምህርት አይነትነት ለመማር ባለ ፍላጎት መካከል የጎላ ልዩነት አለን? ለሚለው ጥያቄ ምላሹ አዎን አለ የሚለውን ምላሽ የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኝቷል። በየክልሎቹ የሚገኙ ተማሪዎች የአማካኝ ውጤት በንጽጽር ሲታይ ልዩነቱ ጉልህና

አስተማማኝ መሆኑን በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ (one way anova) ቀመር መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንተና ማረጋገጥ የሚቻለው የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ከትግራይ ያነሰ መሆኑን የትግራይ ክልል ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አንሶ የተገኘ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአፋር ክልል ተማሪዎች ያነሰ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ከቡድን ተኮር ውይይቱና በፍላጎት መመዘኛ መጠይቁ መሰረት የሁለተኛ ቋንቋን ከአንደኛ ክፍል መማር የሚጀምሩ ተማሪዎች ዘግይተው ከጀመሩት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡ ይሄም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት በብልጫው ቅደም ተከተል መሰረት ሲቀመጡ አፋር> አዲስ አበባ >ትግራይ >ኦሮሚያ የሚል የደረጃ ልዩነት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.4.2 በክልል ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርት የሚስተዋል የአመለካከት ልዩነት

ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት በየክልሉ በሚገኙ ተማሪዎች መካከል የጎላ ልዩነት አለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ለማረጋገጥ የየክልሉን ተማሪዎች የአመለካከት አማካይ ውጤትን በማነጻጸር ታይቷል፡፡ የአማካኝ ውጤት ንጽጽሩ የተከናወነው በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ /One way Anova/ በመጠቀም ነው፡፡ ልዩነቱም ምክንያታዊ መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተገኘውን የ“F” ዋጋ ከ F የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማነጻጸር ታይቷል፡፡ በክልሎች መካከል የተስተዋለው ልዩነትም ከዚህ በታች በቀረበ ሰንጠረዥ መሰረት ተተንትኖና ተተርጉሞ በጥናቱ መነሻ ላይ ለተነሳው ጥያቄም እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

ሰንጠረዥ ሀያ ሁለት ፤ የክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የአመለካከት የአማካይ ልዩነትን የሚያሳይ የሂሳባዊ ስሌት መደበኛ የትንተና ውጤት

| ተላውጠ | ክልል | የመረጃ ሰጪ ብዛት(N) | አማ ካይ ውጤት ($\bar{x}$) | መ/ ልይት (S.d) | 95% የአማካይ ልዩነት የአስተማማኝነት ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| አመለካከት | አፋር | 192 | 53.13 | 7.89 | 50.91 | 53.15 |
| | ኦሮሚያ | 200 | 44.11 | 7.24 | 43.10 | 45.12 |
| | ትግራይ | 198 | 47.19 | 7.52 | 46.13 | 48.24 |
| | አዲስ አበባ | 200 | 51.37 | 7.94 | 50.26 | 52.47 |
| | አጠቃላይ | 790 | 48.95 | 8.29 | 48.06 | 49.22 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው የአመለካከት መመዘኛ መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥራቸው 790 ነው። የአጠቃላዩ አማካይ ውጤት 48.95 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 8.29 ነው፡ የየክልሎቹ አማካኝ ውጤታቸው በተናጠል ሲታይ የአፋር ክልል 53.13፣ የኦሮሚያ 44.11፣ የትግራይ 47.19 እና አዲስ አበባ 51.37 ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር የአፋር ከአራቱ ክልላዊ መስተዳደሮች የአማካይ ውጤት አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነው። አማካይ ውጤቱ በተዋረድ ሲታይ አፋር > ከአዲስ አበባ> ከትግራይ >ከኦሮሚያ መሆኑን ያመለክታል። የአራቱም ክልሎች በአንድ ላይ መደበኛ ልይታቸው ሲታይ አጠቃላዩ 12.72 ነው። በተናጠል የየክልሎቹ መደበኛ ልይታቸው ሲታይ የአፋር፣ የአዲስ አበባ፣ የትግራይ እና የኦሮሚያ በቅደም ተከተላቸው መሰረት 7.89፣ 7.94፣ 7.52 እና 7.24 ሲሆን ከአራቱ ከፍተኛ ልዩነት ያለው የአፋር ክልል ተማሪዎች ላይ ነው።

ከላይ ሰንጠረዥ 22 ላይ በቀረበው የአማካይና መደበኛ ልይት ስሌት መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በባለ አንድ ገጽታ የንጽጽር ትንተና መግለጫ መሰረት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ትናታኔ ተሰጥቶበታል።

ሰንጠረዥ ሀያ ሶስት ፤ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተውል የአመለካከት የልይት ትንተና
አጭር መግለጫ

| ጥገኛ ተላውጠ | የልዩነት ምንጭ | ድምር ካሬ እስኬር | የደርጃ ነጻነት | አማካይ ካሬዎች | የ(F) ዋጋ | የP |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አመለካከት | በቡድን መካከል | 8215.50 | 3 | 2738.50 | 46.81 | .000 |
| | በቡድን ውስጥ | 45985.833 | 786 | 58.51 | | |
| | ጠቅላላ | 54201.34 | 789 | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 23 ላይ እንደቀረበው በኦሮሚያ፣ በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአመለካከት የአማካይ ልዩነትን ለመወሰን በባለ አንድ ገጽታ የአማካይ ውጤት ንጽጽር ትንተና ሲሰላ የተገኘው የ“F” ዋጋ 46.81 ሲሆን ይሄም በ4 ጠሪና 786 ቆጣሪ የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት፤ ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ α=0.05 እና α=0.01 የስህተት ይሁንታ መጠን ላይ ሲታይ የ“F” ሰንጠረዥ ዋጋ 2.86 እና 3.82 ነው፡፡ ከትንታኔው የተገኘው p= 0.000 ላይ ሆኖ የ“F” ዋጋ 46.81 ስለሆነ ከ“F” ሰንጠረዥ ዋጋው ከ2.86 እና ከ3.82 ጋር ሲወዳደር በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ የተገኘ ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ በአፋር፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን በትምህርትነት ለመማር በክልሎቹ መካከል ያለ አመለካከት የጎላ ልዩነት አሳይቷል፡፡

ይህም የአፋር ክልል ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ለሆነው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከኦሮሚያና ከትግራይ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር የጎላና አስተማማኝ ልዩነት ያለ መሆኑን የተገኘው የስሌት ውጤት አረጋግጧል፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው የአፋር ክልል ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎችና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፍተኛ መሆኑና እንደዚሁም የትግራይ ክልል ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከፍተኛ መሆኑን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ያረጋግጣል፡፡ ይሄም ውጤት

አንዱ ክልል ከሌላው ክልል ጋር ያለውን የአማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር ለማየት ሲባል በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

**ሠንጠረዥ ሀያ አራት ፡ በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የአመለካከት የልይይት ትንተና ዝርዝር መግለጫ**

Tukey HSD የብዙ ቡድን ንጽጽር

| ጥገኛ ተላውጦ | (I)ክልል | (J)ክልል | የአማካይ ልዩነት(I-J) | የ (P) ደረጃ | 95%የጉልህነት ደረጃ ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አመለካከት | አፋር | ኦሮሚያ | 8.92* | .000 | 5.93 | 9.91 |
| | | ትግራይ | 5.84* | .000 | 2.85 | 6.84 |
| | | አዲስ አበባ | 1.67 | .82 | -1.32 | 2.66 |
| | ትግራይ | ኦሮሚያ | 3.08* | .000 | 1.10 | 5.05 |
| | አዲስ አበባ | ኦሮሚ | 7.25 | .000 | 5.29 | 9.22 |
| | | ትግራይ | 4.18* | .000 | 2.20 | 6.15 |

*. የአማካይ ልዩነት የአስተማማኝነት ድረጃ 0.05 ላይ ነው፡፡

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ እንደቀረበው በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን አዎንታዊ የአማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ አፋር ከኦሮሚያ በ7.92* በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ደረጃ ከα=0.05 ካነሰና በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካይ ውጤት በልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ከተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው የጥናቱ የጉልህነት ደረጃ የሚያሳየው P = .000 ስለሆነ P ≤ 0.05 ነው፡፡ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 7.92 ከከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ስለተገኘ በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሲታይ ልዩነቱ ሰፊ ሲሆን የአፋር

ክልል ከኦሮሚያ ክልል በ7.92 በልጦ ተግኝቷል። ስለዚህ የተገኘ ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል።

በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን አዎንታዊ የአማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ አፋር ከኦሮሚያ በ4.84* በልጦ ተገኝቷል። ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 ካነሰ(P < 0.05)ና በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካኝ ውጤት በልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ከተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው። ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው የጥናቱ የጉልህነት ደረጃ የሚያሳየው P ዋጋ = .000 ላይ ስለሆነ P < 0.05 ነው። ስለዚህ በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሰፊ ሲሆን የትግራይ ክልል ከአፋር ክልል ተማሪዎች በ4.84* አንሶ ተገኝቷል።

በአፋርና በክልል 14 ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የአማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ =0.86 ላይ ሆኖ አማካኝ ውጤቱ የአፋር ክልል ከክልል 14 በ0.67 በልጦ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር የP ዋጋ ከ α=0.05 ስለሚበልጥ(P > 0.05) በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካኝ ውጤት ልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው አንሶ ስለተገኘ ልዩነቱ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ በአፋርና በክልል 14 ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም።

በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ ትግራይ ከኦሮሚያ በ3.77* በልጦ ተገኝቷል። ይሄውም የP ዋጋ ከ α=0.05 ካነሰ (P < 0.05) እና በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካኝ ውጤት ልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ከተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው። ከዚህ በመነሳት ከመረጃ የትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ የሚቻለው በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሰፊ ሲሆን የኦሮሚያ ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በ 3.77* አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ የተገኘ ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው።

በክልል 14 እና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ስሌት ልዩነት የP ደረጃ =0.000 ሆኖ ክልል 14 ከኦሮሚያ በ7.25* በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 ካነሰ(P < 0.05)ና በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ከተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ከተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ ማረጋገጥ የሚቻለው በክልል 14 እና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሰፊ ሲሆን የኦሮሚያ ክልል ከክልል 14 ተማሪዎች በ 7.25* አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ የተገኘ ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው፡፡

በክልል 14ና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ ክልል 14 ከትግራይ ክልል በ4.18* በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 ካነሰ(P< 0.05)ና በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ከስህተት ይሁንታው ሰንጠረዥ ላይ ከሚነበበው በልጦ ከተገኘ ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ ከውጤቱ ማረጋገጥ የሚቻለው በክልል 14 እና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሰፊ ሲሆን የትግራይ ክልል ከክልል 14 ተማሪዎች በ 4.18* አንሶ ተገኝቷል፡፡ በክልሎች መካከል የሚስተዋል ተመሳስሎና ልዩነትን በግልጽ ለማየት የአመለካከት የአማካይ ውጤቱ የስብስብ ደረጃው የሚያርፍበትን ቦታ ለማሳየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

**ሰንጠረዥ ሀያ አምስት ፤** በአመለካከት በተመሳሳይ የስብስብ ረድፍ ላይ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ

| | የስብስብ ሁኔታ α= 0.05 (Subset for alpha = .05) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥገኛ ነተላውጥ | ክልል | ብዛት (N) | 1 | 2 | 3 |
| | ኦሮሚያ | 200 | 44.11 | | |
| | ትግራይ | 198 | | 47.19 | |
| አመለካከት | አዲስ አበባ | 200 | | | 51.37 |
| | አፋር | 192 | | | 53.13 |
| | P | | 1 | 1 | 0.823 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 25 ላይ ማየት እንደሚቻለው የአራቱም አማካይ ውጤቶች በ0.05 የስህተት ይሁንታ መጠን ላይ ሲታይ በሶስት የተለያየ የረድፍ ስብስብ ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሲሆን አዲስ አበባና አፋር ክልል ደግሞ በተመሳሳይ ረድፍ ወይም ስብስብ ላይ ተገኝተዋል። ይህም ማለት በሁለቱ ክልሎች መካከል ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም አንድነት ያላቸው ሲሆን የተቀሩት ክልሎች ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም አንድነት የላቸውም። ስለዚህ በክልል ተማሪዎች መካከል ለህብረ ብሄር ለጋራ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው የአመለካከት ተመሳስሎ ሲታይ አዲስ አበባና አፋር ብቻ ረድፋዊ ተመሳስሎ ሲኖራቸው የተቀሩት ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም አንድነት የላቸውም። በየክልሎቹ የሚገኙ ተማሪዎች የአመለካከት የአማካይ ውጤት የንጽጽር ጉልህነት ሲታይ በአዲስ አበባና በአፋር መካከል ካለ ተመሳስሎ በስተቀር በሌሎቹ ላይ ልዩነቱ ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ ቀመር መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከላይ ከተደረገው የመረጃ ትንታኔ በተጨማሪ ከየክልሎቹ ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራን እና የቋንቋው መምህራን ጋር በቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ተሰብስቧል። በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበ መረጃ ላይም እንደሚከተው ትናታኔ ተሰጥቷል። ከአፋር ክልል ተማሪዎችና መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ ነገር ግን ከገጠር አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎች ትምህርቱ ከባድ ነው፣ የሚል ስሜት እንዳላቸው ከውይይቱ የተገኘ ትንታኔ ያመለክታል።

ከትግራይ ክልል ተማሪዎችና መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ተማሪዎቹ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጎን ለጎን አማርኛ የብሄራዊ ቋንቋ ስለሆነ ቋንቋውን መማራቸው ከክልላቸው ውጪ ለመግባቢያነትና በስራ ወደ ሌላ ክልል ሄዶ ለመሰራት ሊጠቅም ስለሚችል ቋንቋውን መማሩ አስፈላጊ ነው የሚል እይታና እምነት እንዳላቸው ከመምህራኑም ሆነ ከተማሪዎቹ በቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ይሁን እንጂ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነጻጸር ከአፋርና ከክልል14 ያነሰ ሆኖ ነገር ግን ከኦሮሚያ ክልል ከፍ ብሎ ተገኝቷል።

በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎችና መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተወሰኑት ተወያዮች ስለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን አመለካከትና ቋንቋውን ለመማር ያላቸውን ፍላጎት በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡ ይሄውም ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ በምክንያትነት ያነሱት ጉዳይም አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት መማር የአፍ መፍቻ ቋንቋን (ኦሮሚኛ ቋንቋን) እና የኦሮሞን ባህል በማሳደግ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል የሚል ግምት በመኖሩ ምክንያት እንደሆነና ከዚህም ባሻገር አማርኛ ቋንቋን መማር ለክልሉ ተማሪዎች ጠቀሜታ የለውም በሚል ግንዛቤ ምክንያት ክፍተቱ የመጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሀሳብ በውይይቱ ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል የተወሰኑ ተወያዮች የሰጡት ሀሳብ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ ፊደል ቆጠራ የሚጀመረው ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነና በዛ የክፍል ደረጃ ላይ ፊደል መቁጠር መጀመሩ አሰልቺና አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለይም በአምስተኛ የክፍል ደረጃ ላይ ፊደል መቁጠር መጀመሩ ወደ ህጻንነት የተመለስን ያህል ስሜት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ በዚህ የእድሜ ደረጃ ወደ ፊደል ቆጠራ መገባቱ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁነት እንዳይኖረን አድርጓል ብለዋል፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው የቋንቋ ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምርበት የክፍል ደረጃ ከፍ ማለቱ በተማሪዎቹ ስነ-ልቦና ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን የመረጃ ትንታኔው ያረጋግጣል፡፡

በተጨማሪም ለቋንቋ ትምህርቱ የተመደበለት የክፍለ ጊዜ መጠን ከትምህርቱ ይዘት አንጻር በጣም አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ፊደልን ለማስቆጠርና ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማር ዝግጁ ያለመሆን፣ ከአምስተኛ ክፍል እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የቋንቋው መምህራን ቋንቋውን የማስተማር ችሎታቸው ዝቅተኛ ሆኖ መገኘትና ቋንቋውን ለማስተማር ችሎታው ያላቸውም እንኳን የማስተማር ፍላጎታቸው አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት በተማሪዎቹ አመለካከትና ፍላጎት ላይ ተጽእኖ በማሳደሩ ምክንያት የመጣ እንደሆነ በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ የቀረበው ሀሳብ ያመለክታል፡፡ ዘጠነኛ ክፍል ላይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምሩ መምህራን እንደገለጹት ከሆነ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሆነው የአማርኛ ፊደላትን የማያውቁ ተማሪዎች በርካታ ተማሪዎች እንዳሉ ገልጸው፤ አንዳንድ ጊዜ በዘጠነኛ ክፍል ደረጃ ላይ ፊደላትን አስተምረው ፊደላትን የሚፈትኑበት ጊዜም እንዳለ ከቡድን ተኮር ውይይቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ አንጻር የሁለተኛ ቋንቋን መማር የአፍ መፍቻ ቋንቋን በማሳደግ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል በሚልና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር ጠቀሜታ የለውም በሚል ሀሳብ ዙሪያ የተጻፉ ድርሳናት እንዳሉ ለማየት ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን የቀረበውን ሀሳብ በቀጥታ የሚደግፍ ድርሣንና በጥናት  የተደገፈ መረጃ ማግኘት ተፈልጎ ለጊዜው ማግኘት አልተቻለም። በድርሳናትና በጥናት ላይ የተደገፈ መረጃ የሌለ ከሆነ የሁለተኛ ቋንቋን መማር ወይም መናገር መቻል የአፍ መፍቻ ቋንቋን በማሳደግ ሂደት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል የሚለው ሀሳብ ግምታዊ እንዲሆን ስለሚያደርገው በተጨባጭ መረጃ  ላይ የተደገፈ አባባል መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም።

የኢትዮጵያ(የሀገሪቱ) ህገ መንግስትም ልሳነ ክልኤነትን ወይም ልሳነ ብዙነትን በህብረተሰብም ደረጃ ሆነ በግለሰብ ደረጃ የመኖሩን ሁኔታ ይቀበላል/ያከብራልም። ህገ መንግስቱም ከአፍ መፍቻ ቋንቋው በተጨማሪ የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋን ተማሪው እንዲማር እድል የሚሠጥ ነው እንጂ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋውን እንዳይማሩ የሚያበረታታ አይደለም። እንደውም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት መማር እንዲችሉ እድል የሚሰጥና የሚያበረታታ ነው። ለዚህም መረጃ የሚሆነው በኢትየጵያ ህገመንግስት ላይ በግልጽ የሰፈረው ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን ቋንቋ ባህል እንዲያሳድጉ መብት የሚሰጥ ሆኖ የባህል ውርርስን አንዱ የሌላውን ቋንቋ እንዳይናገር ወይንም የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እንዳይኖር የሚከለክል አይደለም። እንደውም ብሄር ብሄረሰቦች ልዩነትን እንደውበት ይዘው በጋራ እሴታቸው አብሮነታቸውን እንዲያጠናክሩ የሚያደርግና ለዚህም አጽንኦት የሚሰጥ ነው። ይሄውም የጋራ በሆነው ጉዳይ ደግሞ አብሮነትን የጋራ ተግባቦትን የሚፈቅድ ትክክለኛ ህገ-መንግስት ስለሆነ ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ የሚያግባባቸውን ቋንቋ መርጠው በጋራ በህገመንግስታቸው ላይ አጽድቀው ይገኛሉ።

በቡድን ተኮር ውይይት በተሰበሰበው መረጃ ላይ የቀረበው ሀሳብ የሚያመለክተው ግን ከቋንቋችን ውጪ መማር የባእድ ቋንቋን መማር ነው፣ የሚል አስተሣሰብን በመያዝ በትምህርት ቤትም ሆነ በመኖሪያ ቦታ ማንሳቱ ትክክለኛ መሰረት የሌለው መሆኑን በህገመንግስቱ ላይ ከቀረበው ሀሳብ የሚቃረን ሀሳብ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል። ይሄ ጉዳይ የራስን ቋንቋ ታሪክንና ባህልን ማሳደግ የህገመንግስቱ ገገር ህግ  ነው። ይሁን እንጂ በቡድን ውይይቱ ላይ የቀረበው ሀሳብ ግን በህገመንግስቱ ላይ ከቀረበው ሀሳብ ወጪ ተተርጉሞ በቋንቋ ትምህርት ላይና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የማሳደሩ ሁኔታ መነሻው

በግልጽ ባይታወቅም ህገመንግስቱን ከመረዳት አንጻር በአንዳንድ የትምህርት ቤት ባለድርሻ አካላት ላይ ክፍተት ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ ያለውን ክፍተት በማስተካከል ትምህርት ሚኒስቴርና የክልል ትምህትርት ቢሮ ያዘጋጀውን የስርአተ-ትምህርት ተግባራዊ ማድረግን የግድ እንደሚል የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

የሀገር ወስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ ቋንቋን ማወቁና መማሩ የራስን ቋንቋ ከማሳደግ የሚያግድ ሳይሆን የራስን ቋንቋና ባህልን ለሌላው ለማሳወቅ እንዲሁም ለማስተማርና ለማሳደግ መሰረት ሊሆን ይችላል(Weeb,2000; China, 2006)፡፡ እንደውም Campbll (2004) ብዙ ቋንቋዎችን መቻል ስለ ቋንቋና ማህበረሠብ ጥሩ ግንዛቤ እና እይታ እንዲኖር ከማድረጉም በላይ የብዙ ህብረተሰን ባህልና ስነ- ፅሑፍን ለማወቅ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋን የሚናገር ሰው ባህላዊ እሴቶችን በጥልቀት እንዲያስተውል እገዛ ያደርጋል፡፡ ልሣነ-ክልኤ የሆኑ ሰዎች ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ስራዎችን ተግባብቶ ለመስራት ሰፊ እድል ይኖራቸዋል በሚል ሀሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ የሌላን ቋንቋ ባለመናገርና ባለመማር የራስን ቋንቋን ለማሳደግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው የሚል ሀሳብን ማንሳቱ ከቀረበው የክለሳ ድርሳን አንጻር ትክክለኛ ያልሆነና በተለያዩ ጽሁፎችና ጥናቶችም ያልተደገፈ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የየክልሉ ት/ቢሮም ተማሪዎች የራሳቸውን ቋንቋና ባህል ከማሳደግ ጎን ለጎ ከሌሎች ክልሎችና ብሄር ብሄረሰቦች ጋር የሚያግባባቸውን የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት እንዲማሩ በማሰብ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በስርአተ ትምህርት ውስጥ በማስገባት እንዲማሩ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ በትግራይ ክልል፣ በሶማሊያ ክልል፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላና በሌሎችም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ ትምህርቱን በመስጠት የትምህርት ሚኒስቴርን መመሪያ ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ማስተማር ሂደቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል የሚል ሀሳብ የሌለ መሆኑን በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የቀረበው ስርአተ ትምህርት ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ሲታይ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል ለተማሪዎቹ ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምረው የክፍል ደረጃ ከአምስተኛ የክፍል ላይ ሲሆን ይሄም ትምህርት ሚኒስቴር የአማርኛ ትምህርት ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ በሁለተኛ ቋንቋነት እንዲሰጥ ከተወሰነው ድንጋጌና ከሀገር ደረጃ ከሚዘጋጀው ስርአተ ትምህርት ውጪ በሆነ መልኩ ትምህርቱ ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ስለዚህም የማስተማርያ ቋንቋ ኦሮሚኛ ሆኖ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን መማር የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ስለሆነ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በደንብ ለማወቅና ለመረዳት እንደሚቸገሩ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆኑን ከውይይቱ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል በአንደኛ ደረጃ(5-8ክፍል) ቋንቋውን እንዲያስተምሩ የሚመለመሉ መምህራን በተመለከተም በትግራይ የትግርኛን ትምህርት እንዲያስተምሩ ተብሎ የተመለመሉ መምህራን እንደሆኑና በኦሮሚያ ክልል ደግሞ የኦሮሚኛ ቋንቋን ለማስተማር ተብሎ የሚመለመሉ እጩ መምህራን እንደሆኑ በቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ካመላከተው ውስጥ አንደኛው ነው፡፡ እነዚህም መምህራን በቋንቋው በቂ ክህሎትና ችሎታ ስለሌላቸው ቋንቋውን ለማስተማር ይቸገራሉ የሚል ሀሳብ በውይይቱ ላይ ቀርቧል፡፡ ለዚህም ዋናውን መንስኤ ተወያዮቹ ሲያብራሩ በአንደኛ ደረጃ ለቋንቋ መምህርነት ተመልምሎ ተቋም ለመግባት የክልሉን ቋንቋ ማወቁ ብቻ በቂ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ኮሌጅ ከገቡ በኋላ አማርኛ ቋንቋንም ማስተማር ይችላሉ የሚል አስተሣሰብ ስላለ እጩ መምህራኑ ከተመረቁ በኋላ አማርኛን እንዲያስተምሩ ይመደባሉ የሚል ሀሳብም አለ፡፡ ስለዚህም እነዚህ መምህራን አማርኛ ቋንቋን እንዲያተምሩ ሲመደቡ ከልብ ለማስተማር ዝግጁ ያለመሆን ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስለሚያዳሉ የተማሪዎቻቸውን የመማር ፍላጎትን በማነሳሳት ረገድና አመለካከታቸውን በማስተካከል በተማሪዎቹ ላይ የባህሪ ለውጥ በማምጣቱ ረገድ ትልቅ ክፍተት እየፈጠረ እንዳለ በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ የተነሳው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለዚህም በዋና ማረጋገጫነት የቀረበው ከየትምህርት ቤቱ በቡድን ተኮር ውይይት የተነሳው ጥቅል ሀሳብ እንደሚያመለክተው ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ቋንቋን እንዲያስተምሩ በክልሉ ተመልምለው ስልጥነው ከወጡ በኋላ መአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር እደሚቸገሩ በውይይቱ ላይ ቀርቧል፡፡ ከትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራን በተገኘ መረጃ መሰረትም እነዚሁ መምህራን ቋንቋውን እንዲያስተምሩ በሚመደቡበት ጊዜ ፈቃደኛ ያለመሆንና ቋንቋውን በደንብ ስለማያስተምሩ በትምህርቱና በተማሪዎቹ አመለካከትና ፍላጎት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን ከተወያዮቹ

የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡ እንደዚህ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በቡድን ተኮር ውይይት የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ሀሳብና ጥናት እንዳለ ለማየት በተደረገ ጥረት መሰረት የመምህራን አመላመሉንና የአሰለጣጠንን ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ይሄውም ጥላሁን ገ/ክርስቶስ(1997ዓ/ም) ባከናወነው ጥናት መሰረት የመማር ማስተማር ጥበባትንና ሣይንሳዊነትን ተገንዝቦ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ስርአታዊ ለማድረግ ሆን ተብሎ ታልሞ በተዘጋጀ መርሀ ግብር ሰልጥነው የተሰማሩ መምህራን ያለመኖሩን የጥናታቸው ውጤት እንዳሣየ አቅረበዋል፡፡ ይሄ ውጤት በቡድን ተኮር ውይይት ከተገኘው የመረጃ ውጤት ጋር አንድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እንዲያስተምሩ የሚመለመሉ መምህራንና የመምህራኑ አሰለጣጠን ችግር ያለበት መሆኑን በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይሄ ደግሞ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ በተማሪ አመለካከት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መምህር ነው፣ በሚል ከቀረበው ሀሳብ ጋር አንድ እንሆነ ያመለክታል፡፡

ለአመለካከት መፈጠር መነሻነት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ በተለይ እስከ ወጣትነት እድሜ ላሉት ልጆች ወላጆች፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፤ ማህበረሰብ፣ ባህል፣ የእድሜ እኩዮችና መምህራን ለአመለካከት መፈጠር መነሻ ከሚሆኑት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Sills, 1968; Roger, and Houghton, 1995; Malim, and Birch, 1998) በማለት ይገልጻሉ:: በተለይም Browen (2007) መምህሩ በተማሪው የስብዕና እና ባህሪና የመማር ፍላጎትና አመለካከት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል ይላሉ:: ከመማር ፍላጎት አንጻርም Barnard, (1972) እንደሚገልፁት የመምህሩ ስብእና በተማሪው የመማር ልምድና ፍላጎት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል ይላሉ፡፡ ይህም የመምህሩ የስብእና ባህሪይ ተማሪው በሚማረው የትምህርት ፍላጎት ላይ ከግምት ሊገባ በሚችል መልኩ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያስገነዝባሉ፡፡

ይሄንን በተመለከተ በጅማና ከምእራብ ሸዋ ዞን በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት አማርኛን ለማስተማር የሚመደቡ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር ስለሚቸገሩ በዛ ላይ አትመድቡኝ በማለት ለማስተማር ፈቃደኛ እንደማይሆኑ በውይይቱ ላይ ቀርቧል። ለማስተማር ከተመደቡም በኋላ ክፍለ ጊዜውን ለኦሮሚኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት እንደሚጠቀሙበት በውይይቱ የተገኘው መረጃ ያስረዳል። ይሁን እንጂ ከጊዜ እጥረት አንጻር በምልከታ ለማረጋገጥ አልተቻለም።

በተጨማሪም በትግራይ ክልል ፊደል ቆጠራ የሚጀምረው ከአንደኛ ክፍል ሆኖ ነገር ግን አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ተማሪዎች መማር የሚጀምሩት ከሶስተኛ ክፍል ነው። ከላይ የቀረበው ክፍተት እንዳለ ሆኖ በኦሮሚያ ክልል ፊደል ቆጠራ የሚጀምረው ከአምስተኛ ክፍል ሲሆን በዛው አመት ሁለተኛ ወሰነ ትምህርት ላይ ደግሞ ፊደሉንና ቃላቱን በደንብ ለይተው ሳያውቁ ሲጠብቁና ሲላሉ ሁለት ትርጉም የሚሰጡ ቃላትን እንዲማሩ መደረጉ በተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ ላይ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ በቋንቋ መምህራኑ ተነስቷል። ከላይ በቀረበው መሰረት በየደረጃው ላለው የትምህርት ይዘት የተመደበለት ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን፣ የይዘት ክብደት፣ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ የሚዘጋጀው የመጽሀፍ ዝግጅት የክልሉን ተማሪ በሚስብ መልኩ ያለመቅረቡ ለምሳሌ ያህል ለኦሮሚያ ክልል ተማሪ አብዲሳ አጋን፣ ጀነራል ታደሰ ብሩንና የኦሮሚያን ባህል እንዲሁም ትግራይን ባህልን በሚያሳይ መልኩ በይዘቱ ውስጥ ያለመካተቱ በተማሪዎቹ አመለካከትና የመማር ፍላጎት ላይ ተጽእኖ እንዳለው በቡድን ተኮር ውይይተቱ ላይ የተነሱ ሀሳቦች ናቸው።

በተጨማሪም እንደ መንግስት የክልሎቹን ቋንቋ ማሳደግን ዋና ግብ በመደረጉና ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርትንና ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለሚያስተምሩ መምህራን የሙያ ስልጠና ሲሰጥ ነገር ግን በመንግስት በኩል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ለሚገኙ መምህራንን ምንም አይነት የሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንደማይሰጥ በምእራብ ሸዋ ዞንና ከትግራይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረገው ቡድን ተኮር ውይይት ላይ የቀረበው መረጃ ያረጋግጣል። በተለይም በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ዘንድ የአማርኛ ቋንቋ በቀድሞው ስርአት ወቅት ቋንቋው በደል እንደፈጸመ የመመልከት ዝንባሌ መኖሩንና አንዳንድ በሚዲያ (በኦሮሚያና በፌደራል መገናኛ ብዙሀን) የሚተላለፍ መረጃዎች በቋንቋ ትምህርቱ የመማር ፍላጎትና አመለካከት ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድሩ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት የሌለ መሆኑንና ለህዝቡ የሚተላለፍ መረጃዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር በጥንቃቄ ያለመቅረባቸው

በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና አመለካከት ላይ ተጨማሪ ተጽእኖ አሳዳሪ ምክንያቶች መሆናቸውን ከውይይቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከላይ ከቀረበው ዝርዝር ሁኔታዎች አንጻር የቀረቡት ርእስ ጉዳዮች በተማሪዎች አመለካከትና ውጤት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርሱ እንደሚችሉ ከቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የትኞቹ መረጃዎች ሲተላለፉ በተማሪዎች አመለካከትና ፍላጎት ላይ ተጽእኖ እያሳደሩ እንደሚገኙ በጥልቀት የተሰበሰበ መረጃ ስለሌለ በቀጣይ መሰል ጥናት የሚያጠኑ አጥኚዎች ሊመለከቱት ቢችሉ ይሄ ጥናት ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ስለዚህ ከላይ ከቀረበው ርእስ ጉዳይ ላይ ከተሰበሰበው ዝርዝር መረጃ ማረጋገጥ የሚቻለው የመምህራን አመላመል፣ አሰለጣጠንና ስልጥነው ከወጡ በኋላ የትምህርት አሰጣጣቸው ሁኔታ፣ በሚዲያ የሚተላለፉ መረጃዎች፣ የክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን በቋንቋ ትምህርቱ ላይ እያሳደረ ያለው ጫና መሆኑን ከማመልከት አልፎ ርእስ ጉዳዩን በማስመልከት በሌላ ጥናት በጥልቀትና በስፋት ተጠንቶ እያንዳንዱ ችግር በዝርዝር ተለይቶ ቢታወቅና በዙሪያው ያለው ችግር ቢፈታ የሚመረጥ እንደሚሆን ከዚህ ጥናት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

በአጠቃላይ በአመለካከት መመዘኛ ከተሰበሰበሰው መረጃና በቡድን ተኮር ውይይት ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻለው የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ከትግራይና ከአፋር ክልል ተማሪዎች ያነሰ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ከቡድን ተኮር ውይይቱና ከአመለካከት መመዘኛ መጠይቁ ማረጋገጥ የሚቻለው አማርኛ ቋንቋን ከአንደኛ ክፍል መማር የጀመሩት ተማሪዎች ዘግይተው ከሚጀመሩት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ ይህውም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው አዎንታዊ አመለካከትን በተመለከተ

አፋር = አዲስ አበባ > ትግራይ >ኦሮሚያ የሚለውን ያረጋግጣል፡፡

4.3.4..3 በክልል ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ንጽጽር

ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን ትምህርት በሚማሩበት ወቅት በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት በክልል ተማሪዎች ዘንድ ምን ይመስላል? በክልሎች መካከልስ የጎላ ልዩነት አለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ለማረጋገጥ የየክልሉን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ችሎታ ምዘና የአማካይ ውጤት በማነጻጸር ታይቷል። የአማካይ ውጤት ንጽጽሩም በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ /One way Anova/ በመጠቀም የተከናወነ ነው። ልዩነቱም ምክንያታዊ መሆኑን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የተገኘውን የ"F" ዋጋ ከ F የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማነጻጸር ታይቷል። የተስተዋለው ልዩነትም ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት ተተንትኖና ተተርጉሞ በጥናቱ መነሻ ላይ ለተነሳው ጥያቄም እንደሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል።

ሰንጠረዥ ሀያ ስድት፤ መደበኛና አህዛዊ የሆነ የቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና የውጤት ትንተና

| ሳውጦ | ክልል | የመረጃ ሰጪ ብዛት (N) | አማካይ ውጤት($\bar{x}$) | መ/ልይት (S.d) | 95% የአማካይ ልዩነት የአስተማማኝነት ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ውጤት | አፋር | 192 | 67.78 | 13.24 | 65.90 | 69.67 |
| | ኦሮሚያ | 200 | 52.35 | 7.32 | 51.33 | 53.37 |
| | ትግራይ | 198 | 56.05 | 11.42 | 54.44 | 57.64 |
| | አዲስ አበባ | 200 | 69.13 | 11.22 | 67.56 | 70.69 |
| | አጠቃላይ | 790 | 61.41 | 13.16 | 60.35 | 62.19 |

ከላይ በሰንጠረዥ 26 ላይ ማየት እንደሚቻለው የተዘጋጀውን መደበኛ የቋንቋ ፈተና የወሰዱና የተፈተኑ ተማሪዎች አጠቃላይ ቁጥራቸው 790 ነው። የአጠቃላዩ አማካይ ውጤት 61.41 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 13.16 ነው። የየክልሎቹ የትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በተናጠል ሲታይ የአፋር ክልል 67.78፣ የኦሮሚያ 52.35፣ የትግራይ 56.05 እና አዲስ አበባ 69.13 ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ የፈተና አማካይ ውጤት ከአራቱ ክልላዊ መስተዳደሮች አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነው። አማካይ ውጤቱ በተዋረድ ሲታይ

አዲስ አበባ >አፋር > ከትግራይ > ከኦሮሚያ መሆኑን ያመለክታል። የአራቱም ክልሎች አጠቃላዩ የመደበኛ ልይታቸው በአንድ ላይ ሲታይ 13.16 ነው። በተናጠል የየክልሎቹ መደበኛ ልይት ሲታይ የአዲስ አበባ፣ የአፋር፣ የትግራይ እና የኦሮሚያ በቅደም ተከተላቸው መሰረት 11.22፤ 13.24፤ 11.42፣ 7.32 ሲሆን ከአራቱ ከፍተኛ ልዩነት ያለው የአፋር ክልል ሲሆን ዝቅተኛው ልዩነት ያለው ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ነው።

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 26 ላይ በቀረበው የአማካይና መደበኛ ልይት ስሌት መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በአጭር የንጽጽር ትንተና መግለጫ መሰረት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ትናታኔ ተሰጥቶበታል።

**ሰንጠረዥ ሀያ ሰባት ፤ በክልሎቸ መካከል የቋንቋው ትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤት የንጽጽረ ትንተና አጭር መግለጫ**

| ጥገኛ ተላውጦ | የልዩነት ምንጭ | ያጠቃላይ ስኬር | የደርጃ ነጻነት | አማካይ እስኬር | የ(F) ዋጋ | ( P) ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | በቡድን መካከል | 41808.62 | 3 | 13936.21 | 115.41 | .000 |
| | በቡድን ውስጥ | 94911.86 | 786 | | | |
| | ጠቅላላ | 136720.49 | 789 | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ $P \leq 0.01 < 0.05$ ስለዚህ $0.000 < 0.01 < 0.05$

ከላይ በሰንጠረዥ 27 ላይ እንደቀረበው በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በትግራይ ክልልና በክልል በ14 ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የትምህርት አማካይ ውጤት ልዩነትን ለመወሰን በባለ አንድ ገጽታ አማካኝ ውጤት ንጽጽር ትንተና ሲሰላ የተገኘው የ“F” ዋጋ 115.41 ነው። ይሄም (በ3 ጠሪና 786 ቆጣሪ) $\alpha = 0.05$ የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት፤ ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 እና 0.01 የስህተት ይሁንታ መጠን የ“F” ሰንጠረዥ ዋጋ 2.86 እና 3.82 ነው። የተገኘው የ “F” ዋጋ በP=0.000 ደረጃ ላይ 115.41 ስለሆነ ከ“F” የሰንጠረዥ ዋጋ (2.86 እና 3.82) ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ደረጃ ስለሚበልጥ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ

ክልልና በአዲስ አበባ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት የተስተዋለው ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህም የአዲስ አበባና የአፋር ክልል የተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት የውጤት አማካይ ከኦሮሚያና ከትግራይ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር የጎላ ልዩነት ያለ መሆኑን በመረጃ ትንታኔ የተገኘው ውጤት አረጋግጧል፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው የአዲስ አበባና የአፋር ክልል ተማሪዎች ከኦሮሚያና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደዚሁም የትግራይ ክልል ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በቋንቋ ትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ መሆናቸው ጥናቱ ያረጋግጣል፡፡ ነገር ግን በአፋርና በአዲስ አበባ መካከል የተስተዋለው የውጤት ልዩነት የጎላ አለመሆኑን የመረጃው ትንታኔ አመልክቷል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት በዝርዝር ለማየት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ ሀያ ስምንት ፤** በክልል ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርት የምዘና ፈተና ውጤት አማካይ ልዩነት የንጽጽር ትንተና ዝርዝር መግለጫ

ባለብዙ ቡድን ንጽጽር

| ጥገኛ ተላውጦ | (I)ክልል | (J)ክልል | የአማካይ ልዩነት(I-J) | (P)ደረጃ | 95% የጉልህነት ደረጃ ዝቅተኛ | 95% የጉልህነት ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | አፋር | ኦሮሚያ | 15.43* | .000 | 12.57 | 18.29 |
| | | ትግራይ | 11.74* | .000 | 8.88 | 14.61 |
| | ትግራይ | ኦሮሚያ | 3.69* | .005 | 0 .85 | 6.53 |
| | አዲስ አበባ | አፋር | 1.34 | .620 | -1.51 | - 4.20 |
| | | ኦ ሮሚያ | 16.78* | .000 | 13.95 | 19.60 |
| | | ትግራይ | 13.08* | .000 | 10.25 | 15.92 |

*. የአማካይ ልዩነት የአስተማማኝነት ደረጃ 0.05 ላይ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር በክልሎች መካከል የሚስተዋለው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ሁኔታን በተመለከተ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በአዲስ አበባ ተማሪዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ሲታይ የአፋር ከኦሮሚያ በ15.43* በልጦ ተገኝቷል። የአፋር ከትግራይ ደግሞ በ11.74* በልጦ ተገኝቷል። በኦሮሚያና በትግራይ መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በተመለከተ ትግራይ ከኦሮሚያ በ3.69* በልጦ ተገኝቷል። አዲስ አበባ ከአፋር በ1.34፣ ከኦሮሚያ 16.78* እና ከትግራይ በ13.08* የአማካይ ውጤት ብልጫ አሳይቷል። ከዚህ አንጻር በክልል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት መካከል የተስተዋለው ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው። ስለዚህ በሚከተለው መሰረት ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ከላይ በቀረበው መሰረት በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለውን የችሎታ ምዘና የአማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ላይ ሆኖ ልዩነቱ 15.43* ልዩነት አሳይቷል። ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 እና ከα=0.01 የስህተት ይሁንታ አንሶ (0.000< 0.05<0.01) ስለተገኘ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ነው። ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው በአፋርና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል ሰፊ የአማካይ ውጤት ልዩነት መኖሩን ያረጋግጣል። ስለዚህ በአፋርና በትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ሰፊ ሲሆን የትግራይ ክልል ከአፋር ክልል ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር የP ደረጃ P=0.000 ላይ ሆኖ በ11.74* አንሶ ተገኝቷል። ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 እና ከα=0.01 የስህተት ይሁንታ አንሶ (0.000< 0.05<0.01) ስለተገኘ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ነው። ስለዚህ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው የአፋር ክልል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ከትግራይ ክልል ተማሪዎች መብለጡን ነው። ይሄም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የአፋር ክልል ከኦሮሚያና ከትግራይ ክልል በልጦ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱን አስመልክቶ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ ነው።

በአፋርና በክልል 14 ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የትምህርት የፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=.620 ላይ ሆኖ የአፋር ክልል ከአዲስ አበባ በ1.34 አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታው α=0.05 እና α= 0.01 ስለሚበልጥ (0.620 > 0.05> 0.01) በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ በአፋርና በክልል 14 ተማሪዎች

መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ አይደለም፡፡ ከዚህም ማረጋገጥ የሚቻለው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመዘገበ ውጤት ሲታይ በአፋር ክልልና በክልል በ14 መካከል ልዩነት አለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡

በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና የተመዘገበ አማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.005 ላይ ሆኖ ትግራይ ከኦሮሚያ በ3.69* በልጦ ሲገኝ ኦሮሚያ ደግሞ በ3.69* አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከα=0.05 እና ከα=0.01 የስህተት ይሁንታ አንሶ (0.000< 0.05<0.01) ስለተገኘ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ሲታይ የትግራይ ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በውጤት በልጠው መገኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡

በክልል 14 ና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአማርኛ ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ ክልል 14 ከኦሮሚያ በ16.78* በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታው ከα=0.05 እና α=0.01 ካነሰ (0.00 < 0.05 < 0.01) በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካኝ ውጤት ልዩነት ጉልህ ነው፡፡ ስለዚህ የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታው α=0.01 እና α=0.01 ያነሰ ስለሆነ በክልል 14ና በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ልዩነቱ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በክልል 14 ና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የአማካይ ውጤት ልዩነት የP ደረጃ P=0.000 ሆኖ ክልል 14 ከትግራይ ክልል በ13.08* በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም የP ዋጋ ከስህተት ይሁንታው α=0.05 እና α=0.01 ካነሰ(0.000 < 0.05<0.01) በሁለቱ ክልሎች መካከል የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህና ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው በክልል 14 እና ከትግራይ ክልል ተማሪዎች መካከል በቋንቋው ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት የትግራይ ክልል ከክልል 14 ተማሪዎች አንሶ ተገኝቷል፡፡ በሌላ አገላለጽ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የክልል 14 ተማሪዎች ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በልጦ መገኘቱንና ልዩነቱ ሰፊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በክልሎች

መካከል የሚስተዋል ተመሳስሎና ልዩነት በግልጽ ለማየት የአማካኝ ውጤት የንጽጽር ደረጃ የሚያርፍበትን ቦታ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

**ሰንጠረዥ ሀያ ዘጠኝ ፡ የችሎታ ምዘና ውጤት በተመሳሳይ ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ክልሎች መግለጫ**

| | | | የስብስብ ሁኔታ α= 0.05 (Subset for alpha = .05 ) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጥገኛ ተላውጦ | ክልል | ብዛት (N) | 1 | 2 | 3 |
| ውጤት | ኦሮሚያ | 200 | 52.35 | | |
| | ትግራይ | 198 | | 56.05 | |
| | አዲስ አበባ | 200 | | | 69.13 |
| | አፋር | 192 | | | 67.78 |
| | P | | 1 | 1 | 0.617 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 29 ላይ ማየት እንደሚቻለው የአራቱም አማካይ ውጤቶች በα=0.05 የስህተት ይሁንታ መጠን ላይ ሲታይ በሶስት የተለያየ ረድፍ ላይ የተቀመጡ ሲሆን አዲስ አበባና አፋር ክልል ግን በተመሳሳይ ረድፍ (ስብስብ) ላይ ተገኝተዋል፡፡ የህም ማለት በሁለቱ ክልሎች መካከል ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም አንድነት ያላቸው ሲሆን የተቀሩት ክልሎች ረድፋዊ ተመሳስሎ ወይንም አንድነት የላቸውም፡፡ ስለዚህ በክልል ተማሪዎች መካከል ለህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ምዘና አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት ያለ ቢሆንም በአዲስ አበባና በአፋር ክልል በአንድ የረድፍ ስብስብ ውስጥ ስለሚገኙ ረድፋዊ ተመሳስሎ/አንድነት/ አላቸው፡፡ ከዚህም ማረጋገጥ የሚቻለው በየክልሎቹ የሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት የአማካይ ውጤት በንጽጽር ሲታይ በአዲስ አበባና በአፋር ክልል መካከል ካለ ተመሳስሎ በስተቀር በሌሎቹ ላይ ልዩነቱ ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በነጠላ ገጽታ የልይይት ትንተና ዘዴ (one way anova) ቀመር ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.3.4.4 ከጾታ አንጻር ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነው አማርኛ በሁለተኛ የቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት አለን? ከእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ቀደም ብሎ በሌሎች ሀገሮች የነበረው ጽንሰ ሃሳብ በዚህ ሀገር ይሰራል? የሚለውን ጥያቄ በዚህ ጥናት ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ የህብረብሄር ተማሪዎች ቋንቋውን የመማር ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የሶስቱ ተላውጦዎች አማካይ (Mean) በማስላትና በማነጻጸር ለማየት ተችሏል፡፡ በንጽጽሩ የተገኘውን የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የአማካይ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከተገኘው የ“t” ቴስት ውጤትና ከስህተት ይሁንታ ከ0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማስተያየት ትርጓሜ ተሰጥቷል፡፡ የተሰጠው ትርጓሜም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ሰላሳ ፤ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ክልሎች በወንድና በሴት መካከል የሚስተዋል የአማካይ ልዩነትን ለማየት ሲባል የተከናወነ የቡድን ስሌት

| ተላውጦ | ፆታ | N መረጃ ሰጪዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ሴት | 296 | 72.12 | 11.78 |
| | ወንድ | 294 | 72.29 | 13.97 |
| አመለካከት | ሴት | 296 | 48.24 | 8.19 |
| | ወንድ | 294 | 47.20 | 8.20 |
| ውጤት | ሴት | 296 | 59.77 | 12.96 |
| | ወንድ | 294 | 57.45 | 12.36 |

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ ማየት እንደሚቻለው ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 72.12 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 11.78 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 72.29 መደበኛ ልዩነቱ 13.97 ሲሆን ነው፡፡ የሴቶች የአመለካከት አማካይ ውጤት 48.24 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 8.19 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 47.20 መደበኛ ልዩነቱ 8.20 ነው፡፡ የሴቶች የትምህርት ውጤት አማካይ 59.77 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 12.96 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 57.45 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 12.36 ነው፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ወንዶች ከሴቶች 0.17 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ለትምህርቱ ባለ አመለካከት ዙሪያ ደግሞ ሴቶች ከወንዶች በ1.04 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ በትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤትም ሴቶች ከወንዶች በ2.32 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ለመለየት በ‹‹t›› ቴስት ስሌት ተሰልቶ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ሠንጠረዥ ሰላሳ አንድ ፤ ከጾታ አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ክልሎች ላይ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ንጽጽር

| ተላውጦ | የ አማካይ ልዩነት | የደረጃ ነጻነት | ‹‹t›› ቴስት | የ (P) ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | 0.17 | 570 | 0.16 | .875 |
| አመለካከት | 1.04 | 587 | 1.54 | .123 |
| ውጤት | 2.32 | 587 | 2.23 | .026 |

የአስተማማኝ ደረጃ $P \leq 0.01 < 0.05$

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ ማየት እንደሚቻለው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ ያታዊ ልዩነትን መሰረት በማድረግ የትምህርት ፍላጎት፣ የአመለካከትና የምዘና ፈተና ውጤትን መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት(Mean difference) በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ የተገኘው የውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ570 የነጻነት ደረጃና በአቅጣጫ የለሽ መላምት፤ ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ$\alpha$=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ታይቷል፡፡ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ

P= 0.875 ሆኖ የተገኘው የ"t"ቴስት ውጤት 0.17 ነው፡፡ የተገኘው የ"t"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ570 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"t"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በ α=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ ውጤት መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በፆታ መካከል ተገኘው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በፆታ መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ከአመለካከት አንጻር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ የሚስተዋል የአመለካከት ያታዊ ልዩነትን በተመለከተ የአማካይ ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት አስተማማኝ ልዩነትና ጉልህ መሆኑን በ0.05 ላይ ታይቷል፡፡ በስህተት ይሁንታው ላይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ588 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ለትምህርቱ ያለ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.12 ሆኖ የ‹‹t››ቴስት ውጤት/ዋጋ/1.54 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t›› ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ588 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ‹‹t››ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በፆታ መካከል ያለው የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በፆታ መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የአመለካከት ልዩነነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

ከችሎታ ምዘና ውጤት አንጻር ልዩነት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያታዊ ልዩነት መኖሩን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶና በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ በሚችለው በ587 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ወይንም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ ላይ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=026 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ‹‹t››ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 2.23 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት

ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ588 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ‹‹t››ቴስት ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ችሎታ ምዘና ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በፆታ መካከል ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ውጤታማ መሆናቸውን የተገኘው የትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

#### 4.3.4.4.1 በአፋር ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

የአፋር ክልል ተማሪዎች ቋንቋውን የመማር ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የሶስቱን ተላውጦዎች አማካይ (Mean) በማስላትና በማነጻጸር ለማየት ተችሏል፡፡ በንጽጽሩ የተገኘውን የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የአማካይ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከተገኘው የ"ቲ" ቴስት ውጤትና ከስህተት ይሁንታ ከ0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማስተያየት ትርጓሜ ተሰጥቷል፡፡ የተሰጠው ትርጓሜም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሁለት ፡ በአፋር በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካኝ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

| ተላውጦ | ፆታ | N ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይት | ( t) ቴስት | Df የደረጃ ነጻነት | P ዋጋ | የአማካይ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ሴት | 96 | 80.32 | 13.71 | - 1.60 | 189 | .111 | -3.10 |
| | ወንድ | 96 | 83.42 | 13.15 | | | | |
| አመለካከ | ሴት | 96 | 53.62 | 8.21 | 2.85 | 187 | .005 | 3.19 |
| | ወንድ | 96 | 50.44 | 7.25 | | | | |
| ውጤት | ሴት | 96 | 70.50 | 13.70 | 2.90 | 188 | .004 | 5.44 |
| | ወንድ | 96 | 65.06 | 12.25 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 32 ላይ ማየት እንደሚቻለው ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 80.32 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 13.71 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 83.42 መደበኛ ልዩነቱ 13.15 ነው፡፡ የሴቶች የአመለካከት አማካይ ውጤት 53.62 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 8.21 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 50.44 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 7.25 ነው፡፡ የሴቶች የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት አማካይ 70.50 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 13.70 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 65.06 መደበኛ ልዩነቱ 12.15 ነው፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ወንዶች ከሴቶች 3.10 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ለትምህርቱ ባለ አመለካከት ዙሪያ ደግሞ ሴቶች ከወንዶች በ3.19 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ በትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤትም ሴቶች ከወንዶች በ5.44 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ ልዩነት አንጻር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ በፆታዊ ልዩነት አንጻር የትምህርት ፍላጎት፣ የአመለካከትና የምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የተገኘው የማካይ ልዩነት(Mean difference) በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ የተገኘው የውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ189 የነጻነት ደረጃና፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ታይቷል፡፡ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.11 ላይ

ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 1.60 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ182 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ‹‹t›› ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም በፆታ መካከል የተገኘው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በአፋር ክልል ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል።

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ የሚስተዋል ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት አስተማማኝ የሆነ ልዩነት መኖሩን ወይም ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ187 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ (የስህተት ይሁንታ)፣ ላይ ለትምህርቱ ያለ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.005 ሆኖ "ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/2.85 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ187 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ አንሶ ተገኝቷል። በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በአፋር ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ሴቶች ከወንዶች በተሻለ አዎንታዊ የአመለካከት ያላቸው መሆኑን ከተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል።

በአፋር ክልል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ፆታዊ ልዩነት መኖሩን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የኣማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶና በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ188 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ ላይ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ ተሰልቶ የተገኘው የ (P) ዋጋ 0.004 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 2.90 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ188 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ

የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በአፋር ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ችሎታቸው ከፍተኛ ሆኖ መገኘቱን ነው።

### 4.3.4.4.2 በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በጾታ መካከል የሚስተዋል የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች የአማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት የመማር ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል መረጃ ተሰብስቧል። በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የሶስቱ ተላውጦዎች አማካይ (Mean) በማስላትና በማነጻጸር ለማየት ተችሏል። በንጽጽሩ የተገኘውን የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ቀርቧል። ከዚህ አንጻር የአማካይ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከተገኘው የ"ቲ" ቴስት ውጤትና ከስህተት ይሁንታ ከ0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማስተያየት ትርጓሜ ተሰጥቷል። የተሰጠው ትርጓሜም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሶስት፤ በኦሮሚያ ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

| ተላውጠ | ፆታ | N ብዛት | አማካ | መደበኛ ልይት | T ቴስት | Df የነጻነ | P ዋጋ | የአማካይ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ሴት | 100 | 64.1 | 5.74 | .135 | 182 | .893 | .96 |
| | ወንድ | 100 | 63.97 | 7.73 | | | | |
| አመለካከት | ሴት | 100 | 44.56 | 6.66 | .88 | 193 | .381 | 0.9 |
| | ወንድ | 100 | 43.66 | 7.79 | | | | |
| ውጤት | ሴት | 100 | 52.97 | 6.42 | 1.20 | 188 | .232 | 1.24 |
| | ወንድ | 100 | 51.73 | 8.10 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 33 ላይ ማየት እንደሚቻለው ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 64.1 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 5.74 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 63.97 መደበኛ ልዩነቱ 7.73 ነው፡፡ የሴቶች የአመለካከት አማካይ ውጤት 44.56 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 6.66 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 43.66 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 7.79 ነው፡፡ የሴቶች የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት አማካይ 52.97 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 6.42 ነው፡፡ የወንድ ደግሞ 51.73 መደበኛ ልዩነቱ 8.10 ነው፡፡ ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ሴቶች ከወንዶች 0.89 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ለትምህርቱ ባለ አመለካከት ዙሪያ ደግሞ ሴቶች ከወንዶች በ0.9 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ በትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤትም ሴቶች ከወንዶች በ1.24 በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ ልዩነት አንጻር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ"ቲ" ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በሚከተለው መልኩ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ በፆታዊ ልዩነትን መሰረት በማድረግ የትምህርት ፍላጎት፣ የአመለካከትና የትምህርት ችሎታ ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት(Mean difference) በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ የተገኘው የውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን

በ182 የነጻነት ደረጃና፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ታይቷል። የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.893 ላይ ሆኖ የተገኘው የ"t"ቴስት ውጤት 0.135 ነው። የተገኘው የ"t"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ182 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ‹‹t››ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም በፆታ መካከል የተገኘው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ የሚስተዋል ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት አስተማማኝ ልዩነትና ጉልህ መሆኑን በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ193 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ለትምህርቱ ያለ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.38 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"t"ቴስት ውጤት/ዋጋ/0.88 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ193 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"t"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.86 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል። በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነቱ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል የአመለካከት ልዩነት ያሌለ መሆኑን ነው

በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶና በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ188 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ ላይ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር

ሲሰላ P=023 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 1.20 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ188 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል በአማርኛ ቋንቋ የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት ያለመኖሩን ነው፡፡

#### 4.3.4.4.3 በትግራይ ክልል ተማሪዎች በጾታ መካከል የሚስተዋል የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

የትግራይ ክልል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት የመማር ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የሶስቱ ተላውጦዎች አማካይ (Mean) በማስላትና በማነጻጸር ለማየት ተችሏል፡፡ በንጽጽሩ የተገኘውን የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የአማካኝ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከተገኘው የ"ቲ" ቴስት ውጤትና ከስህተት ይሁንታ ከ0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማስተያየት ትርጓሜ ተሰጥቷል፡፡ የተሰጠው ትርጓሜም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሰላሳ አራት ፤ በትግራይ ክልል በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

| ተላውጦ | ፆታ | N ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይት | “ቲ” ቴስት | Df የጳነትደረጃ | P ዋጋ | የአማካይ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ሴት | 100 | 72.31 | 8.50 | 1.49 | 168 | .14 | 1.55 |
| | ወንድ | 98 | 70.00 | 12.87 | | | | |
| አመለካ | ሴት | 100 | 46.75 | 6.85 | -.83 | 189 | .41 | 1.07 |
| | ወንድ | 98 | 47.63 | 8.15 | | | | |
| ውጤት | ሴት | 100 | 56.26 | 10.43 | .27 | 189 | .79 | 1.63 |
| | ወንድ | 98 | 55.82 | 12.40 | | | | |
| የአስተማማኝ ደረጃ | | P≤ 0.01 | ወይም | P≤ 0.05 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 34 ላይ ማየት እንደሚቻለው ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 72.31 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 8.50 ነው። የወንድ ደግሞ 70.00 መደበኛ ልዩነቱ 12.87 ነው። የሴቶች የአመለካከት አማካይ ውጤት 46.75 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 6.85 ነው። የወንድ ደግሞ 47.63 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 8.15 ነው። የሴቶች የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት አማካይ 56.26 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 10.43 ነው። የወንድ ደግሞ 55.82 መደበኛ ልዩነቱ 12.40 ነው። ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ሴቶች ከወንዶች 1.55 በልጠው ተገኝተዋል። ለትምህርቱ ባለ አመለካከት ዙሪያ ደግሞ ወንዶች ከሴቶች በ1.07 በልጠው ተገኝተዋል። በትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤትም ሴቶች ከወንዶች በ1.63 በልጠው ተገኝተዋል። ከዚህ ልዩነት አንጻር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ“ቲ” ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በሚከተለው መልኩ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

ከላይ በሰንጠረገዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ሂደት ላይ በፆታዊ ልዩነትን መሰረት በማድረግ የትምህርት ፍላጎት፣ የአመለካከትና የትምህርት ችሎታ ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ የተገኘው የውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ168 የነጻነት ደረጃና በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ታይቷል፡፡ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.14 ላይ ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 1.49 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ168 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በትግራይ ክልል በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በፆታ መካከል የተገኘው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ በትግራይ ክልል ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ የሚስተዋል ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ189 የነጻነት ደረጃ ላይ ታይቷል፡፡ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ወይም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ለትምህርቱ ያለ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነት በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.83 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/0.41 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ189 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በትግራይ ክልል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በትግራይ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለመኖሩን የመረጃ ትንታኔው ያረጋግጣል፡፡

በትግራይ ክልል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶና በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ189 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ ላይ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.79 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 0.79 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ189 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በትግራይ ክልል ትምህርቱን ለመማር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል በአማርኛ ቋንቋ በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ማረጋገጥ የሚቻለው በትግራይ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል ትምህርቱን ለመማር ያለ ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያለ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት መካከል ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ያረጋግጣል፡፡

## 4.3.4.4.4 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

የክልል 14 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በትምህርትነት የመማር ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የሶስቱ ተላውጦዎች አማካይ (Mean) በማስላትና በማነጻጸር ለማየት ተችሏል፡፡ በንጽጽሩ የተገኘውን የውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የአማካይ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከተገኘው የ"ቲ" ቴስት ውጤትና ከስህተት ይሁንታ ከ0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማስተያየት ትርጓሜ

ተሰጥቷል። የተሰጠው ትርጓሜም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ሰላሳ አምስት ፤** በአዲስ አበባ በጾታ መካከል የሚስተዋል የቡድን የአማካ ይ ልዩነት ንጽጽር ስሌት

| ተላውጠ | ፆታ | N ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት | T ቴስተ | Df የጻነት ደረጃ | P ዋጋ | የአማካይ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ሴት | 97 | 75.20 | 10.78 | .31 | 195 | .76 | .51 |
| | ወንድ | 103 | 74.69 | 13.00 | | | | |
| አመለካከት | ሴት | 97 | 52.21 | 8.81 | 1.45 | 183 | .14 | 1.63 |
| | ወንድ | 103 | 50.58 | 6.97 | | | | |
| ውጤት | ሴት | 97 | 70.47 | 11.82 | 1.65 | 192. | .10 | 2.62 |
| | ወንድ | 103 | 67.85 | 10.53 | | | | |
| የአስተማማኝ ደረጃ | | $P \leq 0.01$ | ወይም | $P \leq 0.05$ | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 35 ላይ ማየት እንደሚቻለው ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 75.20 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 10.78 ነው። የወንድ ደግሞ 74.69 መደበኛ ልዩነቱ 13.00 ነው። የሴቶች የአመለካከት አማካይ ውጤት 52.21 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 8.81 ነው። የወንድ ደግሞ 50.58 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 6.97 ነው። የሴቶች የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት አማካይ 70.47 ሲሆን መደበኛ ልዩነቱ 11.82 ነው። የወንድ ደግሞ 67.85 መደበኛ ልዩነቱ 10.53 ነው። ከዚህ መመልከት እንደሚቻለው ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ሴቶች ከወንዶች 0.51 በልጠው ተገኝተዋል። ለትምህርቱ ባለ አመለካከት ዙሪያ ደግሞ ሴቶች ከወንዶች በ1.63 በልጠው ተገኝተዋል። በትምህርቱ የችሎታ ምዘና ውጤትም ሴቶች ከወንዶች በ2.62 በልጠው ተገኝተዋል። ከዚህ ልዩነት አንጻር ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ"ቲ" ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በሚከተለው መልኩ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ ማየት እንደሚቻለው የአማርኛ  ቋንቋ ትምህርትነትን በመማር ሂደት ላይ ፆታዊ ልዩነትን መሰረት በማድረግ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት፣ የአመለካከትና የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት በሂሳባዊ ስሌት ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t›› ቴስት ቀመር ተሰልቶ ቀርቧል። የተገኘው የውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ መሆኑን በ195 የነጻነት ደረጃና በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ α=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ታይቷል። የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.76 ላይ ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት .31 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን  በ195 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ" ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.86 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት  ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም በፆታ መካከል ተገኘው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ሆኖ ያለመገኘቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት  አመለካከት ላይ የሚስተዋል ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶ  የተገኘው ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ጉልህ ልዩነት መሆኑን በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ183 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ α=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ ለትምህርቱ ያለ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=.14 ሆኖ  የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 1.45 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ183 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ1.94 ነው። የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር  በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማርኛን በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለመኖሩን ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ፆታዊ ልዩነትን በተመለከተ ተሰልቶ የተገኘው የአማካይ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር ተሰልቶና በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ192 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻ ላይ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P= .10 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የ"ቲ"ቴስት ውጤት/ዋጋ/ 1.65 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ192 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.86 ነው፡፡ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት አለመኖሩን ከመ

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ማረጋገጥ የሚቻለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማርኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት መካከል ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

## 4.3.4.5 ከገጠርና ከከተማ ተማሪዎች አንጻር የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርነት ለመማር ያላቸውን ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡትን ውጤት በተመለከተ በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል የጎላ ልዩነት አለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም ከሁለቱ የመኖሪያ አካባቢ አንጻር የተማሪዎች የመማር ፍላጎት፣ የአመለካከትና በትምህርቱ የተመዘገበ ውጤት አማካይ(Mean) በማስላት የሶስቱንም የተላውጦዎች ውጤት በማነፃፀር የውጤቱን ምክንያታዊ ልዩነት በ‹‹t››ቴስት ቀመር መሠረት ተሰልቶ ንጽጽሩ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡ የንጽጽር ውጤቱን ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ማየት ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ ሰላሳ ስድት፤ ከመኖሪያ ቦታ አንጻር የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

ቡድናዊ ሂሳባዊ ሌት

| ተላውጠ | አካባቢያዊ ሁኔታ | (N) የመረጃ ሰጪዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ከተማ | 310 | 75.09 | 12.89 |
| | ገጠር | 280 | 69.01 | 12.17 |
| አመለካከት | ከተማ | 310 | 49.00 | 8.35 |
| | ገጠር | 280 | 46.30 | 7.82 |
| ውጤት | ከተማ | 310 | 61.35 | 12.94 |
| | ገጠረ | 280 | 55.57 | 11.75 |

ከላይ በሰንጠረገፑ ላይ ማየት በእንደሚቻለው የመረጃ ሰጪዎች ብዛት 590 ሆነው ከነዚህ ውስጥ የከተማ ተማሪዎች 310 የሚሆኑ የገጠር ተማሪዎች 280 ናቸው፡፡ ከነዚህ ተጠኚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የከተማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 75.09 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 12.89 ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 49.00 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 8.38 ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 61.35 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 12.94 ነው፡፡

የገጠር ተማሪዎቹ ደግሞ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 69.01 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 12.17 ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 46.30 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 7.82 ነው፡፡ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 55.57 ሲሆን መበኛ ልይቱ ደግሞ 11.75 ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ሲታይ በሶስቱም ተላውጠዎች የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጠ ተስተውሏል፡፡ በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በ"ቲ" ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሰላሳ ሰባት፤ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር

የt- ቴስት አማካይ ውጤት ንጽጽር

| ተላውጠ | የአማካይ ውጤት ልዩነት | df የነጻነት ደረጃ | t ቴስት | የ (p) ዋጋ | 95% የአስተማማኝነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ፍላጎት | 6.07 | 587 | 5.88 | .000 | 4.05 | 8.10 |
| አመለካከት | 2.70 | 587 | 4.05 | .000 | 1.39 | 4.00 |
| ውጤት | 5.78 | 588 | 5.69 | .000 | 3.79 | 7.78 |

የጉልህነት ደረጃ ማረጋገጫ $P \leq 0.01 < 0.05$

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ6.07 በልጦ ተገኝቷል። የገጠር ደግሞ በ6.07 ያነሰ ነው። ስለዚህ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 6.07 ነው። በ587 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ α=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ(Mean difference) በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P= 0.00 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 5.88 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ587 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.645 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.327 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በ α=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል። በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በገጠርና በከተማተ ተማሪዎች መካከል ያለው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ በሁለቱ ቦታዎች(ገጠርና ከተማ) መካከል ያለው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ የሆነ ልዩነት ስለሆነ በከተማ ተማሪና በገጠር ተማሪ መካከል ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ጥናቱ ያረጋግጣል።

ከቦታ አንጻር ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካትን በተመለካከተ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል። ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ2.70 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ2.70 ያነሰ ነው። ስለዚህ አማካይ ውጤቱ በ2.70 ልዩነት አሳይቷል። የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ587 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.00 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 4.05 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ587 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.645 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.327 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ የሆነ ልዩነት በመሆኑ በከተማ ተማሪዎችና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሲታይ የከተማው ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ያረጋግጣል። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ሲታይ በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለ መሆኑንና ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ የከተማ ተማሪዎች ለሕብረ ብሄር የቋንቋ ትምህርት ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ መልኩ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ጥናቱ ያረጋግጣል።

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት ከቦታ አንጻር ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ የሚያስመዘግቡትን ውጤት በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል። ይሄውም ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ5.78 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ5.78 ያነሰ ነው። በሁለቱ አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት 5.78ነው። የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ587 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.00 ሆኖ የተገኘው

የ"ቲ"ቴስት ውጤት 5.69 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ587 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.645 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.327 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የትምህርት ፈተና የአማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ያረጋግጣል። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የፈተና የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ የሆነ ልዩነት ስላለው በከተማ ተማሪዎችና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ውጤት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ውጤቱ ያረጋግጣል። ከመምህራኑ በቀረበ አስተያየት መሰረት በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የችሎታ ክፍተት ስላለ ክፍተቱን ለማጥበብ ሲባል ተጨማሪ የስራ ጫና እያሳደረባቸው እንደሆነ ገልጸው ለልዩነቱ ምክንያት ነው ብለው ከገለጹት ውስጥ አንደኛው ለቋንቋው ያለው የተጋላጭነት መጠን ዝቅተኛ መሆን ነው ሲሉ፤ ሁለተኛው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቋንቋውን የሚያስተምሩ የመምህራን አቅምና የዝግጁነት ችግር መኖሩ ነው ሲሉ፤ ሶስተኛው ደግሞ ትምህርቱን ዘግይተው ከሶስተኛ ክፍል መማር ስለሚጀምሩ እንደሆነ ገልጸዋል።

ስለመምህራን ምልመላ በድጋሚ ለቀረበው ጥያቄም ሲመልሱ፤ መምህራኑ ለመምህርነት ሲመለመሉ የክልሉን ቋንቋ በደንብ ካወቁ በቂ ነው ተብሎ ስለሚገመት የአማርኛ ቋንቋን አወቁትም አላወቁትም በኮሌጅ የተወሰነ ስልጠና ተሰጥቷቸው አማርኛ ቋንቋን በብቃት ያስተምራሉ በሚል እሳቤ ስላለ ቋቋውን እንዲያስተምሩ በመደረጉ ምክንያት ነው። ስለዚህ ቋንቋውን ለማስተማር የአቅምና የዝግጁነት ክፍተት እንዲከሰት መንስኤ እንደሆነ ሀሳባቸውን አቅርበዋል። በተጨማሪም የክልሉ ትምህርት ቢሮም እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ለትምህርቱ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ ስለሆ የአሉታዊ ተጽእኖ መጠኑ በገጠር ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት በገጠሮቹ ላይ የቋንቋ ችሎታ ውስንነት እንዳለባቸው ከሁለተኛ ደረጃ መምህራን ጋር በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ላይ የተሰበሰበው መረጃ ያስረዳል።

ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው አማርኛን በሁለቱነት በሚማሩ የተማሪዎች ላይ ባለው አካባቢያዊ ልዩነት አንጻር የትምህርቱ የችሎታ ምዘና ፈተና የአማካይ ውጤት ሲታይ የጎላ የጎላ ልዩነት መኖሩን የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል። በከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበው ተስተውለዋል። ስለዚህ የከተማ ተማሪዎች በሕብረ

ብሄር የጋራ ቋንቋ በሆነው ትምህርት ውጤት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች አንጻር ሲታይ በተሻለ መልኩ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ጥናቱ ያረጋግጣል፡፡

### 4.3.4.5.1 በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት በተመለከተ ክልሎቹ በተናጠል ሲታዩ

ከላይ በተራ ቁጥር 4.3.4.5 ላይ በቀረበው መሰረት ክልሎቹ በተናጠል ሲታዩ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት ምን እንደሚመስል ለማየት ሲባል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 4.3.4.5.1.1 በአፋር ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በአፋር ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና የውጤት ልዩነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሰላሳ ስምንት፤ በአፋር ክልል ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

ቡድናዊ ሂሳባዊ ስሌት

| ተላውጦ | አካባቢያዊ ሁኔታ | (N) የመረጃ ሰጪዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ከተማ | 111 | 84.32 | 13.44 |
| | ገጠር | 81 | 78.52 | 12.89 |
| አመለካከት | ከተማ | 111 | 53.70 | 8.18 |
| | ገጠር | 81 | 49.74 | 6.88 |
| ውጤት | ከተማ | 111 | 70.22 | 13.12 |
| | ገጠረ | 81 | 64.44 | 12.75 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት በእንደሚቻለው የመረጃ ሰጪዎች ድምር 192 ሆነው ከነዚህ ውስጥ የከተማ ተማሪዎች 111 ሲሆኑ የገጠር ተማሪዎች 81 ናቸው። ከነዚህ ተጠኚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የከተማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 84.32 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 13.44 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 53.70 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 8.18 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 64.44 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 13.12 ነው።

የገጠር ተማሪዎቹ ደግሞ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 78.52 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 12.89 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 49.74 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 6.88 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 64.44 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 12.75 ነው። ከዚህ አንጻር በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ሲታይ በሶስቱም ተላውጦዎች የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ ተስተውሏል። በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በ"ቲ" ቴስት ስሌት መሰረት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ሰላሳ ዘጠኝ፤ በአፋር በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር**

| | | t- ቴስት | አማካይ ውጤት ንጽጽር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተላውጦ | የአማካይ ውጤት ልዩነት | Df የነጻነት ደረጃ | t ቴስት | የ(p) ዋጋ | 95% የአስተማማኝነት ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ፍላጎት | 5.80 | 176 | 3.03 | .003 | 9.61 | 1.10 |
| አመለካከት | 3.96 | 186 | 3.54 | .001 | 2.02 | 6.17 |
| ውጤት | 5.77 | 175 | 3.06 | .003 | 2.05 | 9.49 |

የጉልህነት ደረጃ ማረጋገጫ $P \leq 0.01 < 0.05$

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ5.80 በልጦ ተገኝቷል፡፡ የገጠር ደግሞ በ5.80 ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 5.80 ነው፡፡ በ176 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ(Mean difference) በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P= 0.003 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 3.03 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ176 የደረጃ ነፃነት ላይ በ0.05 ላይ እና 0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ሲሆን በα=0.01 ላይ ደግሞ 2.58 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በአፋር ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ትምህርቱን ለመማር ባለ የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ቦታዎች(ገጠርና ከተማ) መካከል ያለው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ የሆነ ልዩነት ስለሆነ በአፋር ክልል በከተማ ተማሪና በገጠር ተማሪ መካከል ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ ሲሆን በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ጥናቱ ያረጋግጣል፡፡

በአፋር ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ከላይ በሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የአመለካከት የአማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ3.96 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ3.96 ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ አማካይ ውጤቱ በ3.96 ልዩነት አሳይቷል፡፡ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ186 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ የP= 0.001 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 3.64 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ186 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.58 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አኳያ

በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ በመሆኑ በከተማ ተማሪዎችና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ መሆኑን ከትንታኔው የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ በአፋር ክልል የከተማ ተማሪዎች ለሕብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ ትምህርት ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ መልኩ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ጥናቱ ያረጋግጣል፡፡

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት በአፋር ክልል የገጠርና የከተማ ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርቱ የሚያስመዘግቡትን ውጤት በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ይሄውም ከላይ ከሠንጠረገፁ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡት ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ5.77 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ5.77 ያነሰ ነው፡፡ በሁለቱ አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት 5.77ነው፡፡ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ  በ176 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P= 0.003 ሆኖ የተገኘው የ“ቲ”ቴስት ውጤት 3.06 ነው፡፡ የተገኘው የ“ቲ”ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ176 የደረጃ ነፃነት ላይ በ α=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ“ቲ”ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.576 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በ0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ  ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አኳያ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የትምህርት ፈተና የአማካይ  ልዩነት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት  ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ በአፋር ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያለ አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ በሚመዘገብ ውጤት መካከል የሚስተዋል ልዩነትን ለማየት በተደረገ የውጤት ንጽጽር መሰረት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ መልኩ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ በትምህርቱ ያለ አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት  ውጤት ከፍተኛ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.3.4.5.1.2 በኦሮሚያ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና የውጤት ልዩነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አርባ ፤ በኦሮሚያ ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

ቡድናዊ ሂሳባዊ ስሌት

| ተላውጦ | አካባቢያዊ ሁኔታ | (N) የመረጃ ሰጪዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ከተማ | 93 | 66.06 | 6.79 |
| | ገጠር | 07 | 62.27 | 6.32 |
| አመለካከት | ከተማ | 93 | 44.87 | 7.19 |
| | ገጠር | 107 | 43.45 | 7.25 |
| ውጤት | ከተማ | 93 | 53.60 | 8.30 |
| | ገጠረ | 107 | 51.26 | 6.17 |

ከላይ በሰንጠረገዡ ላይ ማየት በእንደሚቻለው የኦሮሚያ ክልል የመረጃ ሰጪዎች ድምር 200 ሆነው ከነዚህ ውስጥ የከተማ ተማሪዎች 93 ሲሆኑ የገጠር ተማሪዎች 107 ናቸው። ከነዚህ ተጠኚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የከማ ተማሪቹ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 66.6 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 6.79 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 44.87 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 7.19 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 53.60 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 8፣30 ነው።

የገጠር ተማሪዎቹ ደግሞ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 62.27 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 6.32 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካኝ ውጤት 43.45 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 7.30 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 51.26 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 6.18 ነው። ከዚህ አንጻር በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ

ተማሪዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ሲታይ በሶስቱም ተላውጦዎች(በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት) የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ ተስተውሏል። በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በ "t" ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አርባ አንድ፤ በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ውጤት የልዩነት ንጽጽር

| t- ቴስት | አማካይ ውጤት ንጽጽር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተላውጦ | የአማካ ውጤት ልዩነት | Df የነጻነት ደረጃ | ( t) ቴስት | የ(p) ዋጋ | 95% የአስተማማኝነት | |
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ፍላጎት | 3.79 | 189 | 4.07 | .00 | 1.97 | 5.63 |
| አመለካከት | 1.38 | 194 | 1.39 | .18 | .60 | 3.44 |
| ውጤት | 2.24 | 168 | 2.28 | .02 | .27 | 4.41 |

የጉልህነት ደረጃ ማረጋገጫ $P \leq 0.01 < 0.05$

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በኦሮሚያ ክልል የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ3.79 በልጦ ተገኝቷል። የገጠር ደግሞ በ3.79 ያነሰ ነው። ስለዚህ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 3.79 ነው። በ189 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ ‹‹t›› ቴስት ቀመር ሲሰላ P= 0.00 ሆኖ የተገኘው የ‹‹t›› ቴስት ውጤት 4.07 ነው። የተገኘው የ‹‹t›› ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ189 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እናα=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ" t"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ሲሆን በα=0.01 ላይ ደግሞ 2.56 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል። ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ቋንቋውን ለመማር ባለ የፍላጎት የአማካይ ውጤት መካከል የተስተዋለው ልዩነት

ምክንያታዊ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው በሁለቱ ቦታዎች(ገጠርና ከተማ) መካከል ያለው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት  አስተማማኝ ስለሆነ በኦሮሚያ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጠ የተገኘ መሆኑንና በሂሳባዊ ስሌቱ መሰረት ልዩነቱም የጎላ መሆኑን ነው።

በኦሮሚያ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከትን በተመለከተ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል። ከላይ ሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው አዎንታዊ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ1.42 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ1.42 ያነሰ ነው። ስለዚህ አማካይ ውጤቱ በ1.42 ልዩነት  አሳይቷል። የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነቱ በ195 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.166 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 1.39 ነው። የተገኘው የ" ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን  በ195 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ሲሆን በ0.01 ላይ ደግሞ 2.58 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ቦታዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ አይደለም። ስለዚህ በከተማ ተማሪዎችና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው  አዎንታዊ አመለካከት  ልዩነት የሌለ መሆኑን ጥናቱ ያረጋግጣል።

በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤትን በተመለከተ የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል። ይሄውም ከላይ በሰንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡት የችሎታ ምዘና ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ2.34 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ2.34 ያነሰ ነው። በሁለቱ አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት 2.34 ነው። የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ168 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ  በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ

የP ዋጋ P=0.01 ላይ ሆኖ የተገኘው የ“ t”ቴስት ውጤት 2.23 ነው፡፡ የተገኘው የ“ t”ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ168 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ“t”ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አኳያ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የትምህርት ፈተና የአማካይ ውጤት በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ በቋንቋ ትምህርቱ ያለ አመለካከት ሲታይ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ምንም ልዩነት የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ በሌላ በኩል በገጠርና በከተማ ተማርዎች መካከል በትምህርቱ ውጤት በኩል ያለው የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

### 4.3.4.5.1.3 በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

በዚህ ክፍል ውስጥ በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና የውጤት ልዩነት ምን እንደሚመስል የቀረበበት ክፍል ስለሆነ በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዥ ላይ ቀርቦ ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አርባ ሁለት፤ በትግራይ ክልል ገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የፍላጎት የአመለካከትና የውጤት ልዩነት

ቡድናዊ ሂሳባዊ ስሌት

| ተላውጦ | አካባቢያዊ ሁኔታ | (N) የመረጃ ሰጪዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይት |
|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ከተማ | 106 | 73.37 | 9.81 |
| | ገጠር | 92 | 68.63 | 11.60 |
| አመለካከት | ከተማ | 106 | 47.70 | 7.03 |
| | ገጠር | 92 | 46.60 | 8፣04 |
| ውጤት | ከተማ | 106 | 58.88 | 10.46 |
| | ገጠረ | 92 | 52.77 | 11.66 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት በእንደሚቻለው በትግራይ ክልል የመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ድምር 198 ሆነው ከነዚህ ውስጥ የከተማ ተማሪዎች 106 ሲሆኑ የገጠር ተማሪዎች 92 ናቸው። ከነዚህ ተጠኚዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የከተማ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 73.37 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 9.81 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 47.70 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 7.07 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 58.88 ሲሆን መደበኛ ልይቱ ደግሞ 10.46 ነው።

የገጠር ተማሪዎቹ ደግሞ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት 68.63 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 11.60 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት አማካይ ውጤት 46.60 ሲሆን መደበኛ ልይቱ 8.04 ነው። ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የውጤት አማካይ ደግሞ 52.77 ሲሆን መበኛ ልይቱ ደግሞ 11.66 ነው። ከዚህ አንጻር በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በሶስቱም ተላውጦዎች ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ ተስተውሏል። በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው ልዩነት ጉልህና አስተማማኝ መሆኑን በ"ቲ" ቴስት ስሌት መሰረት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖና ተተርጉሞ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ አርባ ሶስት፤ በትግራይ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ ምዘና የፈተና አማካይ ውጤት ንጽጽር

t- ቴስት አማካኝ ውጤት ንጽጽር

| ተላውጦ | የአማካይ ውጤት | Df የነጻነት | (t ) ቴስት | የ(p) ዋጋ | 95% የአስተማማኝነት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| ፍላጎት | 4.74 | 179 | 3.07 | .002 | 1.70 | 7.78 |
| አመለካከት | 1.10 | 182 | 1.02 | .31 | -1.01 | 3.23 |
| ውጤት | 6.11 | 184 | 3.85 | .00 | 2.98 | 9.23 |

የጉልህነት ደረጃ ማረጋገጫ $P \leq 0.01 < 0.05$

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በትግራይ ክልል የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት ከገጠር ተማሪዎች በ4.74 በልጦ ተገኝቷል፡፡ የገጠር ደግሞ በ4.74 ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህ የአማካይ ውጤት ልዩነቱ 4.74 ነው፡፡ በ179 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ የትምህርት ፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P=0.002 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 3.07 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በ179 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.94 ሲሆን በα=0.01 ላይ ደግሞ 2.56 ነው፡፡ ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማተ ተማሪዎች መካከል ቋንቋውን ለመማር ባለው የፍላጎት አማካይ ውጤት መካከል የተስተዋለው ልዩነት ስለሆነ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በሁለቱ ቦታዎች(ገጠርና ከተማ) መካከል ያለው የፍላጎት የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ ስለሆነ በትግራይ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ የተገኘ ስለሆነ በተደረገው ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በትግራይ ክልል በከተማና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት በተመለከተ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል። ይሄውም ከላይ በሠንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለመማር ያላቸው አዎንታዊ የአመለካከት የአማካይ ውጤት ልዩነት ከገጠር ተማሪዎች በ1.10 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ1.10 ያነሰ ነው። ስለዚህ አማካይ ውጤቱ በ1.10 ልዩነት አሳይቷል። የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነቱ በ182 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በ0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ P= 0.31 ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 1.01 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ182 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ እና α=0.01 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ሲሆን በα=0.01 ላይ ደግሞ 2.58 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይና በα=0.01 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በትግራይ ክልል  በገጠርና በከተማ ቦታዎች መካከል ያለው የአዎንታዊ አመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝ አይደለም። ስለዚህ በከተማ ተማሪዎችና በገጠር ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ልዩነት የሌለው መሆኑን ጥናቱ ያረጋግጣል።

በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል በቋንቋ ትምህርቱ ችሎታ ያስመዘገቡት ውጤትን በተመለከተ የመረጃ ትንታኔ ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል። ይሄውም ከላይ በሰንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የከተማ ተማሪዎች የህብረ ብሄር ቋንቋ በሆነው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡት ውጤት ከገጠር ተማሪዎች በ6.11 በልጦ የተገኘ ሲሆን የገጠር ደግሞ በ6.11 ያነሰ ነው። በሁለቱ አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት 6.11 ነው። የአማካይ ውጤት ልዩነቱ በ184 የነጻነት ደረጃ፣ በአቅጣጫ የለሽ መላምት ማለትም በባለ ሁለት ጫፍ ፍተሻና በα=0.05 የጉልህ ደረጃ፣ ላይ በ ‹‹t››ቴስት ቀመር ሲሰላ የP ዋጋ P=0.01 ላይ ሆኖ የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት 3.85 ነው። የተገኘው የ"ቲ"ቴስት ውጤት ልዩነት ጉልህ መሆኑን በ184 የደረጃ ነፃነት ላይ በα=0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና የ"ቲ"ቴስት ሰንጠረዥ ዋጋ በα=0.05 ላይ 1.96 ነው። ስለዚህ የተገኘው የ‹‹t››ቴስት ዋጋ በα=0.05 ላይ ከሚነበበው የሰንጠረዥ ዋጋ በልጦ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በገጠርና በከተማ መካከል ያለው የትምህርት

የምዘና ፈተና  አማካይ ውጤት በተደረገው ስሌት መሰረት ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ በትግራይ ክልል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለፍላጎት ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ በቋንቋ ትምህርቱ ያለ አመለካከት ሲታይ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ምንም ልዩነት የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ በሌላ በኩል በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል በትምህርቱ ውጤት በኩል ያለው ልዩነት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ መሆናቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 4.4 ዋና ዋና የግኝቶች ገለፃና ትንታኔ፣

### 4.4.1 በክልሎች መካከል ትምህርቱን ለመማር ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነትን አስመልክቶ የቀረቡ ግኝቶች

ከላይ የቀረበው የመረጃ ትንታኔ ከጋርድነር የማህበራዊ ስነ-ትምህርታዊ ሞዴል ጋር ያለው ትስስር የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይህንን ጥናት የጋርድነር የማህበራዊ ስነ-ትምህርታዊ ሞዴል(Socio-Educational model) ከሚከናወነው ጥናት ጋር በማስተያየት የቀረበ ነው፡፡ የማህበራዊ-ትምህርታዊ ሞዴል መሰረት ሰው በሚኖረው ተነሳሽነት/ንሺ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የሚቃኝ ነው፡፡ ተነሳሽነት/ንሺ ማለት የአንድ ቋንቋ ለማጆች (ተማሪዎች) ቋንቋን መማራቸው አላማቸውን ከማሳካት አንጻር ያላቸውን እሳቤ ወይም አመለካከት መሰረት በማድረግ የቀረበ ዝርዝር ጉዳይ ነው፡፡ ተነሣሽነት በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንደተገለጸው በሁለት መሰረታዊ ክፍሎች ይከፈላል፡፡ ይሄውም ውህዳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Integretive Motivation) እና ቁሳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Instrumental motivation) በመባል ነው፡፡ ውህዳዊ ተነሳሽነት/ንሺ(Integretive Motivation) ይህ አይነቱ ንሺ በቋንቋ ለመዳ ሂደት ተማሪው ለሚማረው ወይንም ለሚለምደው ቋንቋ ያለውን አዎንታዊ አመለካከትና ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር እራሱን ለማዋሀድ ያለውን ፍላጎት የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ቁሳዊ ተነሳሽነት/ንሺ (Instrumental motivation) የሚባለው ደግሞ አንድ የቋንቋ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋውን ለመልመዱ ወይም ለመማሩ ምክንያት የሚያደርገውን ማህበራዊ ወይንም

ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ነው፡፡ ይሄ የሚያሳየው ቋንቋን መማር ያለብን ለምንፈልጋቸው ጉዳዮች ማሳኪያ ወይም ማከናወኛ ተብሎ ለመዳውን/ትምህርቱን ለማከናወን ሲቻል እንደሆነ በGardner (2006) ሀሳብ ላይም በስፋት ቀርቧል፡፡

ለምሳሌ አንድ ህጻን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ስኬታማ እንዲሆን ከሚያደርጉት ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ቤተሰቦቹ ሲሆኑ ቀጥሎም በአካባቢው የሚገኙ የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና ወይም ተቀባይነትን ለማግኘት ካለው ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ያለው ተነሳሽነት ለስኬታማ የቋንቋ ለመዳ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች ወይንም በቋንቋ ለመዳ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች ውስጥ የተማሪው ቤተሰብና ማህበራዊ አውድ መሆኑን በዋናነት ሊሰመርበት እንደሚገባ ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም ለመማር ያለ ተነሳሽነት ብቻውን ለቋንቋው ለመዳ ምክንያት አይደለምና ነው፡፡

ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ሁኔታ ግለሰቡ ወይንም የቋንቋ ተማሪው የሚኖርበትን ከባቢያዊ ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በሌላው ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ ያላቸው እምነትና አመለካከት ቋንቋውን በብቃት በመማርና ባለመማር መካከል ያለውን ልዩነት ይወስናል የሚል ነው፡፡ Lightbown(2011) እንደ አጠቃላይ ሲታይ ማህበረሰባዊ ምክንያቶች በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ላይ፣ ንሺና በትምህርቱ ውጤታማነት ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ Lightbown (2011) ተማሪው ለሚማረው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ አንጻር በተጠኚ ክልሎች የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ማየትና በክልሎች መካከል የሚስተዋለውን የፍላጎት፣ የአመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የሚስተዋለውን የልዩነት ደረጃን መመርመር ስለሆነ የጥናቱ ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ይሄውም ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶና እንዲሁም ቋንቋውን ከመማር አንፃር በገጠርና በከተማ ተማሪዎች በኩልና ከጾታ አንጻር ያለውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና ውጤት ልዩነትንና እነዚሁ ተላውጦዎችን አስመልክቶ ልዩነቶችን

ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘውን ውጤት በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡት ንድፈ ሃሳብና የጥናት ውጤቶች ጋር በማዛመድ የታየ ሲሆን ይሄም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በአራቱ ክልሎች በሚገኙ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት መሠረት ተማሪዎቹ የህብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛን ለጋራ መግባቢያነት ለመማር ባላቸው ፍለጎት፣ አመለካከትና ባስመዘገቡት ውጤት መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ ያለ መሆኑን በጥናቱ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይሄውም ቋንቋውን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎትና አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤትን ሲያስመዘግቡ! በአንፃሩ ደግሞ ለትምህርቱ ዝቅተኛ ፍላጎት፣ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤትን ያስመዘገቡ መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ለምሳሌ አፋር ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት ከሌሎች የክልል ተማሪዎች አንፃር ሲታይ ልዩነቱ ከፍተኛ ሲሆን በትምህርቱም ያስመዘገቡት ውጤት እንደዚሁ ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት ከሌሎች ክልል ተማሪዎች አንፃር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ሲሆን በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤትም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የተገኘው ውጤት በጥልቀት ሲታይ ደግሞ የቋንቋ ትምህርታቸውን ከአንደኛ ክፍል የጀመሩት ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ እያስመዘግቡ ያሉት ውጤት ዘግይተው ከሶስተኛ ክፍልና ከአምስተኛ የክፍል ደረጃ ከጀመሩት ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ የቋንቋ ትምህርታቸውን በጣም ዘግይተው የጀመሩት ተማሪዎች ደግሞ ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ዝቅ ብሎ ተገኝቷል፡፡

በአፋር ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተማሪዎች መካከል ያለው ንጽጽር ትንተና ሲታይ በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት የክፍል ደረጃ በከፊል የተለያየ ነው፡፡ የአፋር ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት ከአንደኛ ክፍል ነው፡፡ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን የተወሰኑት ተማሪዎች ከመዋእለ ህጻናት ጀምሮ እንደሆነና የተወሰኑት ተማሪዎች ደግሞ ከአንደኛ ክፍል እንደሆነ አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያስረዳል፡፡

ይሁን እንጂ በሁለቱ ክልሎች መካከል ባለ ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከትና የምዘና ፈተና አማካይ ውጤት እንደሚያሳየው ከሆነ ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎትና ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከት የአፋር ክልል ተሽሎ ተስተውሏል፡፡ ልዩነቱ አስተማማኝ መሆኑ በልዩነት ንጽጽር ትንተና ተተንትኖ ሲታይ ደግሞ ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት በኩል ያለው ጉልህ ሆኖ የተገኘ ሲሆን በአዎንታዊ አመለካከት በኩል ያለው ልዩነት ግን ጉልህና አስተማማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በትምህርቱ የተመዘገበ የችሎታ ምዘና የአማካይ ውጤትን በተመለከተ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ተማሪዎች የምዘና ውጤት ከአፋር ክልል ተማሪዎች በልጦ ተበኝቷል፡፡ ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን በንጽጽር ትንተና በሚታይበት ወቅት ልዩነቱ ጉልህና አስተማማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ የሚቻለው በአዲስ አበባና በአፋር ክልል መካከል በተደረገ የልዩነት የንጽጽር ትንተና መሰረት የተገኘው ውጤት በአፋር የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት አዲስ አበባ ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ በልጦ ተገኝቷል፡፡ በአመለካከትና በችሎታ ምዘና ውጤት ሲሳይ በሁለቱም በኩል የተስተዋለው ልዩነት የጎላ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ ከተገኘው ውጤትና ከላይ በተራ ቁጽር 4.3.4.1፣ 4.3.4.2 እና 4.3.4.3 ስር በተደረገው የልዩነት ንጽጽር ትንተና ላይ ከተገኘው ውጤት መገንዘብ የሚቻለው የአፋር ክልል ተማሪዎች በአመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እና በችሎታ ምዘና ውጤት ከአዲስ አበባ ተማሪዎች በልጠው መገኘት ሲገባው ነገር ግን ይሄ ሆኖ አልተስተዋለም፡፡ የዚህ ውጤት እንደዚህ ሆኖ መገኘት ምናልባትም ተማሪዎቹ ከመዋእለ ህጻናት ጀምሮ በመማራቸው አለበለዚያም ለቋንቋው ባላቸው ተጋላጪነት ምክንያት የመጣ ውጤት ሳይሆን እንዳልቀረ መገመት የሚቻል ቢሆንም ምክንያቱን ተጨባጭ ለማድረግ በሌላ ጥናት ቢፈተሽ የተሻለ ያደርገዋል፡፡

እንደ አጠቃላይ ሲታይ በተደረገው የልዩነት ንጽጽር ትንተና መሰረት ከክልሎቹ መካከል የተስተዋለው ልዩነት በሚከተለው መልኩ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ፍላጎት ——————→ አፋር > አዲስ አበባ > ትግራይ > ኦሮሚያ

አመለካከት፡- ——————→ አፋር = አዲስ አበባ > ትግራይ > ኦሮሚያ

በችሎታ ምዘና ውጤት ——————→ አዲስ አበባ = አፋር > ትግራይ > ኦሮሚያ

ከላይ ለቀረበው ውጤት መምጣት እንደምክንያት የተረጋገጠው በጋርድነር ሞዴል ላይ እንደቀረበው በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች መሆናቸውን ለማየት ተሞክሯል፡፡ ይሄውም የሁለተኛ ቋንቋ ከመማር ጋር እርስ በርሳቸው ትስስር ያላቸው ሲሆኑ አንደኛው ማህበራዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች፣ ሁለተኛው የግለሰቦች የመማር ችሎታና የዝግጁነት ልዩነት፣ ሶስተኛው ትምህርቱ የሚከናወንበት አውድ እና አራተኛው ቋንቋን መማር በሚያመጣው ውጤትና በዙሪያው ያለ ግንዛቤ አሉታዊ ወይንም አሉታዊ ሆኖ መገኘት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ስለዚህ የአመለካከትና ፍላጎት የትምህርት ውጤት ተዛምዶን በተመለከተ የተገኘው ውጤት በተለያዩ ምሁራን (Girid,1990; Gardener,2003; Hurloc,1980 & Skiner,1985) የጥናት ውጤቶች ላይ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለትምህርቱ ከፍተኛ ፍላጎትና አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ከገለጹት ሀሳብ ጋር አንድ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ማመልከቱን ያረጋጋጣል፡፡ ይሁን እንጂ ብሄር ብሄረሰቦች ልጆቻቸውን የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እንዲያስተምሩ ሲደረግ ክልሎች ወጥ የሆነ የመማር ማስተማር መንገድን ስለማይከተሉ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤት የተለያየ እንዲሆን ማድረግ መቻሉን የተሰበሰበው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ለዚህም በጥናቱ ውስጥ በዋና ምክንያትነት የቀረበው በክልሎች አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምርበት ደረጃ በክልሎች ይሁንታ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተስተውሏል፡፡ ጥላሁን ገብረክርስቶስ (1997) ባከናወኑት ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች በውል ተለይቶ መታወቅና በግልጽ መቀረጽ፣ የይዘቶች መረጣና ክንውን አደረጃጀት ከየክፍሉ ተማሪዎች ሁለንተናዊ እድገት (አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ) አለመቅረብ በችግርነት የተገለጸ ነው በማለት በጥናታቸው ላይ አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም ጥላሁን ገብረክርስቶስ (1997) የመማር ማስተማር ጥበባትንና ሣይንሳዊነትን ተገንዝቦ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ስርአታዊ ለማድረግ ሆን ተብሎ ታልሞ በተዘጋጀ መርሀ ግብር ሰልጥነው የተሰማሩ መምህራን ያለመኖር/ አለመኖራቸውንና አማርኛ ለኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ መግባቢያ መሳሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ መሆኑን ባለማጤን ቋንቋውን በጥላቻ ማየት፣ ከፕሮፖጋንዳ ፖለቲካ ጋር ማያያዝ የመሳሰሉትን አንኳር ችግሮቹ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከፕሮፖጋንዳ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ምክንያት ይሆን እንዴ? የሚለውን ሀሳብ በመውሰድ በቡድን ተኮር ውይይት መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጎ የተገኘው

መረጃ እንዳመለከተው በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አሰጣጥን ባለመከተልና ስለቋንቋ ትምህርቱ ካለ የግንዛቤ ክፍተት የመጣ እንደሆነ ከክለሳ ድርሳናትም ሆነ ከቡድን ተኮር ውይይቱ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

## 4.4.2 እድሜ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና ተጽእኖ

እድሜ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ጋር ያለው ግንኙነትና ተጽእኖ ምን እንደሚመስል የሶስቱንም ክልሎች መረጃ በአንድ ላይ በማድረግ በተደረገ የመረጃ ትንታኔ ከእድሜ ጋር ተያይዞ በተገኘውን ውጤት የተማሪዎች እድሜ ከትምህርት ውጤት፣ አመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር ያለው ዝምድና አሉታዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይሄም ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ የሚመዘገብ የችሎታ ምዘና ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ የተገኘው ውጤት አመልክቷል፡፡ ይህም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ከመጀመሪያ የክፍል ደረጃ ወይም ከአነስተኛ የእድሜ ደረጃ መማር የጀመሩት ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ በአንጻሩ ደግሞ ትምህርቱን ከፍ ካለ የክፍል ደረጃ ወይም ከፍ ካለ ከእድሜ ደረጃ ላይ መማር የጀመሩት ተማሪዎች ውጤታቸው ዝቅ ማለቱን የቀረበው የመረጃ ትንታኔ አረጋግጧል፡፡ የተገኘው ውጤት ከየክልሎቹ ሁኔታ አንጻር በተናጠል ሲታይ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ይሄውም ከእድሜ አንጻር በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ላይ የተገኘው የመረጃ ትንታኔ የተማሪዎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ያረጋግጣል፡፡ ትምህርቱን ከመጀመሪያ የክፍል ደረጃ ጀምሮ ሲማሩ በነበሩት የአፋር ክልል ተማሪዎች ላይ ደግሞ እድሜ ቋንቋውን ለመማር በሚኖር ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ የሚመዘገብ የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ምንም ተጽእኖ እንደሌለው አመልክቷል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪው ትምህርቱን ማልዶ ከመጀመሪያው የክፍል ደረጃ መማር የሚጀምር ከሆነ እድሜ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የጎላ ተጽእኖ እንደማያሳድር የጥናቱ ውጤት ያመልክቷል፡፡

ከዚህ አንጻር ከኦሮሚያ ክልል የቡድን ተኮር ውይይት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ከ5ኛ ክፍልና በ12 አመት የእድሜ ደረጃ ላይ ትምህርቱ መሰጠት ይጀምራል። በዚህን ጊዜ ትምህርቱ የሚጀመረው በፊደል ቆጠራ እንደሆነ ተማሪዎቹ ግልጸዋል። በዚህ የክፍል እና የእድሜ ደረጃ ላይ ወደ ፊደል ቆጠራ ሲገቡ በላያቸው ላይ የሚያሳድረው ስነልቦናዊ ስሜት አሉታዊ መሆኑን ገልጸዋል። ይሄውም በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ሀሳብ ሲገልጹ፤ የህጻንነት ስሜት እንደሚሰማቸውና ወደ ታች እንደተመለሱ አድርገው እንደሚቆጥሩት ነው ያስረዱት። በተመሳሳይ ሁኔታ ለንጽጽር እንዲሆን ከጂማ ዞን የቡድን ተኮር ውይይት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ለኦሮሚኛ ኢ-አፊፊት የሆኑት የኦሮሚኛን ቋንቋን ትምህርት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ መማር በመጀመራቸው ምክንያት ፊደልን በመቁጠር ሂደት እንደገና ወደ ታች እንደተመለሱ አድርገው እራሳቸውን እንደሚቆጥሩ የሰጡት መረጃ ያረጋግጣል። ስለዚህም የኦሮሚኛ ቋንቋንም ሆነ የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት አምስተኛ የክፍል ደረጃ ላይ መማር መጀመራቸው በቋንቋው የተፈለገውን ርቀት ያህል መሄድ አለመቻላቸውን የተሰበሰበው መረጃ ያረጋግጣል።

ከዚህ አንጻር በSkinner (1989) እና Schon'ell (1961) የቀረበው ሀሳብ ትክክለኛ መሆኑን ያመለክታል። ተማሪዎች እንደየ ዕድሜያቸው ፍላጐታቸውና ተግባራቸው ስለሚለያይ ዕድሜያቸውን መሠረት ያደረገ ትምህርት ከተግባርና ፍላጐታቸው ጋር ተቀናጅቶ ቢሰጥ የመማር ማስተማር ሒደቱ በተገቢው መንገድ ሊከናወን እንደሚችልና ሒደቱም ግብ መቺ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር የአምስት አመትና የአስር አመት ተማሪዎች ያላቸው ፍላጐት የተለያየ መሆኑንና የቋንቋ ትምህርቱን ማልዶ መሰጠት እንዳለበት የመረጃ ትንታኔው ያመለክታል።

በFeer Man (1991:207) አገላለፅ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት እድሜ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ከእድሜ አንፃር ይበልጥ ትምህርቱን ለማከናወን ወሳኝ የእድሜ ክልል አለው። ያም የእድሜ ክልል ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ዓመት ድረስ ያለው ነው። ስለዚህ አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን መማር መጀመር ያለበት የእድሜ ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን መማር በሚጀምርበት የእድሜ ደረጃ ላይ መሆን እንዳለበትና ይህም ወሳኝ የእድሜ ክልል መሆኑን ያስገነዝባሉ። Stern(1991) በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ተማሪ ሁሉን ነገር ለማወቅ ካለው ፍላጎት በመነሳት ለሚማረው ትምህርት ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖረዋል በማለት ይገልጻሉ።

ይሄንን በተመለከተ Lightbown (2011) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በቋንቋ ትምህርቱ አላማና ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡ የቋንቋ ትምህርቱ አላማ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ የአፈ-ፈትነትን ችሎታን እንዲኖረው ከተፈለገ በተቻለ መጠን ትምህርቱን ማልዶ መጀመር ይጠበቅበታል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በአፋር ክልል ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩ ሲሆን የእድሜ አማካይ ሲታይ 8 አመት ላይ ነው፡፡ በትግራይ ክልል ትምህርቱ የሚጀምረው ከሶስተኛ ክፍል ሆኖ የተማሪው የእድሜ አማካይ ሲታይ 10 አመት ደረጃ ላይ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል የተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት እድሜና የክፍል ደረጃ ከአምስተኛ የክፍል ሲሆን እድሜያቸው በአማካይ 12 አመት ላይ ነው፡፡ ይሄም የሚያመለክተው በሶስቱም ክልሎች የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት የአጀማመሩ ሁኔታ ከክፍል ደረጃና ከእድሜ አንጻር የተለያየ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይሄውም በአንደኛው ክፍል ማልዶ የሚጀመር ሲሆን በሌላው ክልል ደግሞ ዘግይቶ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

Stern (1991) ማብራሪያ ሲሰጡ ከማንኛውም በተለየ መልኩ በዝቅተኛ የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች አንድን ነገር ለማወቅ በጣም ጉጉ ናቸው፡፡ እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ውስጣዊ ንሺ የሚቀንስ ሲሆን ውጫዊ ንሺ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ውስጣዊ ንሺ ሲባል አንድ ተማሪ ቋንቋን የሚማረው ከሚያገኘው ጥቅም አንጻር ነው፤ በማለት ጥናቶችን በማጣቀስ ሀሳባቸውን ያቀርባሉ፡፡ በመሆኑም የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች የህብረብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች አንጻር ሲታይ በ2 እና በ5 አመት ዘግይተው ነው፡፡ የትግራይ ክልል ተማሪዎች የህብረብሄር ቋንቋ የሆነውን አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር የሚጀምሩበት የክፍል ደረጃ ከሌሎቹ ክልሎች አንጻር ሲታይ በ2 አመት ይዘገያል፡፡ የተማሪዎች እድሜ ሲጨምር ደግሞ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ውጫዊ(instrumental) እየሆነ የሚሄድ መሆኑን ከላይ የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ጥቅም ይሰጠኛል በሚል እንደሚሆን በምሁሩ የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡

ከዚህ አንጻር የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የችሎታ ምዘና ውጤት፣ አዎንታዊ የሆነ አመለካከትና ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ሲታይ ከሌሎች ክልሎች በጣም አንሶ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በትግራይ የሚገኙ ተማሪዎች ከአዲስ አበባና ከአፋር ክልሎች

አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች የተማሪዎች እድሜ እየጨመረ ሲሄድ ውስጣዊ ተነሳሽነት እየቀነሰ እንደሚሄድ Stern (1991) ካቀረቡት ሀሳብ እና ከጥናቱ ከተገኘው የትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ይቻላል።

ከሶስቱ ክልሎች አንጻር እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ግንኙነት ሲታይ የአፋር ክልል ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን በዚህ ክልል እድሜ ከውጤት፣ ከአመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ካለ ፍላጎት ጋር ያለው ግንኙነት ጉልህ ሆኖ አልተገኘም። በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ላይ ግን እድሜ ከፍላጎት፣ ከአዎንታዊ አመለካከትና ከትምህርት ውጤት ጋር አሉታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳለው አመልክቷል። ስለዚህ ከቀረበው ግኝት ማረጋገጥ እንደሚቻለው ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተማሪዎች ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃና የክፍል ደረጃ ሲጨምር ለትምህርቱ ያላቸው በጎ አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ ያመለክታል። ይሄ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ ከላይ Stern (1991)፣ Lightbown (2011)፣ Feer Man (1991:207)፣ Skinner (1989) እና Schon'ell (1961) የቀረበውን ሀሳብ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል እድሜንና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን ከቀረበው ሀሳብ አንጻር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል። ይህውም Cook(2001) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን በማስመልከት ወሳኝ የሆነው ጊዜ መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ ያልተመለሰ ነው። በሌላ አባባል በእድሜና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል ያለው አከራካሪ ጉዳይ በትክክሉ መልስ አላገኘም። ስለዚህ በአዋቂዎች፣ በወጣቶችና በታዳጊ ልጆች መካከል ሲደረግ የነበረው ንፅፅር አርቴፊሻል ነው። ወሳኝ የእድሜ ክልል የተባለው በውል አልታወቀም። ከዚህ ለማየት የተቻለው በትምህርት ሥርአት ውስጥ በየትኛው የእድሜ ክልል የቋንቋ ትምህረት መጀመር እንዳለበት ቁርጥ ያለ መልስ የለም የሚሉ አካላት እንዳሉ ይገልፃሉ።

ከላይ በክለሳ ድርሳናት ላይ ከቀረቡት ሐሳቦች በመነሳት የሚከተሉትን ነጥቦች ማስቀመጥ ይቻላል። የቋንቋ ትምህርት በተለያየ የእድሜ ክልል ማከናወን እንደሚቻል ያስረዳል። ከልጅነት እስከ ከፍተኛ እድሜ ደረጃ ድረስ ቋንቋን መማር እንዲሚቻል ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር ወሳኝ የሆነ የቋንቋ ለመዳ የእድሜ ክልል አለ የሚለውን ማስቀመጥ ይከብዳል የሚለውን ሀሳብ ያጠናክራል። በተወሰነ የእድሜ ክልል የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት አዋቂዎች፣

ታዳጊዎች፣ የተለያየ የመማሪ ስልትን እንደሚጠቀሙ ለማየት የተሞከረ ሲሆን፣ ነገር ግን እያንዳንዱ የእድሜ ክልል የራሱ የሆነ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤትን አሳይቷል፡፡ ይህ ደግሞ የዚህ እድሜ ክልል ወሳኝ ነው የሚለውን ሐሳብ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ ቋንቋን መማር ልክ እንደ ሌሎቹ ክፍሎችና አውቀቶች /ትምህርቶች/ አንድና ወጥ የሆነ አካሄድ አለመኖር የታየ ሲሆን እንደየ እድሜ ክልሉ የሚለያይ መሆኑን ለማየት ተሞክሯል፡፡ ለውጥና እድገት ደረጃ ልዩነቱን የሚያሳይ ግልፅ ሆኖ የቀረበ ልዩነት የለም፡፡ በእያንዳንዱ የእድገት ደረጃና እድሜ በሂደት በቋንቋ ትምህርት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል ያመለክታል፡፡ የትኛው የእድሜ ደረጃ በቋንቋ ትምህረት ወሳኝ መሆኑን ለመወሰንና ትክክለኛ ሐሳብ ላይ ለመድረስ በስነ-ልቦናዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ በጥናት የተደገፈ ሥራ በማየት በጥናቱ የተወሰነ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በየትኛው እድሜ ክልል ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትን ይበልጥ ሊማሩ ይችላሉ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ባይገኝም በልጅነት የአድሜ ክልል ውስጥ የሁለተኛ ቋነቋን መማር የጀመሩ በጊዜ ሂደት በቋንቋ ትምህርቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚችሉ ሁሉንም አጥኚዎች ያግባባል፡፡ በተለያየ የእድሜ ክልል ቋንቋን የመማር ፍላጎት፣ የአመለካከትና የንሺ ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ የተለያየ የማስተማር ዘዴን በመከተል ሁለተኛ ቋንቋን ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ የመሁራኑ ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ይሄንን በተመለከተ Cook (2001) እንደየ እድሜ ክልሉ አመቺ የሆነ የማስተማር ዘዴን መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነም ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ በቀረበው መሰረት ትምህርቱን ማልዶ የጀመረና ጊዜ ወስዶ እተማረ ያለው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በሂደት በቋንቋ ትምህርቱ ከተፈለገው ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል ሁሉንም ምሁራን የሚያስማማ ነው(Stern 1991; Cook 2001 እና Lightbown 2011)፡፡ ከዚህ አንጻር የዚህ ጥናት ውጤት እንዳመለከተውም ተምህርቱን ማልደው የጀመሩትና ሰፊ ጊዜ ወስደው የተማሩት በትምህርቱ ውጤታማ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ እድሜን አስመልክቶ በተደረገ የክለሳ ድርሳናትና ከተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት መሰረት ሁለት ዋና ዋና ግኝቶችን ማውጣት ይቻላል፡፡ ይሄውም አንደኛው ማልደው ትምህርታቸውን መማር የሚጀምሩና ለትምህርቱ ሰፊ ጊዜ የተሰጣቸው ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን፣ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካት ያላቸውና በችሎታ ምዘና ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ሁለተኛው እድሜ ሲጨምር የተማሪዎች ፍላጎት መቀየሩን፣ ከህገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እድሜ ሲጨምር በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ላይ ስነልቦናዊና የማህበራዊ ተጽእኖው መኖሩንና በቋንቋ

ትምህርቱ አመለካከት፣ ወጤትና ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ መሆኑን ከተከናወነው የጥናት ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.4.3 ከጾታ አንጻር የፍላጎት፣የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት

ከጾታ አንጻር የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ ውጤት መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሄ ሆኖ መገኘቱ በፆታ መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በሌላ በኩል ለትምህርቱ ካላቸው አመለካከት አንጻር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነትም አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በፆታ መካከል ቋንቋን ለመማር ያለ የአመለካከት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ ከችሎታ ምዘና ውጤት አንጻር ግን በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በአማርኛ ቋንቋ የትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በፆታ መካከል ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ውጤታማ መሆናቸውን የተገኘው የትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና አመለካከት ዙሪያ ጾታዊ ልዩነት የሌለ ሲሆን ከችሎታ ምዘና ውጤት አንጻር ግን ሴቶች ከወንዶች ተሽለው ተስተውለዋል፡፡

ከጾታ አንጻር እያንዳንዱ ክልሎች በተናጠል ሲታዩ በፍላጎት፣ በአመለካከትና ከችሎታ ምዘና ውጤት ዙሪያ የተስተዋለ ልዩነት በአፋር ክልል ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ሲያረጋግጥ ለትምህርቱ የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት በተመለከተ የሴት ተማሪዎች ከወንዶቹ ተሽሎ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱም አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሄውም በአፋር ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ሴቶች ከወንዶች በተሻለ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ በችሎታ ምዘና ውጤት

በተመለከተም የተስተዋለው የአማካይ ውጤት የሴቶች ተማሪዎች ከወንዶቹ ተሽሎ የተገኘ ሲሆን ልዩነቱም አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በአፋር ክልል ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት ጾታዊ ልዩነት ባይኖርም ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከትና በችሎታ ምዘና ውጤት ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት የሴቶች በልጦ ቢገኝም አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ዘንድ በፆታ መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ ከአመለካከት አንጻር በኦሮሚያ ክልል በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ እንዲሁም በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በአማርኛ ቋንቋ በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከቀረበው መረጃ ማረጋገጥ የሚቻለው በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ በፍላጎት፣ በአመለካከትና በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ በፆታ መካከል ልዩነት ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በትግራይ ክልል በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት፣የአመለካከትና በትምህርት የችሎታ ምዘና ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የሴቶች በልጦ ቢስተዋልም ልዩነቱ አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በትግራይ ክልል በፆታ መካከል የተገኘው የፍላጎት፣ የአመለካከት የችሎታ ምዘና ላይ ጾታዊ ልዩነት አለመኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን ለመማር የተስተዋለው የፍላጎት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ስላልተገኘ በፆታ መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ያለመኖሩን የተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ የአመለካከት አማካይ ውጤት ልዩነት አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ ባለመገኘቱ ምክንያት አማርኛን በመማር ሂደት ላይ በፆታ መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለመኖሩንና በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ የተስተዋለው የአማካይ ውጤት ልዩነት

አስተማማኝና ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ያለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት መካከል ምንም ያታዊ ልዩነት ያለመኖሩን ከተገኘው የመረጃ ትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ማረጋገጥ የሚቻለው በኦሮሚያ፣ በትግራይ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ላይ ለትምህርቱ ባለ ፍላጎት፣ አመለካከትና በችሎታ ምዘና ውጤት ያታዊ ልዩነት ያለመኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን በአፋር ክልል ግን ለትምህርቱ ባለ አመለካከትና በችሎታ ምዘና ውጤት ሴቶች ከወንዶች ተሽለው ተገኝተዋል፡፡

ከላይ የቀረበውን ግኝት መሰረት በማድረግ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ዙሪያ ቀደም ብሎ የተከናወኑ ጥናቶችና በምሁራን ዘንድ የሚነሱ ሀሳቦች ሲታዩ Hurlock (1965) እና Garrison (1965) ባገኙት ግኝት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ትምህርትን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ይኖራቸዋል፤ ከሚለው ሃሳብ ጋር አይገናኝም፡፡ ስለዚህ ይህ ውጤት እንደሚያመለክተው በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባለው ፍላጎት በተወሰኑ ክልሎች ልዩነት ሲታይ በተቀሩት ደግሞ የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡ እንዲሁም Skinner (1995) Tyler (1955)ን ጠቅሰው ሲገልፁ ወንድ ልጆች የተፈጥሮ ሳይንስንና ሂሳብን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው ሴት ልጆች ደግሞ ለቋንቋ ለማህበራዊ ሳይንስና ለእደ ጥበብ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው በማለት የቀረበን የጥናት ውጤት በማስረጃነት ያቀርባሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አጠቃላይ በተደረገው የመረጃ ትንታኔ መሰረት የቀረበው የጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት በአመለካከትና በፍላጎት ረገድ ግንኙነቱ የላላ ነው፡፡ ምክንያቱም በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የጎላ የፍላጎትና የአመለካከት ልዩነት አለመኖሩን ነው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

Bätz et al. (2010) የIPA (2003) ጠቅሶ በተከናወነ ጥናት ለሂሳብ የትምህርት መስክ፣ ለተፈጥሮ ሣይንስ የትምህርት መስክ፣ በችግር ፈቺነት ዙሪያ በሚገኙ ተግባራት ላይ በጾታ መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ የጥናት ውጤት እንዳመለከተ ያቀርባሉ፡፡ ሌሎች አጥኚዎች ደግሞ በወንዶችና በሴቶች መካከል በተወሰነ ደረጃ ልዩነት መኖሩን አመልክተዋል(Bätz et al.,2010; Hanaa, 2000; and Kaiser,and Steisel, 2000)፡፡ እንዲሁም Bätz et al.(2010) እና kassels (2004) ጠቅሶ ወንዶች በሂሳብ ነክ ትምህርቶችና ለፊዚክስ የትምህርት

ዓይነት ከሴቶች በተሻለ መልኩ ከፍተኛ የመማር ፍላጎት እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡ ደሳለኝ (2004) ወንዶች ከሴቶች በተሻለ ሁኔታ በሂሳብ ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት በአማራ ክልልና በኦሮሚያ ክልል ልዩነት አለመኖሩንና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን ሴቶች ከወንዶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን የጥናታቸው ውጤት ማሳየቱን አመልክተዋል፡፡ Pintrich and Schunk (2002) የትምህርት ሁኔታ ጾታን መሰረት በማድረግ ሲታይ ሴቶች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም ውጤታማ ናቸው፡፡

ወንዶች ለፊዚክስ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ትምህርቱን ለመማር ይመርጡታል (Baram-Tsabari et al,2008; Jenkins, 2006; and kessls, 2004)፡፡ በዚህም ምክንያት ፊዚክስ የወንዶች ትምህርት ተብሎ ይታወቃል(Tsabari et al,2008; Jenkins, 2006; kessls, 2004)፡፡ ተማሪዎች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት አይነት ምርጫ በሚያከናውኑበት ወቅት በጀርመን የባውዩሎጂ ትምህርትን ለመማር የሚመርጡት በአብዛኛው ሴቶች ስለሆኑ የሴቶች ትምህርት ነው ይሉታል (Baram-Tasbari et al, 2008)፡፡ ሴቶች ስነ-እንስሳ(zoology)ና የአትክልትና የአዝርእት ጥናት(botany) ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው(krombass, Urhahne and Harms,2008)፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ በሴትና በወንድ መካከል የትምህርት ፍላጎት ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ እንዲሁም እንደየ ትምህርት አይነቱ በሴቶችና በወንድ ተማሪዎች መካከል የውጤት ልዩነት ይስተዋላል፡፡ በተለይም በቋንቋ ትምህርት ከተፈጥሮ ሳይንስ ውስጥ የስነ-ህይወት(biology)፣ ስነ-እንስሳ (zoology)ና ስነ-አትክልትና የአዝርእት ጥናት(botany) የትምህርት አይነቶችን ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ ለመማር ፍላጎት ስላላቸው ትምህርቶቹን እንደሚመርጧቸው በውጪ ሀገራት የተደረገ ጥናት ያመለክታል፡፡ Bätz et al. (2010) Gehlhaar et ai (1999) ጠቅሰው ሴቶች ለእንስሳና ለእስሳት ፓርክ ጉብኝት ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናታቸው ውጤት እንዳመለከተ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ውስጥም ሴቶች የቋንቋ ትምህርትን ለመማር ፍላጎት እንዳላቸው ቀርቧል፡፡ ከዚህ አንጻር የዚህ የጥናት ውጤት እንደሚያሳየው ግን በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች በህብረ ብሄር የቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት፣አመለካከትና መካከል የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡ በትምህርት ምዘና ባስመዘገቡት ውጤት ግን ልዩነቱ ጉልህ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ካሳዩት ውጤት ጋር አመለካከትንና ፍላጎትን

በተመለከተ ምንም ግንኙነት የሌለው ሲሆን ነገር ግን ከውጤት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በተጨማሪም Hurlock (1965) እና Garrison (1965) የገለጹት የጥናት ግኝት እንደሚያስረዳው ሴት ተማሪዎች ለትምህርቱ ካላቸው ከፍተኛ በሆነ አመለካከት፣ ዝንባሌና ፍላጎት የተነሳ ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ በቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ጥናቶችን ጠቅሰው በመጻፋቸው ላይ አስፍረዋል፡፡ እንዲሁም Skinner (1985) Tyler (1985)'ን ጠቅሰው ከወንዶች ይልቅ ለሴት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ አመለካከትና ፍላጎት እንዳላቸውና ትምህርቱም ለሴት ተማሪዎች ምቹ ስለሚሆን ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ላይ የተገኘው ውጤት በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ቋንቋ ትምህርቱ አመለካከትና ፍላጎት መካከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንታኔ መሰረት በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች መካከል የህብረ ብሄር የሆነው በቋንቋ ትምህርት ወቅት በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት ልዩነት ቢኖርም፣ ለትምህርቱ ባላቸው አመለካከትና ፍላጎት መካከል የጾታን ልዩነት ማዕከል ባደረገ መልኩ የጎላ ልዩነት እንደሌለ ከጥናቱ ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ማጠቃለል የሚቻለው ጾታን መሰረት በማድረግ በሶስቱ ክልሎች የሚገኙ ተማሪዎች በትግራይና በኦሮሚያ ክልሎች ላይ በተናጠል ሲታዩ የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎት አመለካከትና በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመታየቱ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡ እንደ አጠቃላይ ሲታይ በሶስቱ ክልሎች የሚገኙ ሴት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት የጎላ ልዩነት ባይኖረውም በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት አንጻር ሲታይ ግን የጎላ ልዩነት ተስተውሏል፡፡ ይሄም የጥናት ውጤት የተለያዩ ምሁራን በጥናታቸው ካመለከቱት ውጤት አንጻር ሲታይ በኦሮሚያና በትግራይ ላይ ሲታይ በተመሳሳይ ደረጃ አልተገኙም፡፡ ለምሣሌ ያህል Bätz et al.(2010)፣ Skiner (1985); Garison (1965); Hurloc (1980) በጥናታቸው እንዳመለከቱት ሴት ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ከፍተኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት ያላቸው ስለሆነ ትምህርቱ ከወንዶች ይልቅ በይበልጥ ምቹ የሚሆነው ለሴት

ተማሪዎች ስለሆነ በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤትን እንደሚያስመዘግቡ በጥናታቸውና በጻፉት መጽሀፋቸው ላይ አመልክተዋል፡፡

በሌላ በኩል ከኦሮሚያና ከትግራይ ክልል አንጻር በተናጠል ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት እንዳይኖር ያደርገው በሴቶች ላይ ተጽእና የሚያሳድር ነገር ሊኖር ስለሚችል ያንን ተጽእኖ አሳዳሪ ተላውጦ ማወቅ የግድ ይላል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚገልጹት ከሆነ ሴቶች በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ ጫና ስላለባቸው ምናልባትም በጾታዎች መካከል የሚስተዋለው የቋንቋ ትምህርት ልዩነት የሴት ተማሪዎች ከወንዶች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የፍላጎት፣ የአመለካከትና የውጤት ብልጫ እንዳይኖር ሊያደርግ እንደሚችል ይጠቁማል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ አማራጭ ሊሆን የሚችለው በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ያለው የቋንቋ ትምህርት ሁኔታ በቂ የጥናት ጊዜ ከመኖርና ካለመኖር ጋር ተያይዞ ሴቶች በቤት ውስጥ ሥራ ስለሚጠመዱ ይሄንን ችግር ተቋቁመው ከወንዶች ጋር በእኩል ደረጃ ላይ ወይንም በልጦ መገኘት መቻል አዳጋች ነው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በጥልቀት ሲታይ ውጤቱ ጉልህ ባይሆንም እንኳን ሴቶች ከወንዶች በትምህርት ፍላጎት፣ አመለካከትና በምዘና ፈተና ውጤት ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ ይሄ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ በውጪው ሀገር የተደረገው የጥናት ውጤት ከኢትዮጵያ አንጻር ሊሰራ የሚችል መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ ወደፊት በዚህ ዙሪያ ከላይ በቀረበው ሀሳብ ላይ ተመስርቶ **"በሴት ተማሪዎች ላይ በሚስተዋል ማህበራዊና ባህላዊ ተጽእኖ ምክንያት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የሚስተዋል የቋንቋ ትምህርት ልዩነት"** በሚል ርእስ ሌላ ጠለቅ ያለ ተጨማሪ ጥናት በማጥናት ልዩነቱን አይቶ ከጾታ አንጻር ለሚስተዋለው ችግር መፍትሄ መስጠት እንደሚያስፈልግ የጥናቱ ውጤት ይጠቁማል፡፡

### 4.4.4 ከገጠርና ከከተማ አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት በመማር ሂደት የተስተዋለ የፍላጎት፣ የአመለካከትና የችሎታ ምዘና ውጤት ልዩነት

የከተማ ተማሪዎች በሕብረ ብሄር የጋራ ቋንቋ በሆነው በአማርኛ ትምህርት የችሎታ ምዘና ውጤት፣ ለትምህርቱ ባለ ፍላጎትና በአዎንታዊ አመለካከት የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች በተሻለ መልኩ በከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በGardner (1982; 2007) በማህበራዊ ትምህርት ሞዴል የሁለተኛ ቋንቋ ከመማር ጋር እርስ

በርሳቸው ትስስር ያላቸው ናቸው፤ በማለት ካቀረባቸው ውስጥ አራቱ ማህበራዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች የግለሰቦች የመማር ችሎታ ልዩነት ትምህርቱ የሚከናወንበት አውድ እና ቋንቋውን መማር የሚያመጣው ውጤት ናቸው(Gardner,1982)። ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ሁኔታ ግለሰቡ ወይንም የቋንቋው ተማሪ የሚኖርበትን ከባቢያዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው። ይህም ሁኔታ የአንድ ማህበረሰብ አባላት ለሌላው ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ ያላቸው እምነትና አመለካከት ቋንቋውን በብቃት በመማርና ባለመማር መካከል ያለውን ልዩነት ይወስናል፤ የሚል ነው። ከዚህ አንጻር ማህበራዊ አውድንና አካባቢያዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ለትምህርቱ ባለ ፍላጎት፣ አመለካከትና በቋንቋ ትምህርቱ ውጤታማ ከመሆን አንጻር ልዩነት እንደሚኖር ያመለክታል።

ይሄም አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ያለው ተነሳሽነት ለስኬታማ የቋንቋ ለመዳ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች ወይንም በቋንቋ ለመዳ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች ውስጥ የተማሪው ቤተሰብና ማህበራዊ አውድ መሆኑ ቀርቧል። ምክንያቱን ጋርድነር ሲገልጹ ለመማር ያለ ተነሳሽነት ብቻውን ለቋንቋው ለመዳ ምክንያት አይደለም ይላሉ።

በተጨማሪም Schonell (1965); Tudor (1996); Spolisky (1989) በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ውስጥ አንደኛው እራሱ ተማሪው የሚገኝበት አውድ ነው ይላሉ። ይሄውም ተማሪው ከሌላ ተማሪ ጋር ያለው ግንኙነት፣ ከተለያየ የማህበረሰብ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት፣ አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ቤተሰብ፣ ፖለቲካዊ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች እና የተማሪው የንቃተ ህሊና ደረጃ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይገልጻሉ።

ስለዚህ የተገኘው ውጤት ከምሁራኑ ገለጻ አንጻር ሲታይ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት ሲመረመር ልዩነቱ ተማሪው የሚገኝበት አውድ/መቸት በትምህርት ፍላጎት ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ያረጋግጣል። ይሄውም የተገኘው የትንታኔ ውጤት የሚያሳየው ተማሪው የሚገኝበት አውድ/መቸት አንድን ትምህርት ለመማር አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር አመልክቷል። ምክንያቱም በገጠር የሚገኘው አውድና በከተማ የሚገኘው አውድ የተለያየ በመሆኑ ከክልሎች አንጻር ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት የተለያየ ሆኖ ተስተውሏል።

በከተማ የሚገኙ ተማሪዎች ከገጠር ከሚመጡ ተማሪዎች በተሻለ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡ ክልሎቹ ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እያንዳንዱ ክልል በተናጠል ሲታይ ደግሞ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት በሁሉም ክልሎች ላይ በትምህርቱ በተገኘ የምዘና ውጤትና ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት መካከል የከተማዎቹ በገጠር ከሚኖሩት ተማሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከት መካከል ያለ ልዩነት ሲታይ ደግሞ የከተማዎቹ በገጠር ከሚኖሩት ተማሪዎች በልጦ ቢገኝም የተገኘው ልዩነት በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ላይ በተናጠል ሲታይ ልዩነቱ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ ተማሪው ከሚገኝበት አውድ አንጻር የምሁራን አስተያየት ሲታይ Spolsley (1969) እና Masgort & Gardner (2003) ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩበት አውድ በአመለካከታቸው ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዓኖ እንደሚያሣድር ይገልፃሉ፡፡ ተማሪው ቋንቋን የሚማርበት አውድ ሲባል የማስተማር ዘዴው፣ የመርጃ መሣሪያው፣ የተማሪው አካባቢያዊ ሁኔታ፣ የመምህሩ አቀራረብ፣ ትምህርቱ በፍቃደኝነት ላይ የመሆኑ ወይም ያለመሆኑ፣ ተማሪው ትምህርቱን በጥሩ እይታ የሚከታተልበት መንገድን እንደሚያጠቃልል እና እንዲሁም የትምህርት አውድ በተማሪው አመለካከት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖን ሊያሳድር ይችላል በማለት ይገልጻሉ፡፡


ከምሁራኑ ሀሳብ አንጻር የተማሪው አመለካከት ከቦታ አንጻር ሲታይ በተጨባጭ ሁኔታ ልዩነት ያለ መሆኑን የመረጃው ትንታኔ ያረጋግጣል፡፡ ይሄውም በከተማ የሚገኙ ተማሪዎች በገጠር ከሚኖሩ ተማሪዎች ይልቅ ለህብረ ብሄር የቋንቋ ትምህርት የተሻለ አመለካከት ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡

ይሄም ውጤት ተማሪው ከሚገኝበት አውድ አንጻር ምሁራን ካቀረቡት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር Spolsley (1969) እና Masgort & Gardner (2003) ተማሪዎች ቋንቋን የሚማሩበት አውድ በአመለካከታቸው ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዓኖ እንደሚያሣድር ከገለጹትና Schonell (1965)፣ Tudor (1996); Spolisky (1989) በተማሪ ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው የሚገኝበት አውድ ነው ብለው ከገለፁት ሀሳብ ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ የአመለካከት፣ የፍላጎትና ውጤት የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው በዚህ ጥናትና Masgort & Gardner (2003) ካከናወኑት ጥናት ጋርም ሶስቱ ተላውጦዎች የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ስለሚያረጋግጥ የጥናቱ ውጤት ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪም በቡድን ተኮር ውይይት ወቅትም መምህራኑ የሰጡት ምላሽ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩንና ልዩነቱን ለማጥበብ ተጨማሪ ስራ እንደሚሰሩ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል የሚያስተምሩ መምህራን ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ በፍላጎትና በአመለካከት መመዘኛ መጠይቁና በምዘና ፈተናው የተገኘው ውጤት ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል በአመለካከት፣ በፍላጎትና በውጤት ዙሪያ የተገኘው የጥናት ውጤት በከተማ የሚገኙ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች ተሽለው መገኘታቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 4.4.5 አጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በሚከተለው ሞዴል መሰረት እንደሚወሰን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡

ሰንጠረዥ አርባ አራት ፤ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች ትስስር



ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው አካባቢያዊ አውድ (ክልል፣ ገጠርና ከተማ)፣ የተማሪው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ(ጾታ፣እድሜ)፣ የትምህርት ፖሊሲ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው የአመለካከት ሁኔታ ከክልል ክልል የተለያየ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ አካባቢያዊ አውድ (ክልል፣ ገጠርና ከተማ)፣ የተማሪው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ (ጾታ፣እድሜ)፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር በሚኖራቸው ፍላጎት፣ በትምህርቱ በሚኖራቸው አመለካከትና በትምህርት ውጤት ላይ የሚያሳድረው ተጽኖ ጉልህና ከፍተኛ መሆኑን ከቀረበው የመረጃ ትንታኔ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይሄንንም ከላይ ከተራ ቁጥር 4.3.4 ጀምሮ ካለው የመረጃ ትንታኔና ሰንጠረዥ ላይ በስፋት መመልከት ይቻላል።

ይሄውም ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት በክልል፣ በመኖሪያ ቦታ(ገጠርና ከተማ)፣ ትምህርቱን መማር የሚጀመርበት እድሜ በመለያየቱ ምክንያት ያላቸው ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ የሚመዘገብ ውጤት የተለያየና በክልሎች መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ከጥናቱ የመረጃ ትንታኔ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል። ለአብነት ያህል ውጤቱ ዘርዘር ተደርጎ ሲታይ የከተማ ተማሪዎች ከገጠር አካባቢ መጥተው ከሚማሩ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ በተመዘገበ የችሎታ ምዘና ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

ተማሪው የሚገኝበት ማህበራዊ መስተጋብር በእድሜና በአካባቢያዊ ሁኔታ ላይ፣ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ ተጽእኖ እንዳለው የተገኘው መረጃ ትንታኔ አመልክቷል። በጥቁር እንጨኒ ከአማርኛ ክፍለጊዜ ውጪ ቋንቋውን በመናገርም ሆነ በመለማመድ ረገድ ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን በቡድን ተኮር ውይይቱ ላይ ቀርቧል። በምሳሌነትም ሲያቀርቡ ከትግራይ ክልል ከተፈጥሮ ሳይንስ ውስጥ አንዱን የትምህርት አይነት እንዲያስተምር የተመደበ መምህር ከተማሪዎች ጋር ለመግባባትና ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪነት ሀሳቡን ለማስረዳት እንዲሁም ተማሪዎቹም ከኦሮሚኛ ቋንቋ ውጪ በእንግሊዘኛው ሆነ በአማርኛ ለመግባባት እተቸገሩ መሆናቸውን በቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል። አማርኛ ቋንቋን መናገር የሚችል ተማሪም ሆነ የተወሰኑ የአካባቢው ማህበረሰብ ቢኖሩም በአማርኛ ቋንቋ ለመናገር ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር እንዳለ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ይሄ ሆኖ መገኘት ደግሞ በተማሪው እራሱ በማህበራዊ አውዱ ላይ ተጽእኖ አሳዳሪ እንደሚሆን ያመለክታል። Gerry(1970) አመለካከት ከግለሰባዊና ማህበራዊ ተግባር የሚመጣ ነው። ማህበራዊ ሲባል

እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ለሚከተለው የጋራ አቋም በጽናትና በእይታ አንድ መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ግላዊ ተግባር ሲባል ደግሞ አንድ ሰው ከአካባቢው የሚያዳብረውና በተፈጥሮው የሚኖረው ግላዊ ግንዛቤንና እይታን መሰረት ያደረገ ነው፤ይሉታል፡፡ ከዚህ አንጻር ተማሪው ከማህበራዊ አውድ ከሚያገኘው አመለካከት ለውጥ በተጨማሪ እራሱ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ለአሉታዊና አዎንታዊ አመለካከት መከሰት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ለቋንቋ ትምህርቱ በሚኖረው ፍላጎት ላይም የራሱ የሆነ ተጽእኖ ይኖረዋል ላሉ፡፡ ይሄ መሆኑ ደግሞ በሚማረው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ችሎታና ውጤቱ ላይም አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽእኖን እንደሚያሳድር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በተለይም Gardnere (1984) የቋንቋ ትምህርት ስኬታማ እንዲሆን ከሚያደርጉት ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ቤተሰቦቹ ሲሆኑ ቀጥሎም በአካባቢው የሚገኙ የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና ወይም ተቀባይነትን ለማግኘት ካለው ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር አንድ ተማሪ የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ያለው ተነሳሽነት ለስኬታማ የቋንቋ ለመዳ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች ወይንም በቋንቋ ለመዳ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች ውስጥ የተማሪው ቤተሰብና ማህበራዊ አውድ መሆኑን በዋናነት ሊሰመርበት እንደሚገባ ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም ለመማር ያለ ተነሳሽነት ብቻውን ለቋንቋው ለመዳና ትምህርት ምክንያት አይደለምና ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ በሞዴሉ ላይ እንደቀረበው የተላውጦዎች ትስስርና በተላውጦዎቹ መካከል የሚስተዋልን ጎናዊና ተዋረዳዊ የሆነ የተጽእኖን የሚያሳ ነው፡፡ ይሄውም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ውጤት ላይ ተጽእኖ የሚሳድረው የተማሪው ለትምህርቱ ያለው አመለካከት፤ ትምህርቱን ለመማር ያለፍላጎት፣ ተማሪው የሚኖረበት ከባቢያዊ ሁኔታና እድሜ ደረጃ መሆናቸው በጥናቱ ጠረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተማሪው አመለካከት፣ ፍላጎትና የተማሪው እድሜና መኖሪያ አካባቢን መሰረት በማድረግ ተጽእኖ አሳዳሪ ምክንያቶች የሚባሉት ደግሞ በጋርድነር ሞዴል ላይ በቀረበው መሰረት ዋና ዋና ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም አንደኛው ማህበራዊ፣ ባህላዊና አስተዳደራዊ ተጽእኖዎች፣ ሁለተኛው የግለሰቦች የመማር ችሎታና የዝግጁነት ልዩነት፣ ሶስተኛው ትምህርቱ የሚከናወንበት አውድ እና አራተኛው ቋንቋን መማር በሚያመጣው ውጤትና በዙሪያው ያለ ግንዛቤ አሉታዊ ወይንም አሉታዊ ሆኖ መገኘትን እና እነዚህም ደግሞ በተገላቢጦሽ ተጽእኖ እየተደረገባቸው መሆኑን ሞዴሉ ያረጋግጣል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ

### 5.1 ማጠቃለያና መደምደሚያ

ይህ ጥናት በአራት ክልሎች ማለትም በአፋር፣ በትግራይ፣ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱም የህብረ-ብሄር ተማሪዎች አማርኛ ለጋራ መግባቢያ ቋንቋነት እንዲያገለግል ለመማር ባላቸው አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ ባላቸው ውጤት መካከል ያለውን ዝምድናን በመመርመርና ከሶስቱ ተላውጦዎች አንጻር በክልሎች መካከል፣ ከአካባቢያዊ ሁኔታ፣ ከእድሜ፣ ከጾታ አንጻር ያለውን ልዩነትና የልዩነት ደረጃ መመርመን አላማ አድርጎ የተነሳ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር ጥናቱ በመንደርደሪያነት የቀረቡ ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከት፣ በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤትና እድሜ መካከል ያለ ዝምድና (ግንኙነት) ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ምን ይመስላል?
2. ከእድሜ አንጻር የአማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በተማሪው ውጤት፣ አመለካከትና ፍላጎት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ምን ይመስላል?
3. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርነት ለመማር ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርነት ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ይመስላል?
5. የህብረ ብሄር ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርነት በመማር ሂደት ላይ የሚያስመዘግቡት ውጤት ምን ይመስላል?
6. የህብረ ብሄር ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ትምህርትን በተለያየ የክፍል ደረጃ መማር በመጀመራቸው ምክንያት ዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ላይ ሲደርሱ በሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤት ላይ ልዩነት ይፈጥር ይሆን?

7. ከወንድና ከሴት ተማሪዎች አንጻር ቋንቋን ለመማር ባለ ፍላጎት፣ ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል የታየ መሰረት ያደረገ ልዩነት ይኖር ይሆን?
8. በገጠርና በከተማ አካባቢ ከሚኖሩ ተማሪዎች አንጻር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲማሩ በተማሪዎች ውጤት፣ አመለካከትና ፍላጎት ላይ የሚስተዋል ልዩነት፣ ተጽእኖና የተላውጠዎቹ የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን ይመስላል ?
9. አማርኛን በአንደኛና በሁለተኛ የቋንቋ ትምህርትነት በተለያየ የትምህርት ዝግጅትና ስርአት ሲማሩ ለነበሩ ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በአንድ አይነት የትምህርት ዝግጅትና ስርአተ-ትምህርት እንዲማሩ መደረጉ የተማሪዎችን የቀደምት እውቀትና ችሎታን ማዕከል አድርጎ የቀረበ ነው? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡

ለጥያቄዎቹም ምላሽ ለማግኘት አጥኚው የተለያዩ የአጠናን ዘዴዎችን (የጥናቱን አካባቢ፣ የጥናቱን መረጃ ሰጭዎችን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ለመወሰንም ሆነ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ ዘዴዎችን) ተጠቅሟል፡፡ ለጥናቱ ከተመረጡት አራት ክልሎች ውስጥ የሙከራ ጥናቱን ጨምሮ 24 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በአመቺ የንሞና ዘዴ በመጠቀም ከተመረጡ በኋላ በትምህርት ቤቶቹ ከሚገኙ የክፍል ደረጃዎች ውስጥም የዘጠነኛ ክፍልን በምክንያታዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ መርጧል፡፡ ከዘጠነኛ ክፍል ደረጃም ከላይ በስነ ዘዴው ላይ በተገለጸው መሰረት የሙከራ ጥናቱን ጨምሮ ከኦሮሚያ 286፣ ከትግራይ 270 እና ከአፋር 256 ተማሪዎችንና ከአዲስ አበባ 260 በድምሩ 1072 ተማሪዎች ጾታዊና አካባቢያዊ ስብጥሩን በጠበቀ ሁኔታ ለመረጃ ሰጪነት ተወስደዋል፡፡

የተመረጡት ተማሪዎች ለህብረ-ብሔር የጋራ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከትና ፍላጎት ሊለካ ወይም ሊመዝን የሚችል የጽሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ የመጠይቁም አዘገጃጀት በስነ-ዘዴው ላይ በቀረበው መሰረት በተለያዩ ምሁራን የቀረቡትን መመዘኛዎችንና በምሁራኑ የቀረቡ ጽንሰ-ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የመጠይቁን ትክክለኛነት ለማየት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ የስነልቦና መምህራን እንዲታይ በማድረግ ተጨማሪ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መጠይቁ የአስተማማኝነት ደረጃም ከተረጋገጠ በኋላ መጠይቁ በናሙናነት ለተመረጡ ተማሪዎች ታድሎ በመመሪያው መሰረት እንዲሞሉ በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡

የተማሪዎችን ውጤት በተመለከተ ደረጃውን የጠበቀ ፈተና ተዘጋጅቷል። የተዘጋጀውን ፈተና ሃገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና በፈተናዎች ኤጀንሲ እንዲታይ በመስጠት ተገቢነቱ በድጋሚ እንዲታይ ተደርጎ የመጨረሻ ማስተካከያ በማድረግ ተዘጋጅቷል።

የፈተናውን የአስተማማኝነት ደረጃን ለማወቅ ደግሞ ተማሪዎቹ ከተፈተኑ በኋላ ፈተናውን በማረም ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ተጠኚዎች 20%ቱን ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ተፈታኞች ደግሞ 20% የሚሆኑትን በመውሰድ በመመሪያው ከተፈተኑ በኋላ ፈተናውን በማረም ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከሰጡት መልስ በመነሳት ትንታኔ ተሰጥቶ ታይቷል። ከዚያም የአስተማማኝነት ደረጃውን ለመለካት በፈተናው ውጤት መሰረት ተማሪዎቹ በትክክል የመለሱትንና ስህተት የሆኑትን ጥያቄ በመመዝገብ በአስተማማኝ መለኪያ ቀመር መሰረት ተሰልቶ ታይቷል። በስሌቱ መሰረት የተገኘው ውጤት በጣም ከፍተኛ ሆኖ በመገኘቱ በመረጃ ስብሰባ ተግባር ላይ ውሏል።

የፈተናው ተቀባይነትና የአስተማማኝነት ደረጃ ከተረጋገጠ በኋላ በናሙናነት ለተመረጡት ተማሪዎች በማቅረብና በመፈተን ለእያንዳንዱ ተማሪ በተሰጠ የአመለካከትና የፍላጎት መለኪያ መጠይቅ ጋር እየተገናዘበ ኮድ እየተሰጠ መረጃ ተሰብስቧል። ከዚያም ፈተናውን በኮዱ መሰረት በመሰብሰብና በማረም የተገኘው ውጤት ለሂሳብ ስሌት በሚያመች መልኩ ወደ መቶኛ ተለውጦ ከተመዘገበ በኋላ ተማሪዎቹ ያስመዘገቡትን ውጤት ትምህርቱን ለመማር ካላቸው ፍላጎትና ለትምህርቱ ካላቸው አመለካከት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማየት ሲባል የእያንዳንዱን ተላወጠ አማካኝና መደበኛ ልዩነት በማስላት በተላውጠዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ታይቷል።

በተጨማሪም እያንዳንዱ ተላውጦዎች ከክልል አንጻር፣ ከገጠርና ከከተማ፣ ከጾታ፣ ከእድሜ አንጻር ያላቸውን ልዩነትና ተመሳስሎ ለማወቅ ተችሏል። ልዩነትና ተመሳስሎአቸውን ለማየት ሲባል የእያንዳንዱን ተላውጠ አማካኝ ውጤትን የ"ቲ" ቴስትና በባለ አንድ ገጽታ የንጽጽር ትንተና(one way Anova) ቀመርን በመጠቀም ያለውን ልዩነትና ተመሳስሎን ለማረጋገጥ ተችሏል። በልዩነት ማወዳደሪያ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ምክንያታዊ መሆኑን በእያንዳንዱ የተላውጠ የደረጃ ነጻነት ላይ $P \leq 0.05$ መሆኑን በማየት የአስተማማኝ ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ዘዴዎችና ሂሳባዊ ስሌቶች መሰረት በሚከተለው ውጤት ላይ ተደርሷል።

- ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ባላቸው ፍላጎት፣ ለቋንቋ ትምህርቱ ባላቸው አመለካከትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ተማሪዎች የህብረ ብሄር የጋራ መግባቢያ ቋንቋ የሆነውን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውና ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ በተቃራኒው ዝቅተኛ ፍላጎትና አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ደግሞ በትምህርቱ ዝቅተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል፡፡

- ከክልሎች አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ፍላጎትና አመለካከት ያላቸው ከፍተኛ ውጤትን አስመዝግበው ተስተውለዋል፡፡ የአፋር ክልል ከትግራይ ክልል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ትግራይ ክልል ከኦሮሚያ ክልል አንጻር ሲታይ ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተቃራኒው የኦሮሚያ ክልል ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ከሶስቱ ክልሎች አንጻር ሲታይ ዝቅ ብሎ የተገኘ ሲሆን በትምህርቱ የተመዘገበው ውጤትም ዝቅ ብሎ ተገኝቷል፡፡

- የቋንቋ ትምህርታቸውን ከአንደኛ ክፍል የጀመሩት ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዘግይተው (ከሶስተኛ ክፍልና ከአምስተኛ ክፍል ደረጃ) ከጀመሩት ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የቋንቋ ትምህርታቸውን በጣም ዘግይተው የጀመሩት ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ዝቅ ብሎ መገኘቱን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

- በተገኘው የቡድን ተኮር ውይይት መሰረት ከፍ ካለ የክፍል ደረጃ ላይ(ከአምስተኛና ከሶስተኛ ክፍል) ፊደል መቁጠር መጀመሩ በተማሪዎቹ ላይ ወደ ህጻንነት የተመለሱ

ያህል ስሜትን እያሳደረ መሆኑን የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ በዚህ የእድሜ ደረጃ ወደ ፊደል ቆጠራ መገባቱ ትምህርቱን ለመማር ዝግጁነት ላይ ተጽኖ እያሳደረ መሆኑን ጭምር የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ከቀረበው መረጃ ማረጋገጥ የሚቻለው የቋንቋ ትምህርቱ መሰጠት የሚጀምርበት የክፍል ደረጃ ከፍ ባለ ቁጥር በተማሪዎቹ ስነ-ልቦና ላይ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን የመረጃ ትንታኔው ውጤት ያረጋግጣል፡፡

- ከጾታ አንጻር ለትምህርቱ ያለ የአመለካከትና ትምሕርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት መካከል የጎላ ልዩነት የሌለ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በትምህርቱ የተመዘገበ ውጤትን በተመለከተ ግን ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውንና ክልሎች በተናጠል ሲታዩ ግን በትግራይና በኦሮሚያ ክልል የጾታን ልዩነት መሰረት አድርጎ ለትምህርቱ ባለ ፍላጎት፣ አዎንታዊ አመለካከትና በምዘና ፈተና ውጤት ላይ የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- የቋንቋ ትምህርት በቂ የማማር ማስተማር ክፍለ ጊዜን የሚጠይቅ ቢሆንም በየክልሎቹ ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት የተለያየ መሆኑንና በየክልሉ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ ችሎታ ያላቸው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

- የከተማ ተማሪዎች ከገጠር ተማሪዎች አንጻር ሲታይ የከተማ ተማዎች በገጠር ከሚኖሩት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከትና ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው በትምህርቱም የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ክልሎቹ ካሉበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በተናጠል ሲታይም በገጠርና በከተማ ተማሪች መካከል ያለ ልዩነትን በተመለከተ በአፋር፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች የምዘና ፈተና ውጤትና ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎት በተመለከተ የተስተዋለው የከተማዎቹ በገጠር ከሚኖሩት ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ በልጠው ተገኝተዋል፡፡ ለትምህርቱ ባለ አዎንታዊ አመለካከት በኩል የከተማዎቹ በገጠር ከሚኖሩ ተማሪዎች በልጠ ቢገኝም የተገኘው ልዩነት በትግራይና በኦሮሚያ ክልል ላይ ግን ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡

- የቋንቋ ትምህርታቸውን ከአንደኛ ክፍል የጀመሩት ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት ውጤት ዘግይተው (ከሶስተኛ

ክፍልና ከአምስተኛ ክፍል ደረጃ) ከጀመሩት ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የቋንቋ ትምህርታቸውን በጣም ዘግይተው የጀመሩት ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍላጎትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት ዝቅ ብሎ መገኘቱን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ይሄም በየክልሉ ያሉ ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ላይ ሲደርሱ በአመለካከት፣ በፍላጎት እና በትምህርቱ ውጤት በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ጥናቱ አመልክቷል፡፡

- ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ለአንደኛና ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአንድ አይነት ስርአተ-ትምህርት ተዘጋጅቶ እንዲማሩ መደረጉ የተማሪዎችን የቀደምት እውቀትና ችሎታን ማዕከል ያደረገ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው የችሎታ ምዘና ውጤት፣ አመለካከትና ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት የተለያየ በመሆኑ ምክንያት በመካከላቸው ያለውልዩነት የጎላ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል፡፡

- ከእድሜ አንጻርም ሲታይ ትምህርቱን መማር የሚጀምሩበት የእድሜ ደረጃ ሲጨምር ለትምህርቱ ያላቸው በጎ አመለካከት፣ ፍላጎትና ውጤት እየቀነሰ እንደሚሄድ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተለይም ከእድሜ አንጻር ተማሪዎች መካከል የተስተዋለው ልዩነት ከፍተኛ ሆኖ የተገኘው ትምህርቱን ዘግይተው ከሶስተኛና ከአምስተኛ የክፍል ደረጃ መማር በጀመሩ የክልል ተማሪዎች ላይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በነዚህ ክልሎች እድሜ ሲጨምር ትምህርቱን ለመማር ያለ ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርቱ የሚያስመዘግቡት የችሎታ ምዘና ውጤት የሚቀንስ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአፋር ክልል ላይ ልዩነት ቢኖርም ልዩነቱ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከግኝቶቹም በመነሳት የሚከተለው የመፍትሄ ሀሳብና አስተያየት ቀርቧል፡፡

- በቋንቋ ትምህርቱ ላይ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊና የመማር ማስተማሩ አውድ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ መሆኑን ጥናቱ ያረጋገጠ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ደግሞ ከሌሎቹ ክልሎች በተለየ መልኩ ተጽእኖው ከፍተኛ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብና አስተያየት

- በተለያየ ክልል የሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በመማር ሂደት በአመለካከት፣ ትምህርቱን ለመማር ባለ ፍላጎትና በችሎታ ምዘና ውጤት ላይ በተለያየ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ት/ሚኒስቴር ወጥ ሆነ የትምህርት አሰጣጥ ስርአት እንዲኖር ማድረግ አለበት። ወይንም ሌላ አማራጭ በመፈለግ እንደልዩነታቸው ከ1 - 12 ክፍል ድረስ በልዩነታቸው መሰረት በትምህርቱም ሆነ በፈተናውም መስተናገድ አለባቸው። አለበለዚያም ወጥ የሆነ የቋንቋና የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲን በማውጣት ክልሎች ወጥ የሆነ አሰራርን መከተል ይኖርባቸዋል።

- ወጥ የሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ፣ የክልል ስራ ቋንቋ፣ የፌደራል ቋንቋና የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ በመንግስት ደረጃ በማውጣት ክልሎች ያንን ተግባራዊ እንዲደርጉ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል።

- የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚመለመሉ መምህራን ቋንቋን ለማስተማር ካላቸው ችሎታንና ፍላጎት አንጻር ተመልምለው በአግባቡ ሰልጥነው ቢወጡና ቋንቋውን እንዲያስተምሩ ቢደረግና ክልሎችም በቋንቋው ችሎታ ያለቸው መምህራን ተመልምለው እንዲሰለጥኑ ማድረግ ቢችሉ በዚህ ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች ሊፈቱ ይችላሉ።

- በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ክፍተት በአብዛኛው በአንደኛ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን በቋንቋው የችሎታ ማነስ ምክንያት የመጣ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ስለዚህ ክፍተት ተወግዶ ተማሪዎቹ በፌደራል ተቋማት እኩል የመሳተፍ እድላቸው ቢመቻች።

- በየክልሎቹ በአንዱ ክልል አንድ፣ በአንዱ ክልል ሁለት፣ በአንዱ ክልል ሶስት የሁለተኛ ቋንቋን የሚማሩ አሉ። ስለዚህ ይሄንን ለማመጣጠንና ዜጎችን የበለጠ ለማቀራረብ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አንድ ሌላ የሀገሪቱን ቋንቋ በምርጫቸው እንዲማሩ ቢደረግ ያለውን ያልተመጣጠነ የቋንቋ የትምህርት ክፍተትን ይሞላል።

- ማንኛውም ትምህርት ጊዜን ይፈልጋል በእኩል ጊዜና የእድሜ ደረጃ መማር ያልጀመሩትን በእኩል ደረጃ ላይ ይደርሳሉ በሚል በተመሳሳይ ካሪኩለም እንዲማሩ ከመደረጉና 10ኛ ክፍል ላይ ተመሳሳይ ፈተና እንዲፈተኑ ከመደረጉ በፊት ክፍለጊዜውን የማስተካከል ስራ ቢሰራና ወደ አንድ ደረጃ የማምጣቱ ስራ እንዲሰራ ትምህርት ሚኒስቴር የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ቢያደርግና ክልሎችም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በተሰጠው በማስተካከያ መሰረት በክልሎቹ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶቹን ቢስተካከሉ ችግሩ ሊወገድ ይችላል፡፡

- በጥናቱ በተገኘው ውጤት መሠረት አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ሲሰጥ ተማሪዎቹ ለቋንቋው ያላቸውን አመለካከት፣ ቋንቋውን ለመማር ባላቸው ፍላጎት ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር ክልሎች ወጥ የሆነ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ስርአትን መከተል ይጠበቅባቸዋል፡፡

  ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት እንዲያስተምሩ የሚመለመሉ መምህራንና የመምህራኑ አሰለጣጠን ችግር ያለበት መሆኑን በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይሄ ደግሞ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም፡፡ በተማሪ አመለካከት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መምህሩ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

- አማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ በክልሎች መካከል የሚስተዋለውን የአመለካከት፣ የፍላጎትና የውጤት ልዩነትን ማጥበብ ከማስቻሉም በላይ ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠት መጀመር ያለበትን የክፍል ደረጃ ሲገልጹ 85 በመቶ አካባቢ የሚሆኑት ከአንደኛ ክፍል መሆን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ለተማሪው ቢሰጥ የተስተዋለውን የስነልቦና ተጽእኖ ስለሚቀርፍ በቋንቋ ትምህርቱ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሄ ሆኖ መገኘቱ ደግሞ ለተማሪው በፌደራል ደረጃና በተለያየ ክልሎች ሄዶ የመስራት እድል ይፈጥርለታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ወደ ሌላ ክልል

ለማስፋፋት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ስለሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋንም ለማሳደግ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

- በተለይም በኦሮሚያ ክልል በተወሰኑ ተማሪዎች ዘንድ የአማርኛ ቋንቋ በቀድሞው ስርአት ወቅት ቋንቋው በደል እንደፈጸመ የመመልከት ዝንባሌና ክፍተት በመኖሩንና አንዳንድ በሚዲያ (በኦሮሚያና የፌደራል መገናኛ ብዙሀንና) የሚተላለፍ መረጃዎች በቋንቋ ትምህርቱ የመማር ፍላጎትና አመለካከት ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድር መረጃ በሚያስተላልፉበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላው መንገድ በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና አመለካከት ላይ ተጨማሪ ተጽእኖ እንዳያሳድር አደርገው መረጃዎችን ቢያስተላልፉ ይመረጣል።

- የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት ለማስተማሪያነት ተብሎ መጽሀፍ ሲዘጋጅ መጽሀፉን የሚያዘጋጁ አካላት የትምህርቱን አቢይ አላማን መሰረት በማድረግ የሁሉንም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ያማከላ ሁሉንም በእኩል ደረጃ ሲስብ በሚችል መልኩ ማዘጋጀት አለባቸው። ስለዚህ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ለሚያዘጋጁት አካላት የመማሪያ መጻህፍቱ ሊያካትታቸው የሚገባውን መስፈርት አውጥቶ ለሚያዘጋጁት አካላት ቢሰጥና ማእከላዊነቱን የተበቀ መጽሀፍ ማዘጋጀትን የግድ ይላል።

- በመገናኛ ብዙሀንም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ ቋንቋን በተመለከተ ለህበረሰቡ የሚተላለፉ መረጃዎች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ተጽእኖ እንዳያሳድሩ በጥንቃቄ መተላለፍ አለባቸው። በመስኩ በየደረጃው የሚገኙ ሀላፊዎችም ሆነ መንግስት አስፈላጊውን ቁጥጥር ቢያደርግ ችግሩ ልስተካከል ይችላል።

## ዋቤ መጻህፍት


ሙሉእመቤት ዘነበ። (1989ዓ/ም)። *"ስነጽሁፍ በቅድመ 1966 በበአማርኛ ስርአተ ትምህርት ውስጥ የነበረው ድርሻና አሁን ሊኖረው የሚገባው ሚና፣ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ (ከ9ና- 12ኛ ክፍሎች) ለዐውደ ጥናት የቀረበ የጥናት ጽሁፍ።"*አዲስ አበባ፣ ስ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ.. /ያልታ ተመ/።

ማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና የኦዲዮ ቪዥዋል መምሪያ። (1994ዓ/ም)። *የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊስ መንግስት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ፕሮግራሞች።* አዲስ አበባ፣ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ፕሬስ።

ብርሀኑ ገበረማሪያም። (!976ዓ/ም)። *"ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት።" ያልታተመ፣ የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (1981ዓ/ም *"የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ፖሊሲ ጥናት።")* ጥራዝ አንድ፣ አዲስ አበባ /ያልታተመ/።

አበበ ሽፈራ። (1990ዓ/ም)። *"አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በሰባት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት።" ያልታተመ፣ ለኢጁኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ።* ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ።

እሸቱ ወንድሙ። (1997ዓ/ም)። *"ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለ ግንኙነት(በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን)።" ያልታተመ፣የ አርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡

አጠቃላይ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት። (1986ዓ/ም) አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ድ።

የትምህርት ስልጠና ፖሊሲና አተገባበር። (1994ዓ/ም) አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተር ፕራይዝ።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት። (1986ዓ/ም) አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ። (2001ዓ/ም)። *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር።* ባህርዳር፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

ደረጀ ተረፈ። (1991ዓ/ም)። *በአዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ የማስተማር ቋንቋዎች ፖሊሲ አፈፃፀም ሒደትና የገጠሙ ቴክኒካዊ ችግሮች (በወርሃዊ የትምህርት ሚኒስቴር ባለሙያዎች ውይይት የቀረበ ውስን ዝግጅት)* አዲስ አበባ፣ ስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት ት/ሚኒስቴር።

ዳንኤል መኮንን። (1997ዓ/ም)። *"በሀዲያኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በሆሳእና ከተማ የሚገኙ የሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት።"* ፣ለኢጁኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ/ያልታተመ/።

ድንቁሳ ዴሬሳ። (1996ዓ/ም)። *"በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማርኛ ቋንቋ አፈ-አፈትና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል ኢ-አፈፈት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች።"* አዲስ አበባ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/።

ጥላሁን ገብረክርስቶስ። (1997 ዓ.ም.፣ ግንቦት)። *"አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር - ማስተማር አንዳንድ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች።"* የቋንቋ ጥናት ተቋም 17ኛው ዓመታዊ ጉባኤ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

Aggarwal, J. C. (1996). *Principles Methods and Techniques of Teaching.* New Delhi: Vakas Publishin House Put Lts.

Aggarwal, J. C. (1998). *Essentials of Educatioanl Psychology Reprinted.* New Delhi: Yakas Publishing Hous Put Ltd.

Appel, R. and Muysken, P.(1992). *Language contact and Bilingualism.*NewYork: USA by Routledge, Chapmanand Hall, Ine.

Arcmo, S. T. (1997). *Quality in Education: An Implementation Hand Education.* New delhi: Venity Books Internatioanl.

Au, S. (1988). *A Critical Appraisal of Gardner's Social-Psychological Theory of Socond language learning.* Language learning,38,75-100.

Baram-Tsabari et ai,. (2008). *Asking scientists: a decade of questions analyzed by age, gender, and country.* Science Education, 93(1), 131-160.

Bätz et al,.(2010). *Differences between Boys and Girls in Extracurricular Learning settings.* International Journal of Environmental & Science Education. Vol. 5, No. 1,51-64.

Bernard, H. W. (1972*). Psychology of Learning and Teaching.* New York: McGraw-Hill Book Company.

Bickley, V. (1990*). Lanugague use Language Teaching and the Curriculum.* Hong Kong: Institute of Lanugauge in Education Department.

Brown, H. D. (1993). *Principles of Language Learning and Teaching (3rd ed*). London: prentice Hall International (Uk) Limited

------------------(2005). *Principles of Language Learning and Teaching.* USA: Printted in united States of America.

-----------------(2007). *Principles of Language Learning and Teaching.* San Francisco State of University: Pearson longman.

Bugelsk, R.B. (1971). *The Psychology of Learning Applied to Teaching.* New York: The Bobbs Merrill Company, Inc.

Bloor, T and Tamrat, W. (1996). *Issues in Ethiopian Language Policy and Education.* Journal of Multilingual and Multicultural Development Vol. 17 No. 5 pp. 321-337

Bloor, T and Tamrat, W. (1995). *Multilingualism and Education*: The Case of Ethiopia. In

Buros, K. O. (1959). *The Fifth Mental Measurement Year Book.* New Jersey: T he Graphon Press.

Callahan, F. J. (1988). *Teaching in the Middle and Secondary,Schools Planning for Competence.* (3rd ed). New York: Macmillan Publishing Compony.

Campbll, L. (2004). *Historical Lingustical an Introduction.* Edinourgh Unviersity Press.

Celce-murcia, M.(1991).*Teaching English as secocond language or Forign language.* Publishing house Pvt .ltd.

Chia E. N. (2006). *African Langauge and Development of African Communities (La Linguistics Africanie etle Development desCommuntes Africanes Councilfor the Development of Social Science Research in Africa).* Oxford Univerity CoDESRIA.

Creswell, J. W.(2012). *Educationl Research Planninig, Condacting,and Evaluating Quantitative and Qualitative Research.* Boston or New York: University of Nebraska_Lincoln.

Cookes, G. and Schmidt, R.(1991). *Motivation: Cambrige the research agenda.* Language learning.41,469-384.

Cook V. (2001).*Second language learning and language teaching.* New York: Oxford univertity press Inc.

-------------.(2003). *‹The Poverty-of-the-stmules argument and stracture—dependency in L2 usersof English.›* *International Reviews of Applied Lingustics* 41/3: 201-269.

Crombach, L. L. (1963). *Educatinal psychology.* London: horcurt, prac and Worled Inc.

Coulmas, Florian (1997). *Sociolinguistics.* Germany: Black well Hand bodes in Lingustics.

Cummins, J. (1981). *The role of primary language development in promoting Educatinal success for language Minority students in "Schooling &*

*learning minority students A Theoretical Frame work." California State of University;* Evaluation and Assessment Center.

Daniel, S. A. and Abebayehu, A. T.(2006). *Instractional Language Policy in Ethiopia Motivated by Poletics or the Educational need of Children?.* Vol, 37 No, 3&4 PP, 151-168.

Desalegn, Chalchisa.(2004). *Comparativ e Studye of Student Achivment In English and Mathmatics In Addis Ababa, Amhara and Oromiya Regional States Ethiopia.* Department of Education College of arts and commerce Undhra Universtiy Visakhapatnam 530003.

Davit, R. J. and Samuel, B. (1970*). Pyschology of the Educational Process.* New York: mcgraw-Hall Book Company.

Dembo, M. H. (1994). *Applying Educational Psychology.* London: University of Southern California.

DÖrnyei. Z.(2007). *The Research Method in Applied linguistics Quantitative, Qualitiative and Mixed Methodologies.* New York: Oxford University Press.

Edwards, J. (1994). *Mulilinualism* .New York: Routledge London.

Ellis, R. (1997). *SLA Research and language Teaching.* Oxford. Oxford Universti press.

Evans, K. M. (1965). *Attitude and Interest in Education.* London: Routelege and Kegno Paul Lted.

Fasold, R. (1987). *The Sociolingustics of Society.* England: Basil Black Well

Federal Dmocratic Republic of Ethiopia. (2010). *Curriculum Framework for Ethiopian Education (KG-Grade 12).* Addis Ababa: Ministryof Education.

Fishman, A. J. (1972). *Advances in the Sociology of Language.* Paris: Mouton-the Hague.

Gagne, R. M. (1977). *The conditions of Learning.* New york: John wiley and sons.Inc.

Gardner, R. C. (1968). "*Attitude and Motivation: Their Role in Second-Language Acquistion" Tessol A Jornal for Teacher of English to Speakers of other Languages Vol.* 2, No. 3, PP. 141-151

----------------(1985). *The Attitude/ Motivation Test Battery: technical Report.* UniverSity of western Ontario.

---------------- (1985). *Social psychology and second-language learning: The role of attitudes andmotivation.* London, England: Edward Arnold

---------------- (1982). *Social factors in language retention.* Chapter 2 in R. D. Lambert & B.Freed (Eds.), Loss of language skills. Rowley, MA: Newbury House.

---------------- (2001). *Integrative motivation and second language acquisition.* In Z. Dörnyei &R. Schmidt (Eds.), Motivation and second language acquisition. Honolulu, HI: The University of Hawaii, Second Language Teaching & Curriculum Center, 1-19.

---------------- (2006). *The socio-educational model of second language acquisition: A researc paradigm.* In S. H. Foster-Cohen, M. Medved Krajnovic, & J. Mihaljevic Djigunovic(Eds.), EUROSLA Yearbook, 6, Amsterdam, John Benjamins Publishing Company.

---------------- (2007). *Motivation and second language acquisition.* Porta Linguarum, 8, 9-20.

Garrison, K. C. (1965). *Psycholgoy of Adolescence .* New jersey: Engle wood cliffs, N. J Prentic-hall.

Garry, R. (1970). *The Nature and Conditions of Learning.* New Jese. prentice. Hall. Inc.

Gidi, S. (1990). "Interest and its Contribution as a Mental Resource for Learning". *Review of Educatioanl Research.* V. 60:4 Washington. Dc: AERA Publication Department.

Good, T. And Brophy, J. (1990). *Educatioanl Psychology 4th ed.* New York: McGraw-Hill Book Cmpay.

Gordon, M.E. (1980). *Attitudes and motivation in second language achievement: A study of primaryschool students learning English in Belize, Central America.* Unpublished doctoraldissertation, University of Toronto, Canada.

Hadsoin, A. R. (1980). *Soioloinguistics.* New York: Cambridge University Press.

Hancock, R. D. (2004). "Effects of test Anxiety and Evaluation Threat on Students' Achievement and Motivation." *Educatioanl J ornal.* Vol. 97, No. 3, PP 294-289.

Harmer, F. J. and Michel. H.A.B. (1989). *Bilinguality and Bilingualsim.* New York: Cambridge University press

Harmer, J. (1983). *The Practic of English Language Teaching.* New York: Longman.

-------------- (1991). *Hand Book of Lanugage Teachers. The Practice of English Language Teaching (New Edution*). New York: Langman.

Hanna, G. (2000). *Declining gender differences from FIMS to TIMSS.* ZDM — The International Journal on Mathematics Education, 23(1), 11-17.

Harms, U. & Krombass, A. (2008). *Lernen im museum -das contextual model of learning.* Unter-richtswissenschaft,36(2), 150-166.

Hoffman, Charlotte .(1991). *An Introduction to Bilingualism.* New York: Longman.

Hurlock, E. B. (1965). *Adolescent Development 3rd ed.U.* S.A: McGraw-Hill Inc.

------------------ (1972). *Child Development.* New York: MacGraw-Hill Book Company.

------------------(1980). *Developmental Psychology: a Life Span Approach.* New Delhi: Tata McGraw-Hill Publication Company.

---------------------(1996). *Developmental Psychology: A life span-Approch.* New delhi: Megraw.HallPublishing company Ltd.

Jenkins, E.W. (2006). *Student opinion in England about science and technology.* Research in Science & Technological Education, 24(1), 59-68.

Johnson,S.J. and Elissa, L. N. (1989) "Cognitive Psychology"Critical Period Effects in Second Language learning .*The Infulance of maturation State on the AcQuisition of English as asecond language.* University of Illinois.

Kaiser, G., & Steisel, T. (2000). *Results of an analysis of the TIMS study from a gender perspective.* ZDM —The International Journal on Mathematics Education, 23(1), 18-24

Krashen, S. D. (1982). *Prinsiples and Practic In Second language acquisition.* NewYork and London: Universti of South California.

----------------- (2009). *Prinsiples and Practic In Second language acquisition.* NewYork and London: Phoenix ELT.

Kuhlen, G. R. (1968). *Studies in Educatioanl Psychology.* Toronto: blaisdell Publishing Company.

Kuppuswamy, B. (1984). *Advanced educational psychology.* New delhi: nsterling mublishes,private Ltd.

Laisi, K. (2002). *Comparing the situation of Language Policy Change in Ethiopia and Guatemala. The cases of Orom Maya. Presented* at: Congres Mondial sur Les Politiques Linguistiques, Barcelona, 16 — 20April, 2002. available at:

Lambert, w. w. and wallace, E.C. (1964). *Social psychology.* New jersey: prentice Hall.Inc.

*Lambert, D. and David, L.(2000). Understanding Assessment, Purpose, Perceptions, Practice. London. New York: Tayler and Francis Group.*

Larson- Freeman, D. (1991).*In Introduction to Second Language Acquisition Research.* New York: Longman.

Larson-Freeman,D., and M. H. long. (1994). *In Introduction to Second Language Acquisition Research*. London: Longman.

*Lightbown, P. M. (2011). How Language are Learned. Oxford university press.*

*Linn, L.R. and Norman, E.G. (2000). Measurment and Assessmetn in Teaching. New Delhi; India Baba Barkha Printers.*

Little-wood,w.(1984). *Foreign and second language learning.* New York: Canberidge university press.

Mackey, F. W. (1965). *Language Teaching Analysis*. Hong Kong: Longman.

Malim, T. and Ann, Birch, E.C. (1998). Introductory psychology. London: Macmillan press Ltd.

*Malesevic, S. (2004). The Sociology of Ethnicity. New Delhi. SAGE publications*

*Marzano, J. R. and Dehra J.P. (1993). Assessing Student out-come: Verginia USA Association for Supervision and Curriculum*

Masgoret, M. A. and R.C. Gardner .(2003). *"Attitudes, Motivation and Second Languge Learning: A Meta-Analysis of studies Conucted by Gardner and Associates."* Lanuguage Learning A Jornal of Research in Language Studies. Vol. 53, No. 1 PP. 123-159

*May, S. and Harnberger, N. H (eds) .(2008). Encyclopedia of Language and Educational, 2nd edition, volume 1. Language Policy and Political Issues in Education 15-25 Springer science + Business media CLC.*

McCombs, L. B. (1997). *The Learner Centered Class Room and School Strategies for Increasing Student Motivation and Achievement.* Sanfrancisco: Jossey Bass Publishers.

Mclauphlin Barry .(1987).*Theories of Second Language Learning.* London; Edward Arnold.

McMillan, J. H.,and Schumacher, S.(2006). *Research in Education. Evidence-based inquiry.* 6TH ed. Bosten: Pearson.

Medhaine, Haregiorgis .(1986). "*The attitude of elevence grade sttudents Towards the Learning of English as foreign language" Un published M.A Thesis.* Addis Ababa university.

Mitcheil, V. J. (1985). *The ninth Mental Measuremens Year Book.* Valume. II, Lincon, Neberska: University of Neberaska Press.

Morgan , C.T. etal .(1986). *Introduction to Psychology.* New york: Megraw-Hill book company

*Mutasa, D E(ed) (2006). African Langauges in the 21st century the Main Challenges. Pretoria: Simba Guru Publishers.*

*Nderson, C. J. (1995). Langauge Test Construction and Evaluation. London Cambridge Unviersity Press.*

Noll. H. P., Scannell. P. D. & Craing. C.R (1979). *Introduction to Educational Measurment* (Forth Edition). Boston: Library of Congress.

Obeidat M. M.(2005). *Attitudes and Motivation in Second Language Learning: Journal of Faculty of Education* UAEU ,18, NO 22 p. 1_17.

Oller, J.(1981). *Language as Intelligence?* Language learninig,32,183-189.

Oyama,S.E. (1990). *Maturatinal Constraints on Language Learning.* "cognitive Science,14,"1128.

Pride, B. J & Jante, H. (1979*). Sociolinguistics.* New York: Hazell Watson and Viney Ltd.

Punkhurst, R. (1976). *"Historical Background of Education in Ethiopia in Bender, M. L and et. Al.*" language in Ethiopia: Oxford University Press.(305-323)

*Race, P.,Sally, B. and Brenda, A. (2005). (500 Tips) on Assessmen. New York: Nouthlegefalmer.*

Robinson, P. (2001). *Cognition and Seconhd Language Instruction.* U.N: Cmbridge Univeresity Press.

Rojer, D. (1995). *Mastering Psychology.* London: MaCmill Press.

*Rubin, J. & Bjoral, H. J. (1971). Can Language be Planned? Sociolinguistic theory and practice for developing nations. An east west center book the University pres of Hawaii.*

Rokeach, M. (1968) . "In sills. D.L. (ed). *Introduction to Enciclopedia of The Social Science.* Vol.1. New York: The Macmillan company and the free mess (449-457).

Russell, L. (1989) . *"Development attitude and attitudes ,Interests, and values" In skinner, C. E. (ed) educational psychology.* New delhi : prentice .Hall of India (375-83).

Schanell, J. F. (1961*). The Psychology and Teaching of Reading.* Landon: Oliver and Boyd.

Selinger, H. W. and Shohamy,E.(2011). *Second Language Research Methdology.Shangay:* Oxford University Press.

Sherif . etal,.(1965) . *Attitude and Attitude Change. Philadeiphia.* W.B. students company

Silberman, et al, .(1992). *The Psychology of Open Teaching and Learning.* New York: McGraw-Hill Book Company.

Sills, D.L.(1968). *International Encyclopedia of Social Science.* Vol.1 and 2 . New York: the Macmillan Company andfree Psess.

Skinner, E. C. (1985*). Educatioanl Psychology. 4th ed,* New York: Prentice-Hall, Inc.

Skinner, E. C. (1989). *Educatioanl Psychology.* New delhi: Mentice Hall of India Private Limited.

Smith, M. B.(1968). *"Attitude change" in Sikll, D.L. international Encyclopedia of the social science.* Vol.1 and 2, New York: the Macmillan company and the free press(458-66).

Snow, C. E. (1977). *Age Differences in Pronunciation of Foreign sounds.* Language and speech,20,357-365.

Snow, C. E. & Hoefnagel - Hoehle, M. (1978). *The critical Period for language AcquiSition:* Evidence for Second language learning "Chiled development, 49,"1114-28.

Spolsky.B.(1969*)."Attitude aspects of social Language Learning"* val. xix, Nos. 3 and 4 (271-83)

----------(1990) *.Conditions of Second Language Learning.* Oxford: Oxford university press.

---------- (1998*). Condition For second Language Learning.* New York: oxford University Press.

Stern, H. H. (1983). *Fundamental concepts of Language Teaching.* New York: oxford university Press inc.

-------------- (1991). *Fundamental concepts of Language Teaching.* New York: oxford university Press inc.

Stewart, W. A. (1968). *'National Development and Language Diversity*' in Fishman, J. . (ed). Reading in Sociology of Language Paris: Moutons and Co, Printers, (44-216)

*Tamrat,W. and Bloor. T.(1996). Issues in Ethiopian Language Policy and Education. Journal of Multilingual and Multicultural Development. Vol. 17, No. 5, 1996.*

*Tollefson, W. J. (1991). Planning Language, Planning inequality language Policy in the Community.* New York: Longman.

Turi, M. B. (2003). *Understanding Expertise in Teaching Case Studies of ESL Teachers.* Hongkong: Cambridge University Press.

Tudor, I. (1986). *Learner Centeredness as Language Education.* New York: Cambridge University Press.

Turner, S. B. (1996). *The Black well Companion to Social Theory.* Oxford Uk: Black well Publishers Ltd.

USAID Ethiopia.(2010). *Ethiopia Early Grade Reading Assessment.* (Data analytic report: Language and early learning, Ethiopia.

USAID Ethiopia.( December 2004 ). *Ethiopian Second National Learning Assessment of Grade 4 students:* National Organization for Examinations Addis Ababa

*Wardhaugh, R. (1992). An Introduction to Sociolinguistics. USA. Oxford UKE Cambridge.*

Warriner, E. J. (1989). *English Grammar and Composition.* New York: Harcourt Brace Jovanouich. inc.

Webb,V. and Kembo-Sure(2000). *African Voices an introduction to the languages and linguistics of Africa.*Cape Towen: oxford university press southern Africa.

Weeden, P.; Jan, W. and Patrica, B. *(2002). Assessment what's in it for School. London: Routledgefalmer Taylor and Francis Group.*

Welmer, M. (1993). *Improving your Classroom Teahing. London*: Internatioanl Educational Publisher.

Wikepieda .(2009). *Multilingualism.* Retrieved on January 20 from Wikepieda the free Encyclopieda

Wilso S. S.(1971). *Interest and Disciplin in Education.* London: Routledge and Kegan Paul Ltd.

Wondwosen, T. and Bloor,T.(1996). *Issues in Ethiopian Language Policy and Education.* Addis Ababa: Kotobe College of Teachear Education.

## አባሪ 1 ፡-የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት መፍቻ

ሁኔታዊ ፍራቻ ........................................................ Situational anxiety

ሃይል ........................................................ Reinforcement

ህብረ- ብሄር........................................................ pluralistic socity

ለራስ ያለ የብቃት ስሜት........................................ self-efficacy

ርሳት ........................................................ Lapsing

መደበቅ ........................................................ disguised

ሚና መጫወት ........................................................ Role playing

ማስተማር ........................................................ Teaching

ምላሽ ........................................................ Response

ምክንያታዊ ንምና ........................................................ Purposive sampling

ምኞት ........................................................ Ambitions

ቋንቋን የመናገር ፍርሃት ........................................ Languages anxiey

አዕምሮአዊ ብቃት/ጉብዝና/........................................ Intelligence

ሥነየማህበራዊ - ትምህርታዊ ሞዴል........................ Socio-Educational model

ሥነ ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና ........................................ Educational Psychology

ሥርአተ ትምህርት ........................................ Curriculum

ሥነ ትምህርት ........................................................ Education

ሥነ ልቦና ........................................................ Psychology

ቋንቋን የመማር ችሎታ ........................................ Language aPtitude

ሥፍረታዊ/ቁሳዊ/ ዝንባለ........................................ Instrumental orientation

ለራስ ያለ የብቃት ስሜት........................................ self-efficacy

ስሜት ........................................................ Feeling

ስብዕና ........................................................ Personality

ስሜታዊ ........................................................ Affective

ተሰጥኦ ........................................................ Aptitudes

ተላውጦ ........................................................ Variables

ተስተምህሮ (መማር) ........................................................ Learning

ታታሪነት ........................................................................ Interprising

ትንቢት ........................................................................... Prophecy

ትኩረት ማስተዋል ........................................................ Concentration

ንሺ/ተነሳሽነት/ .......................................................... Motivation

አላባውያን .................................................................... Elements

አመለካከት.......................................................................... Attitude

አስጊ ደረጃ(ዋጋ) ............................................................. Critical value

አቅመ አዳምና አቅመ ህይዋን............................................ puberty

አዕምሮአዊ ...................................................................... Cognitive

አእምሮአዊ ብቃት ........................................................... Intelligence

ክንውን ........................................................................... Success

ውህዳዊነት ....................................................................... Integrativeness

ውጫዊ/ስፍርታዊ/ቁሳዊ/ ንሺ/ተነሳሽነት/ ......................... Instrumental motivation

ውህዳዊ ንሽ/ (ውስጣዊ ንሺ). ......................................... Integrative motivation

ውህዳዊ ዝንባሌ (ውስጣዊ ዝንባሌ)................................. Intergrative orientation

ውጤት ............................................................................ Achievement

ውጫዊ/ውጫዊ/ስፍርታዊ/ቁሳዊ ዝንባሌ ......................... Instrumental orientation

የመማር ስልት .................................................................. .Learning style

የመማር ችሎታ/ክህሎት/ ................................................... Language aptitude

የሚግባባ (ግልጽ የሆነ) .................................................... Extroversion

የማወቅ ፍላጎት ................................................................ Curiousity

የማይግባባ (ዝምተኛ) ....................................................... Extroversion

የትምህርት ውጤት .......................................................... Academic Achievement

የንስሺ ባህሪያት ............................................................... Motivational behaviour

የአስተማማኝነት ደረጃ ..................................................... significant level

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ........................................................... first language

የደረጃ ነፃነት ........................................................................ Degree of freedom

የጉርምስና/የኮረዳነት ደረጃ................................................ Adolescent

የፍላጎት መመዘኛ (መለኪያ) ............................................ Interest Inventory

ጉጉት ................................................................................ Curiousity

ግንኙነት ............................................................................ Correlation

ፈላጊ ................................................................................. Desirable

ፍላጎት ..............................................................................  Interest

## አባሪ 2 ፡- በአማርኛ የተዘጋጀ የአመለካትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ

## በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

*መግቢያ*

የዚህ መጠይቅ ዓላማ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል፣ በመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ነው፡፡ ጥናቱም ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ካላቸው ፍላጎትና አመለካከት አንጻር በተለይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ እንዲሆን ለማድረግና በዙሪያው ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ስለሚረዳ ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን ዕገዛ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

ስለዚህ ለጥናቱ መሳካት እርስዎ የሚሰጡት ትክክለኛና እውነተኛ መረጃ ወሳኝ ስለሆነ የሚያምኑበትን ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጡ ትብብርዎን በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ለሚያደርጉት ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

*መመሪያ* I

መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

**መመሪያ I፡ ከተራ ቁጥር 1 - 6 ለቀረቡት ጥያቄዎች በጥያቄው መሰረት ትክክለኛውን መረጃ በጽሁፍ መልስ ስጡ**

1. አሁን ከምትማሯቸው ትምህርቶች ከሚወዱት ጀምረው በቅደም ተከተል ይጻፉ

   1. -------------- 2. ---------------- 3. -------------- 4. --------------5. --------------6.--------------

   7. --------------8. --------------- 9. -------------------10. -------------------11. ------------------

2. ስለራሳችሁ የሚፈለግ መረጃ 1. የሚማሩበት ት/ቤት ስም ----------------2.የክፍል ደረጃ ---------- 3. ፆታ-------------- 4. ዕድሜ ---------------------- 5. የአፍ መፍቻ ቋንቋ----------------------

3. ስለቤተሰብዎ የሚፈለግ መረጃ

   የአባት 1. የመጀመሪያ ቋንቋ -----------------2. የሁለተኛ ቋንቋ ---------------3. እምነት --------- ብሄር--------------------

   የእናት 1. የመጀመሪያ ቋንቋ -----------------2. የሁለተኛ ቋንቋ ---------------3. እምነት---------- ብሄር-------------------------

4. የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ያልሆነ ስንት የቋንቋ ትምህቶችን እየተማሩ ይገኛሉ --------------- ስማቸውን ይግለጹ---------------------- ------------------- -----------------------

5 ከሚማሩት የአንደኛና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቶች ከሚወዱት ጀምረው በቅደም ተከተል ያስቀምጧቸው፡፡

ሀ. ---------------------- ለ. ------------------------ ሐ. ------------------------- መ. ------------------

6. የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋነቋ ትምህርትነት ከስንተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ጥሩ ነው ብለው ይገምታሉ?

-----------------------------------ለምን ---------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

መመሪያ ll ከዚህ በታች ለአማርኛና ለቋንቋው ትምህርት ያለዎትን አመለካከትና ፍላጎት የሚያመለክቱ ሀሣቦች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ መስማማት አለመስማማትዎትን ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ተራ ቁጥር ድረስ አማራጮች የተሰጡ ሲሆን ከምርጫዎቹ ውስጥ አንዱን በመምረጥ በተመረጠው ቁጥር ላይ በማክበብ ይመልሱ፡፡

## የምርጫ ቁጥሮቹ መግለጫ

5. በጣም እስማማለሁ 4. እስማማለሁ 3. አልወሰንኩም 2. አልስማማም 1. ፈፅሞ አልስማማ

| ተ.ቁ | የፍላጎት መለኪያ | ምርጫዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.. | በአማርኛ ቋንቋ መጣጥፎችን መጻፍ ያስደስተኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.. | የእረፍት ጊዜዬን የአማርኛን ልቦለድ በማንበብ ማሳለፍ ያስደስተኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3. | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ትምህርት እንዳያልፈኝ እፈልጋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር ያስደስተኛል | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5. | የአማርኛ መምህሬን የማስተማር ዘዴ ስለምወደው ቋንቋውን መማር እፈልጋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6. | የአማርኛ ትምህርትን መማር የምፈልገው ወደፊት ከሚሠጠኝ ጥቅም አንጻር ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7. | የአማርኛ ትምህርትን የምወደው መምህሩን ስለምወደው ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8. | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መሳተፍ አልፈልግም | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9. | የአማርኛ መምህሬ ሲያስተምሩ በጥሞና እከታተላለሁ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 10. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በትምህርትነት መሰጠት መቻሉ ቋንቋውን ለመማር ያለኝን ፍላጎት መልሶልኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 11. | የአማርኛ ቋንቋ ትምህረት ከስርአተ ትምህርቱ ውስጥ ቢወጣ ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 12. | ከትምህርት ቤት ውጪ ከጓደኞቼ ጋር በመሆን አማርኛ ቋንቋን ማጥናት እወዳለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 13. | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጎበዝ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 14. | በአማርኛ ትምህርት የሚሰጠኝን የቤት ስራና የክፍል ስራ የመስራት ተነሳሽነት የለኝም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 15. | የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ፕሮግራም አውጥቼ እያጠናሁ እገኛለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.+ | የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሲያልፈኝ ቅር ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 7. | የአማርኛ ቋንቋን ማዳመጥ ብችል ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋን መናገር ብችል ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋን ማንበብ ብችል ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 20 | የአማርኛ ቋንቋን መጻፍ ብችል ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 21.- | አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርትነት መማር አልፈልግም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 22. | አማርኛ በትምህርትነት መሰጠቱ ያስደስተኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 23. | የአማርኛ መምህሬ የሚሰጡኝን የቤት ስራ እየሰራሁ እመጣለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 24. | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሩ ማነቃቂያ ስለሚያደርጉ ትምህርቱን ከልብ እማራለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 25. | በአማርኛ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛና ደራሲ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 26- | ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር አልፈልግም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 27 | የአማርኛ መምህሬ ለቱቶሪያል ትምህርት ሲጠሩኝ ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 28 | አብዛኛዎቹ የአማርኛ ትምህርት ዘርፎች ከፍላጎቴ ጋር ይጣጣማሉ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | **የአመለካከት መለኪያ** | | | | | |
| 29- | አማርኛ ለእኔ ከባድ ትምህርት ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 30 | አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት መሰጠቱ አስፈላጊ ነው ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 31 | የአማርኛ ቋንቋን መማር እንደማንኛውም ትምህርት ጥቅም ይኖረዋል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 32- | ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብዙ ክፍለ ጊዜ ቢሰጠው አያስደስተኝም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| - | የአማርኛ ቋንቋን መማር ማለት ጊዜን መግደል ነው | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 33 | የአማርኛ ትምህርት እንደሌሎቹ የትምህርት አይነቶች በእኩል አይን አየዋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 34- | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለእኔ የተንዛዛ አሰልቺ ትምህርት ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 35- | የአማርኛን ቋንቋ በስራ ዓለምም ሆነ በሌላው ማህበራዊ ህይወት ብዙ ጥቅም ይኖረዋል ብዬ አልገምትም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 36- | አማርኛ ቋንቋን መማር በስራ ዓለምም ሆነ በሌላው ሕይወቴ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 37- | የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት መሰጠቱን አልደግፍም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 8.- | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብዙም ጠቀሜታ ስለሌለው ብዙውን ሰዓቴን በእሱ ትምህርት ላይ ማጥፋት አልፈልግም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9- | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ስለማልወደው በትምህርትነት መቅረቡን አልፈልግም፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| !0 | አማርኛ የአፍሪካ ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1- | የአማርኛ ትምህርት ስለሚቀለኝ እንቀዋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 42- | የአማርኛ ቋንቋ ያስጠላኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3 | ሳዳምጥ ከሌሎቹ ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበ ሲሆን ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 14 | ሳነብ ከሌሎቹ ቋንቋዎች ይልቅ በደንብ የሚገባኝ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበ ሲሆን ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 45 | አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማስተማሪያ ቋንቋ ቢሆን ደስ ይለኛል፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 46 | አማርኛ ቋንቋን እንደማንኛውም ቋንቋ በእኩል ደረጃ እመለከተዋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 47 | አማርኛ የፌደራል መንግስት ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆኑን እቀበለዋለሁ ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣48 | የአማርኛ ተናጋሪዎችን ወግና ባህል እወዳለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣49 | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሄረሰቦችን እወዳቸዋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣50 | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብሄረሰቦችን አከብራቸዋለሁ፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ¥51 | ብዙውን ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤቴ ዝቅተኛ ነው፡፡ | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

52. በየአመቱ ያማርኛ ትምህርት ውጤት በአማካኝ ከሚከተሉት ውስጥ በየትኛው ላይ ያርፋል?

ሀ. ከ40 በታች ለ. ከ40-50 ሐ. ከ50-60 መ. ከ60-70 ሠ. ከ70-80 ረ. ከ80 በላይ

## አባሪ 3 :- በአፋን ኦሮሞ የተዘጋጀ የአመለካትና የፍላጎት መመዘኛ መጠይቅ

# Yuniivarsiitii Finfiinneettii Gaaffiiwwaan Kutaa Mummee Afaanoota/loqodoota Itiiyoophiiyaa fi Hogbarruu

Kaayyoon gaaffii kanaa barattoota Mana baruumsaa Sadarkaa 1ffaa,Jiduu galeessaa fi Sadarkaa Lammaffaa keessattii Jiranii feedhii fi ilaalcha Baruumsa Afaan Amaaraa barachuuf qabanii sadrkaa maaliirrattii akka jiruu beekuufii.Qo`aniichii ilaalchaa fi feedhii Barattoonnii Afaanicha barachuuf qabaniirraa, keessumatuu barattoota Afaan Amaaraa afaan lammaffaa godhanii kan baratanii adeemsa barachuu fi barrsiisu irrattii mijaa`aa akka ta`u taasiisu fi rakkolee naanno kanattii jiranii dhabamsiisuuf waan gargaaruuf barattootaaf gargaarsa barbaachiisaa ta`ee keennuuf faayiidaa guddaa qabaa jedhamee yaadamaa.

Ijaa kanaaf Milkaa`iina qo`annaa kanaaf Odeeffannoo dhugaa fi siirrii ta`e isiin keenniitanii murteessaa waan ta`eef,odeefanoo siirriittii ittii amantanii akka keeniitan gargaarsa keesan kabajaan gaafannaa. Gargaarsa keesanif Galatoomaa.

**Qajeelfama I**

Gaaffii kana irrattii maqaa barreesuun hinbarbaachiisu

**Qajeelfama I: Lakk.1-6 gaffiiwaan dhiiyaataniif haala gaafiisaatiin odeefannoo sirrii ta`e barreefamaaan keennii**

1. Amma barnoota barachaa jirtanii keessaa kan jaalataniirraa egalaatii tarreesatii barreessaa

1. ------------------- 2. ---------------- 3. -------------- 4. ----------------5. -------------------------

6.------------------ 7. --------------8. -------------- 9. -------------------------10. -----------------

2. Odeefannoo waa`e keesanii

1 Mana baruumsaa ---------------------------- kutaa ------------- 3. Saala ---------------
4. Uumurii ----------------------- 5. Afaan ittiin hiktanii -------------------------

3. Odeefannoo waa`ee maatii

**Kan abbaa** Afaan jalqabaa ----------------------Afaan lammaffaa ------------------- Amantaa ---------------
gosa--------------------

**kan haadhaa** Afaan jalqabaa --------------------- Afaan lammaffaa -------------------- Amantaa -----------------
gosa----------------------------

4. Afaan lammaffaatiin baruumsa meeqa barchaa jirtuu ? --------------------------------

maqaa isaanii ibsaa 1. ------------------------------ 2. -------------------------------- 3. ----------------

5. .Baruumsa afaan jalqabaa fi lammaffaa keessaa kan jaalataniirraa kaasee tartiibaan kaa`aa

1. ----------------------- 2. -------------------------- 3. ------------------------------ 4. -----------------

6. Baruumsa Afaan Amaaraa kutaa meqarra yo kennamuu jalqaabe gameesa jetaani

yaltuu? -----------------------------------------maliifi-----------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**Qajeelfama II** Ilaalchaa fi feedhii Afaanichaa fi baruumsa isaatiif qabdanii yaadnii hubachiisu gadiifageeynaan armaan gaditti dhiiyaateeraa.waliigaluu fi waliigaluu dhabuu keesani lakk. 1-5 filannoon kan keenamee waan ta`eef filannoo keesa lakoofsaa filatan'eraatii marsuudhan deebiisaa.

**Ibsa filanno lakoofsa**

**1.** Baayeettii hinwaliigaluu **2.** Hin waliigaluu **3.**Hinmurteesiinneee **4.** Waliigaleeraa **5.** Baayeettii waliigaleeraa

| Lakk | Gaaffii feedhii | filanno | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.. | Barreefamoota addaddaa afaan Amaaraatiin barreesuun nagamachiisaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 2.. | Yeroo baqonnaakoottii Asoosama Afaan Amaaraa dubbiisuudhaan dabarsuun nagamachiisaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 3. | Sagantaa Afaan Amaaraa akka nadarbuu hinbarbaaduu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 4. | Baruumsa Afaan Amaaraa barachuun nagamachiisaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 5. | Mala barsiisaa Afaan Amaaraakoo wanan jaaladhuuf baruumsa Afaan Amaaraa barachuu nan barbaadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6. | Baruumsa Afaan Amaaraa kanan barachuu barbaadu bu`aa fuulduuraaf argachu danda`u irraa kan ka`eedhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| -7. | Baruumsa Afaan Amaaraa kanan jaaladhuu barsiisiicha waanan jaaladhuufii | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| -8. | Sagantaa baruumsa Afaan Amaaraarrattii hirmaachuu hinbarbaaduu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 9. | Barsiisaan Afaan Amaaraa yommuu barsiisu xiiyyeefannoodhaan nan hordofaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 10. | Baruumsii Afaan Amaaraa baruumsaan keenamuu danda`uu isaa feedhii barachuuf qabuu naaf deebiiseeraa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| -11. | Baruumsii Afaan Amaaraa Siirna baruumsaa keessaa otoo bayee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 12. | Mana baruumsatin ala hiriiyoota koo waliin ta`uun afaan Amaaraa Qo`chuu nan jaaladhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 13. | Baruumsa Afaan Amaaraatiin cimaa ta`u nan barbaadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| -14. | Afaan Amaaraa waan hinjaalanneef assa'ementi nafkkenaamufi hojii manaa hojjeecu fedhii hinqabu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 15. | Afaan Amaaraa qo`achuuf sagantaa basuudhaan qo`achaan jiraa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 16.+ | Sagantaan Afaan Amaaraa yoo nadarbee nan gaabbaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 17. | Afaan Amaaraa otoon dubbachuu danda`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 18 | Afaan Amaaraa otoon dhaga`u, danda`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 19 | Afaan Amaaraa otoon dubbiisuu danda`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | Afaan Amaaraa otoon barreessu danda`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 21. | Afaan lammaffaa barachuu hinbarbaaduu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 22. | Afaan Amaaraa baruumsaan kenamuun'esaa nagamachiisaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 23. | Hojii manaa barsiisaan Afaan Amaaraa naaf keennu hojjadheen dhufaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 24. | Sagantaa Afaan Amaaraarattii barsiisaan wanta dadamaqsuu waan godhaniif baruumsiicha lapheekoo irraa nan baradhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 25. | Baruumsa Afaan Amaaraatiin cimee Gaazeexeesaa fi barreessaa ta`u nan barbaadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 26. | Dhirqama waan nattii ta`eefi malee baruumsa Afaan amaaraa barachuu hin barbaduu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 27 | Barsiisaankoo Afaaan Amaaraa baruumsa tiitooriiyaaaliif yemmu nawaaman nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 28 | Akaakuu Afaan Amaaraa keessa jiran irra caalattii feedhii koo waliin walsiimaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | Gafii illalchaa | | | | | |
| 29- | Baruumsii Afaan Amaaraa anaaf ulfaataadhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 30 | Afaan Amaaraa baruumsaan keenamuun'esa barbaachisaadha | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 31 | Baruumsa Afaan Amaaraaf Barachuun akkuuma baruumsa kammiiyyuttii faayiidaa qabaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 32- | Baruumsa Afaan Amaaraaf sagantaa heedduun otoo keenamee ana hingamachiisu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| - | Afaan Amaaraa barachuu jeechuuni yeroo guubu jeechudhaa. | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 33 | Baruumsa Afaan Amaaraa akkuuma baruumsa birootttii walqiixan ilaalaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 34- | Baruumsii Afaan Amaaraa aanaaf baruumsa dadhabsiisaadhaaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 35- | Afaan Amaaraan bakka hojii fi jireeyna haawaasuumattii faayiidaa heedduu qabaa jedheen hin yaadu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 36- | Afaan Amaaraa barachuun bakka hojiittiis ta`ee jireeyna koo birootttii ilaalcha barbaachiisaadhaa jedhu hinqabuu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 37- | Baruumsii Afaan Amaaraa baruumsaan keenamu isaa hindeegaruu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 38.- | Baruumsii Afaan Amaaraa faayiidaa heedduu waan hinqabaanneef sa`aa heeddu irrattii balleesu hinbarbaadu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 39- | Baruumsa Afaan Amaaraa waanan hinjaalanneef bifa baruumsaatiin akka dhiyaatuu hinbarbaaduu | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| .40 | Afaannii Amaaraa Afaan Afriikaa otoo ta`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 41- | Baruumsii Afaan Amaaraa Waan nattii salphatuuf nan tuuffadhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| .42- | Afaan Amaaraa najibiisiisaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 43 | Yaroon dhaga`u Afaan biroo irraa caalmaan Afaan Amaaraa otoo ta`ee sirriittii ifa naaf ta`aa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 44 | Yaroon dubbiisuu Afaan biroo irraa caalmaan Afaan Amaaraa otoo ta`ee sirriittii ifa naaf ta`aa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 45 | Afaannii Amaaraa Afaan baruumsaa Sadarkaa lammaffaa otoo ta`ee nan gamadaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 46 | Afaannii Amaaraa akuuma afaan birootttii sadrkaa walqiitaatiin nan ilaalaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 47 | Afaannii Amaaraa Afaan Biyyoolleesa Itiiyoophiyaa ta`u saa fudhatamaa qabaa. | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣48 | Afoolaa fi adaa saba Amaaraa nan jaaladhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣49 | Sabaa fi sablammoota dubbatoota Afaan Amaaraa nan jaaladhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ♣50 | Sabaa fi sablammoota dubbatoota Afaan Amaaraa nan kabajaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| ¥51 | Yeroo heeddu baruumsii afaan Amaaraatiin qabxiin koo gadbuu`aadhaa | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |

52. Qabxiiwwaan baruumsa afaan amaaraatiin waggaa waggaattii argatanii jidduu galeesaan kan armaan gadii keessaa essattii argamaa ?

A. 40 gadii B. 40-50 C. 50-60 D. 60-70 E. 70-80 F. 80 olii

## አባሪ 4 ፡- የቡድን ተኮር ውይይት ርእሰ ጉዳይ

ክልል-------------------------ት/ቤት-----------------------------

1. ለክልሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት መሰጠቱ ምን ፋይዳ ይኖረዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ?
2. አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማርና ለማስተማር በምቹ ሁኔዎች የሚጠቀሱ ካሉ እስኪ ግለጹአቸው፡፡
3. የአማርኛ ቋንቋን በትምህርትነት በመማር የሚገኘውን ጠቀሜታ ወይም ጉዳት ይኖራል ብላችሁ የምትገምቱትን ብትገልጹ? በምን ምክንያት?
4. የአማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች አሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?
5. ችግሮች አሉ የምትሉ ከሆነ ችግሮቹ ምንድናቸው? የችግሮ መንስኤዎች ናቸው ብላችሁ የምትገምቱትን እስኪ ግለጹ?
6. ችግሮቹን በምን መንገድ መፍታት ይቻላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?
7. በመማር ማስተማር ሂደት በመምህሩና በተማሪው መካከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?
8. ተማሪዎች ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ በአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ? በተማሪዎች መካከል ልዩነት አለ? ልዩነቱ ካለ ከየት የመጣ ይመስላችኋል?
9. በቋንቋው ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመቀመጥ ሁኔታ ምን ያነስላል? በንቃት ይሳተፋሉ?

10.ልዩነት በመኖሩ ምክንያት በትምህርት ቤታችሁ የተከሰተ ችግር አለ? እስኪ ግለጹ?

11.ልዩነቱን ለማጥበብ የምትጠቀሟቸው ዘዴዎች ካሉ ቢገልጹ? ተማሪዎቹ ቋንቋውን ተጠቅመው ከክፍል ውጪ ለመናገር የሚያደርጉት ጥረት ካለና የተገነዘባችሁትን ብትገልጹ?

12.እስከ አሁን በተወያየነው ውይይት መሰረት አማርኛ ቋንቋ መማር ማለት ጊዜን እንደማቃጠል እቆጥረዋለሁ የሚል ሀሳብ ቢቀርብለዎት ይስማማሉ? በላዉላይ ሀሳብ ካለዎት ቢገልጹ

13.የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋነቋ ትምህርትነት ከስንተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ጥሩ ነው ብለው ይገምታሉ? ------------------------------------ለምን----------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ 5 ፡- የፈተና ጥያቄዎች

በሁለተኛ ደርጃ ት/ቤት የ2005 ዓ/ም የሁለተኛ ወሰነ ትምህርት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

ስም-------------------------------------- ት/ቤት---------------------------ተ.ቁጥ.----------

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቀረቡት መመሪያዎች መሰረት ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

መመሪያ I. ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ድረስ የቀረቡት ቃላትን የሚመለከቱ በስራቸው አራት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ በጥያቄዎቹ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ፡፡

1. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በሚሠጠው ፍቺ የሚለየው የትኛው ነው?

   ሀ. ፈነጨ ለ. ፈነደቀ ሐ. ቦረቀ መ. ተወራጨ

2. “አቶ ሰለሞን ለአየለ ያበደረውን ገንዘብ ተቀበለ፡፡” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው፡፡

   ሀ. ወሰደ ለ. ሰጠ ሐ. ተረከበ መ. ሰበሰበ

3. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በፍች ልዩ የሆነው የትኛው ነው፡፡

   ሀ. ታጨች ለ. ተሸለመች ሐ. ተመረጠች መ. ተመለመለች

4. “አቶ ቃሲም ሰዎቹን ለማግባባትና ለማሣመን የተጠቀመበት ስልት ውጤታማ ነበር፡፡” በስሩ የተሠመረበት ቃል አውዳዊ ፍች የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ብልሐት ለ. አላማ ሐ. አነጋገር መ. ተግባር

5. “ልጅቱ ንብ ነች፡፡” በሚለው ዓአረፍተ-ነገር ውስጥ የንብ ፍካሬያዊ ፍች የቱን ይወክላል?

   ሀ. ተናዳፊነትን ለ. ታታሪነትን ሐ. በራሪ አንስ መሆንን መ. ተንኮለኛነትን

6. “አይን የበላ” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ተቃራኒ ፍቺ ያለው _________ ነው፡፡

   ሀ. አይን አውጣ ለ. አንገተ ሰባራ ሐ. ጋጥ ወጥ መ. ቅልብልብ

7. “እርሙን አወጣ” ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር በፍቺ የሚስማማው __________ነው፡፡

   ሀ. ማለ ለ. አለቀሰ ሐ. ወቀሠ መ. ታረቀ

8. “አድማሱ ወደ ት/ቤት መሄዱ ስለረፈደበት በቁሙ እንጀራውን ________ አድርጎ እየሮጠ ሄደ፡፡” በሚለው አረፍተ-ነገር ውስጥ ለባዶ ቦታው ይበልጥ ተገቢነት ያለው የትኛው ነው፡፡

ሀ. ዋጥ ዋጥ ለ. ጉረስ ጉረስ ሐ. አኝክ አኝክ መ. ቃም ቃም

9. ትክክል ያልሆነው አባባል የትኛው ነው?

ሀ. አይኔን ሰነፈጠኝ። ለ. አፍንጫዬን ሠነፈጠኝ።

ሐ. ሆዴን ቆረጠኝ። መ. አንጀቴ አረረ።

**መመሪያ II. ከተራ ቁጥር 10 እስከ 14 ድረስ የቀረቡት የሰዋስን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሲሆኑ በስራቸው አምስት አምስት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል። በጥያቄዎቹ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ።**

10. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ነጻ ምእላድ የሆነው--------------ነው?

ሀ. በሬዎች ለ. ተንኮለኛ ሐ. እግር መ. ተራራማ

11.ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ትክክል የሆነው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ውሀዎች ለ. ቀበሮች ሐ. ምጣድዎች መ. እጆች

12."ረጅሙ አበበ ትናንት በሬዎቹን ሸጠ።" በሚለው አረፍተ-ነገር ውስጥ የስም ገላጭ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አበበ ለ. ረጅሙ ሐ. በሬዎች መ. ትናንት

13.ከሚከተሉት ዓአረፍተ-ነገሮች ውስጥ አሉታዊ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ሃገሪቱ ሞቃትና ውብ ናት።

ለ. ሃገሪቱ በልምላሜ ያሸበረቀች አይደለችም።

ሐ. አዲስ አበባ የሃገሪቱ ዋና ከተማ ናት።

መ. ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ማማ ናት።

14.ትክክል የሆነው አረፍተ-ነገር የትኛው ነው?

ሀ. ሃይሌ በልቶ እራቱን በግዜ ተኛ። ለ. በልቶ ተኛ ሐይሌ እራቱን በግዜ።

ሐ. ሃይሌ እራቱን በግዜ በልቶ ተኛ። መ. ሃይሌ በግዜ በልቶ ተኛ እራቱን።

**መመሪያ III. ከተራ ቁጥር 15 - 17 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ድርሰትን የሚመለከቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች አራት አማራጭ ቀርቦላቸዋል። በጥያቄዎቹ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ ስጭ/ስጥ።**

15.ትክክለኛ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ያለበት አረፍተ-ነገር የትኛው ነው?

ሀ. አየለ መቼ መጣ። ለ. አየለ ትላንትና መጣ?

ሐ. አየለ መቼ መጣ? መ. አበበ መቼ ሄደ? አለ ጫላ።

16.“አቶ በቀለ በጣም አሟቸው ስለነበር ትላንትና አረፉ።” በሚለው አረፍተ-ነገር ውስጥ የአረፍተ-ነገሩ መልዕክት የቱን ይወክላል?

ሀ. አቶ በቀለ ሞቱ የሚለውን

ለ. አቶ በቀለ ስለደከማቸው ትንፋሽ ወሰዱ የሚለውን

ሐ. አቶ በቀለ ከሠማይ ላይ መሬት ወረዱ የሚለውን

መ. አቶ በቀለ ስለደከማቸው እረፍት ወሰዱ የሚለውን

17.ከታች ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ድረስ ቁጥር የተሰጣቸው አረፍተነገሮች ቀረበዋል፡፡

1. ዶ/ር ሰለሞን ግርማ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በህክምና ሳይንስ ትምህርት በወሎ ዩኒቨርስቲ ተምሮ በከፍተኛ ማእረግ ተመርቋል፡፡ 2. ዶክተር ሰለሞን ግርማ በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ በ1983ዓ/ም ተወለደ፡፡ 3. ከዛም በመንግስት ሆስፒታል በሰለጠነበት የሙያ መስክ ተመድቦ በመስራት የዜግነት ግዴታውን እየተወጣ ይገኛል፡፡ 4. እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እዛው በተወለደበት ከተማ ተምሯል፡፡

ከላይ የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል ቢቀመጡ ነው፤ የሀሳብ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አንድ አንቀጽ መመስረት የሚችለው?

ሀ. 1፣2፣3፣4  ለ. 2፣3፣4፣1  ሐ. 2፣4፣1፣3  መ. 2፣4፣3፣1

ክፍል ሁለት አንብቦ መረዳት

ከዚህ በታች የቀረበው የምንባብ አላማ ምንባቡን በዝግታ አንብባችሁ ከምንባቡ ፍሬ ነገሮችን ማውጣት እንድትችሉ ነው፡፡ ስለዚህ በምንባቡ መሰረት ከተራ ቁጥር 21-35 ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

ምንባብ

እሱባለውና ቶሎሣ ጓደኛሞችና የአንድ ሠፈር ልጆች ናቸው፡፡ የሚማሩበት ትምህርት ቤትና የክፍል ደረጃቸውም ተመሳሳይ ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት ጓደኛሞች የጥናት እቅዳቸውን አብረው ያዘጋጃሉ፡፡ በአንድ ላይ ሆነው ያጠናሉ፡፡ ያሏቸውን የትምህርት መሣሪያዎች በጋራ ይጠቀማሉ፡፡ የከበዳቸውን ትምህርት ነክ ጉዳዮች በጋራ በመወያየትና በመስራት ይረዳዳሉ፡፡ አንዱ ያለውን እውቀትና ችሎታ ለአንደኛው በማካፈል እርስ በእርስ በመረዳዳት ይማማራሉ፡፡

መምህር በሌለበት ክፍለ ጊዜም ለሌሎች የክፍል ተማሪዎች እውቀታቸውን ለማካፈል ጥረት ያደርጋሉ። እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች እገዛ ያደርጋሉ። ከክፍላቸው፣ ከክፍል ደረጃ እና ከትምህርት ቤታቸው አንደኛና ሁለተኛ በመውጣት በየአመቱ ሦስት ሦስት ሽልማቶችን ያግበሰብሳሉ። ስለሆነም በትምህርት ቤታቸውና በአካባቢው ምስጉን፣ ውጤታማና የተደነቁ ናቸው።

የሚገርመው ነገር ግን ትምህርታቸውን እርስ በእርስ የሚማማሩ ቢሆንም፣ በትምህርት ደረጃቸው አንዱ አንደኛውን ለመብለጥ የሚያደርጉት ውድድርና በሚያደርጉት ጥረት ምክንያት ብዙውን ጊዜ ውጤታቸው ተቀራራቢ ቢሆንም ከሌሎቹ ተማሪዎች በደረጃ እንዲበልጡ አድረጓቸዋል። አንዳንዴ እሱባለው አንደኛ ሲወጣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ቶሎሣ የአንደኝነትን ደረጃ በመያዝ ተከታትለው ደረጃ ይይዛሉ።

አስራ ሁለተኛ ክፍል እንደደረሱም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤታቸው ሁለቱም እኩል አራት ነጥብ በማምጣት ቶሎሣ ጐንደር ዩኒቨርስቲ፣ እሱባለው ደግሞ ጥቁር አንበሣ ተመድበው ሁለቱም የሚመኙትን የሕክምና ሳይንስ ትምህርት ተምረዋል። በተመደቡበት የትምህርት ዘርፍም በጥሩ ውጤት ተመርቀው በአሁኑ ሰአት በመንግስት ሆስፒታል በህክምና ስራ ላይ እየሰሩ ያሉ ሲሆን፤ በጋራ ደግሞ የግል ድርጅት ከፍተው በግላቸው ተጠቃሚ ሲሆኑ ለሃገሪቱ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

መመሪያ IV:_ከተራ ቁጥር 18-24 የቀረቡት ጥያቄዎች ከአራት በላይ ምርጫዎች አሏቸው። በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጡ።

18. እሱባለውና ቶሎሣ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንት የተገለጸበት አንቀጽ ከሚከተሉት ውስጥ በየትኛው አንቀጽ ላይ ነው?

ሀ. አንቀጽ አንድና ሁለት ለ. አንቀጽ አንድና ሶስት

ሐ. አንቀጽ ሁለትና ሶስት መ. በሁለም

19. እሱባለውና ቶሎሣ አሁን እየሰሩ ያሉበት የስራ መስክ የተገለጸበት አንቀጽ በየትኛው አንቀጽ ላይ ነው?

ሀ. አንቀጽ አንድ ለ. አንቀጽ ሁለት ሐ. አንቀጽ ሶስት መ. በሁለም ላይ

20. እሱባለውና ቶለሳ ምን አይነት ጓደኞች ናቸው?

ሀ. የጥሩ ጓደኛ ምሳሌዎች ለ.የመጥፎ ጓደኛ ምሳሌች

ሐ. የጥሩና የመጥፎ ጓደኛ ምሳሌዎች መ. መልስ የሚሆን አማራጭ አልቀረበም

21. ከእሱ ባለውና ከቶለሳ ጓደኝነት ምን ትማራላችሁ?

ሀ. የጥሩ ጓደኛ ውጤቱ ጥሩ መሆኑን ለ. ማንኛውም ጓደኛ አስፈላጊ መሆኑን

ሐ. በእሱባለውና በቶለሣ መካከል የመቀናናት መንፈስ መኖሩን መ. ግልጽ አይደለም

22. ምንም እንኳ ቶለሣና እሱባለው በትምህርት እርስ በርስ የሚረዳዱ ቢሆንም፤ በውስጣቸው የመወዳደር ስሜት እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበበት አንቀጽ የትኛው ላይ ነው?

ሀ. አንቀጽ አንድ ለ. አንቀጽ ሁለት ሐ. አንቀጽ ሶስት መ. በሁለም

23. ለምንባቡ ርእስ መሆን የማይችለው ከሚከተሉት ርዕሶች ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ. ጥሩ ጓደኛ ለ. መጥፎ ጓደኛ ሐ. ጓደኛና ውጤቱ መ. ውጤታማ ጓደኛ

24.ምንባቡን ከአምስት መስመር ሳይበልጥ በአንድ አነቀጽ አሳጥረሽ/ህ በራስሽ/ህ አባባል እንደገና ጻፊው/ጻፈው፡፡

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ V፡- ከተራ ቁጥር 25- 28 ለቀረቡ ጥያቄዎች አራት አማራጮች ቀርበላቸዋል፡፡ በጥያቄው መሰረት ትክክል የሆነውን በመምረጥ መልስ ስጡ፡፡***

25. "ዋህድ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ አርፍዶ በመነሳቱና በሰአቱ ትምህርት ቤት ባለመድረሱ ምክንያት የሚወደው የትምህርት ክፍለ ጊዜ አለፈው፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ በውጤትነት የቀረበው የትኛው ነው?

ሀ. አርፍዶ መነሳት ለ. የክፍለ ጊዜ ማለፍ ሐ. ከትምህርት ቤት መዘግየት መ. ቅጣት

26.ከሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የግል አስተያየት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ስራ ተሰራም አልተሰራም ሰው የሚበላውን ነገር አያጣም፡፡

ለ. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. ኤች አይቪን ጨምሮ በሽታ የሚተላለፈው በንክኪ ነው፡፡

መ. አንድ ሰው ውጤታማ መሆን የሚችለው በርትቶ በመስራቱ ሳይሆን በእድል ጉዳይ ነው፡፡

27. "በሬው ታሞ ---------- በታመመ በሶስተኛ ቀኑ ሞተ፡፡" በባዶ ቦታው ላይ ሊገባ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. በመሆኑ ለ. ስለሆነ ሐ. ስለነበር መ. ቆይቶ

28. "ዳርጌ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡" ------------ ውጤቱ ዝቅተኛ ነው፡፡" በባዶ ቦታው ላይ ሊገባ የሚችለው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ታድያ ለ. ስለሆነም ሐ. ነገር ግን መ. ሆኖም

**መመሪያ VI. ከተራ ቁጥር 29 - 32 ድረስ የቀረቡት ስዋስዋዊ ስርአትን ተከትለው የተጻፉ አይደለም፡፡ ሰዋስዋዊ ስርአትን እንዲጠብቁ አድርጋችሁ በማስተካከል እንደገና ጻፊ/ፍ፡፡**

29. ጫላ ተሸለመ ከክፍሉ አንደኛ ስለወጣ፡፡

..........................................................................................

30. ብዙ ገንዘብ እንዳለው ሰው ይቆጠራል ብዙ ቋንቋዎችን መናገር የሚችል ሰው፡፡

..........................................................................................

31. አበበ በአራት ብር ገዛ አንድ ደብተር፡፡

..........................................................................................

32. ትምህርት ቤት ሄዶ አድሀኖም መጣ፡፡

..........................................................................................

## አባሪ 6 ፦ መረጃን ለመተንተን ያገለገሉ ቀመሮች

ጥቅም ላይ የዋሉ አማራጭ የሂሳባዊ የስሌት መሳሪያዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የግንኙነት መለኪያ ቀመር

$$r_{xy} = \frac{N\sum_{xy} - \sum_x \sum_y}{\sqrt{[N\sum_x^2 - (\sum_x)]\ [N\sum_y^2 - (\sum_y)^2]}}$$

**2.** የውጤቱ ከፍተኛ ደረጃን (Significant level) የ «T» ቴስት ቀመርን በመጠቀም ትንታኔ የሚሰጥበት፡፡

$$t = \frac{\bar{x_i} - \bar{x_2}}{\sqrt{\frac{SD_1 (n_1 + 1) + SD_2^2 (n_2 - 1)}{(n_1 + n_2) - 2}\left(\frac{1}{n_1} + \frac{1}{n_2}\right)}}$$

3. የመጠይቁን አስተማማኝነት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር (The reliability of the questionnaire)

$$Rxx = \frac{K}{K-1}\left(1 - \frac{\sum (SI)^2}{SD^2}\right)$$

4. "t" የግንኙነት የአስተማማኝ ደረጃን ለመለካት የሚያገለግል ቀመር

$$t = r\frac{\sqrt{n-2}}{\sqrt{1-r^2}}$$

5. የፈተና የአስተማማኝነት ደረጃ ለመለካት የሚያገለግል ቀመር

K- R = 20 Kuder Richardson estimated

$$r_{xx} = \frac{K}{K-1}\left\{1 - \frac{\sum pq}{S^2_{xx}}\right\}$$

6. df (የአማካኝ የነጻነት ደረጃ) $\dfrac{\left(\dfrac{s_1^2}{n_1} + \dfrac{s_2^2}{n_2}\right)^2}{\dfrac{\left(\dfrac{s_1^2}{n_1}\right)^2}{n_1 - 1} + \dfrac{\left(\dfrac{s_2^2}{n_2}\right)^2}{n_2 - 1}}$

## እያንዳንዱ ቀመር በዝርዝር ሲታይ ዝርዝር ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል

### 1. የግንኙነት መለኪያ ቀመር

$$r_{xy} = \frac{N\sum_{xy} - \sum_x \sum_y}{\sqrt{[N\sum_x^2 - (\sum_x)]\ [N\sum_y^2 - (\sum_y)^2]}}$$

$r_{xy} =$ ተማሪዎች ለትምህርት ያላቸውን ፍላጎት፣ አመለካከትና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ዝምድና የሚያሳይ የግንኙነት መለኪያ መስፈርትነት የቀረበ ቀመር ነው::

x = ተማረርዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸውን አመለካከት ወይም ፍላጎትን ይመለከታል

Y = የትምህረቱን ውጤትን ይመለከታል

N = በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎችን ብዛት ይመለከታል

**2.** የውጤቱ ከፍተኛ ደረጃን (Significant level) የ «T» ቴስት ቀመርን በመጠቀምትንታኔ የሚሰጥበት::

$$t = \frac{\bar{X}_1 - \bar{x}_2}{\sqrt{\dfrac{(n_1 + 1) + SD_2^2 (n_2 - 1)}{(n_1 + n_2) - 2}\left(\dfrac{1}{n_1} + \dfrac{1}{n_2}\right)}}$$

ይህ በሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለውን የልዩነት የአስተማማኝ ደረጃን ለማየት ማለትም በሁለት ክልሎች መካከል፣ በሁለት አካባቢዎችች መካከል፣ በሁለት ውጤቶች መካከል እና በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች

መካከል ለቋንቋ ትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት፣ ለትምህቱ ያላቸውን ፍላጎት እና የውጤት ልዩነትን ለመለካት የሚያገለግል ቀመር ነው።

$\overline{X1}$= የመጀመሪያ ቡድን አማካኝ

$\overline{X2}$= የሁተኛ ቡድን አማካኝ

$SD_1^2$ = የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ያሉ መደበኛ ልይት

$SD_2^2$ = በሁለተኛ ደረጃ ላይ ያሉ መደበኛ ልይት

3. **የመጠይቁን አስተማማኝነት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር** (The reliability of the questionnaire)

$$Rxx = \frac{K}{K-1}\left(1 - \frac{\sum (SI)^2}{SD^2}\right)$$

K = በመጠይቁ ላይ የቀረቡት የትያቄዎች ብዛት

$SD_1^2$ = የመጠይቁ ተለዋዋጭነት መደበኛ ልይት

$SD_2^2$ = በስሌት የቀረበው የመጠይቁ ተለዋዋጭነት መደበኛ ልይት

4. **"t" የግንኙነት የአስተማማኝ ደረጃን ለመለካት የሚያገለግል ቀመር**

$$t = r\frac{\sqrt{n-2}}{\sqrt{1-r^2}}$$

**የፈተናውን ስተማማኝነት ለመለካት የተጠቀመው ቀመር**

r = በ X እና Y መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው።

n= በጥናቱ ላይ ተሳተፉትን ተማሪዎች ብዛት ይመለከታል።

t= የ t ቴስት ዋጋነው።

5. **የአስተማማኝነት ደረጃ ለመለካት የሚያገለግል ቀመር**

K- R = 20 Kuder Richardson estimated

$$r_{xx} = \frac{K}{K-1}\left\{1 - \frac{\sum pq}{S^2_{xx}}\right\}$$

$r_{xx}$ = reliability

K= number of the Item in test

P= proportion of People who answer item correctly

P= proportion of People who answer item in correctly

$S^2_{xx}$ = variance of the total test

$\sum pq$ = Summation of pq

$\sum$= summation of sine indicating that pq is summed over all items

e = error of score

t = true Score

6. df (የአማካኝ የነጻነት ደረጃ)

$$\frac{\left(\frac{s_1^2}{n_1} + \frac{s_2^2}{n_2}\right)^2}{\frac{\left(\frac{s_1^2}{n_1}\right)^2}{n_1 - 1} + \frac{\left(\frac{s_2^2}{n_2}\right)^2}{n_2 - 1}}$$

$n_1$ = በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ያሉ የቡድኖች ቁጥር

$n_2$ = በሁለተኛ ደረጃ ላይ ያሉ የቡድኖች ቁጥር

t = የ "t" ቴስት ቀመርን የሚያሳይ ቀመር

## አባሪ 7 :- የመረጃ ትንታኔ ውጤት የሚያሳይ ጥሬ መረጃ

## Discrptiv statistic of anova

**Descriptives**

| | | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error | 95% Confidence Interval for Mean | | Minimum | Maximum |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | Lower Bound | Upper Bound | | |
| nterest | afar | 192 | 81.7865 | 13.39771 | .96690 | 79.8793 | 83.6936 | 51.00 | 100.00 |
| | oromia | 200 | 64.0350 | 6.79223 | .48028 | 63.0879 | 64.9821 | 47.00 | 89.00 |
| | tigray | 198 | 71.1667 | 10.91395 | .77562 | 69.6371 | 72.6963 | 41.00 | 96.00 |
| | Addis ababa | 200 | 74.9350 | 11.94841 | .84488 | 73.2689 | 76.6011 | 43.00 | 100.00 |
| | Total | 790 | 72.8962 | 12.71923 | .45253 | 72.0079 | 73.7845 | 41.00 | 100.00 |
| attitude | afar | 192 | 53.1303 | 7.88657 | .56916 | 50.9086 | 53.1539 | 36.00 | 68.00 |
| | oromia | 200 | 44.1100 | 7.24433 | .51225 | 43.0999 | 45.1201 | 26.00 | 57.00 |
| | tigray | 198 | 47.1869 | 7.51651 | .53417 | 46.1334 | 48.2403 | 31.00 | 64.00 |
| | Addis ababa | 200 | 51.3650 | 7.93578 | .56114 | 50.2584 | 52.4716 | 33.00 | 99.00 |
| | Total | 790 | 48.6430 | 8.28832 | .29489 | 48.0642 | 49.2219 | 26.00 | 99.00 |
| achiveme | afar | 192 | 67.7813 | 13.24375 | .95579 | 65.8960 | 69.6665 | 30.00 | 90.00 |
| | oromia | 200 | 52.3500 | 7.31677 | .51737 | 51.3298 | 53.3702 | 35.00 | 76.00 |
| | tigray | 198 | 56.0404 | 11.42081 | .81164 | 54.4398 | 57.6410 | 30.00 | 85.00 |
| | Addis ababa | 200 | 69.1250 | 11.22226 | .79353 | 67.5602 | 70.6898 | 37.00 | 97.00 |
| | Total | 790 | 61.2722 | 13.16371 | .46834 | 60.3528 | 62.1915 | 30.00 | 97.00 |

[DataSet1] D:\PHD desertationስ\Faynal data analisis23\XYZ. 4 sav2.sav

## Oneway

**ANOVA**

| | | Sum of Squares | df | Mean Square | F | Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|
| interest | Between Groups | 32302.834 | 3 | 10767.611 | 88.770 | .000 |
| | Within Groups | 95340.655 | 786 | 121.299 | | |
| | Total | 127643.489 | 789 | | | |
| attitude | Between Groups | 8215.503 | 3 | 2738.501 | 46.807 | .000 |
| | Within Groups | 45985.833 | 786 | 58.506 | | |
| | Total | 54201.337 | 789 | | | |
| achiveme | Between Groups | 41808.623 | 3 | 13936.208 | 115.411 | .000 |
| | Within Groups | 94911.864 | 786 | 120.753 | | |
| | Total | 136720.487 | 789 | | | |

## Post Hoc Tests

**Multiple Comparisons**

ey HSD

| pendent iriable | (I) region | (J) region | Mean Difference (I-J) | Std. Error | Sig. | 95% Confidence Interval | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | Lower Bound | Upper Bound |
| nterest | afar | oromia | 17.75146* | 1.11277 | .000 | 14.8866 | 20.6163 |
| | | tigray | 10.61979* | 1.11552 | .000 | 7.7478 | 13.4917 |
| | | Addis ababa | 6.85146* | 1.11277 | .000 | 3.9866 | 9.7163 |
| | oromia | afar | -17.75146* | 1.11277 | .000 | -20.6163 | -14.8866 |
| | | tigray | -7.13167* | 1.10413 | .000 | -9.9743 | -4.2890 |
| | | Addis ababa | -10.90000* | 1.10136 | .000 | -13.7355 | -8.0645 |
| | tigray | afar | -10.61979 | 1.11552 | .000 | -13.4917 | -7.7478 |
| | | oromia | 7.13167* | 1.10413 | .000 | 4.2890 | 9.9743 |
| | | Addis ababa | -3.76833* | 1.10413 | .004 | -6.6110 | -.9257 |
| | Addis ababa | afar | -6.85146* | 1.11277 | .000 | -9.7163 | -3.9866 |
| | | oromia | 10.90000* | 1.10136 | .000 | 8.0645 | 13.7355 |
| | | tigray | 3.76833* | 1.10413 | .004 | .9257 | 6.6110 |
| ttitude | afar | oromia | 7.92125* | .77282 | .000 | 5.9316 | 9.9109 |
| | | tigray | 4.84438* | .77473 | .000 | 2.8498 | 6.8389 |
| | | Addis ababa | .66625 | .77282 | .824 | -1.3234 | 2.6559 |
| | oromia | afar | -7.92125* | .77282 | .000 | -9.9109 | -5.9316 |
| | | tigray | -3.07687* | .76682 | .000 | -5.0511 | -1.1027 |
| | | Addis ababa | -7.25500* | .76489 | .000 | -9.2242 | -5.2858 |
| | tigray | afar | -4.84438* | .77473 | .000 | -6.8389 | -2.8498 |
| | | oromia | 3.07687* | .76682 | .000 | 1.1027 | 5.0511 |
| | | Addis ababa | -4.17813* | .76682 | .000 | -6.1523 | -2.2039 |
| | Addis ababa | afar | -.66625 | .77282 | .824 | -2.6559 | 1.3234 |
| | | oromia | 7.25500* | .76489 | .000 | 5.2858 | 9.2242 |
| | | tigray | 4.17813* | .76682 | .000 | 2.2039 | 6.1523 |
| hiveme | afar | oromia | 15.43125* | 1.11026 | .000 | 12.5728 | 18.2897 |
| | | tigray | 11.74085* | 1.11301 | .000 | 8.8754 | 14.6063 |
| | | Addis ababa | -1.34375 | 1.11026 | .620 | -4.2022 | 1.5147 |
| | oromia | afar | -15.43125* | 1.11026 | .000 | -18.2897 | -12.5728 |
| | | tigray | -3.69040* | 1.10165 | .005 | -6.5266 | -.8542 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | Addis ababa | -16.77500* | 1.09888 | .000 | -19.6041 | -13.9459 |
| tigray | afar | -11.74085* | 1.11301 | .000 | -14.6063 | -8.8754 |
| | oromia | 3.69040* | 1.10165 | .005 | .8542 | 6.5266 |
| | Addis ababa | -13.08460* | 1.10165 | .000 | -15.9208 | -10.2484 |
| Addis ababa | afar | 1.34375 | 1.11026 | .620 | -1.5147 | 4.2022 |
| | oromia | 16.77500* | 1.09888 | .000 | 13.9459 | 19.6041 |
| | tigray | 13.08460* | 1.10165 | .000 | 10.2484 | 15.9208 |

*. The mean difference is significant at the 0.05 level.

**interest**

\Tukey HSD[a,b]

| region | N | Subset for alpha = 0.05 | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| oromia | 200 | 64.0350 | | | |
| tigray | 198 | | 71.1667 | | |
| Addis ababa | 200 | | | 74.9350 | |
| afar | 192 | | | | 81.7865 |
| Sig. | | 1.000 | 1.000 | 1.000 | 1.000 |

Means for groups in homogeneous subsets are displayed.

a. Uses Harmonic Mean Sample Size = 197.445.

b. The group sizes are unequal. The harmonic mean of the group sizes is used. Type I error levels are not guaranteed.

**attitude**

Tukey HSD[a,b]

| region | N | Subset for alpha = 0.05 | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 |
| oromia | 200 | 44.1100 | | |
| tigray | 198 | | 47.1869 | |
| Addis ababa | 200 | | | 51.3650 |
| afar | 192 | | | 52.0313 |
| Sig. | | 1.000 | 1.000 | .823 |

Means for groups in homogeneous subsets are displayed.

a. Uses Harmonic Mean Sample Size = 197.445.

b. The group sizes are unequal. The harmonic mean of the group sizes is used. Type I error levels are not guaranteed.

**achiveme**

Tukey HSD[a,b]

| region | N | Subset for alpha = 0.05 | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 |
| oromia | 200 | 52.3500 | | |
| tigray | 198 | | 56.0404 | |
| afar | 192 | | | 67.7813 |
| Addis ababa | 200 | | | 69.1250 |
| Sig. | | 1.000 | 1.000 | .617 |

Means for groups in homogeneous subsets are displayed.

a. Uses Harmonic Mean Sample Size = 197.445.

b. The group sizes are unequal. The harmonic mean of the group sizes is used. Type I error levels are not guaranteed.

**Correlations**

| | | interest | attitude | achiveme | age |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Pearson Correlation | 1 | .637** | .739** | -.179* |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 | .000 | .027 |
| | N | 590 | 590 | 590 | 590 |
| attitude | Pearson Correlation | .637** | 1 | .703** | -.285** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | | .000 | .000 |
| | N | 590 | 590 | 590 | 590 |
| achiveme | Pearson Correlation | .739** | .703** | 1 | -.303** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | .000 | | .000 |
| | N | 590 | 590 | 590 | 590 |
| age | Pearson Correlation | -.179* | -.285** | -.303** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .027 | .000 | .000 | |
| | N | 590 | 590 | 590 | 590 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

*. Correlation is significant at the 0.05 level (2-tailed).

Faynal data analisis23\t-afar2.sav

**Group Statistics**

| | sex | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Female | 96 | 80.3229 | 13.70939 | 1.39921 |
| | Male | 96 | 83.4271 | 13.15234 | 1.34236 |
| attitude | Female | 96 | 53.6250 | 8.20815 | .83774 |
| | Male | 96 | 50.4375 | 7.24868 | .73982 |
| achiveme | Female | 96 | 70.5000 | 13.70056 | 1.39831 |
| | Male | 96 | 65.0625 | 12.24729 | 1.24998 |

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) |
| interest | Equal variances assumed | .219 | .640 | -1.601 | 190 | .111 |
| | Equal variances not assumed | | | -1.601 | 189.674 | .111 |
| attitude | Equal variances assumed | 1.292 | .257 | 2.852 | 190 | .005 |
| | Equal variances not assumed | | | 2.852 | 187.138 | .005 |
| achiveme | Equal variances assumed | 4.392 | .037 | 2.899 | 190 | .004 |
| | Equal variances not assumed | | | 2.899 | 187.660 | .004 |

**Independent Samples Test**

| t-test for Equality of Means | | | |
|---|---|---|---|
| Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | Lower | Upper |
| -3.10417 | 1.93900 | -6.92889 | .72056 |
| -3.10417 | 1.93900 | -6.92893 | .72060 |
| 3.18750 | 1.11765 | .98291 | 5.39209 |
| 3.18750 | 1.11765 | .98269 | 5.39231 |
| 5.43750 | 1.87556 | 1.73791 | 9.13709 |
| 5.43750 | 1.87556 | 1.73761 | 9.13739 |

```
Faynal data analisis23\t--oromiya1.sav
```

**Group Statistics**

| | sex | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Female | 100 | 64.1000 | 5.74456 | .57446 |
| | Male | 100 | 63.9700 | 7.72828 | .77283 |
| attitude | Female | 100 | 44.5600 | 6.65957 | .66596 |
| | Male | 100 | 43.6600 | 7.79306 | .77931 |
| achiveme | Female | 100 | 52.9700 | 6.41566 | .64157 |
| | Male | 100 | 51.7300 | 8.10394 | .81039 |

**Independent Samples Test**

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) |
| interest | Equal variances assumed | 5.260 | .023 | .135 | 198 | .893 |
| | Equal variances not assumed | | | .135 | 182.813 | .893 |
| attitude | Equal variances assumed | 2.423 | .121 | .878 | 198 | .381 |
| | Equal variances not assumed | | | .878 | 193.302 | .381 |
| achiveme | Equal variances assumed | 3.874 | .050 | 1.200 | 198 | .232 |
| | Equal variances not assumed | | | 1.200 | 188.097 | .232 |

| t-test for Equality of Means | | | |
|---|---|---|---|
| Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | Lower | Upper |
| .13000 | .96295 | -1.76894 | 2.02894 |
| .13000 | .96295 | -1.76992 | 2.02992 |
| .90000 | 1.02509 | -1.12150 | 2.92150 |
| .90000 | 1.02509 | -1.12180 | 2.92180 |
| 1.24000 | 1.03361 | -.79829 | 3.27829 |
| 1.24000 | 1.03361 | -.79895 | 3.27895 |

Faynal data analisis23\tigray1.sav

**Group Statistics**

| | sex | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Female | 100 | 72.3100 | 8.49563 | .84956 |
| | Male | 98 | 70.0000 | 12.86568 | 1.29963 |
| attitude | Female | 100 | 46.7500 | 6.85400 | .68540 |
| | Male | 98 | 47.6327 | 8.14860 | .82313 |
| achiveme | Female | 100 | 56.2600 | 10.42590 | 1.04259 |
| | Male | 98 | 55.8163 | 12.40415 | 1.25301 |

**Independent Samples Test**

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | | | | | Lower | Upper |
| est | Equal variances assumed | 14.659 | .000 | 1.494 | 196 | .137 | 2.31000 | 1.54650 | -.73991 | 5.35991 |
| | Equal variances not assumed | | | 1.488 | 167.622 | .139 | 2.31000 | 1.55267 | -.75532 | 5.37532 |
| de | Equal variances assumed | 1.347 | .247 | -.825 | 196 | .410 | -.88265 | 1.06927 | -2.99140 | 1.22610 |
| | Equal variances not assumed | | | -.824 | 189.080 | .411 | -.88265 | 1.07113 | -2.99555 | 1.23025 |
| eme | Equal variances assumed | 2.566 | .111 | .273 | 196 | .785 | .44367 | 1.62719 | -2.76538 | 3.65273 |
| | Equal variances not assumed | | | .272 | 189.031 | .786 | .44367 | 1.63004 | -2.77173 | 3.65907 |

Faynal data analisis23\Addis ababa.sav

**Group Statistics**

| | sex | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Female | 97 | 75.1959 | 10.78061 | 1.09461 |
| | Male | 103 | 74.6893 | 13.00078 | 1.28100 |
| attitude | Female | 97 | 52.2062 | 8.80570 | .89408 |
| | Male | 103 | 50.5728 | 6.96997 | .68677 |
| achiveme | Female | 97 | 70.4742 | 11.81903 | 1.20004 |
| | Male | 103 | 67.8544 | 10.52952 | 1.03750 |

**Independent Samples Test**

| | Levene's Test for Equality of Variances | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | | | | Lower | Upper |
| Equal variances assumed | 5.329 | .022 | .299 | 198 | .765 | .50656 | 1.69440 | -2.83484 | 3.84795 |
| Equal variances not assumed | | | .301 | 194.919 | .764 | .50656 | 1.68497 | -2.81656 | 3.82968 |
| Equal variances assumed | .495 | .483 | 1.459 | 198 | .146 | 1.63337 | 1.11963 | -.57455 | 3.84129 |
| Equal variances not assumed | | | 1.449 | 182.808 | .149 | 1.63337 | 1.12740 | -.59103 | 3.85777 |
| Equal variances assumed | .817 | .367 | 1.657 | 198 | .099 | 2.61986 | 1.58086 | -.49763 | 5.73734 |
| Equal variances not assumed | | | 1.651 | 192.123 | .100 | 2.61986 | 1.58635 | -.50904 | 5.74876 |

## Correlations

[DataSet1] D:\PHD desertation Faynal data analisis23\t-afar2.sav

**Correlations**

| | | interest | attitude | achiveme | age |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Pearson Correlation | 1 | .556** | .663** | .004 |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 | .000 | .956 |
| | N | 192 | 192 | 192 | 192 |
| attitude | Pearson Correlation | .556** | 1 | .745** | -.119 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | | .000 | .101 |
| | N | 192 | 192 | 192 | 192 |
| achiveme | Pearson Correlation | .663** | .745** | 1 | -.095 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | .000 | | .191 |
| | N | 192 | 192 | 192 | 192 |
| age | Pearson Correlation | .004 | -.119 | -.095 | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .956 | .101 | .191 | |
| | N | 192 | 192 | 192 | 192 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

## T-Test

[DataSet1] D:\PHD desertation Faynal data analisis23\t-afar2.sav

**Group Statistics**

| | location | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | urban | 111 | 84.3243 | 13.44157 | 1.27582 |
| | rural | 81 | 78.5185 | 12.89294 | 1.43255 |
| attitude | urban | 111 | 53.7027 | 8.18046 | .77645 |
| | rural | 81 | 49.7407 | 6.87710 | .76412 |
| achiveme | urban | 111 | 70.2162 | 13.12070 | 1.24536 |
| | rural | 81 | 64.4444 | 12.74951 | 1.41661 |

**Independent Samples Test**

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | | | | | Lower | Upper |
| interest | Equal variances assumed | .933 | .335 | 3.007 | 190 | .003 | 5.80581 | 1.93090 | 1.99706 | 9.61456 |
| | Equal variances not assumed | | | 3.027 | 176.486 | .003 | 5.80581 | 1.91831 | 2.02003 | 9.59158 |
| attitude | Equal variances assumed | 1.612 | .206 | 3.540 | 190 | .001 | 3.96196 | 1.11919 | 1.75432 | 6.16960 |
| | Equal variances not assumed | | | 3.637 | 186.157 | .000 | 3.96196 | 1.08939 | 1.81283 | 6.11109 |
| achiveme | Equal variances assumed | .545 | .461 | 3.046 | 190 | .003 | 5.77177 | 1.89471 | 2.03440 | 9.50914 |
| | Equal variances not assumed | | | 3.060 | 175.292 | .003 | 5.77177 | 1.88619 | 2.04920 | 9.49434 |

## Correlations

```
CORRELATIONS
  /VARIABLES=interest attitude achiveme age
  /PRINT=TWOTAIL NOSIG
  /MISSING=PAIRWISE.
[DataSet1] D:\PHD desertation\Faynal data analisis23\t--oromiya1.sav
```

**Correlations**

| | | interest | attitude | achiveme | age |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Pearson Correlation | 1 | .476** | .609** | -.185** |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 | .000 | .009 |
| | N | 200 | 200 | 200 | 200 |
| attitude | Pearson Correlation | .476** | 1 | .625** | -.200** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | | .000 | .004 |
| | N | 200 | 200 | 200 | 200 |
| achiveme | Pearson Correlation | .609** | .625** | 1 | -.369** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | .000 | | .000 |
| | N | 200 | 200 | 200 | 200 |
| age | Pearson Correlation | -.185** | -.200** | -.369** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .009 | .004 | .000 | |
| | N | 200 | 200 | 200 | 200 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

## T-Test

```
T-TEST GROUPS=location(1 2)
  /MISSING=ANALYSIS
  /VARIABLES=interest attitude achiveme
  /CRITERIA=CI(.95).
[DataSet1] D:\PHD desertation\Faynal data analisis23\t--oromiya1.sav
```

**Group Statistics**

| | location | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | urban | 93 | 66.0645 | 6.78522 | .70359 |
| | rural | 107 | 62.2710 | 6.31645 | .61063 |
| attitude | urban | 93 | 44.8710 | 7.19484 | .74607 |
| | rural | 107 | 43.4486 | 7.25575 | .70144 |
| achiveme | urban | 93 | 53.6022 | 8.29895 | .86056 |
| | rural | 107 | 51.2617 | 6.17716 | .59717 |

**Independent Samples Test**

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | | | | | Lower | Upper |
| t | Equal variances assumed | .476 | .491 | 4.092 | 198 | .000 | 3.79349 | .92695 | 1.96553 | 5.62145 |
| | Equal variances not assumed | | | 4.072 | 189.484 | .000 | 3.79349 | .93162 | 1.95580 | 5.63117 |
| e | Equal variances assumed | .214 | .644 | 1.388 | 198 | .167 | 1.42237 | 1.02464 | -.59824 | 3.44297 |
| | Equal variances not assumed | | | 1.389 | 194.576 | .166 | 1.42237 | 1.02403 | -.59726 | 3.44199 |
| me | Equal variances assumed | 6.832 | .010 | 2.280 | 198 | .024 | 2.34047 | 1.02652 | .31615 | 4.36478 |
| | Equal variances not assumed | | | 2.234 | 168.104 | .027 | 2.34047 | 1.04746 | .27259 | 4.40834 |

```
GET
```

## Correlations

```
  FILE='D:\PHD desertation/Faynal data analisis23\tigray1.sav'.
DATASET NAME DataSet1 WINDOW=FRONT.
CORRELATIONS
  /VARIABLES=interest attitude achiveme age
  /PRINT=TWOTAIL NOSIG
  /MISSING=PAIRWISE.
[DataSet1] D:\PHD desertation\Faynal data analisis23\tigray1.sav
```

**Correlations**

| | | interest | attitude | achiveme | age |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | Pearson Correlation | 1 | .769** | .734** | -.347** |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 | .000 | .000 |
| | N | 198 | 198 | 198 | 198 |
| attitude | Pearson Correlation | .769** | 1 | .676** | -.209** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | | .000 | .003 |
| | N | 198 | 198 | 198 | 198 |
| achiveme | Pearson Correlation | .734** | .676** | 1 | -.337** |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | .000 | | .000 |
| | N | 198 | 198 | 198 | 198 |
| age | Pearson Correlation | -.347** | -.209** | -.337** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | .003 | .000 | |
| | N | 198 | 198 | 198 | 198 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

## T-Test

```
T-TEST GROUPS=location(1 2)
  /MISSING=ANALYSIS
  /VARIABLES=interest attitude achiveme
  /CRITERIA=CI(.95).
```

```
[DataSet1] D:\PHD desertation/Faynal data analisis23\tigray1.sav
```

**Group Statistics**

| | location | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| interest | urban | 106 | 73.3679 | 9.81090 | .95292 |
| | rural | 92 | 68.6304 | 11.60401 | 1.20980 |
| attitude | urban | 106 | 47.6981 | 7.03213 | .68302 |
| | rural | 92 | 46.5978 | 8.03708 | .83792 |
| achiveme | urban | 106 | 58.8774 | 10.45690 | 1.01566 |
| | rural | 92 | 52.7717 | 11.66294 | 1.21595 |

**Independent Samples Test**

| | | Levene's Test for Equality of Variances | | t-test for Equality of Means | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | F | Sig. | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Std. Error Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | | | | | Lower | Upper |
| erest | Equal variances assumed | 2.477 | .117 | 3.113 | 196 | .002 | 4.73749 | 1.52193 | 1.73603 | 7.73895 |
| | Equal variances not assumed | | | 3.076 | 179.172 | .002 | 4.73749 | 1.54002 | 1.69857 | 7.77641 |
| tude | Equal variances assumed | 2.852 | .093 | 1.027 | 196 | .305 | 1.10029 | 1.07088 | -1.01164 | 3.21221 |
| | Equal variances not assumed | | | 1.018 | 182.338 | .310 | 1.10029 | 1.08103 | -1.03266 | 3.23323 |
| iiveme | Equal variances assumed | 1.458 | .229 | 3.884 | 196 | .000 | 6.10562 | 1.57213 | 3.00515 | 9.20609 |
| | Equal variances not assumed | | | 3.854 | 184.459 | .000 | 6.10562 | 1.58433 | 2.97988 | 9.23135 |

# አባሪ 8 :- የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አስተማማኝነትን የሚያሳይ ጥሬ መረጃ

## Reliability

[DataSet1] D:\PHD desertation\interest inventory.sa

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 46 | 100.0 |
| | Excluded[a] | 0 | .0 |
| | Total | 46 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .830 | 18 |

## Reliability

[DataSet1] D:\PHD desertation\reliability of ATTITUDE INVENTORY.sav

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 41 | 100.0 |
| | Excluded[a] | 0 | .0 |
| | Total | 41 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .818 | 16 |

## Reliability

[DataSet2] D:\PHD desertation\reliability of the Achivment test.sav

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 55 | 96.5 |
| | Excluded[a] | 2 | 3.5 |
| | Total | 57 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .852 | 30 |

## Reliability

Afan Oromifa

[DataSet1] C:\Users\Eshetu\Desktop\reliability of  ATTITUDE INVENTORY.sav

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 28 | 100.0 |
| | Excluded[a] | 0 | .0 |
| | Total | 28 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .803 | 16 |

## Reliability

Oromigna

[DataSet1] D:\PHD desertation\reliability interest inventory.sav

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 28 | 54.9 |
| | Excluded[a] | 0 | 0 |
| | Total | 28 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .812 | 18 |